# ተስማማ

## ሮሜ

### ከእግዚአብሔር፣ ከራሳችንና ከሌሎች ጋር እንዴት እንደምንስማማ


ጽሑፍ:- በዋረን ደብልዩ. ዌርዝቢ
ትርጉም:- በመሐሪ ታደሠ
እርማት:- በወርቁ ኤጀሬና ይግረም ረታ



የመጀመሪያ እትም 1997 ዓ.ም (2004 A.D.)



Copyright
© 2003 by SIM, Addis Ababa, Ethiopia. Originally published in English under the title of BE RIGHT. Copyright © 1977 by SP Publications, Inc. Cook Communications Ministries, 4050 Lee Vance View, Colorado Springs Colorado 80918 U.S.A.
All rights reserved.



BIBLE BASED BOOKS
SIM PUBLISHING

መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ያደረጉ መጻሕፍት

# ማውጫ

መቅድም ........................................................................

1. ወደ ሮም ለመጓዝ መዘጋጀት (1:1-17) ......................... 1
2. እግዚአብሔር አሳልፎ ሲሰጥ (1:18-3:20) ..................... 15
3. አባታችን አብርሃም (3:21-4:25) ................................ 29
4. እንደ ንጉሥ መኖር (5:1-21) ........................................ 43
5. ለመኖር መሞት (6:1-23) .............................................. 55
6. ሕግና ክርስቲያኖች (7:1-25) ........................................ 67
7. ፍጻሜና ነጻነት (8:1-39) ............................................... 80
8. እግዚአብሔር ይሳሳታልን? (9:1-33) ............................. 93
9. የተዛባ ጽድቅ (10:1-21) ................................................ 104
10. እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ ያለውን ነገር አልቋጨም (11:1-36) ............................................ 115
11. ትክክለኛ ግንኙነቶች ማለት ትክክለኛ ኑሮ ነው (12:1-13:14) ....................................................... 127
12. ክርስቲያኖች በማይስማሙበት ጊዜ (14:1-15:7)........... 141
13. በእንቅስቃሴ ላይ ያለ ሰው (15:8-16:27)....................... 155

# መቅድም

በራስህ ሕይወት፣ በሌሎች ሰዎችና በዓለም ላይ ያሉትን የተሳሳቱ ነገሮች ከማየትህ የተነሣ ዝለህ ከሆነ፣ ጳውሎስ የጻፈው የሮሜ መልእክት ለአንተ ነው።

የሮሜ መልእክት ፍሬ ነገር «የእግዚአብሔር ጽድቅ» ነው። በዚህ መልእክቱ ከእግዚአብሔር፣ ከራሳችንና ከሌሎች ጋር እንደምንስማማ ይነግረናል። በተጨማሪም ጳውሎስ አንድ ቀን እግዚአብሔር ፍጥረትን ሁሉ እንደሚያስተካክልና በተለይም «ለአይሁዳውያን ችግር» መፍትሔ ሰጥቶ፣ ሰላምን በምድር ላይ እንደሚያመጣ ያብራራል።

የሮሜ መልእክት የተጻፈው ለዝንጉዎች (ለልበ ቢሶች) ወይም ሃይማኖታዊ በታዎችን ለሚኃበኙ ሰዎች አይደለም። ይህንን መልእክት ስታጠና ብዙ ልታስብ ይገባሃል፤ ሆኖም የምታገኘው በረከት ከጥናትህ ጋር የሚመጣጠን ይሆናል። የሮሜን መልእክት ከተረዳህ፣ የቀረውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ለማጥናት ቁልፉን አገኘህ ማለት ነው። ከዚያም በላይ፣ የውጤታማ ክርስቲያናዊ አኗኗርን ምሥጢር ታገኛለህ።

«ተስማማ» የሮሜ መልእክት ዝርዝር ማብራሪያ አይደለም። የመልእክቱን ዋና መልእክት እንድትረዳና ዛሬ በኑሮህ እንድትተገብረው ፍታቲያዊ አሰሳ ነው። ይህንን መጽሐፍ በሚገባ ከተረዳህ በኋላ፣ ጥልቅ ትንታኔ ወደሚሰጡ የማብራሪያ መጻሕፍት ብትመለከት የበለጠ ልትጠቀም እንደምትችል አምናለሁ።

ዋረን ደብልዩ. ዌርዝቢ

# ሮሜ 1:1-17

ሐዋርያ ሊሆን የተጠራ የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ ጳውሎስ በነቢያቱ አፍ በቅዱሳን መጻሕፍት አስቀድሞ ተስፋ ለሰጠው ለእግዚአብሔር ወንጌል ተለየ:: ይህም ወንጌል በሥጋ ከዳዊት ዘር ስለ ተወለደ፣ እንደ ቅድስና መንፈስ ግን ከሙታን መነሣት የተነሣ በኃይል የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ ስለ ተገለጠ ስለ ልጁ ነው፤ እርሱም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: በእርሱም ስለ ስሙ በአሕዛብ ሁሉ መካከል ከእምነት የሚነሣ መታዘዝ እንዲገኝ ጸጋንና ሐዋርያነትን ተቀበልን፤ በእነርሱም መካከል የኢየሱስ ክርስቶስ ልትሆኑ የተጠራችሁ እናንተ ደግሞ ናችሁ:: በእግዚአብሔር ለተወደዳችሁና ቅዱሳን ልትሆኑ ለተጠራችሁ በሮሜ ላላችሁት ሁሉ፣ ከእግዚአብሔር ከአባታችን ከጌታም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን::

እምነታችሁ በዓለም ሁሉ ስለተሰማች አስቀድሜ ስለ ሁላችሁ አምላኬን በኢየሱስ ክርስቶስ አመሰግናለሁ:: በልጁ ወንጌል በመንፈሴ የማገለግለው እግዚአብሔር ምስክሬ ነውና፤ ምናልባት ብዙ ቆይቼ ወደ እናንተ አሁን እንድመጣ በእግዚአብሔር ፈቃድ መንገዴን እንዲያቀናልኝ እየለመንሁ ሁልጊዜ ስጸልይ ስለ እናንተ ሳላቋርጥ አሳስባለሁ:: ትጸኑ ዘንድ መንፈሳዊ ስጦታ እንዳካፍላችሁ ላያችሁ እናፍቃለሁና፤ ይህንም ማለቴ በመካከላችን ባለች በእናንተና በእኔ እምነት አብረን በእናንተ እንድንጽናና ነው:: ወንድሞች ሆይ፣ በሌሎች አሕዛብ ደግሞ እንደ ሆነ በእናንተም ፍሬ አገኝ ዘንድ ብዙ ጊዜ ወደ እናንተ ልመጣ እንዳሰብሁ እስከ አሁን ግን እንደተከለከልሁ ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ:: ለግሪክ ሰዎችና ላልተማሩም፣ ለጥበበኞችና ለማያስተውሉም ዕዳ አለብኝ፤ ስለዚህም በሚቻለኝ መጠን በሮሜ ላላችሁ ለእናንተ ደግሞ ወንጌልን ልሰብክ ተዘጋጅቼአለሁ::

በወንጌል አላፍርምና አስቀድሞ ለአይሁዳዊ ደግሞም ለግሪክ ሰው፣ ለሚያምኑ ሁሉ የእግዚአብሔር ኃይል ለማዳን ነውና:: ጻድቅ በእምነት ይኖራል ተብሎ እንደ ተጻፈ የእግዚአብሔር ጽድቅ ከእምነት ወደ እምነት በእርሱ ይገለጣልና::

# 1

## ወደ ሮም ለመግዝ መዘጋጀት

ግንቦት 24 ቀን 1738 (እ. ኤ. አ)፣ አንድ ተስፋ የቆረጠ ሚስዮናዊ «ሳይፈልገው» በለንደን ከተማ ወደሚገኝ አንድ መንፈሳዊ ጉባኤ ሄደ:: በዚያም ተአምር ተፈጸመ:: እርሱም በማስታወሻ ደብተሩ ላይ የሚከተለውን ጻፈ:: «ለዘጠኝ ሰዓት ሩብ ጉዳይ ሲሆን፣ ልቤ ባልለመድኩት ሁኔታ ሲሞቀኝ ተሰማኝ:: ለደኅንነቴ በክርስቶስ ብቻ እንዳመንኩ ተሰማኝ:: ኃጢአቴንም በሙሉ ወስዶ ከኃጢአት ሕግና ከሞት እንዳዳነኝና ከኃጢአትና ከሞት ሕግ እንዳዳነኝ ዋስትና አገኘሁ::»

ያ ሚሲዮናዊ ጆን ዌስሊ ነው:: በዚያ ዕለት ማታ የሰማው መልእክት የማርቲን ሉተርን የሮሜ ማብራሪያ መቅድም ነበር:: ከጥቂት ወራት በፊት፣ በዚሁ ማስታወሻ ደብተሩ ላይ፣ «እኔ ለህንዶች ለመስበክ ወደ አሜሪካ ሄድኩ፤ እኔን ግን ማን ይለውጠኝ ይሆን?» ብሎ ጽፎ ነበር:: በዚያ ምሽት በአልደርስጌት ጎዳና ጥያቄው መልስ አገኘ:: ፍጻሜውም መላውን እንግሊዝ ያነቃነቀና ሕዝቡን የለወጠ ታላቁ የዌስሊይ መንፈሳዊ ተሐድሶ ነበር::

ጳውሎስ የጻፈው የሮሜ መልእክት የማርቲን ሉተርንና የጆን ዌስሊን ብቻ ሳይሆን፣ ዛሬም የሰዎችን ሕይወት እየለወጠ ነው:: ከሌሎች የቅዱሳት መጻሕፍት ቃላት በላይ ማርቲን ሉተርን ከተራ ሃይማኖተኝነት በጸጋ በእምነት ወደሚገኝ የደኅንነት ደስታ ያመጣው ሮሜ 1:17 ነበር:: «ጻድቅ በእምነት ይኖራል»:: የፕሮቴስታንት ተሐድሶም ሆነ የዌስሊ መንፈሳዊ መነቃቃት ጳውሎስ ከቆሮንቶስ ሆኖ በ56 ዓ.ም የጻፈው የሮሜ መልእክት ፍሬዎች ናቸው:: መልእክቱን ወደ ሮም ያደረሰችው የቤተ ክርስቲያኒቱ ዲያቆን ፌቤን (ሮሜ 16:1) ነበረች::

እስኪ አስቡት! እኔና እናንተም ለሉተርና ለዌስሊ ሕይወትና ኃይል የሰጣቸውን የእግዚአብሔርን ቃል ማንበብና ማጥናት

እንችላለን! እነርሱን ያስተማረው መንፈስ ቅዱስ እኛንም ያስተምረናል! ከዘመናት በፊት የነበሩትን የእምነት ሰዎች የለወጠውን መልእክት እኛም ብንረዳው፣ እኔ እናንተ በልባችን፣ በቤታችንና በቤተ ክርስቲያናችን መንፈሳዊ መነቃቃትን ልንለማመድ እንችላለን።

በመልእክቱ መግቢያ ባሉት ቁጥሮች ላይ፣ ጳውሎስ ራሱን በሮም ላሉት አማኞች ያስተዋውቃል። በመልእክቱ መጨረሻ እንደተገለጠው አንዳንዶቹን በግሉ ያውቃቸዋል ምክንያቱም በስም ጠቅሶ ሰላምታ ልኮላቸዋል፤ አብዛኛዎቹን ግን አይቷቸው አያውቅም። ስለሆነም በመጀመሪያዎቹ 17 ቁጥሮች ጳውሎስ ራሱን በሮም ከነበሩ አማኞች ጋር ለማዛመድ ሦስት መንገዶችን ተጠቅሟል።

## 1. ራሱን አስተዋወቀ (1:1-7)

በድሮ ዘመን አንድን መልእክት የሚጽፍ ሰው መጻፍ የሚጀምረው ስሙን በመግለጽ ነበር። ነገር ግን በዚያ ዘመን ብዙ ጳውሎሶች በመኖራቸው ለአንባቢዎቹ የጻፈላቸውን መልእክት የመጻፍ መብት እንዳለው ለማሳወቅ ተጨማሪ መግለጫ ስለራሱ መስጠት ነበረበት። ለመሆኑ የጳውሎስ ተልእኮ ምን ነበረ?

ሀ) *የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ ነው* (1:1) - ጳውሎስ «ባሪያ» በማለት የተጠቀመበት ቃል በዚያ ዘመን ለነበሩ ሮማውያን ትልቅ ትርጉም ነበረው። በሮም ግዛት ወደ ስድስት ሚሊዮን የሚጠጉ ባሪያዎች ነበሩ። ባሪያ ደግሞ እንደ ሰው ሳይሆን፣ እንደ ዕቃ (ንብረት) ነበር የሚታየው። ጳውሎስ የክርስቶስ ባሪያ በመሆን ሊታዘዝና የጌታን ፈቃድ ሊፈጽም በፍቅር ራሱን ሰጥቷል።

ለ) *ሐዋርያ ነው* (1:1) - ሐዋርያ «በባለ ሥልጣን አንድን ዓላማ ሊፈጽም የተላከ» ማለት ነው። በዚያ ዘመን ለንጉሠ ነገሥት ወይም ለንጉሥ መልእክተኛ ይጠቀሙበት ነበር። ሐዋርያ የመሆን አንዱ መመዘኛ ከሞት የተነሣውን ክርስቶስን ማየት ነበር (1ኛ ቆሮ. 9:1-2)። ጳውሎስ ክርስቶስን በደማስቆ

መንገድ ላይ አይቶታል (የሐዋ. 9:1-9)፣ ደግሞም የአሕዛብ ሐዋርያ እንዲሆን ክርስቶስ የጠራው ያኔ ነበር:: ጳውሎስም ለአብያተ ክርስቲያናት የሚያካፍለውን መለኮታዊ መገለጥ ከክርስቶስ ተቀበለ::

ሐ) *ወንጌል ሰባኪ ነው* (1:1-4) - የአይሁድ መምህር ሳለ እንደ ፈሪሣዊ ለአይሁድ ሕግና ወግ ራሱን ለይቶ ነበር:: ለክርስቶስ በተረታ ጊዜ ደግሞ ለወንጌል አገልግሎት ተለየ:: ወንጌል «የምሥራች» ማለት ነው:: ወንጌል ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን እንደ ሞተ፣ እንደ ተቀበረ፣ ከሞት እንደ ተነሣና የሚያምኑበትን ሊያድናቸው እንደሚችል የሚገልጥ መልእክት ነው (1ኛ ቆሮ. 15:1-4):: ወንጌል ከእግዚአብሔር የመነጨ እንጂ በሰው ሃሳብ የመጣ ስላልሆነ «የእግዚአብሔር ወንጌል» ነው (ሮሜ 1:1):: አዳኙን ክርስቶስን ማዕከል ስለሚያደርግ «የክርስቶስ ወንጌል» ነው (1:16):: የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት ስለሚያውጅም ጳውሎስ ይህን ወንጌል «በልጁ ወንጌል» ብሎታል (1:9):: በሮሜ 16:25-26 ጳውሎስ «ወንጌሌ» ብሎታል:: በዚህም ለቤተ ክርስቲያን አስተምህሮና አሕዛብ በእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ ስላላቸው ስፍራ የተለየ ትኩረት የሰጠ መሆኑን ለማመልከት ነው::

ወንጌል አዲስ መልእክት አይደለም፤ ከዘፍጥረት 3:15 ጀምሮ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ተጠቅሷል:: ነቢዩ ኢሳይያስ በምዕራፍ 1:8 እና በምዕራፍ 53 ና 55 ላይ ይህን ወንጌልን በትክክል ሰብኳል:: ዛሬ እኛ ተጠቃሚዎች የሆንንበት ደኅንነት ምንም እንኳን ነቢያት የሰበኩትንና የጻፉትን ነገር በሙላት ባይረዱትም ተስፋውን ግን አውጀዋል (1ኛ ጴጥሮስ 1:10-12)::

ኢየሱስ ክርስቶስ የወንጌል መልእክት እምብርት ነው:: ጳውሎስም ሰው፣ አይሁዳዊና የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነም ገልጾታል:: የተወለደውም ከዳዊት ወገንና ከድንግል በመሆኑ (ኢሳ. 7:14፤ ማቴ. 1:18-25)፣ በዳዊት ዙፋን ላይ እንዲቀመጥ ያስችለዋል:: ኢየሱስ ስለ ዓለሙ ሁሉ ኃጢአት ሞቶአል፣

ከሞትም ተነሥቶአል:: ወንጌል ጌታ በምትካችን የመሞቱንና ድል የተጎናጸፈበትን የትንሣኤ ታምራት የሚያካትት ሲሆን፣ ጳውሎስም የሰበከው ወንጌል ይህንኑ ነበር::

መ) *ለአሕዛብም የተላከ ነው* (1:5-7) - *ሚስዮናዊ የሚለው ቃል* በላቲን ቋንቋ «ሐዋርያ - የተላከ» ከሚለው ቃል ጋር አቻ ነው:: ምናልባት በሮም የነበረችው ቤተ ክርስቲያን አንድ ሳትሆን ብዙ ጉባዔዎች ነበሯት፣ ምክንያቱም ጳውሎስ በሮሜ 16 ላይ ለብዙ የቤት ለቤት ቤተ ክርስቲያናት ሰላምታ ጽፏል (16:5፣ 10፣ 11፣ 14):: እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት እንዴት እንደተጀመሩ በእርግጠኛነት ባናውቅም፣ በበዓለ ኀምሳ ቀን በኢየሩሳሌም የተገኙት ሮማውያን ወደ አገራቸው ሲመለሱ ያቋቋሟቸው ሳይሆኑ አይቀሩም (የሐዋ. 2:10):: ጳውሎስ በዚህ መልእክቱ አይሁድንም አሕዛብንም መጥቀሱ፣ እነዚያ ኅብረቶች አይሁድንም አሕዛብንም ያቀፉ እንደነበረ የሚያመለክት ነው:: (አይሁድ: 2:17-29፤ 4:1፤ 7:1፤ አሕዛብ: 1:13፤ 11:13-24፤ 15:15-21::) በሮም ያሉት አብያተ ክርስቲያናት የተመሠረቱት በጴጥሮስ ወይም በሌሎች ሐዋርያት አልነበረም:: እንደዚህ ቢሆን ኖሮ ሐዋርያት ወዳልደረሱበት ለመሄድ የተጠራው ጳውሎስ ሊጎበኛቸው ባሳወቀ ነበር (ሮሜ 15:20-21)::

«ለተጠራችሁ» የሚለው ቃል መደጋገሙን አስተውሉ:- ጳውሎስ ሐዋርያ ሊሆን ተጠርቷል፣ አማኞች ደግሞ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የተጠሩ ናቸው፣ ቅዱሳንም ተብለው ተጠርተዋል:: (ቅዱሳን «ለመሆን» አይደለም የተጠሩት፣ ቀድሞውኑም ቅዱሳን ናቸውና:: ቅዱስ ማለት የተለየ ማለት ነው:: አንድ ሰው በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ካመነ ይለያል እርሱም ደግሞ ቅዱስ ነው):: ደኅንነት እኛ ለእግዚአብሔር የምንሠራው ነገር አይደለም፤ ነገር ግን እርሱ እግዚአብሔር በጸጋው ይጠራናል (2ኛ ተሰ. 2:13-14):: በክርስቶስ ስታምኑ በጸጋው ትድናላችሁ፣ ሰላሙን ትለማመዳላችሁ::

የጳውሎስ ዋና ተልእኮ ወንጌልን ለአሕዛብ ማዳረስ ሲሆን፣ የአሕዛብ መናኸሪያ ወደሆነችው የሮማ ግዛት ሊሄድ ያሰበውም ለዚሁ ነበር:: እርሱ ወንጌል ሰባኪ ነው፣ ወንጌል ደግሞ የተሰጠው ለአሕዛብ ሁሉ ነው:: ለነገሩ፣ ጳውሎስ የክርስቶስን መልእክት ይዞ ወደ ስፔን ለመሄድ አስቦ ነበር (ሮሜ 15:28)::

እንዴት እንደ ተሾመ ካተተ በኋላ፣ ጳውሎስ በእርሱና በሮም በነበሩት አማኞች መካከል ያለውን ትስስር ያጠናክራል::

## 2. ጭንቀቱን ገለጸላቸው (1:8-15)

ጳውሎስ ለመሠረታቸው አብያተ ክርስቲያናት ግድ እንደሚለው በሚገባ እናውቃለን:: ነገር ግን በሮም ለነበሩት አማኞች ምን አሳሰበው? ብዙዎቹ ጳውሎስን ባያውቁትም እንኳ፣ እርሱ ስለ እነርሱ ደኅንነት ግን ግድ እንደሚለው ሊያረጋግጥላቸው ፈልጓል:: ጳውሎስ ግድ እንዳለው የሚያሳዩ መረጃዎችን እንመልከት::

ሀ) *ስለ እነርሱ አመሰገነ* (1:8) - «በዓለም ሁሉ» የሚለው የሚያመለክተው - የሮማን ግዛት በሙሉ ሲሆን፣ በሮም የነበሩት ክርስቲያኖች እምነት በዓለም ሁሉ ተሰምቷል:: «መንገዶች ሁሉ ወደ ሮም ያመራሉ» እንደሚባለው፣ በዚያን ዘመን ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ መጓጓዝ ይዘወተር ነበር:: ለዚህም ነበር የቤተ ክርስቲያኗ ምስክርነት በየስፍራው የተሰማው:: በዚህም ምክንያት ይህ አካባቢውን በማዳረስ ላይ የነበረ ምስክርነት ጳውሎስ ከቦታ ቦታ ካለ ብዙ ችግር በመነሣት እየተዘዋወረ ማገልገል እንዲችል እንደረዳው ግልጽ ነው:: ለዚህም ነው ይህንን ምስክርነት ያወሳው::

ለ) *ጸለየላቸው* (1:9-10) - ጳውሎስ በጸሎት እንዳገዛቸው ባያውቁም፣ ጌታ ግን አውቆታል፤ አክብሮታልም:: (ስንቶቻችን ስለ እኛ የሚጸልዩ ሰዎችን እናውቅ ይሆን?) ጳውሎስ ከነበሩት የጸሎት ሸክሞች አንዱ ወደ ሮም ሄዶ በዚያ ያሉትን አብያተ ክርስቲያናት ለማገልገል ነበር:: ቀደም ብሎ ሊጎበኛቸው ቢያስብም አገልግሎት ስለበዛለት ጊዜ አላገኘም ነበር (ሮሜ

15:15-33):: በኢየሩሳሌም ለነበሩት አይሁድ ቅዱሳን ከአሕዛብ አብያተ ክርስቲያናት የተሰበሰበውን ልዩ ስጦታ ሊያደርስ ከቆሮንቶስ ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ በዝግጅት ላይ ነበር:: በዚህም ከኢየሩሳሌም ወደ ሮም ከዚያም ወደ ስፔን የሚያደርገው ጉዞ የተሳካ እንዲሆን ተስፋ አድርጓል::

ለነገሩ፣ የጳውሎስ ጉዞ ከባድ መከራ የበዛበት ስለ ነበር፣ ወደ ሮም የገባው እሥረኛም ሰባኪም ሆኖ ነበር:: በኢየሩሳሌም በአይሁድ ባለሥልጣናት በሐሰት ክስ ስለተመሠረተበት በቤተ መቅደስ ውስጥ ታስሮ ነበር:: ከዚያም በቄሣር ፊት ለመቅረብ የንጉሡ እስረኛ ሆኖ ወደ ሮም ተላከ:: ጳውሎስ ይህንን መልእክት በጻፈበት ጊዜ እሥረኛ እንደሚሆንና ሮም ከመድረሱ በፊት የመርከብ መሰበር አደጋ እንደሚደርስበት አያውቅም:: በመልእክቱ መደምደሚያ (15:30-33) ላይ፣ በሮም የነበሩ አማኞች ስለአሰበው ጉዞ እንዲጸልዩ አሳስቧቸዋል:: መጸለያቸውም ለበጎ ነበር::

ሐ. *ይወዳቸዋል* (1:11-12) - «ላያችሁ እናፍቃለሁ!» ይህ በታላቁ ሚስዮናዊ ጳውሎስ ውስጥ የነበረ የእረኝነት ልብ ነው:: በሮም ከነበሩት ቅዱሳን አንዳንዶቹ የጳውሎስ የልብ ወዳጆች ነበሩ:: ለምሳሌ፣ ጵርስቅላና አቂላ ስለ ጳውሎስ በነፍሳቸው የተወራረዱ ነበሩ (16:3-4)፣ «የተወደደችው ጠርሲዳ» (16:12) ና ሌሎችም ከጳውሎስ ጋር መከራን የተቀበሉ ሁሉ የልብ ወዳጆቹ ነበሩ:: በተጨማሪም የማያውቃቸውንም አማኞች ይወዳቸዋል:: አንዳንድ መንፈሳዊ ስጦታን ሊያካፍላቸው ናፍቋል:: በክርስቶስ ፍቅር ያለውን በረከት አብሯቸው የሚካፈልበትን ጊዜ ናፍቋል::

መ. *የእነርሱ ዕዳ ነበረበት* (1:13-14) - የአሕዛብ ሐዋርያ እንደ መሆኑ መጠን ወንጌልን በሮም የመስበክ ግዴታ ነበረበት:: ይህንን ዕዳውን በጊዜ መወጣት ነበረበት:: ነገር ግን ሌሎቹ ተግባራት ይህ እንዳይሆን አዘገዩት:: አንዳንድ ጊዜ በሰይጣን ውጊያ ዕንቅፋት ይገጥመው ነበር (1ኛ ተሰ. 2:17-20)፤ እዚህ

ላይ ግን ያዘገየው የጌታ ሥራ ነበር። በእስያና በግሪክ ብዙ ሥራ በመኖሩ ወደ ሮም ለመሄድ ጊዜ አልነበረውም። ነገር ግን ጳውሎስ ወንጌል የመስበክ ዕዳውን በሮምም መወጣት ነበረበት፣ ከጌታ ትእዛዝን ተቀብሏልና።

ግሪኮች ግሪካዊ ያልሆነን ሰው እንደ አረመኔ ነበር የሚቆጥሩት። በፍልስፍና ለዘመናት የታወቁ በመሆናቸው ግሪኮቹ ራሳቸውን እንደ ጠቢባን ሌሎችን ደግሞ እንደማያስተውሉ ይቆጥሩ ነበር። እኛ ለዓለም ሁሉ ሸክም ሊሰማን እንደሚገባ ሁሉ፣ ጳውሎስም ስለ ሰው ሁሉ ግድ ይለው ነበር። በክርስቶስ ያለውን የደኅንነት የምስራች አቅሙ የቻለውን ያህል ለሰዎች ካልተናገረ፣ ከተጣለበት ዕዳ ነፃ አይሆንም።

*ሠ. ሊጎበኛቸው ጓጉቷል* (1:15) - በግሪክ ቋንቋ «ተዘጋጅቻለሁ» የሚለው ቃል ሁለት ዓይነት ትርጓሜ አለው። አንደኛው፣ በሐዋርያት ሥራ 21:13 እንደ ተገለጸው «ለመሞት እንኳ ተሰናድቼአለሁ» የሚለው መሰናዳትን ሲገልጽ፤ ሁለተኛው ደግሞ፣ በሮሜ 1:15 እንደ ተጻፈው «በሙሉ ልቦና» ለመሄድ መቁረጡን ያሳያል። ጳውሎስ ለመሞት ቢዘጋጅም፣ ለመሞት ግን አልጓጓም። የጓጓው በሮም ያሉትን አማኞች ሊጎበኛቸውና ሊያገለግላቸው ነበር። የእርሱ ጉጉት እነርሱንና አገራቸውን ለማየት ሳይሆን፣ ነፍሳትን ለመማረክ ነበር።

የሮም ቅዱሳን ጳውሎስ ለሮም ክርስቲያኖች ግድ እንደሚለው የሚገልጹትን እነዚህን አምስት ማስረጃዎችን ሲያነቡ፣ ጳውሎስ ስለ እነርሱ ላለው ሸክምና የፍቅር አገልግሎት ስለ እርሱ እግዚአብሔርን ከማመስገን ውጭ የሚሉት ነገር አልነበረም። ጳውሎስ ለሮማውያን በጻፈው መልእክቱ የሚሰብከውን ወንጌል ምንነት መግለጹ አማኞቹን ለጉብኝቱ የሚያዘጋጅበት መግቢያ ነበር። በዚህ ጊዜ የስሕተት አስተማሪዎች ወደ ሮም ገብተው በዚያ ያሉትን ክርስቲያኖች በጳውሎስ ላይ በክፉ ለማስነሣት መሻታቸው አይጠረጠርም (ሮሜ 3:8)። አንዳንዶች ሕግን እንደሚቃወም አድርገው ይከሱታል፤ ሌሎች ደግሞ ይሁዲነትን

እንደ ካደ ይናገራሉ:: አንዳንዶች ደግሞ ስለ ጸጋ የሚያስተምረውን ትምህርት እያጣመሙ በኃጢአት መኖርን ያበረታታል ይሉ ነበር:: በዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ጳውሎስ ወደ ሮም ለመሄድ መናፈቁ የሚያስገርም አይደለም:: የክርስቶስን የወንጌል ሙላት ሊያካፍላቸው ወዷል::

ነገር ግን የክርስቶስ ወንጌል በሌሎች ቦታዎች ውጤታማ እንደሆነ ሁሉ፣ በታላቋ የሮም ከተማ ውስጥስ ይሠራ ይሆን? ጳውሎስስ ይሳካለት ወይስ አይሳካለት ይሆን? ሐዋርያው ያለምንም ጥርጥር እነዚህ ጥያቄዎች በሕሊናው ውስጥ በመነሣታቸው ነው በእርሱና መልእክቱን በጻፈላቸው ሰዎች መሐል ሦስተኛ የመገናኛ መንገድ ያበጀው::

## 3. መተማመኑን አረጋገጠላቸው (1:16-17)

እንዴት ድንቅ ምስክርነት ነው:- «ዕዳ አለብኝ! ተዘጋጅቼአለሁ! አላፍርም!» ለመሆኑ ጳውሎስ ወደ ሮም ለመጓዝ ካሰበ በኋላ ስለ ኃፍረት የሚፈተነው ለምንድን ነው? አንዱና ምክንያት፣ ወንጌል የሚታወቀው ስለ አንድ ድሃ አይሁዳዊ ዐናፂ ስቅለት በመናገሩ ነው:: ሮማውያን አይሁዳውያንን ብዙም አያደንቋቸውም፣ በተጨማሪም በስቅላት መሞት አንድ ወንጀለኛ የሚገደልበት መንገድ ነው:: ስለሆነም ተሰቅሎ በሞተ አይሁድ እንዴት አድርገው ይታመናሉ?

ሮም ትምክህተኛ ከተማ ናት:: ወንጌል ደግሞ የመጣው ሮማውያን ድል አድርገው ከተቆጣጠሯቸው ትንንሽ አገሮች መካከል ከሆነችው ከኢየሩሳሌም ነው:: የዚያን ዘመን ክርስቲያኖች ደግሞ የማኅበረሰቡ ቁንጮዎች (ምሁራን ክፍል) አልነበሩም:: ተራ ሰዎች እንዲያውም ባሪያዎች ነበሩ:: ሮም ደግሞ ብዙ ፈላስፋዎችንና ፍልስፍናን ያውቃሉ:: ታዲያ ከሞት ስለተነሣ አንድ አይሁዳዊ ምን ግድ ይላቸዋል? (1ኛ ቆሮ. 1:18-25) ክርስቲያኖች እርስ በርሳቸው በክርስቶስ አንድ ሆነው እንደ እኅትና ወንድም መተያየታቸው ከሮማውያን ኩራትና ክብር

ልማድ ውጭ ነበር። አንድ ትንሽ ድንኳን ሰፊ ወንጌልን ሊሰብክ ወደ ሮም እንደሚሄድ ማሰቡማ ጭራሽ ቀልድ ይመስላል።

ነገር ግን ጳውሎስ በወንጌል አላፈረም! በመልእክቱ ድፍረት የነበረው ሲሆን፣ የማያፍርበትን ብዙ ምክንያቶችን ደግሞ በዝርዝር አቅርቦልናል።

*ሀ) የወንጌል አመጣጥ:* ወንጌሉ የክርስቶስ ወንጌል ነው (1:16) - ከቄሣር የሚወጣ ሕግ ሁሉ የሮማውያንን ትኩረት ያገኛል። ነገር ግን የወንጌል መልእክት የመጣውም ሆነ የሚናገረው ስለ እግዚአብሔር ልጅ ነው! በመግቢያ ዐረፍተ ነገሩ ላይ ጳውሎስ ይህንን መልእክት «የእግዚአብሔር ወንጌል» (1:1) ብሎ ጠርቶታል። መልእክቱ ከእግዚአብሔር ከመጣና የመልእክቱም ማዕከል ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሆነ ጳውሎስ ለምን ያፍርበታል?

የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ሳለሁ፣ የትምህርት ቤታችንን ቢሮ እንድጠብቅ ተመርጬ ነበር። ሌሎቹ ጠባቂዎች በሕንፃው የተለያዩ ክፍሎች ቢመደቡም፣ እኔ ግን የትምህርት ቤቱ ዋና ቢሮ በር ላይ ነበር የምቀመጠው። በዚህም ምክንያት ጠቃሚ መልእክቶችን ለተለያዩ መምህራንና ሠራተኞች እንዲሁም አንዳንዴ ለሌሎች ትምህርት ቤቶች አደርስ ነበር። በትምህርት ክፍለ ጊዜ አቋርጦ መልእክት ማድረስ እንዴት ያስደስታል መሰላችሁ? ከርእሰ መምህሩ መልእክት ይዤ እንደምመጣ መምህራን ስለሚያውቁ ዘልፈውኝ አያውቁም። መልእክቱ ከየት እንደመጣ ስለማውቅ ፍርሃትና ኃፍረት ተሰምቶኝ አያውቅም።

*ለ) የወንጌል ዘመቻ:* ወንጌል የእግዚአብሔር ኃይል ነው (1:16) - ስለምን በወንጌል ኃይል እናፍራለን? ሮም ስትኩራራ የነበረው ኃይሏን ተማምና ነው። ለግሪክ ሰዎች ትምክህታቸው ፍልስፍናቸው ይሆናል። ለሮም የነበረው ፍርሐት በግዛቷ ሁሉ ላይ እንደ ደመና ሠፍሮ ነበር። አሸናፊዎቹ እነርሱ አልነበሩም? በዚያ ዘመን በታወቀው የዓለም ክፍል ሁሉ የሠፈሩት አዕላፋት ሮማውያን አልነበሩምን? ነገር ግን ሮም ይህ ሁሉ የጦር ኃይል እያላት ደካማ ነበረች። ሴኔካ የተባለው ፈላስፋ የሮምን ከተማ

«በደል ማጠራቀሚያ ጉድጓድ» ብሎ ሲጠራት፣ ጸሐፊው ጁቨናል ደግሞ «የግዛቱ አተላ የሚያልፍበት ቆሻሻ ቧንቧ» ብሏታል።

ጳውሎስ ያለማፈሩ አያስደንቅም፣ ምክንያቱም ሰዎችን የመለወጥ ኃይል ያለውን መልእክት ይዞ ኃጢአተኛ ወደ ሆነችው ሮም እየሄደ ነበር። ጳውሎስ ወንጌልን እንደ ቆሮንቶስና ኤፌሶን በመሳሰሉ በክፋት የተሞሉ ከተሞች ሲሠራ አይቷል። ከዚህም የተነሣ በሮም እንደሚሠራም እምነት ነበረው። የራሱን ሕይወት ለውጦት ስላየ፣ የሌሎችንም ሕይወት እንደሚለውጥ ተገንዝቧል። ጳውሎስ በወንጌል ያላፈረበት ሦስተኛ ምክንያትም አለ።

ሐ. *የወንጌል ውጤቱ:* ለሚያምኑ ሁሉ የእግዚአብሔር ኃይል ለማዳን ነውና (1:16) - *«መዳን»* የሚለው *ቃል* በእነጳውሎስ ዘመን ብዙ ትርጉም ነበረው። *መሠረታዊ* ትርጉሙ «አርነት» ሲሆን፣ ከግለሰብ እና ከአገር ጋር የሚያያዝ ነው። ከበሽታ የሚያድናችሁን ሐኪም እንደምታዩት ሁሉ፣ ንጉሥም እንደ አርነት አውጪ ነበር የሚወሰደው። ወንጌል ኃጢአተኞችን ከኀጢአት ቅጣትና ኃይል ነፃ ያወጣል። በዚህ መልእክት መዳን (ደኅንነት) ዋናው አሳብ ነው። «ደኅንነት» ለሰው ዘር በጣም አስፈላጊ ነው። (ሮሜ 10:1፤9-10ን ተመልከቱ)። ወንዶችና ሴቶች ለመዳን የሚችሉት በወንጌል እንደታወጀው በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ነው።

መ. *በወንጌል መድረስ:* «ለሚያምን ሁሉ» (1:16) - ይህ መልእክት ለአይሁድ ወይም ለአሕዛብ ብቻ አልነበረም። ሰዎች ሁሉ መዳን ስላለባቸው ለሰው ዘር በሙሉ ነው። «ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ስበኩ» የሚለው የክርስቶስ ትእዛዝ ነው (ማር. 16:15)። «መጀመሪያ ለአይሁድ» ማለቱ አይሁዳውያን ከአሕዛብ መሻላቸውን አይገልጥም። በፍርድም ሆነ በደኅንነት «ልዩነት የለምና» (ሮሜ 2:6-11፤ 10:9-13)። በኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎት (ማቴ. 10:5-7) እና በሐዋርያት አገልግሎት (የሐዋ. 3:26) ወንጌል በመጀመሪያ ለአይሁድ መጣ። ወደ ሰዎች

ሁሉ የሚደርስ ኃይል ያለው መልእክት ማግኘት እንዴት ድንቅ ነገር ነው!

እግዚአብሔር ሰዎችን የጠየቀው ጥሩ ባሕርይ እንዲኖራቸው ሳይሆን፣ እንዲያምኑበት ነው። ኃጢአተኛውን የሚያድነው በክርስቶስ ያለው እምነቱ ነው። በሕይወታቸው የትም ደረጃ ላይ ቢደርሱና ፍላጎታቸው የቱንም ያህል ቢሆን፣ ለሰዎች ሁሉ የሚሆን ስጦታ በክርስቶስ የሚገኘው የዘለዓለም ሕይወት ነው።

ሮሜ 1:17 የሮሜ መልእክት ቁልፍ ጥቅስ ነው። በዚህም ጳውሎስ «የእግዚአብሔር ጽድቅ» ብሎ አውጆታል። «ጽድቅ» የሚለው ቃል በዚህ መልእክት ብቻ በቀጥታና በተዘዋዋሪ ከስልሳ ጊዜ በላይ ተጠቅሷል። የእግዚአብሔር ጽድቅ በወንጌል ተገልጧል። በክርስቶስ ሞት እግዚአብሔር ጽድቁን፣ ኃጢአትን መቅጣቱን በክርስቶስ ትንሣኤም ለሚያምኑ ኃጢአተኞች ደኅንነት በማቅረብ ጽድቁን ገልጧል። «ቅዱስ እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን ሳይቀጣ ይቅር እያለ እንዴት ቅዱስ ሊሆን ይችላል?» ለሚለው ጥያቄ መልስ ያገኘው በወንጌል ነው። በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ እግዚአብሔር «ጻድቅና አጽዳቂ» እንደሆነ ታይቷል (ሮሜ 3:26)።

ወንጌል በእምነት የሆነውን ጽድቅ ይገልጣል። በብሉይ ኪዳን ጽድቅ በሥራ ስለነበር ኃጢአተኞች ደግሞ የእግዚአብሔርን ሕግ በመጠበቅ የጽድቅ መመዘኛውን እንደሚያሟሉ ተገነዘቡ። በዚህ ስፍራ ጳውሎስ ዕንባቆም 2:4ን ይጠቅሳል፣ «ጻድቅ በእምነት ይኖራል።» ይህ ጥቅስ በአዲስ ኪዳን ሦስት ጊዜ ተጠቅሷል፤ ሮሜ 1:17፣ ገላትያ 3:11 እና ዕብራውያን 10:38። ሮሜ የሚያብራራው «ጽድቅ» የሚለውን፣ ገላትያ የሚያብራራው «በሕይወት መኖር» የሚለውን ሲሆን፣ ዕብራውያን «በእምነት ብቻ» የሚለውን ነው። እምነትና አለማመንን በተመለከተ ከ60 (ከስልሳ) በላይ ማጣቀሻዎች ተጽፈዋል፣ ምክንያቱም ኃጢአተኛ በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ የሚሆነው «በእምነት» ብቻ ነውና።

ጳውሎስ በዚህ ቦታ የመልእክቱን ዝርዝር ቢጽፈው ኖሮ፣ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን መልክ ሊይዝ ይችል ነበር፡-

*ዋና ሐሳብ፡-* የእግዚአብሔር ጽድቅ

*ምንባብ፡-* «ጻድቅ በእምነት ይኖራል»

*መግቢያ* - 1:1-17

I) ኃጢአት - *የጽድቅ አስፈላጊነት* 1:18-3:20

1. የአሕዛብ በደል - 1:18-32
2. የአይሁድ በደል - 2:1-3:8
3. የመላው ዓለም በደል-3:9-20

II) ደኅንነት - *ጽድቅ ሲታወጅ* 3:21-5:21

1. የጽድቅ መሠረት ሲጣል 3:21-31
2. ጽድቅ በአብርሃም ምሳሌነት - 4
3. ጽድቅ በአዳም ምሳሌነት - 5

III) መቀደስ - *ጽድቅን መታደግ* 6-8

1. ድል-*ሥጋን* - 6
2. ከሕግ ነፃ መውጣት - 7
3. በመንፈስ መጠበቅ- 8

IV) ሉዓላዊነት - የጽድቅ ማሽቆልቆል 9-11

1. የእስራኤል ያለፈው ሀብቷ- 9
2. የእስራኤል መገፋት - 10
3. የእስራኤል የወደፊት መታደስ - 11

V) አገልግሎት - ጽድቅ ሲገለጥ 12:1-15:7

1. በቤተ ክርስቲያን አካል - 12
2. በማኅበረሰብ - 13
3. ለደካማው አማኝ - 14:1-15:7

*መደምደሚያ* - 15:8-16:27

ሮሜን ስታጠኑ፣ ወደ ፍርድ ዙፋን እየቀረባችሁ ነው። መጀመሪያ፣ ጳውሎስ አሕዛብንና አይሁዳውያንን ወደ ፍርድ ሳጥን የጠራቸው ቢሆንም፣ ሁሉም ግን በእግዚአብሔር ፊት

በደለኛ ሆነው ተገኙ:: ቀጥሎ እግዚአብሔር ያዘጋጀውን የደኅንነት መንገድ ገለጠ:: እርሱም «በእምነት የሚገኘው ጽድቅ» ነው:: በዚህ ስፍራ ለከሳሾቹ መልስ በመስጠት ለእግዚአብሔር የደኅንነት መንገድ ተሟገተ:: ሰዎቹም፣ «የዚህ ዓይነቱ የደኅንነት ዕቅድ ሰዎችን ለኃጢአት ያበረታታል» ብለው ጮኹ:: «የእግዚአብሔርን ሕግ ይቃወማል» አሉ:: ነገር ግን ጳውሎስ ተሟገተና ረታቸው:: በዚህም ክርስቲያን ድልን፣ ነጻነትንና፣ ደኅንነትን እንዴት እንደሚለማመድ ገለጠላቸው::

ከምዕራፍ 9-11 ያለው ክፍል በቅንፍ የተቀመጠ አይደለም:: በሮም ጉባኤ ውስጥ የነበሩት አይሁድ አማኞች ስለነበሩ «የእስራኤልስ ጉዳይ?» «ለመሆኑ በዚህ አዲስ የቤተ ክርስቲያን ዘመን የእግዚአብሔር ጽድቅ ለአይሁድ የሚደርሰው በምን ዓይነት መንገድ ነው?» ብለው መጠየቃቸው የማይቀር ስለሆነ፣ ጳውሎስ የእስራኤልን የቀድሞ፣ የአሁኑንና የወደፊት ታሪኳን አጠቃልሎ አቅርቧል::

ከዚያም በአንድ አማኝ ሕይወት የእግዚአብሔር ጽድቅ እንዴት በተግባር እንደሚገለጥ በማሳየት መልእክቱን ደምድሟል:: ይህም ለእግዚአብሔር በመስጠት ይጀመርና (12:1-2)፣ በቤተ ክርስቲያን በማገልገል ይቀጥላል (12:3-21)፣ ከዚያም ለመንግሥታት በመታዘዝ ነው (13:1-14) ይደመድማል:: በተጨማሪም፣ አይሁድና አሕዛብ፣ ብርቱና ደካማው እንዴት በመስማማትና በደስታ እንደሚኖሩ ነግሯቸዋል:: በመዝጊያውም ላይ (15:14-16:27)፣ ጳውሎስ የወደፊት ዕቅዱን በማሳወቅ ለወዳጆቹ ሰላምታ አቅርቧል::

ስታጠቃልሉት፣ የሮሜ መልእክት ለእኛ የሚናገረን እንዲህ ነው - «እንደሚገባ ኑሩ!» ከእግዚአብሔር፣ ከሌሎች ጋርና ከራስህ ጋር በአግባብ እንድትኖር ነው:: በእምነት የሚገኝ የእግዚአብሔር ጽድቅ እንደሚገባ እንድንኖር ያስችለናል:: ለሮም ይህ መልእክት ያስፈልጋት ነበር:: እንዲሁም ዛሬ ለእኛም እንደሚገባ ኑሩ ያስፈልገናል:: እንደሚገባ ኑሩ!

«እውነትን በዓመፃ በሚከለክሉ ሰዎች በኃጢአተኝነታቸውና በዓመፃቸው ሁሉ ላይ የእግዚአብሔር ቍጣ ከሰማይ ይገለጣልና፤ እግዚአብሔር ስለ ገለጠላቸው፣ ስለ እግዚአብሔር ሊታወቅ የሚቻለው በእነርሱ ዘንድ ግልጥ ነውና:: የማይታየው ባሕርይ እርሱም የዘላለም ኃይሉ ደግሞም አምላክነቱ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሠሩት ታውቆ ግልጥ ሆኖ ይታያልና፤ ስለዚህም እግዚአብሔርን እያወቁ እንደ እግዚአብሔርነቱ መጠን ስላላከበሩትና ስላላመሰገኑት የሚያመካኙት አጡ፣ ነገር ግን በአሳባቸው ከንቱ ሆኑ የማያስተውለውም ልባቸው ጨለመ::» (ሮሜ 1:18-20)

«ስለዚህ እግዚአብሔር ለሚያስነውር ምኞት አሳልፎ ሰጣቸው፣ ሴቶቻቸውም ለባሕርያቸው የሚገባውን ሥራ ለባሕርያቸው በማይገባው ለወጡ፤ እንዲሁም ወንዶች ደግሞ ለባሕርያቸው የሚገባውን ሴቶችን መገናኘ ት ትተው እርስ በርሳቸው በፍትወታቸው ተቃጠሉ፤ ወንዶችም በወንዶች ነውር አድርገው በስሕተታቸው የሚገባውን ብድራት በራሳቸው ተቀበሉ::

እግዚአብሔርን ለማወቅ ባልወደዱት መጠን እግዚአብሔር የማይገባውን ያደርጉ ዘንድ ለማይረባ አእምሮ አሳልፎ ሰጣቸው::» (ሮሜ 1:26-28)

«ስለዚህ፣ አንተ የምትፈርድ ሰው ሁሉ ሆይ፣ የምታመካኘው የለህም፤ በሌላው በምትፈርድበት ነገር ራስህን ትኰንናለህና፤ አንተው ፈራጁ እነዚያን ታደርጋለህና:: እንደዚህም በሚያደርጉት ላይ የእግዚአብሔር ፍርድ እውነተኛ እንደ ሆነ እናውቃለን:: አንተም እንደዚህ በሚያደርጉ የምትፈርድ ያንም የምታደርግ ሰው ሆይ፣ አንተ ከእግዚአብሔር ፍርድ የምታመልጥ ይመስልሃልን? ወይስ የእግዚአብሔር ቸርነት ወደ ንስሐ እንዲመራህ ሳታውቅ የቸርነቱንና የመቻሉን የትዕግሥቱንም ባለ ጠግነት ትንቃለህን? ነገር ግን እንደ ጥንካሬህና ንስሐ እንደማይገባ ልብህ የእግዚአብሔር ቅን ፍርድ በሚገለጥበት በቍጣ ቀን ቍጣን በራስህ ላይ ታከማቻለህ:: እርሱ ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው ያስረክበዋል፤» (ሮሜ 2:1-6)::

# 2

# እግዚአብሔር አሳልፎ ሲሰጥ

ሮሜ 1:18 ወደ እግዚአብሔር ፍርድ ቤት የሚያደርሰን ስለሆነ፣ ጳውሎስ «አንድ ጊዜ አድምጡ! አንድ ጊዜ አድምጡ! ዳኛው ተሰይመው የፍርድ ሥርዐቱ ተጀምሯል!» የሚሉትን አስፈሪ ቃላት መጠቀም ይችል ነበር:: የሮሜ ዋና አሳብ የእግዚአብሔር ጽድቅ ነው:: ነገር ግን ጳውሎስ በሰዎች ኃጢአተኝነት መጀመር ነበረበት:: ሰው ኃጢአተኛነቱን ካላወቀ፣ እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የሰጠውን ደኅንነት ሊያደንቅ አይችልም:: ጳውሎስ መሠረታዊውን የመጽሐፍ ቅዱስ ፈለግ ተከትሏል:: እርሱም በመጀመሪያ ሕግና ፍርድ፣ ቀጥሎ ደግሞ ጸጋና ደኅንነት::

በዚህ ክፍል ሰዎች ሁሉ ኃጢአተኛ መሆናቸውንና ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሚያስፈልጋቸው ለማስረገጥ ሦስት አዋጆችን አወጀ::

## 1. አሕዛብ በደለኞች ናቸው! (1:18-32)

ጳውሎስ በዚህ ስፍራ የሚቀባው ሥዕል መልካም አይደለም:: በቺካጎ ከተማ መኪና ሳሽከረክር የማልፈልጋቸው መንደሮች ስላሉ፣ ሌላ መንገድ ለመጠቀም እሞክራለሁ:: መንገድ ቀይሬ መሄዴ እነርሱን አይለውጣቸውም፤ አያጠፋቸውምም:: እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን የሚገልጽበት መንገድ ያማረ ባይሆንም፣ ከዚህ ግን ለማምለጥ አንችልም:: ይህ ክፍል ስለ አዝጋሚ ለውጥ (ሰው ከሌላ ዓይነት አካል በዕድገት እንደመጣ) የሚያስተምር አይደለም:: ነገር ግን በተቃራኒው ሰው በኃጢአት ምክንያት ከላይ ጀምሮ ወደታች በማሽቆልቆሉ ከአራዊት በታች መውረዱን የሚያስተምር ነው:: የሰውን አሳዛኝ ማሽቆልቆል የሚያመለክቱ አራት መለያዎች አሉ::

ሀ) *ዕውቀት* (1:18-20) - የሰው ታሪክ የሚጀምረው ሰው እግዚአብሔርን በማወቁ ነበር:: የሰዎች ታሪክ ጣዖታትን

የሚያመልክ የአውሬ ታሪክ በጊዜ ሂደት ውስጥ ተለውጦ አንድ እግዚአብሔርን ማምለኩን የሚተርክ አይደለም:: የሰው ልጅ ታሪክ ከላይ ካልነው ተቃራኒ ነው:: ሰው እግዚአብሔርን ማወቅ ቢጀምርም፣ ነገር ግን ከእውነት ተቀልብሶ እግዚአብሔርን ተወ:: እግዚአብሔር ራሱን ለሰው ልጅ በፍጥረት አማካይነት ገለጠ:: በዙሪያው ከሚያየው ዓለም በመነሣት የሰው ልጅ የማቀድ ጥበብና የመፍጠር ኃይል ያለው አምላክ እንዳለ ዐወቀ:: ሰውም ይህ ፈጣሪ ዘለዓለማዊ መሆኑን ዐወቀ፣ «የዘለዓለም ኃይሉ ደግሞም አምላክነቱ» (ቁ. 20)፣ እግዚአብሔር ፈጣሪ እንጂ ፍጡር አለመሆኑን ተረዳ:: እነዚህ ሁሉ የእግዚአብሔር ዕውነታዎች በፍጥረት ውስጥ የተደበቁ አይደሉም:: «ግልጥ ሆኖ ይታያልና» (ቁ. 20):: «ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ፣ የሰማይም ጠፈር የእጁን ሥራ ያወራል» [መዝ. (19):1]::

በቁጥር 18 ላይ «በሚከለክሉ» ተብሎ የተረጎመው ቃል «በሚጨቁኑ፣ በሚጫኑ» ተብሎ መተርጎም ይችላል:: ሰዎች የእግዚአብሔርን እውነት ቢያውቁም፣ ነገር ግን ይህ እውነት በሕይወታቸው እንዲሠራ አልፈቀዱለትም:: እግዚአብሔር እንዳይወቅሳቸውና እንደፈለጉ ለመኖር የእግዚአብሔርን እውነት ከለከሉ:: መጨረሻውም፣ እውነትን አንቀበልም በማለት (1:21-22)፣ እውነቱን በውሸት ለወጡ (1:25):: በፍጻሜውም፣ ሰው እውነትን ጥሎ በአስተሳሰቡና በኑሮው እንደ እንስሳ ሆነ::

ለ) *አለማወቅ* (1:21-23) - ሰው እግዚአብሔርን ማወቁ ግልጽ ነው:: ሆኖም እግዚአብሔርን እንደሚገባ ሊያውቀውና ሊያከብረው አልወደደም:: እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ስለሰጠው ሁሉ ሊያመሰግነውና የሚገባውን ክብር ሊሰጠው አልፈቀደም:: ሰው የእግዚአብሔርን ስጦታ ለመጠቀም ይፈልጋል፣ ነገር ግን ስለ ስጦታው ሊያመልከውና ሊያመሰግነው ፈቃደኛ አልነበረም:: ውጤቱም በአሳቡ ከንቱ የሆነና በልቡናውም የጨለመ ሆነ:: አምላኪ መሆን የሚገባው ሰው ፈላስፋ ሆነ:: ነገር ግን ከንቱ በሆነው ጥበቡ ሞኝነቱን ገለጠ:: ጳውሎስ የግሪክን ታሪክ

«ያለማወቅ ዘመን. . .» በሚል አንድ ቃል ይቋጨዋል (የሐዋ. 17:30)። ለዚህ ነጥብ 1ኛ ቆሮንቶስ 1:18-31ን ማንበቡ ይጠቅማል።

የእግዚአብሔርን እውነት እየከለከለ የእግዚአብሔርን ክብር ወደ ጎን በመተው ሰው ያለ አምላክ ቀረ። ከዚህም የተነሣ እውነተኛውን አምላክ የማያመልክ ከሆነ፣ የሐሰት አማልክትን ለማምለክ ይገደዳል- *የራሱንም ፈጥሮ ቢሆን እንኳን።* ይህ የሰው ባሕሪው ደግሞ ጣዖት የማምለክ ዝንባሌውን ያረጋግጣል። የሰው ልጅ የእውነተኛውን አምላክ ክብር ራሱ በሠራቸው አማልክት ለወጠ። ክብርን በውርደት ለወጠ፣ መልካም ምግባርን በምግባረ ብልሹነት፣ እውነትን ደግሞ በውሸት ለወጠ።

ማስተዋል ያለብን በሐሰተኛ አማልክት ተራ ከተሰለፉት መካከል ቅድሚያውን የሚይዘው ሰው ራሱ መሆኑን ነው። በዚህም ሰይጣን ለሔዋን፣ «እንደ እግዚአብሔር ትሆናላችሁ!» (ዘፍጥ. 3:5) ብሎ የነገራትን፣ «ክብር ለሰው በአርያም» የሰው ዘር እንዲል በማስቻል የሰይጣንን ዐላማ ያሳካል። ሰው በእግዚአብሔር አምሳል በመፈጠሩ ፋንታ፣ የሰው ልጅ በራሱ አምሳል አማልክትን ሠራ። በዚህም ዝቅ ብሎ አዕዋፍን፣ አውሬዎችንና ምናምንቴዎችን አመለከ።

ሐ. *የማይወደድ ተግባር መፈጸም* (1:24-27) - ጣዖት ከማምለክ ወደ ዐመፅ ለመራመድ የሚጠይቀው አጭር እርምጃ ብቻ ነው። ሰው የራሱ አምላክ ከሆነ፣ መሻቱንና ደስ የሚያሰኘውን ፍርድን ሳይፈራ መፈጸም ይችላል። ሰው የእግዚአብሔርን እውነት ሙሉ በሙሉ በመተው እውነቱን «በውሸት» በመለወጥ ከእግዚአብሔር እውነት ጋር በሚያደርገው ውጊያ ጡዘት ላይ ደርሷል። «ውሸቱም» ሰው የራሱ አምላክ ነው፣ በፈጣሪው ፋንታ ራሱን ማምለክና ማገልገል አለበት የሚል ነው። ይህን «ውሸት» በመጠቀም ነበር ሰይጣን ሔዋንን በዔድን ገነት ወደ ኃጢአት የነዳት፡- «እንደ እግዚአብሔር ትሆናላችሁ!» ሰይጣን ሁልጊዜ ለእግዚአብሔር የሚገባውን አምልኮ መውሰድ ይፈልጋል

(ማቴ. 4:8-10)። ጣዖታት ሲመለኩ ደግሞ አምልኮው ለእርሱ ነው (1ኛ ቆሮ. 10:19-21)።

የዚህ ራስን መለኮት የማድረጉ ፍሬ የማይገባውን ማድረግ ነው። በዚህ ስፍራ ጳውሎስ በዘመኑ የነበረውን የግብረሰዶም አስቃቂ ኃጢአት በእግዚአብሔር ቃል ተደጋግሞ ተወግዟል (ዘፍጥ. 18:20 ጀምሮ፣ 1ኛ ቆሮ. 6:9-10፣ ይሁዳ 7)። ጳውሎስ «አስነዋሪ» እና «ለባሕሪ የማይገባ» እንዲሁም «ከተፈጥሮ ሕግ ውጭ» ብሎ ገልጾታል። በዚህ ኃጢአት ወንዶች ብቻ ሳይሆኑ ሴቶችም ሕግን ጥሰዋል።

በዚህ ኃጢአታቸው ምክንያት «እግዚአብሔር አሳልፎ ሰጣቸው» (1:24፣26)፣ ይህም በኃጢአታቸው እንዲገፉበትና ፍሬያቸውንም እንዲያጭዱ ተዋቸው ማለት ነው። እነርሱም «በስሕተታቸው የሚገባውን ብድራት በራሳቸው ተቀበሉ» (1:27)። የሮሜ 1:18 ትርጉም ይህ ነው፣ «የእግዚአብሔር ቁጣ ከሰማይ ይገለጣልና. . .»። እግዚአብሔር ቁጣውን የገለጠው እሳት ከሰማይ በመላክ ሳይሆን፣ የማይገባቸውን ያደርጉ ዘንድ ለፍትወት አሳልፎ በመስጠት ነው። ነገር ግን አንድ ተጨማሪ ደረጃ አለ።

*መ. ንስሐ አለመግባት* (1:28-32)- ሰው የኃጢአቱን አስቃቂ ውጤት መጎንጨቱ ሲሰማው በንስሐ ተመልሶ እግዚአብሔርን ይፈልጋል ብላችሁ ታስቡ ይሆናል። ሆኖም የተገለጠው እውነታ የዚህ ተቃራኒ ነበር። ሰው በእግዚአብሔር ስለተተወ፣ ጭራሹኑ እየባሰበት ሄዶ እግዚአብሔርን ማወቁን እንኳ በሕሊናው ማሳየት አልፈለገም! በዚህም ምክንያት «ለማይረባ አእምሮ አሳልፎ ሰጣቸው» (1:28)። ይህም አእምሮው ትክክለኛው ፍርድ መስጠት ያለመቻሉን የሚያሳይ ነው። በዚህም ሰዎች ራሳቸውን ለኃጢአት አሳልፈው ሰጡ። ጳውሎስ 24 ኃጢአቶችን በስማቸው ዘርዝሯቸዋል፤ ዛሬ ሁሉም አብረውን አሉ። (ተጨማሪ ዝርዝር ለማየት ማር. 7:20-23፤ ገላ. 5:19-21፤ 1ኛ ጢሞ. 1:9-10 እና 2ኛ ጢሞ. 3:2-5ን ይመልከቱ)።

መልካም ያልሆነው ነገር ሊመጣ አለው:: ሰዎች እግዚአብሔርን በግልጽ ለመቋቋም ይህን ኃጢአት ራሳቸው ብቻ ሳይሆን ያደረጉት፤ ሌሎችም ሲፈጽሙት እያጨበጨቡ አበረታተዋል:: ሰው የወደቀው ምን ያህል ነው! እግዚአብሔርን በማክበር ጀምሮ ያንን ክብር ለጣዖታት በመለወጥ ፈጸመ:: እግዚአብሔርን በማወቅ ጀምሮ በልቡም ሆነ በአሳቡ የእግዚአብሔርን አምሳል ባለመቀበል ጨረሰ:: በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረ የፍጥረት ሁሉ ቁንጮ በመሆን ጀምሮ አራዊትን እንደ አማልክት በማምለኩ ከእንስሳት በታች ሆኖ ደመደመ:: ፍርዱ ታዲያ ምንድን ነው? «የሚያመካኙት አጡ!» (1:20)::

ይህ ምንባብ አረማውያን እንደጠፉ በቂ ማስረጃ ይሰጣል:: ዳን ክራውፎርድ የተባለ በአፍሪካ ያገለገለ እንግሊዛዊ ሚስዮናዊ እንደተናገረው፣ «አረማውያን ኃጢአትን የሚሠሩት እንደ ጎርፍ በሚወርድ ብርሃን ላይ ነው» ብሏል:: ለሰዎች ሁሉ ወንጌልን ልናደርስ የግድ ነው:: ምክንቱም የሚድኑበት መንገድ ይኸው ብቻ ነውና::

## 2. አይሁድ በድለዋል! (2:1-3:8)

የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች ጳውሎስ ሮሜ 2:1-16 ያለውን ክፍል ለማን እንደ ጻፈው በሚመለከት በአሳብ ይለያያሉ:: አንዳንዶቹ ጳውሎስ ይህንን የጻፈው በሮሜ 1:18-32 ያለውን ኃጢአት ለፈጸመ፣ ነገር ግን በጥሩ ሥነ ምግባር ለመኖር ለሚሻ አረማዊ ነው ይላሉ:: ለእኔ እንደሚመስለኝ ጳውሎስ የጻፈው ለአይሁዳውያን አንባቢዎቹ ነው:: በምዕራፍ 2:12-16 ስለ ሕግ ያቀረበው ሐተታ ከአሕዛብ ይልቅ ለአይሁዳውያን ትርጉም ይሰጣቸዋል:: በ2:17 ላይ በግልጽ አንባቢዎቹ «አይሁዳውያን» እንደሆኑ አስፍሯል:: በዚህ ስፍራ አይሁዳዊ በማለቱ በምዕራፍ 2 የመጀመሪያ ክፍል ላይ ለአሕዛብ የሚናገር ቢሆን ኖሮ አባባሉ እንግዳ ይሆን ነበር::

አይሁዳውያን ሕግ እንደ ጣሱ ማወቅ በጣም አስቸጋሪ ነው። ምክንያቱም እግዚአብሔርን ለመታዘዝ በተመለከተ አይሁዳውያን ሊናዘዙት የማይፈልጉት ነገር ነው። የብሉይ ኪዳን ነቢያት እስራኤልን ስለ ኃጢአቷ በመክሰሳቸው ተሰድደዋል። ኢየሱስም በዚሁ ምክንያት በመስቀል ተሰቅሏል። የአይሁድ ሕዝብ ሕግ መተላለፋቸውን ለማስረዳት ጳውሎስ አራት ምስክሮችን ይጠራል።

ሀ) *አሕዛብ* (2:1-3)- እርግጥ ነው ጳውሎስ አሕዛብን በሮሜ 1:18-32 ላይ ፍርድ እንደሚገባቸው በመናገሩ አይሁድ ይስማማሉ። በእርግጥ፣ የአይሁዳውያን የይሁዲነትና የሃይማኖታቸው ትምክህት አሕዛብን እንዲጠሏቸውና «እንደ ውሻ» እንዲያዩአቸው፣ እንደዚሁም ከእነርሱ ጋር ምንም ነገር እንዳያደርጉ ያበረታታል። ጳውሎስ እነዚህ በሌሎች ላይ የሚፈርዱ አይሁዳውያን አሕዛብን በሚፈርዱበት ነገር ራሳቸውም መጠመዳቸውን አረጋገጠባቸው። በእግዚአብሔር የተመረጡ ሕዝቦች በመሆናቸው ከእግዚአብሔር ፍርድ የሚያመልጡ መስሏቸው ነበር። ጳውሎስ ግን የአይሁድ በእግዚአብሔር መመረጥ ያለባቸውን ኃላፊነትና ተጠያቂነት የበለጠ እንደሚያደርገው አረጋገጠላቸው።

የእግዚአብሔር ፍርድ በእውነት ላይ የተመሠረተ ነው። ለአይሁድ አንድ መስፈርት ለአሕዛብ ደግሞ ሌላ መስፈርት የለውም። ሮሜ 1:29-32ን ያነበበ ሰው እያንዳንዱ ሰው ከተዘረዘሩት ኃጢአቶች ቢያንስ በአንዱ ከሕግ ተላላፊ ከመሆን እንደማያመልጥ ይገነዘባል። «ሥጋን የሚያረክሱና መንፈስን የሚያረክሱ» (2ኛ ቆሮ. 7:1) ኃጢአቶች አሉ፣ «አባካኝ ልጆች አሉ»፣ «ታላቅ ወንድሞችም» አሉ (ሉቃስ 15:11-32)። አይሁድ በአሕዛብ ኃጢአት ላይ ሲፈርዱ በራሳቸው እየፈረዱ ነው። ልክ ጥንት እንደተነገረው አባባል «አመልካች ጣትህን ወደ ሰው ስትጠቁም፣ የቀሩት ሦስቱ ጣቶችህ የሚያመለክቱት ወደ አንተው ነው።»

ሐ) *የእግዚአብሔር በረከት* (2:4-11) - አይሁድ ከእግዚአብሔር በተቀበሉት ስጦታ ያገኙት የተለየ እንክብካቤ ሳይሆን እነዚህ በረከቶች እርሱን ይታዘዙትና ያከብሩት ዘንድ ትልቅ ኃላፊነትን ነው የጣለባቸው። በቸርነቱ እግዚአብሔር ለእስራኤል ቁሳዊና መንፈሳዊ ሀብትን ሰጥቷቸዋል። እነርሱም አስደናቂ ምድር፣ ጽድቅን የተሞላ ሕግ፣ ቤተ መቅደስና ክሕነት፣ የእግዚአብሔር እንክብካቤና በጣም ብዙ በረከቶችን ጭምር ነበር። እግዚአብሔር የእስራኤልን ብዙ ኃጢአትና ዐመፅ ታግሶ እንደገና የገዛ ልጁ መሢሕ ይሆናቸው ዘንድ ላከላቸው። እስራኤላውያን ክርስቶስን ከሰቀሉት በኋላ እንኳ እግዚአብሔር ፍርዱን አቆይቶ ወደ አርባ ዓመት የሚጠጋ የጸጋ ዘመን ሰጣቸው። ሰዎችን ወደ ንስሐ የሚያቀርበው የእግዚአብሔር ፍርድ ሳይሆን፣ ደግነቱ ነው። ሆኖም እስራኤል በንስሐ አልተመለሰችም።

በሮሜ 2:6-11 ጳውሎስ ደኅንነት በመልካም ባሕርይ ወይም በመልካም ሥራ የሚገኝ መሆኑን እያስተማረ ሳይሆን፣ ሌላኛውን የእግዚአብሔር መሠረታዊ የፍርድ መመሪያ ሊያብራራ ፈልጎ ነው። እግዚአብሔር በእውነት እንደሚፈርድ ሁሉ፣ በሥራችን መጠን ነው የሚፈርደው። ጳውሎስ በዚህ ምንባብ የሚያተኩረው አንድ ሰው በሕይወቱ ስለሚፈጽማቸው ወጥ ድርጊቶች ነው፣ ይህም የባሕርይውና የፀባዩ ድምር ውጤት ይሆናል። ለምሳሌ፣ ዳዊት አስጸያፊ ኃጢአቶችን ፈጽሟል። ነገር ግን ሕይወቱን በአጠቃላይ ስናይ እግዚአብሔርን በመታዘዝ ላይ ያተኮረ ነበር። ይሁዳ ኃጢአቱን ተናዝዞ የወሰደውንም ገንዘብ ለመጻተኞች የቀብር ቦታ መግዥያ ሰጥቷል። ነገር ግን መላ ሕይወቱን ስንመዝን ባለመታዘዝና በጥርጥር የተሞላ ነበር።

አልፎ አልፎ ወቅታዊ መውደቅ ቢኖርም፣ እውነተኛና የሚያድነን እምነት በውጤቱ መታዘዝና እግዚአብሔርን መምሰል ነው። እግዚአብሔር የአይሁድን ሥራ ሲመዝነው፣ ከፋታቸው እንደ አሕዛብ ሆኖ አገኘነው። አይሁድ አልፎ አልፎ በዓላትን ቢያከብሩም፣ ሰንበትን ቢጠብቁም ዕለታዊ ኑሮአቸው ሲታይ ለእግዚአብሔር ባለመታዘዝ ላይ ያተኮረ መሆኑን

አይለውጠውም። የእግዚአብሔር በረከት ወደ ንስሐ አልመራቸውም።

ሐ) *የእግዚአብሔር ሕግ* (2:12-24)- ጳውሎስ በቁጥር 11 ላይ የተናገረው፣ «እግዚአብሔር ለሰው ፊት አይደላምና» አይሁድን ያስደነግጣቸዋል። ምክንያቱም ጳውሎስ ራሱ በእግዚአብሔር የተመረጠ በመሆኑ የተለየ ነገር እንደሚገባው አድርጎ ቆጥሯልና። ነገር ግን የአይሁድ ሕግ ኃጢአታቸውን እንዳበዛው ጳውሎስ አብራርቷል። እግዚአብሔር አሕዛብ በሕግ እንዳይጠየቁ ሕግን አልሰጣቸውም። ለአሕዛብ ሕጉ ማለትም «በዚህም ለአማልክት እስከ *መሥዋት* ድረስ» መንገድ እናገኛለን።

አይሁድ በሕግ ይታበያሉ። ጣዖታትን ከሚያመልከው አሕዛብ ባልንጀራው ራሱን የተሻለ አድርጎ ይቆጥራል። ነገር ግን ጳውሎስ ዋናው ነገር ሕግን ማወቁ ሳይሆን መጠበቁ እንደሆነ በግልጽ አስፍሮታል። አይሁድ አሕዛብን እንደ ዓይነ ስውር፣ በጨለማ እንዳሉ፣ ሞኝ፣ ያልበሰሉና አላዋቂ አድርገው ያዩአቸዋል። ሕግ ሳይኖራቸው የተጣሉት አሕዛብ ኃጢአተኛ ሆነው ከተገኙ፣ ሕግ ያላቸው አይሁድማ እንዴት የከፉ ኃጢአተኞች ናቸው! እግዚአብሔር የሚፈርደው በእውነትና (2:2) እንደ *ሥራችን* መጠን ብቻ ሳይሆን (2:6)፣ «በሰው ዘንድ የተሰወረውንም» ጭምር ነው (2:16)። እርሱ በልብ ያለውን ሁሉ ያያልና።

የአይሁድ ሕዝብ የነበራቸው ሃይማኖት በውስጣቸው ያለውን አስተሳሰብ የሚያጠራ ሳይሆን፣ ውጫዊ ድርጊት ላይ የሚያተኩር ነበር። በውጫዊ ድርጊታቸው ምናልባት መልካም ይሆኑ ይሆናል፣ ነገር ግን ልባቸውስ? ጌታችን በማቴዎስ 23 ላይ በፈሪሳውያን ላይ ያቀረበው ክስ ለዚህ መርህ ጥሩ ምሳሌ ይሆነናል። እግዚአብሔር የሚያየው የተገለጠ *ሥራን* ብቻ ሳይሆን፣ የሚታሰበውንና በልብ ውስጥ ያለውን ሁሉ ነው (ዕብ. 4:12)። ማንኛውም አይሁድ ሰው ባያየውም ሊሠርቅ፣ ሊዘሙት፣ ጣዖትን ሊያመልክ ይችላል (ዕብ. 4:12)። በተራራው

ስብከት ሰው እንደዚህ ዓይነት ኃጢአቶችን በልቡ ሊፈጽም እንደሚችል ተነግሮናል።

በአሕዛብ መካከል እግዚአብሔርን በማክበር ፈንታ፣ አይሁዳውያን እግዚአብሔርን አዋረዱ፣ በዚህም ምክንያት ጳውሎስ ይህን ሥራቸውን ለማስረገጥ ኢሳይያስ 52፡5ን ጠቀሰ። አረማውያን አሕዛብ ከአይሁድ ጋር በንግድና ለሎች ምክንያቶች ይገናኙ ነበር። ነገር ግን በአይሁድ ሕግ አክባሪነት ተታልለው አያውቁም። አይሁድ አሕዛብ እንዲታዘዙለት የወደዱት ሕግ መልሶ እነርሱኑ ከሰሳቸው።

*መ) ግርዘት* (2:25-29) - ግርዘት የቃል ኪዳን ምልክት ሲሆን፣ የተጀመረውም የአይሁድ ሕዝብ አባት በሆነው አብርሃም ነበረ (ዘፍጥ. 17)። አሕዛብ ለአይሁድ «ያልተገረዙ ውሾች» ናቸው። የሚያሳዝነው አይሁድ ይህ ምልክት ከሚወክለው መንፈሳዊ እውነታ ይልቅ ለአካላዊ ምልክት መገዛታቸው ነው (ዘዳግ. 10፡6፤ ኤሬ. 9:26፤ ሕዝ. 44:9)። እውነተኛ አይሁድ ውጫዊና አካላዊ ቀዶ ጥገና የተደረገለት ሳይሆን፣ በልቡ ውስጣዊ መንፈሳዊነት ያለው ነው። ዛሬም ሰዎች ጥምቀትን ወይም የጌታን እራትን ወይም የቤተ ክርስቲያን አባልነትን በተመሳሳይ መልኩ እየተመለከቱ ሲሳሳቱ እናያለን።

እግዚአብሔር በውጫዊ ሥርዓት ብቻ አይማረክም። ፍርዱም እግዚአብሔር በሰው ልብ በተሰወሩት ምሥጢራት ላይ ተመርኩዞ ይፈርዳል (ሮሜ 2:16)። ከማይታዘዝ የተገረዘ አይሁድ ይልቅ ያልተገረዘ ታዛዥ አሕዛብ ተቀባይነት ይኖረዋል። እግዚአብሔር ልብን ስለሚያይ የተገረዘና የማይታዘዝ አይሁድ መገረዙን በእግዚአብሔር ዓይን ወደ አለመገረዝ ይለውጠዋል። አይሁድ ሕግን ስለመታዘዛቸው እርስ በርሳቸው ይወዳደሳሉ። ነገር ግን ትልቁ ነገር «የእግዚአብሔር ምሥጋና» እንጂ የሰው ምሥጋና አይደለም (ቁ. 29)። «አይሁድ» የሚለው ስም «ይሁዳ» ከሚል ቃል የመጣ ሲሆን፣ ትርጉሙም «ምሥጋና» ማለት

ነው። ከላይ ያየነው ዐረፍተ ነገርም አዲስ ትርጉም ተሰጥቶታል (ዘፍጥ. 29:35፣ 49:8)።

አራቱም የጳውሎስ ምስክሮች ይስማማሉ። አይሁድ በእግዚአብሔር ፊት ሕግን ተላልፈዋል። በሮሜ 3:1-8 ጳውሎስ ክርክሩን በማጠቃለል ሊሞግቱት የሚሞክሩት አይሁድ ትክክል አለመሆናቸውን ያስረዳል። እነርሱ ሦስት ጥያቄዎችን አነሡ። (1) «እንግዲህ የአይሁዳዊ ብልጫው ምንድን ነው?» መልሱም፣ በሁሉ ነገር ብዙ ነው አስቀድሞ የእግዚአብሔር ቃል አደራ ተሰጣቸው። (2) «አይሁድ አለማመናቸው የእግዚአብሔርን ታማኝነት ያስቀራልን? መልስ፣ በፍጹም፣ እንዲያውም ያጸናዋል። (3) «ዐመፃችን የእግዚአብሔርን ጽድቅ የሚያስረዳ ከሆነ ምን እንላለን? እግዚአብሔር እንዴት ይፈርድብናል?» መልስ፣ መልካም እንዲመጣ ክፉ አናደርግም። እግዚአብሔር በዓለም ላይ በቅንነት ይፈርዳልና።

## 3. ዓለሙ ሁሉ በደለኛ ነው ! (3:9-20)

ሦስተኛው ዐዋጅ ግልጽ ነው፣ ምክንያቱም ጳውሎስ አይሁድና አሕዛብ በእግዚአብሔር ፊት በደለኞች መሆናቸውን አስረድቷልና። በመቀጠል የሰው ዘር በሙሉ ኃጢአተኛ ስለ መሆኑ ከብሉይ ኪዳን ብዙ ምንባቦችን በመጥቀስ አስረድቷል። «ሁሉም» እና «ማንም» የሚሉትን ቃላት ድግግሞሽ አስተውሉ። እነዚህም በደለኝነት በሰው ሁሉ ዘንድ የሚገኝ ወይም ዓለም ዐቀፋዊ ይዘት ያለው መሆኑን ያስረግጣሉ።

የመጀመሪያው ጥቅስ የተወሰደው ከመዝሙር 14:1-3 ነው። ይህ መዝሙር የሚጀምረው «ሰነፍ በልቡ እግዚአብሔር የለም ይላል» በሚለው ነው። አስተካክለን ስንጽፈው የሚከተለውን ትርጉም ይሰጣል። «ሰነፍ በልቡ፣ <እግዚአብሔርን የለም> አለ።» ይህም በሮሜ 1:18-32 ባለው ክፍል ላይ እንደተገለጸው የሰውን በተቃራኒ አቅጣጫ መጓዝ በአንጻራዊነት ይገልጻል።

እነዚህ ቁጥሮች የሚያመለክቱት የሰው ውስጣዊ ሰብዕናው በሞላ በኃጢአት ቁጥጥር ሥር መዋሉን ነው። ይህም አእምሮው

(አይገነዘብም)፣ ልቡ (እግዚአብሔርን አይፈልግም)፣ ፈቃዱም (ደግ ነገር አይሠራም) ጭምር ለኃጢአት ተገዝቷል ማለት ነው:: በእግዚአብሔር ፍጹም ጽድቅ ሲለካ፣ ከኃጢአት የነጸ የሰው ዘር የለም:: ማንም ኃጢአተኛ እግዚአብሔርን አይፈልግም:: ስለሆነም እግዚአብሔር ኃጢአተኛውን መፈለግ ነበረበት (ዘፍጥ. 3:8-10፤ ሉቃስ 19:10):: ሰው በተሳሳተ መንገድ በመጓዙ ለራሱም ሆነ ለእግዚአብሔር የተረፈው ነገር የለም :: በሉቃስ 15 የተዘገበው የጌታችን ምሳሌ ይህን ጉዳይ ግሩም አድርጎ ያብራራዋል::

ከቁጥር 13-18፣ ጳውሎስ በአንድ ኃጢአተኛ ላይ ከራስ ፀጉሩ እስከ እግር ጥፍሩ ድረስ የተደረገውን የራጅ ምርምራ አቅርቦልናል:: የተወሰዱት ጥቅሶች የሚከተሉት ናቸው ቁ. 13 ሀ. - ከመዝሙር 5:9፤ ቁ. 13 ለ- ከመዝሙር 14:3፤ ቁ. 14- ከመዝሙር 10:7፤ ቁ. 15-17- ከኢሳይያስ 59:7-8፤ ቁ. 18 - ከመዝሙር 36:1 ናቸው:: ሙሉውን ሐሳብ ለመረዳት እነዚህ ምንባቦች በዐውዳቸው መነበብ አለባቸው::

ቁ. 13ና 14 ጉሮሮ፣ ምላስ፣ ከናፍርና አፍን በመጠቀም ስለ ሰው ንግግር አጽንኦት ይሰጣል- ማለትም የቃላትና የባሕርይ ትስስር በማቴዎስ 12:34 ታይቷል:: «በልብ ሞልቶ ከተረፈው አፍ ይናገራልና::» ኃጢአተኛው በፍጥረቱ በመንፈስ ሙት ነው (ኤፌ. 2:1-3)፣ ስለሆነም ከአንደበቱ የሚወጣው ሞት ብቻ ነው:: ይህ የተፈረደበት አንደበት ተለውጦ «ኢየሱስ ጌታ» መሆኑን ያውጃል (ሮሜ 10:9-10):: «ከቃልህ የተነሣ ትጸድቃለህና፣ ከቃልህም የተነሣ ትኰነናለህ» (ማቴ. 12:37)::

በቁጥር 15 ና 16 ጳውሎስ የኃጢአተኛውን እግር በሥዕላዊ መልኩ ያቀርባል:: ቃሎቹ አታላዮች እንደሆኑ ሁሉ፣ መንገዶቹም የጥፋት ናቸው:: የክርስቲያን እግሮች የሰላም ወንጌልን የተጫሙ ናቸው (ኤፌ. 6:15)፤ ሙት ኃጢአተኛ ግን በሚሄድበት ሁሉ ሞትን፣ ጥፋትን፣ ጉስቁልናን ያመጣል:: እነዚህ አሰቃቂ ነገሮች ምናልባት ወዲያው ባይፈጸሙም፣ መምጣታቸው ግን አይቀሬ ነው:: ኃጢአተኛ ወደ ጥፋት በሚወስደው ሰፊ ደጅ ላይ ነው

(ማቴ. 7:13-14)፤ ንስሐ ሊገባ፣ ኢየሱስ ክርስቶስን ሊያምንና ወደ ሕይወት በሚመራው ጠባብ ደጅ ሊገባ ያስፈልገዋል::

ቁጥር 17 የኃጢአተኛን ሕሊና ይዳስሳል: የእግዚአብሔርን የሰላም መንገድ አያውቅም:: ጌታ ኢየሱስን ለኢየሩሳሌም እንዲያለቅስለት ያደረገው ይኸው ነበር (ሉቃስ 19:41-44):: ኃጢአተኛ የእግዚአብሔርን እውነት በማወቅ ፈንታ (ሮሜ 1:21፤25፤28)፣ የሰይጣንን ውሸት ማመን ይመርጣል:: የእግዚአብሔር የሰላም መንገድ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት የሚገኝ ነው፣ «እንግዲህ በእምነት ከጸደቅን በእግዚአብሔር ዘንድ ቤጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምን እንያዝ» (ሮሜ 5:1)::

በቁጥር 18 መዝሙር 36:1ን ጠቅሶ የኃጢአተኛን ከንቱ ትዕቢት ይገልጣል፣ «በዓይኖቻቸው ፊት እግዚአብሔርን መፍራት የለም::» ሙሉ ገጽታውን ለማግኘት መዝሙሩን በሙሉ ማንበብ ያስፈልጋል:: በሮሜ 3:17 የተጠቀሰው አለማወቅ ምክንያቱ በቁጥር 18 ላይ የተዘገበው ትዕቢት ነው:: የጥበብ ሁሉ መጀመሪያ «እግዚአብሔርን መፍራት» ነውና (ምሳሌ 1:7)::

የእግዚአብሔር ሕግ ከሆነው ብሉይ ኪዳን የተጠቀሱት ምንባቦች ወደ አንድ ድምዳሜ ያመራሉ:: *ዓለም ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት በደለኛ ነው!* መከራከር የሚፈልጉ ይኖሩ ይሆናል፣ ነገር ግን አፍም ሁሉ ተዘግቷል:: ክርክርም ሆነ ሙግት የለም:: ዓለም ሁሉ አይሁድም አሕዛብም ሕግን ጥሰዋል:: አይሁድ በሚኮሩበት ሕግ ተፈረደባቸው:: አሕዛብም ደግሞ በፍጥረት በተገለጠውና በሕሊናቸው በተጻፈው ተፈርዶባቸዋል::

በቁጥር 20 ላይ «ስለዚህም» የሚለው ቃል «ምክንያቱም» ለሚለው ቃል የተሰጠውን ትርጉም ስለሚይዝ ዓለም ሁሉ ለምን በደለኛ እንደሆነች ምክንያቱን ያቀርባል:: የእግዚአብሔርን ሕግ በመጠበቅ *ሥጋ* ለባሽ በእግዚአብሔር ፊት አይጸድቅም:: እውነት ነው በእግዚአብሔር ፊት «ሕግን የሚያደርጉ ይጸድቃሉ» (ሮሜ 2:13)፣ ነገር ግን ሕጉ የሚያዝዘውን የሚፈጽም አንድም የለም::

ይህን መፈጸም አለመቻላቸው ሰዎች ኃጢአተኛ መሆናቸውን የሚያውቁበት መንገድ ነው። ሕግን ለመጠበቅ ሲሞክሩ ፈጽሞ ሊያደርጉት ስለማይችሉ የእግዚአብሔርን ምሕረት ለማግኘት ይጮኻሉ። አይሁድም ሆኑ አሕዛብ የእግዚአብሔርን ሕግ መጠበቅ አይችሉም። ስለሆነም እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን የሚያድንበት ሌላ መንገድ መኖር አለበት። ስለዚህም ጳውሎስ በቀሪው የሮም መልእክት ምንባቦቹ ሰዎች የሚድኑበትን መንገድ ለመግለጽ ተጠቅሞባቸዋል።

ይህንን ክፍል ለመደምደም የሚሻለው መንገድ ቀላል ጥያቄ በመጠየቅ ነው። አንደበታችሁ (አፋችሁ) ተዘግቶ ያውቃል ወይ? በራሳችሁ ጽድቅ እየተመካችሁ በትዕቢት በእግዚአብሐር ፊት ስለራሳችሁ ትሟገታላችሁ ወይ? ከሆነ፣ በእግዚአብሔር ጸጋ አልዳናችሁም ማለት ነው። እግዚአብሔር የሚያድነን በፊቱ እንደ ኃጢአተኝነታችን በጸጥታ ስንቆም ነው። ስለ ራሳችን አስተያየት በመስጠት የምንሟገት ከሆነ፣ በእግዚአብሔር ጸጋ ልንድን አንችልም። ዓለም ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት በደለኛ ነው- ይህ እኔንና አንተንም ያካትታል!

# ሮሜ 3:21-4:25

አሁን ግን በሕግና በነቢያት የተመሰከረለት የእግዚአብሔር ጽድቅ ያለ ሕግ ተገልጦአል፣ እርሱም፣ ለሚያምኑ ሁሉ የሆነ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የሚገኘው የእግዚአብሔር ጽድቅ ነው፤ ልዩነት የለምና፤ ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጐድሎአቸዋል፤ በኢየሱስ ክርስቶስም በሆነው ቤዛነት በኩል እንዲያው በጸጋው ይጸድቃሉ:: እርሱንም እግዚአብሔር በእምነት የሚገኝ በደሙም የሆነ ማስተስሪያ አድርጎ አቆመው፤ ይህም በፊት የተደረገውን ኃጢአት በእግዚአብሔር ችሎታ ስለ መተው ጽድቁን ያሳይ ዘንድ ነው፣ ራሱም ጻድቅ እንዲሆን በኢየሱስም የሚያምነውን እንዲያጸድቅ አሁን በዚህ ዘመን ጽድቁን ያሳይ ዘንድ ነው::

ትምክህት እንግዲህ ወዴት ነው? እርሱ ቀርቶአል:: በየትኛው ሕግ ነው? በሥራ ሕግ ነውን? አይደለም፣ በእምነት ሕግ ነው እንጂ (ሮሜ 3:21-27)::

እንግዲህ በሥጋ አባታችን የሆነ አብርሃም ምን አገኘ እንላለን? አብርሃም በሥራ ጸድቆ ቢሆን የሚመካበት አለውና፣ ነገር ግን በእግዚአብሔር ዘንድ አይደለም:: መጽሐፍስ ምን አለ? አብርሃምም እግዚአብሔርን አመነ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት:: ለሚሠራ ደመወዝ እንደ ዕዳ ነው እንጂ እንደ ጸጋ አይቈጠርለትም፤ ነገር ግን ለማይሠራ፣ ኃጢአተኛውን በሚያጸድቅ ለሚያምን ሰው እምነቱ ጽድቅ ሆኖ ይቈጠርለታል:: እንደዚህ ዳዊት ደግሞ እግዚአብሔር ያለ ሥራ ጽድቅን ስለሚቆጥርለት ስለ ሰው ብፅዕና ይናገራል፣ እንዲህ ሲል:-

ዓመፃቸው የተሰረየላቸው ኃጢአታቸውም የተከደነላቸው ብፁዓን ናቸው፤ (ሮሜ 4:13-17)

# 3

# አባታችን አብርሃም

ጳውሎስ በመልእክቱ በሁለተኛው ክፍል ያሰፈረው ጭብጥ ደኅንነት - የጽድቅ ዐዋጅ የሚለውን ነው:: በመጀመሪያ ሰው ሁሉ ኃጢአተኛ መሆኑን አረጋገጠ:: ቀጥሎ ኃጢአተኞች እንዴት እንደሚድኑ ገለጠ:: የዚህ ደኅንነት ሥነ መለኮታዊ ስያሜ «በእምነት የሚገኝ ጽድቅ» ነው:: መጽደቅ ማለት በእግዚአብሔር ተሠርቶ ባለቀው የክርስቶስ የመስቀል ላይ ሥራ የሚያምንን ኃጢአተኛ ጻድቅ ብሎ የሚጠራበት የእግዚአብሔር ሥራ ነው:: እያንዳንዱ ፍቺ ጠቃሚ በመሆኑ በጥንቃቄ ልናየው ይገባል::

ለመጀመር ያህል ጽድቅ ሂደት ሳይሆን፣ እግዚአብሔር የሚያደርገው ነገር ነው:: ጽድቅ የደረጃ ልዩነት የለውም:: እያንዳንዱ አማኝ በእግዚአብሔር ፊት የመቆም መብት አለው:: እንዲሁም ጽድቅ የእግዚአብሔር እንጂ፣ የሰው ሥራ አይደለም:: ማንም ኃጢአተኛ ራሱን በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ ማድረግ አይችልም:: ከሁሉም በላይ ማወቅ ያለብን እግዚአብሔር እኛን ጻድቅ አድርጎ ይሠራናል ማለት ሳይሆን፣ ጻድቅ ናችሁ ብሎ ያውጃል:: ጽድቅ ሕጋዊነት ያለው ነገር ነው:: እግዚአብሔር የክርስቶስን ጽድቅ በእኛ የኃጢአተኝነት ፋይል ውስጥ ያስቀምጣል:: ይህንን መዝገብ ደግሞ ማንም ሊለውጠው አይችልም::

ጽድቅንና ቅድስናን ግን አናምታታቸው:: ቅድስና እግዚአብሔር አንድ አማኝ የበለጠ ክርስቶስን እንዲመስል የሚያደርግበት ሂደት ነው:: ቅድስና ከቀን ወደ ቀን ሊለያይ ይችላል:: ጽድቅ ግን በፍጹም አይለወጥም:: አንድ ኃጢአተኛ በክርስቶስ ሲያምን፣ እግዚአብሔር ጻድቅ አድርጎ ይቆጥረዋል:: ይህንን ዐዋጅ ሊሽር የሚችል ማንም የለም:: እግዚአብሔር እኛን የሚያየን ከዚህ በፊት ኃጢአት አድርገን እንደማናውቅ አድርጎ ነው::

ነገር ግን አንድ ቅዱስ አምላክ እንዴት አድርጎ ነው ኃጢአተኞችን እንደ ጻድቅ የሚቆጥረው? ለመሆኑ ጽድቅ እውነተኛ መሠረት የሌለው «ልብ ወለድ» ነውን? በሮሜ መልእክት በዚህ ክፍል ጳውሎስ እነዚህን ጥያቄዎች በሁለት መልኩ መልስ ሰጥቶባቸዋል:: በመጀመሪያ፣ ጽድቅ በእምነት መሆኑን ገለጠ (3:21-31)፤ ቀጥሎም የአብርሃም እምነት ጽድቅ ሆኖ እንደተቆጠረለት የሚገልጽ ምሳሌ አቀረበ (4:1-25)::

## 1. ጽድቅ ሲገለጥ (3:21-31)

«አሁን ግን በሕግና በነቢያት የተመሰከረለት የእግዚአብሔር ጽድቅ ያለ ሕግ ተገልጦአል» (ሮሜ 3:21):: እግዚአብሔር በሙላት በወንጌል አማካይነት ራሱን ከመግለጡ በፊት ራሱን በብዙ መንገዶች ገልጾአል፤ እርሱም:- ሕጉ፣ በኃጢአት ላይ መፍረዱ፣ በነቢያት በኩልና የሚታዘዙትን በመባረክ ናቸው:: ነገር ግን በወንጌል የተገለጠው አዲስ ዐይነት ጽድቅ ነበር (ሮሜ 1:16-17):: የዚህ ጽድቅ ባሕርያት ደግሞ በዚህ ክፍል ቀጥለው የቀረቡት ናቸው::

ሀ) *ያለ ሕግ* (3:21) - በብሉይ ኪዳን ሕግ፣ ጽድቅ የሚገኘው በሰው *ሥራ* ነበር:: በወንጌል ግን፣ ጽድቅ የሚገኘው በእምነት ነው:: ሕግ በራሱ የእግዚአብሔርን ጽድቅ ይገልጣል:: ምክንያቱም «ሕግ ቅዱስ ነው ትእዛዚቱም ቅድስትና ጻድቅት በጎም ናት» (ሮሜ 7:12):: ምንም እንኳ ሕግ ጽድቅን ባይሰጥም፣ በወንጌል ለሚገኘው ጽድቅ ምስክር ሆኗል:: ከዘፍጥረት 3:15 ጀምሮ በጠቅላላው የብሉይ ኪዳን ደኅንነት የሚገኘው በክርስቶስ በማመን ለመሆኑ ምስክር ሆኗል:: በብሉይ ኪዳን የተደረጉት መሥዋዕቶች፣ ትንቢቶች፣ አምሳያዎች እና ታላቅ «የወንጌል ቃል» (ለምሳሌ ኢሳይያስ 53) ሁሉም ለዚህ እውነት ምስክርነት ሰጥተዋል:: ሕግ የእግዚአብሔርን ጻድቅነት የሚያሳይ ሲሆን፣ ለኃጢአተኛው ሰው ግን ጽድቅን አልሰጠውም:: ይህን ማድረግ የሚችል ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው (ገላ. 2:21ን ይመልከቱ)::

*ለ) በክርስቶስ በማመን* (3:22) - እምነት የሚያዋጣው የምናምንበት ነገር የሚያዋጣ ከሆነ ነው:: ሰዎች ሁሉ በአንድ ነገር ያምናሉ፣ ካጡ ደግሞ በራሳቸው ይታመናሉ:: ነገር ግን ክርስቲያን የሚያምነው በክርስቶስ ነው:: በሕግ የሚገኝ ጽድቅ የሥራችን ዋጋ ነው:: በወንጌል የሚገኘው ጽድቅ ግን በእምነት የሚገኝ ስጦታ ነው:: ብዙ ሰዎች፣ «በእግዚአብሔር አምናለሁ» ይላሉ፤ ነገር ግን የሚያድነን ይሄ አይደለም:: አንድን ኃጢአተኛ የሚያድነውና ጻድቅ አድርጎ የሚያስቆጥረው እምነት፣ ሰው በግሉ በኢየሱስ ሲያምን ነው:: በሲኦል ያሉትም አጋንንት በእግዚአብሔር ያምናሉ ይንቀጠቀጡማል:: ነገር ግን ይህ አያድናቸውም (ያዕቆብ 2:19)::

*ሐ) ለሰዎች ሁሉ* (3:22-23)- እግዚአብሔር ሕግን የሰጠው ለአይሁድ እንጂ ለአሕዛብ አይደለም:: ነገር ግን በክርስቶስ የሚገኘው ደኅንነት የምሥራች የተሰጠው ለሰው ሁሉ ነው:: ሰዎች ሁሉ ሊድኑ ያስፈልጋቸዋል:: ፍርድን በተመለከተ በአይሁድና በአሕዛብ መካከል ልዩነት የለም:: «ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋል የእግዚአብሔርም ክብር ጐድሎአቸዋል» (ሮሜ 3:23):: እግዚአብሔር ለሰው ዘር ሁሉ የደኅንነትን ነፃ ስጦታ ለመስጠት ሰዎች ሁሉ ኃጢአተኛ እንደሆኑ ቆጥሯል (ዐውጇል)::

*መ) በጸጋ* (3:24) - እግዚአብሔር ሁለት ዓይነት ባሕርያት አሉት:- ፍጹም (እርሱ በራሱ የሆነው)፣ እና አንጻራዊ (ከሰዎችና ከዓለም ጋር ኅብረት የሚያደርግበት):: ፍጹም ከሆኑት ባሕርያቱ መካከል አንዱ ፍቅር ነው:: «እግዚአብሔር ፍቅር ነው» (1ኛ ዮሐ. 4:8):: እግዚአብሔር ይህንን ፍቅሩን ለእኔና ለእናንተ ሲያካፍለን፣ ጸጋና ምሕረት ይሆናል:: እግዚአብሔር በምሕረቱ ምክንያት የሚገባንን አልከፈለንም:: በጸጋው ደግሞ የማይገባንን ይሰጠናል:: «በነፃ» የሚለው የግሪክ ቃል በዮሐንስ 15:25 ላይ እንደተመለከትነው «እንዲያው» የማለት ያህል ነው:: እግዚአብሔር ጻድቅ አድርጎ የቆጠረን እንዲያው ነው:: የእግዚአብሔርን ምሕረት እንድናገኝ የሚያበቃን ምንም ነገር በእኛ ውስጥ የለም! ሁሉም በጸጋው ነው!

ሠ) *በእግዚአብሔር ታላቅ ክፍያ* (3:24-25)- ደኅንነት ነፃ ነው፣ ነገር ግን ርካሽ አይደለም:: እግዚአብሔር ለደኅንነታችን የከፈለውን ዋጋ የሚያሳዩ ሦስት ቃላት አሉ:: እነርሱም ቁጣን ማብረድ፣ መዋጀትና ደም ናቸው:: በሰው አነጋገር «ቁጣን ማብረድ» ማለት የተቆጣን ሰው በስጦታ በማባበል ማቀዝቀዝ ማለት ነው:: በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጠው ግን እንዲህ አይደለም:: «ቁጣን ማብረድ» ማለት ቅዱስ የሆነውን የእግዚአብሔርን ሕግ ተገቢውን መመዘኛ በማሟላትና በመጠበቅ እግዚአብሔርን ማስደሰትና ኃጢአተኛው በክርስቶስ አማካይነት ወደ እግዚአብሔር ሲመጣ ምሕረት እንዲያገኝ ማስቻል ነው:: «ደም» የሚለው ቃል የሚነግረን የሚከፈለው ዋጋ ምን ያህል ከፍተኛ ዋጋ ያለው መሆኑን ነው:: ሕጉን ለመጠበቅና ኃጢአተኞችን ለማጽደቅ ኢየሱስ መሞት ተገባው::

ይህንን እውነት ለማብራራት የተሻለው መንገድ በዘሌዋውያን 16 የተጠቀሰው የስርየት ቀን ነው:: በመሠዊያው ሁለት ፍየሎች ይቀርባሉ:: ከሁለቱ አንደኛው ይሠዋል:: ፍየሉ ይሠዋና ደሙ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ተወስዶ የቃል ኪዳን ታቦቱ በተሸፈነበት ከወርቅ የተሠራ የስርየት መክደኛ ላይ ይረጫል:: የሚረጨው ደም በታቦቱ ውስጥ ያሉትን ሁለት የሕግ ጽላቶች ይሸፍናል:: የፈሰሰው ደም ቅዱስ የሆነውን የእግዚአብሔርን ጥያቄ ለጊዜው ያሟላል::

ካህኑ በመቀጠል እጁን በሌላኛው ፍየል ራስ ላይ ጭኖ ስለ ሕዝቡ ኃጢአት ይናዘዛል:: <u>ካህኑ በመቀጠል እጁን በሌላኛው ፍየል ራስ ላይ ጭኖ ስለ ሕዝቡ ኃጢአት ይናዘዛል</u>:: ፍየሉ ኃጢአታቸውን መሸከሙን ለማመላከት ፍየሉን ወደ ምድረ በዳ ይሰደዋል:: «ምሥራቅ ከምዕራብ እንደሚርቅ እንዲሁ ኃጢአታችንን ከእኛ አራቀ» [መዝ. (103):12]:: በብሉይ ኪዳን ዘመን የእንስሳት ደም ኃጢአትን ፈጽሞ ሊያስወግድ አይችልም:: ነገር ግን ጌታ ኢየሱስ መጥቶ ደኅንነትን በመፈጸም እስኪገዛን ድረስ ኃጢአትን ይሸፍን ነበር:: እግዚአብሔር ልጁ አንድ ቀን መጥቶ ሥራውን እንደሚጨርስ በማወቁ፣ ከማመን በፊት

የተደረገውን ኃጢአት (ሮሜ 3:25)፣ «ትቶት ነበር»:: በሞቱና በትንሣኤው አማካኝነት «መዋጀት» ይኖራል ይህም ኃጢአተኛ ውን በመግዛት ነፃ መውጣት ነው::

ዶክተር ጂ. ካምቤል ሞርጋን የተባለ ሰው ደኅንነት ነፃ ስጦታ መሆኑን የድንጋይ ከሰል ለሚቆፍር ሰው ለማስረዳት ሲሞክር ቆፋሪው ሊገነዘብ አልቻለም:: «እኔ ራሴ ለደኅንነቴ ዋጋ መክፈል አለብኝ» እያለ ይከራከር ጀመር:: ዶክተር ሞርጋን እግዚአብሔር ረድቶት የሚከተለውን ጥያቄ ጠየቀው:: «ዛሬ በማለዳ ለቁፋሮ ወደ ጉድጓዱ በምን ወረድክ?» ሰውየውም ለምን ቀላል ጥያቄ ጠየቅኸኝ አለና፣ «በአሳንሰር (ሊፍት) ነው ወደ ታች የወረድኩት» ብሎ ነገረው::

ሞርጋንም ድጋሚ ጠየቀው፣ «ቀላል ነበር አይደል? ለመሆኑ ዋጋ አልከፈልክም?»

ሰውየው ሳቀና፣ «ምንም አልከፈልኩም፤ ነገር ግን የምሠራለት ኩባንያ ይህን ሊፍት ለመትከል ብዙ ገንዘብ አውጥቷል::» በዚህም ሰውየው እውነቱን መገንዘብ ቻለ:: «ለመዳን እኔ የከፈልኩት ዋጋ የለም፣ ነገር ግን እግዚአብሔር እኛን ለማዳን የገዛ ልጁን ከፍሏል::»

ረ) *ፍጹም ፍትሕ* (3:25-26) - እግዚአብሔር ፈጽሞ የማይለወጥ ባሕርይ አለው:: የራሱን ሕግ አያጥፍም፣ ባሕርይውንም አይተላለፍም:: «እግዚአብሔር ፍቅር ነው» (1ኛ ዮሐ. 4:8):: እንዲሁም «እግዚአብሔር ብርሃን ነው» (1ኛ ዮሐ. 1:5):: የፍቅር አምላክ ኃጢአተኛን ይቅር ማለት ይፈልጋል:: ሆኖም የቅድስና አምላክ የራሱን ጽድቅ በማቆም ኃጢአትን ይቀጣል:: እንዴት ነው እግዚአብሔር «ጻድቅ ሆኖ ሳለ ኃጢአተኞችን ጻድቅ አድርጎ የሚቆጥረው»? ለዚህ መልሱ ያለው በኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: ኢየሱስ ስለ ዓለሙ ሁሉ ኃጢአት በመስቀል ላይ ሲሠቃይ የእግዚአብሔርን ቁጣ ለማብረድ የእግዚአብሔር ሕግ የጠየቀውን ሁሉ አሟልቷል:: በዚህም የእግዚአብሔርን የልቡን ፍቅር አሳይቷል:: በብሉይ ኪዳን

የነበሩት የእንስሳት መሥዋዕቶች ኃጢአትን አላስወገዱም:: ነገር ግን ኢየሱስ በሞተ ጊዜ ቀደም ሲል እስከ አዳም ድረስ የነበሩትን ኃጢአቶች በሙሉ አነጻ:: ማንም ይሁን ማን (ሰይጣንም ጭምር) እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ኃጢአት ሸፍኖ ቢያልፍም አድሎአዊና ግፈኛ አድርጎ ሊከስሰው አይችልም::

ሰ) *ሕግን ለማጽናት* (3:27-31) - የመልእክቱ አንባቢዎች አይሁድም ስለነበሩ በወንጌልና በሕግ መካከል ያለውን ግንኙነት በተመለከተ ብዙ ለማለት ፈለገ:: ጽድቅ በእምነት መሆኑ ሕግን የሚቃረን ሳይሆን፣ የሚያጸና ነው:: እግዚአብሔር የደኅንነት ዕቅዱን ያሟላው የራሱን ሕግ ታዝዞ ነው:: ኢየሱስ በኑሮውና በሞቱ ሕግ የሚጠይቀውን ሙሉ በሙሉ አሟልቷል:: እግዚአብሔር አንድ አምላክ ስለሆነ ለአይሁድ አንድ ለአሕዛብ ደግሞ ሌላ በድምሩ ሁለት የደኅንነት መንገድ የለውም:: እርሱ በባሕርይውም ሆነ በሕጉ የማይለዋወጥ ነው:: ደኅንነት የሚገኘ ው በሕግ ቢሆን ኖሮ፣ ሰዎች በተመኩ ነበር:: ነገር ግን የእምነት ሕግ ሰዎች እንዳይመኩ ያደርጋቸዋል:: አንድ ዋናተኛ ከመስመጥ ቢድን፣ ሰዎችን ከመስመጥ ለማዳን በተቀጠረ ዋናተኛ ተመክቶ አይፎክር:: ከዚህ ሌላ ምን ሊያደርግ ይችላል? አንድ ኃጢአተኛ በእምነት ጻድቅ ሆኖ ቢቆጠር፣ በእምነቱ ሊኩራራ አይችልም፣ ነገር ግን ድንቅ በሆነው አዳኙ ሊመካ ይችላል::

በሮሜ ምዕራፍ 4 እስከ 8 ባለው ክፍል ጳውሎስ የእግዚአብሔር የደኅንነት ዕቅድ ከብሉይ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት ጋር እንደሚስማማ አብራርቶአል:: ጳውሎስ ማብራሪያውን የጀመረው የአይሁድ ሕዝብ አባት በሆነው በአብርሃም ነው::

## 2. ጻድቅ ሆኖ የመቆጠር ምሳሌ (4:1-25)

በሮም የነበሩት አይሁድ ክርስቲያኖች ወዲያውኑ የሚከተለውን ጥያቄ መጠየቃቸው አይቀርም፣ «ይህ በእምነት መጽድቅ የሚለው አስተምህሮ ከታሪካችን ጋር እንዴት ይዛመዳል? ጳውሎስ ሆይ፣ አንተ ይህ አስተምህሮ በሕግና

በነቢያት ተመስክሮለታል ትላለህ:: ታዲያ፣ አብርሃም እንዴት ሊሆን ነው?» ይላሉ::

ጳውሎስም በፊቱ የቀረበውን ተግዳሮት ተቀብሎ አብርሃም እንዴት እንደዳነ ያብራራል:: አብርሃም የአይሁድ ሥጋዊ አባት በመሆኑ፣ «አባታችን» ተብሎ ተጠርቷል:: ነገር ግን በቁጥር 11 ላይ አብርሃም በክርስቶስ «ለሚያምኑ ሁሉ አባት» ተብሎ ተጠርቷል (ገላ. 3:1-18ን ይመልከቱ):: የአባታቸው አብርሃም ደኅንነት ዛሬ ካለው አማኝ ጋር ተመሳሳይ መንፈሳዊ ልምምድ መሆኑን ለማስረዳት ጳውሎስ እውነታዎችን ዘርዝሯል::

*ሀ) አብርሃም የጸደቀው በእምነት እንጂ በሥራ አይደለም* (4:1-8)- ይህንን አባባሉን ለማረጋገጥ ጳውሎስ ሁለት ምስክሮችን ያቀርባል:- ሙሴ (ዘፍጥ. 15:6) እና ዳዊት [መዝ. (32):1-2]:: ከቁጥር 1-3 በዘፍጥረት 15 የተተረከውን የአብርሃምን ልምምድ ፈተሽ:: አብርሃም ነገሥታቱን ድል ነሥቶ ሳለ (ዘፍጥ. 14) ተመልሶ ይዋጉት እንደሆነ አስቦ ነበር:: እግዚአብሔር ግን ተገልጦለት እርሱ ጋሻው እንደሆነና «ዋጋህ (የአብርሃም) እጅግ ታላቅ ነው» በማለት ዋስትናን ሰጠው:: አብርሃም አጥብቆ የፈለገው ግን ወራሽ የሚሆነውን ወንድ ልጅ ነበር:: እግዚአብሔር ወንድ ልጅ እንደሚሰጠው ቃል የገባለት ቢሆንም፣ እስካሁን ግን ተስፋው ሙላት አላገኘም::

በዚህ ጊዜ ነበር እግዚአብሔር አብርሃም ከዋክብትን እንዲመለከት የነገረው:: እግዚአብሔርም፣ «ዘርህ እንዲሁ ይሆናል!» ብሎ ተናገረ:: አብርሃምም የእግዚአብሔርን ተስፋ አመነ ተብሎ የተተረጎመው የዕብራይስጥ ቃል «አሜን» ማለት ነው:: እግዚአብሔር ተስፋን ሰጠ:: አብርሃምም «አሜን» በማለት ምላሽ ሰጠ:: ጽድቅ ሆኖ የተቆጠረለት ይህ እምነት ነበር::

በሮሜ 4:3 ላይ የተጻፈው «ጽድቅ ሆኖ ተቆጠረለት» የሚለው ቃል «በአንድ ሰው የባንክ ሂሳብ ገንዘብ በስሙ ማስቀመጥ» ማለት ነው:: የባንክ ሰዎች የሚጠቀሙበት ስያሜ ነው:: ይህ ቃል በዚህ ምዕራፍ ብቻ 11 ጊዜ ተጠቅሷል (ከቁጥር 4-11፣21-

24):: አንድ ሰው ሲሠራ ደመወዝ ይቀበላል:: ይህም በስሙ በባንክ ሊቀመጥለት ይችላል:: ነገር ግን አብርሃም ደኅንነቱን አልሠራውም:: ዝም ብሎ የእግዚአብሔርን ተስፋ አመነ:: ሥራውን የሠራው ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሲሆን፣ የእርሱ ጽድቅም ለአብርሃም ተቆጠረለት::

ቁጥር 5 ላይ አንድ የሚያስገርም ዐረፍተ ነገር አለ፣ «ኃጢአተኛውን በሚያጸድቅ በእግዚአብሔር» ይላል:: ሕጉ «እኔ ኃጢአተኛውን አላጸድቅምና» (ዘጸ. 23:7) ይላል:: በብሉይ ኪዳን ፈራጆች «ጻድቁን ደኅና ነህ፣ የበደለውንም- በደለኛ ነህ» እንዲሉ ታዝዘዋል (ዘዳግ. 25:1):: ሰሎሞን ቤተ መቅደሱን በመረቀ ጊዜ እግዚአብሔርን በበደለኛ ላይ ፍርድ ንጹሑንም አጸደቀው፤ በማለት ጠይቋል (1ኛ ነገ. 8:31-32)! ነገር ግን በፊቱ ሥራቸው ሊያጸድቃቸው የሚችሉ ጻድቃን ባለመኖራቸው እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን ያጸድቃል:: ኃጢአታችንን በክርስቶስ ላይ አድርጎ የክርስቶስን ጽድቅ ደግሞ በእኛ ላይ አደረገ::

ከቁጥር 6-8 ባለው ክፍል ላይ ጳውሎስ ንጉሥ ዳዊት ከቤርሳቤህ ጋር ከተኛ በኋላ የንስሐ መዝሙሩን በመጥቀስ ምስክር አድርጎ ቆጥሮታል [መዝ. (32):1-2]:: ዳዊት ሁለት ድንቅ አባባሎችን ተናግሯል:- (1) እግዚአብሔር ኃጢአትን ይቅር ይላል:: ጽድቅንም ከሥራ ውጭ ያደርጋል፣ (2) እግዚአብሔር የኃጢአታችን ኃላፊነት አይጠይቀንም:: በሌላ አባባል፣ አንድ ጊዜ ድድቅ ተደርገን ከተቆጠርን፣ የሕይወት መዝገባችን የክርስቶስን ፍጹም የሆነ ጽድቅ ይይዛል እንጂ ኃጢአታችንን አይይዝም:: እውነት ነው ክርስቲያኖች ኃጢአት ይሠራሉ:: እነዚህ ኃጢአቶች ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ለማድረግ እንችል ዘንድ ይቅር መባል አለባቸው (1ኛ ዮሐ. 1:5-7):: *ነገር ግን እነዚህን ኃጢአቶች በእኛ ላይ ለክስ አያቀርባቸውም::* ክርስቶስ ሲመጣ ሽልማት እናገኝ ዘንድ እግዚአብሔር ሥራችንን ይመዘግባል እንጂ::

ለ) *የጸደቀው በጸጋ እንጂ፣ በሕግ አይደለም* (4:9-17) - እንደተመለከትነው፣ አይሁድ በመገረዝ ሥርዓትና በሕግ ይመኩ ነበር። አንድ አይሁድ በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ ለመሆን መገረዝና ሕግን መጠበቅ አለበት። ጳውሎስ በሮሜ 2:12-29 ሕግን በውስጣችን እንድንጠብቅና «የልብ መገረዝ» እንደሚያስፈልግ በግልጽ አስፍሯል። የጠፋን ኃጢአተኛ ውጫዊ ሥርዓቶች ብቻቸውን በፍጹም ሊያድኑት አይችሉም።

አብርሃም ጽድቅ ሆኖ የተቆጠረው ገና ሳይገረዝ ነበር። በአይሁድ ዕይታ አብርሃም አሕዛብ ነበር። አብርሃም ሲገረዝ 99 ዓመቱ ነበር (ዘፍጥ. 17:23-23)። ይህ ደግሞ ዘፍጥረት 15 ከተፈጸመ ከዐሥራ አራት ዓመታት በኋላ መሆኑ ነው። ድምዳሜው ግልጽ ነው። ግርዘት ለአብርሃም ጽድቅ ምንም ድርሻ የለውም።

ታዲያ እንደዚህ ከሆነ ግርዛት ለምን አስፈለገ? ማኅተምና ምልክት ነበር (ሮሜ 4:11)። ምልክት ነው ስንል፣ እርሱ የእግዚአብሔር መሆኑንና የተሰጠውንም ተስፋ ማመኑን ለማስረገጥ ነው። ማኅተምነቱ ደግሞ እግዚአብሔር ተስፋ እንደ ገባለትና የገባውንም ተስፋ እንደሚፈጽም ለማስታወስ ነበር። ዛሬ አማኞች በመንፈስ ቅዱስ ታትመዋል (ኤፌ. 1:13-14)። በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ አሮጌውን ሰዋችውን አስወግደዋል እንጂ አካላዊ ቀዶ ጥገና አላደረጉም። ስለሆነም መንፈሳዊ የሆነ የልብ ግርዘትን ይለማመዳሉ (ቆላ. 2:10-12)። ግርዛት ለአብርሃም ደኅንነት የጨመረው ነገር የለም፣ ማስረጃ ብቻ ሆነ እንጂ።

አብርሃም ጻድቅ ሆኖ የተቆጠረው ሕግ ከመሰጠቱ በፊት ሲሆን፣ ይህንንም ጉዳይ ጳውሎስ ከቁጥር 13-17 ባለው ክፍል ዳስሶታል። የእግዚአብሔር ሕግ በሙሴ በኩል ገና ስላልመጣ፣ አብርሃም ጻድቅ ሆኖ የተቆጠረው አብርሃም የእግዚአብሔርን ተስፋ በማመኑ እንጂ ሕግን በመጠበቁ አልነበረም። በዚህ ክፍል ያለው ቁልፍ ቃል «ተስፋ» የሚለው ነው። ለአብርሃም የተሰጠው ተስፋ በሥራው ወይም በጥረቱ ሳይሆን፣

በእግዚአብሔር ጸጋ ነው:: ዛሬም እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን የሚያጸድቀው ሕግ ስለጠበቁ ሳይሆን፣ የጸጋውን ተስፋ ስላመኑ ነው:: ሕግ የተሰጠው ለሰዎች ደኅንነት ለመስጠት ሳይሆን፣ መዳን እንዳለባቸው ለማሳየት ነው (ሮሜ 4:15)::

የአብርሃም በሕግ ሳይሆን በጸጋ ጻድቅ ሆኖ መቆጠር ደኅንነት ለሰዎች ሁሉ እንደሆነ ያረጋግጣል:: አብርሃም የአይሁድም ሆነ የአሕዛብ የእምነት አባት ነው (ሮሜ 4:16፣ ገላ. 3:7፣29):: ስለዚህ አይሁድ አብርሃም በሕግ ባለመዳኑ ከማጉረምረም ይልቅ የእግዚአብሔር ደኅንነት ለሰዎች ሁሉ በመሆኑ ሊደሰትና አብርሃም የሥጋ ዝርያ እስራኤል እንዳለው ሁሉ፣ መንፈሳዊ ቤተሰቦቹም (እውነተኛ አማኞች በሙሉ) እንዳሉት ሊያውቅ ይገባዋል:: ጳውሎስ ይህ የዘፍጥረት 17:5 «ለብዙ አሕዛብ አባት አድርጌሃለሁ» የሚለው ቃል ፍጻሜ መሆኑን ያመለክተናል::

ሐ) *የጸደቀው በሰው ብርታት ሳይሆን፣ በትንሣኤው ኃይል ነበር* (4:18-25)- እነዚህ ቁጥሮች «ለሙታን ሕይወት በሚሰጥ» የሚለው የቁጥር 17 ቅጥያዎች ናቸው:: ጳውሎስ ያረጀው የአብርሃም ሰውነት እንደ ወጣት መታደሱ (መቀስቀሱ) በእርጅናው የሞቱት የአብርሃም ስሜቶች እንደ ወጣት ስሜት መነሣታቸው የሙታን ትንሣኤ ተምሳሌት እንደሆነ በማየት ከክርስቶስ ትንሣኤ ጋር አያያዘው::

እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለሣራ የልጃቸውን መወለድ ያዘገየበት አንደኛው ምክንያት ተፈጥሮአዊው ሥጋዊ ብርታታቸው እንዲጠፋና ፈጽሞ እንዲወገድ ነበር:: የ99 ዓመት ሽማግሌ የ89 ዓመት ካላት ማኅፀን ውስጥ ልጅ ይወልዳል ማለት የማይታሰብ ነበር! ከሥነ ተዋልዶ ዕውቀት አኳያ ሲታይ ሁለቱም ምውት ነበሩ:: ነገር ግን አብርሃም በእምነት እንጂ በማየት አልተመላለሰም:: እግዚአብሔር ተስፋ የገባውን ይፈጽማል:: ከእኛ የሚጠበቀው ማመን ብቻ ነው:: በዘፍጥረት 15 የተዘገበው የአብርሃም እምነት በቀጣዮቹ ዓመታት አልደበዘዘም:: በዘፍጥረት 17 ና 18 እንደሚታየው አብርሃም

«በእምነት በረታ»:: ይህ እምነቱ ነበር አብርሃም በስተርጅናው እንዲወልድ ያስቻለው::

የደኅንነት ምሥጢር ግልጽ ነው:- አንድ ኃጢአተኛ ራሱን መርዳት ሳይችል ቀርቶ «ሙት» እስኪሆን ድረስ እግዚአብሔር የመዳን ኃይሉን ያዘገየዋል:: በኃጢአቱ የጠፋ ሰው፣ እግዚአብሔርን በራሱ ለማስደሰት እንደሚችል ብቁ አድርጎ ራሱን ከቆጠረ፣ በጸጋ ሊድን አይችልም:: አብርሃም «ሙት» መሆኑን ሲያምን ነው፣ የእግዚአብሔር ኃይል በሥጋው የሠራው:: እግዚአብሔር አንድን ኃጢአተኛ የሚያድነው ይህ ሰው በመንፈስ ሙት መሆኑንና ራሱን መርዳት እንደማይችል ሲናዘዝ ነው::

በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ምክንያት ወንጌል «የእግዚአብሔር የማዳን ኃይል ነው» (ሮሜ 1:16):: ሮሜ 4:24 እና ሮሜ 10:9-10 ይነጻጸራሉ:: ኢየሱስ ክርስቶስ «ስለ በደላችን አልፎ ተሰጠ፣ እኛን ስለማጽደቅም ተነሣ» (ሮሜ 4:25):: የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ እግዚአብሔር የልጁን መሥዋዕት መቀበሉንና የራሱን ሕግ ሳይሰብር ከራሱም ጋር ሳይቃረን ኃጢአተኞች ጻድቅ ተደርገው ሊቆጠሩ እንደሚችሉ ማረጋገጫ ነው::

ቁልፉ «ለምናምን ለእኛ» (ቁ. 25) የሚለው ነው:: በሮሜ መልእክት እምነትንና አለማመንን የሚገልጹ ከ60 በላይ ምንባቦች አሉ:: የእግዚአብሔርን የማዳን ኃይል የሚለማመዱት በክርስቶስ ያመኑቱ ናቸው (ሮሜ 1:16):: የእርሱ ጽድቅ በእርሱ ለሚያምኑት ተሰጥቶአቸዋል (ሮሜ 3:22):: የጸደቅነው በእምነት ነው (ሮሜ 5:1):: የምንታመንበት ደግሞ ስለ እኛ በሞተውና ዳግመኛ በተነሣው በኢየሱስ ክርስቶስ ነው::

እነዚህ ሁሉ እውነታዎች የአብርሃምን እምነት የበለጠ ግሩምና ድንቅ ያደርጉለታል:: የሚያነበው መጽሐፍ ቅዱስ አልነበረውም:: ነገር ግን የእግዚአብሔርን ተስፋ ብቻ ይዞ ነበር:: በጽሑፍ የሰፈረ ረጅም የእምነት ገድልን ወደ ኋላ ሄዶ ማየት አይችልም ነበር:: ነገር ግን እርሱ ራሱ ያን ለመጻፍ ሞከረ እንጂ:: ይሁን

እንጂ አብርሃም በእግዚአብሔር አመነ:: ዛሬ ሰዎች የሚያነቡት መጽሐፍ ቅዱስ አላቸው:: በቤተ ክርስቲያን ኅብረት አላቸው:: ካስፈለገም ለዘመናት ወደ ኋላ መለስ ብለው በመጽሐፍ ቅዱስና በቤተ ክርስቲያን ታሪክ የተዘገቡ እምነቶችን ማየት ይችላሉ:: ብዙዎች ግን ለማመን አይፈልጉም::

ለዐሥራ ስምንት ዓመታት በቺካጐ የሙዲ ቤተ ክርስቲያን መጋቢ የነበሩት ዶክተር ሃሪ አይረንሳይድ፣ በዕረፍት ጊዜያቸው ብቅ ብለው ስለጎበኙት የሰንበት ትምህርት የሚከተለውን ተናግረዋል:: አስተማሪው፣ «በብሉይ ኪዳን ሰዎች የሚድኑት እንዴት ነበር?» በማለት ጠየቀ::

ከተወሰነ የዝምታ ጊዜ በኋላ አንድ ሰው፣ «ሕግን በመጠበቅ» በማለት መለሰ:: አስተማሪውም፣ «ልክ ነው» አለ::

ነገር ግን ዶክተር አይረንሳይድ ጣልቃ ገብተው፣ «የእኔ መጽሐፍ ቅዱስ የሕግን ሥራ በመሥራት ሥጋ የለበሰ ሁሉ በእርሱ ፊት አይጸድቅም» ይላል አሉ:: አስተማሪው አፍሮ፣ «ሌላ መልስ ያለው አለን?» በማለት ሲጠይቅ፣ ሌላ ተማሪ፣ «ለእግዚአብሔር መሥዋዕትን በማቅረብ ነው የዳኑት» ብሎ መለሰ::

አስተማሪውም፣ «ልክ ነው» ብሎ ትምህርቱን ሊቀጥል ሲሞክር፣ ዶክተሩ አሁንም ጣልቃ ገብተው፣ «የእኔ መጽሐፍ ቅዱስ የኮርማዎችና የፍየሎች ደም ኃጢአትን ሊያስወግድ አይችልም ይላል» አሉ::

በዚህ ጊዜ በደንብ ያልተዘጋጀው መምህር ይህ አዲስ ሰው ከእርሱ በተሻለ መልኩ መጽሐፍ ቅዱስን እንደሚያውቅ ስለተገነዘበ፣ «እንግዲያውስ ደህና እርስዎ በብሉይ ኪዳን ሰዎች እንዴት እንደዳኑ ይንገሩን!» አለ::

ዶክተር አይረንሳይድም ዛሬ ሰዎች በእምነት እንደሚድኑ የብሉይ ኪዳን ሰዎችም በእምነት እንደ ዳኑ አብራሩ::

በዕብራውያን ምዕራፍ 11 ላይ «በእምነት» የሚለውን ቃል ሃያ አንድ ጊዜ ተጽፎ ታገኙታላችሁ።

አይሁድ ከሆናችሁ በሥጋ የአብርሃም ልጅ ናችሁ። ነገር ግን በመንፈስ የአብርሃም ልጆች ናችሁን? አብርሃም በኢየሱስ ክርስቶስ ለሚያምኑና በእምነት ለጸደቁ ሁሉ አባት ነው። አሕዛብ ከሆናችሁ በሥጋ የአብርሃም ዘር ልትሆኑ አትችሉም። ነገር ግን መንፈሳዊ ዝርያዎቹ ልትሆኑ ትችላላችሁ። አብርሃም «በእግዚአብሔር አመነ ጽድቅም ሆኖ ተቆጠረለት»።

# ሮሜ 5:1-21

እንግዲህ በእምነት ከጸደቅን በእግዚአብሔር ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምን እንያዝ፤ በእርሱም ደግሞ ወደ ቆምንበት ወደዚህ ጸጋ በእምነት መግባትን አግኝተናል፤ በእግዚአብሔር ክብርም ተስፋ እንመካለን። ይህም ብቻ አይደለም፣ ነገር ግን መከራ ትዕግሥትን እንዲያደርግ፣ ትዕግሥትም ፈተናን ፈተናም ተስፋን እንዲያደርግ እያወቅን፣ በመከራችን ደግሞ እንመካለን፣ በተሰጠንም በመንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን ስለ ፈሰሰ ተስፋ አያሳፍርም።

ገና ደካሞች ሳለን ክርስቶስ ዘመኑ ሲደርስ ስለ ኃጢአተኞች ሞቶአልና። **(5:1-6)**

ስለዚህ ምክንያት ኃጢአት በአንድ ሰው ወደ ዓለም ገባ በኃጢአትም ሞት፣ እንደዚሁም ሁሉ ኃጢአትን ስላደረጉ ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰ፤ ሕግ እስከ መጣ ድረስ ኃጢአት በዓለም ነበረና ነገር ግን ሕግ በሌለበት ጊዜ ኃጢአት አይቆጠርም፤ ነገር ግን በአዳም መተላለፍ ምሳሌ ኃጢአትን ባልሠሩት ላይ እንኳ፣ ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ ድረስ ሞት ነገሠ፤ አዳም ይመጣ ዘንድ ላለው ለእርሱ አምሳሉ ነውና። **(5:12-14)**

በደልም እንዲበዛ ሕግ ጭምር ገባ፤ ዳሩ ግን ኃጢአት በበዛበት፣ ኃጢአት በሞት እንደ ነገሠ፣ እንዲሁ ደግሞ ጸጋ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ የተነሣ በጽድቅ ምክንያት ለዘላለም ሕይወት ይነግሥ ዘንድ፣ ጸጋ ከመጠን ይልቅ በለጠ። **(ሮሜ 5:20-21)**

# 4

## እንደ ንጉሥ መኖር

የሮም መልእክት ሥነ አመክንዮአዊ መጽሐፍ እስከሆነ ድረስ፣ «ስለዚህና እንግዲህ» የሚሉ ቃላትን በብዛት የያዘ መጽሐፍ ነው:: በምዕራፍ 3:20 «ስለዚህ» ፍርድን አስመልክቶ፣ «እንግዲህ 5:1 ላይ (አዲሱን መደበኛ ትርጉም - ይመልከቱ) ጽድቅን በማስመልከት 8:1 ላይ ኩነኔን እና እንግዲህ 12:1 ላይ ደግሞ ራስን አሳልፎ መስጠትን በተመለከተ የሚናገሩ ክፍሎችን ይዟል:: ጳውሎስ ሙግቱን ሲያቀርብ ዓለም ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት በደለኛ እንደሆነችና ማንም ሰው ሕግን እንደ መጠበቅ ሥርዓትን በመሳሰሉ ሃይማኖታዊ ሥራዎቹ ሊድን እንደማይችል አረጋግጧል:: የእግዚአብሔር የደኅንነት መንገድ ምንጊዜም ቢሆን «በጸጋውና በእምነት» (ኤፌ. 2:8-9) እንደሆነ ገልጾ፣ አብርሃምን እንደ ምሳሌ በመጠቀም አቅርቧል:: የመልእክቱ አንባቢ እዚህ ላይ ቢያቆም መዳን እንደሚገባውና ሊድን እንደሚችል ያውቃል::

ነገር ግን ኃጢአተኛው በእምነት ስለሚገኘው ጽድቅ ሊያውቃቸው የሚገቡ ብዙ ነገሮች አሉ:: ይህ እንደሚያዛልቅ እርግጠኛ መሆን ይችላልን? በክርስቶስ የመስቀል ላይ ሞት እግዚአብሔር እንዴት ኃጢአተኞችን ሊያድን ይችላል? ምዕራፍ 5 ጳውሎስ በምዕራፍ 4 ላይ የጠቀሳቸውን ሁለት ቃላት «ይቆጠርልን» የሚሉትን ያብራራል:: ሁለት እውነታዎችን ገልጧል:: እነርሱም ጻድቅ ተደርገን የመቆጠራችን በረከቶች (5:1-11)፣ እና ጻድቅ ተደርገን የመቆጠራችን ምክንያቶች (5:12-21) ናቸው::

### 1. ጻድቅ ተደርገን የመቆጠራችን በረከቶች (5:1-11)

እነዚህን በረከቶች በመዘርዘር፣ ጳውሎስ ሁለት ዓላማዎቹን አሳክቷል:: በመጀመሪያ፣ ክርስቲያን መሆን እንዴት ድንቅ

እንደሆነ ተናግሯል:: ጽድቃችን የመንግሥተ ሰማያት ዋስትና ብቻ ሳይሆን፣ በዚህ ሳለን ዛሬም የምንለማመዳቸው ብዙ በረከቶችም ምንጭ ነው::

ሁለተኛው ዓላማው ደግሞ ጽድቅ ዘለቄታ ያለው መሆኑን ለአንባቢዎቹ ማረጋገጥ ነው:: በተለይ አይሁድ የመልእክቱ አንባቢዎች «ይህ መንፈሳዊ ልምምድ ሕግን ካልጠበቅን ይዘልቅ ይሆንን?» ብለው መጠየቃቸው አይቀርም:: በሕይወት የሚገጥሙን መከራዎችና ፈተናዎችስ? ስለሚመጣው ፍርድስ? እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ጻድቃን አድርጎ ሲቆጥረን፣ እንደማንጠፋ ዋስትና ይሆኑ ዘንድ ሰባት መንፈሳዊ በረከቶችን ሰጥቶናል::

ሀ) *ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም* (5:1) - ያልዳነ ሰው የእግዚአብሔርን ሕግ መጠበቅም ሆነ ፈቃዱን መፈጸም ስለማይችል «ከእግዚአብሔር ጋር በጠላትነት» ይገኛል (ሮሜ 5:10፤ 8:7):: በኢሳይያስ መጽሐፍ የሚገኙት ሁለት ጥቅሶች ነገሩን የበለጠ ያብራሩልናል:- «ለክፉዎች ሰላም የላቸውም ይላል እግዚአብሔር» (ኢሳ. 48:22):: ሌላው ደግሞ፣ «የጽድቅም ሥራ ሰላም. . . ይሆናል» (ኢሳ. 32:17) ይላል:: ኩነኔ ማለት እግዚአብሔር እኛን ኃጢአተኛ ናችሁ በማለት ጦርነት ሲያውጅብን ማለት ነው:: ጽድቅ ደግሞ እግዚአብሔር ጻድቃን አድርጎ ሲቆጥረን ሲሆን፣ ይህም ደግሞ በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ አማካኝነት የሰላም ዐዋጅ ነው:: [በመዝ. (185):10] ላይ እንደ ተጻፈው «ምሕረትና እውነት ተገናኙ ጽድቅና ሰላም ተስማሙ::» «ሕጉ መቅሰፍትን ያደርጋልና» (ሮሜ 4:15)፣ በሕግ የተፈረደባቸው ከእግዚአብሔር ጋር የሰላምን ደስታ ማግኘ ት አይችሉም:: ነገር ግን በእምነት ስትጸድቁ፣ ሕግ እናንተን ሊኮንናችሁ ወይም ጦርነት ሊያውጅባችሁ አይችልም::

ለ) *ወደ እግዚአብሔር የመቅረብ ዕድል ማግኘት* (5:24)- የእግዚአብሔር ሙላት ካለበት ቤተ መቅደስ አይሁድ የተለዩት በመጋረጃ ሲሆን፣ አሕዛብ ደግሞ መጋረጃውና እንዲሁም በትልቅ

ግድግዳና በላዩ ላይ በተጻፈው «ከዚህ ያለፈ አሕዛብ ይገደላል» በሚለው ማስጠንቀቂያ ወደ መቅደስ ከመግባት ተገድበው ይኖሩ ነበር:: ነገር ግን ጌታ ኢየሱስ በሞተ ጊዜ፣ መጋረጃው ተቀደደ (ሉቃ. 23:45)፣ ግድግዳውም ፈረሰ (ኤፌ. 2:14):: በክርስቶስ ያመኑ አይሁድና አሕዛብ ወደ እግዚአብሔር የመቅረብ መብት አገኙ (ኤፌ. 2:18፤ ዕብ. 10:19-25)፤ ከዚህም የተነሣ ወደማያልቀው የእግዚአብሔር የጸጋው ባለጠግነት ሊቀርቡ ቻሉ (ኤፌ. 1:7፣ 2:4፣3:8):: የቆምነው «በጸጋ» እንጂ «በሕግ» አይደለም:: ጽድቃችን የመቆማችንን ጉዳይ ሲያመለክት፣ ቅድስና ደግሞ ሕይወታችን ያለበትን ሁኔታ ያሳያል:: የንጉሥ ልጅ ምንም ይሁን ምን ወደ አባቱ መግባት ይችላል::

ሐ) *የከበረ ተስፋ* (5:2) - «ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም መሆን» ያለፈውን ሕይወታችንን ያጠራዋል:- እርሱም በኃጢአታችን ሊከሰን አያስብም:: «ወደ እግዚአብሔር መቅረባችን» ደግሞ የአሁኑ ሕይወታችንን ይዳስሳል:- እርዳታ ባስፈለገን ጊዜ ወደ እርሱ መቅረብ ያስችለናል:: «የእግዚአብሔር የክብሩ ተስፋ» ደግሞ የወደፊቱን ዕጣ ፈንታችንን አስተማማኝ ያደርጋል:- አንድ ቀን ከክብሩ እንካፈላለንና:: «መደሰት» የሚለው ቃል «መመካት» ተብሎ ሊተረጎም ይችላል:: ይህን ደግሞ በቁጥር 2 ብቻ ሳይሆን፣ በቁጥር 3 እና 8 ላይም እናገኘዋለን:: ኃጢአተኞች ሳለን፣ የእግዚአብሔር ክብር ስለጎደለን የምንመካበት ምንም አልነበረንም (ሮሜ 3:27፣ 3:23):: ነገር ግን በክርስቶስ ክብርና ጽድቅ እንመካለን! ይህንን ጳውሎስ በሮሜ 8:18-30 አጉልቶ አቅርቦታል::

መ) *ክርስቲያናዊ ባሕርይ* (5:3-4) - ጻድቅ መሆን ከኑሮ ፈተና ማምለጥ አይደለም:: «በዚህ ዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ» (ዮሐ. 16:33):: መከራዎች አማኙን ይቀርጹታል እንጂ አያጠፉትም:: ከጌታ ፍቅር ሊለየን የሚችል መከራ የለም (ሮሜ 8:35-39)፤ ነገር ግን መከራ ወደ ጌታ ያስጠጋንና በዚያውም ጌታን እንድንመስል ያደርገናል:: መከራ ክርስቲያናዊ ባሕርያችንን እንድንገነባ ያደርጋል:: በቁጥር 4 «ፈተና» የሚለው ቃል

ትርጉሙ «የተፈተነ ባሕርይ» ማለት ነው:: ቅደም ተከተሉም፣ መከራ- ትዕግሥት - ፈተና (የፈተና ባሕርይ)- ተስፋ ይሆናል? «መከራ» የሚለው ቃል በጳውሎስ ዘመን እህል ለማበጠር የሚጠቀሙበት መንሽ ማለት ነው:: ይህም መንሽ ስንዴውን ከገለባ ይለያል:: በመከራ ውስጥ ስናልፍ በእግዚአብሔር ጸጋ ከታመንን፣ መከራው ያጠራናል፣ በሕይወታችን ያለውንም ገለባ እንድናስወገድ ያግዘናል::

ሠ) *በውስጣችን የሚኖር የእግዚአብሔር ፍቅር* (5:5-8)- «የምትዘገይ ተስፋ ልብን ታሳዝናለች» (ምሳሌ 13:12):: ነገር ግን ይህ ተስፋችን እስኪሞላ ስንጠብቅ፣ የእግዚአብሔር ፍቅር «በልባችን ይፈስሳል»:: የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ የሆኑትን ፍቅር (ቁ 5)፣ ደስታ (ቁ. 2)፣ ሰላምን (ቁ. 2) እንለማመዳለን:: ከመዳናችን በፊት፣ እግዚአብሔር ክርስቶስ ለእኛ ይሞትልን ዘንድ በመላክ ፍቅሩን ገለጸ:: አሁንማ ልጆቹ ስለሆንን የበለጠ ይወደናል:: በመከራ ስናልፍ አጽንቶ የሚያቆመን በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት በውስጣችን የምንለማመደው ይህ ፍቅር ነው::

ለብዙ ወራት ሰውነቱ ተቃጥሎ ለሞት የተቃረበውን ወጣት ሆስፒታል እየተመላለስኩ እጠይቀው ነበር:: በእነዚህ ወራት ውስጥ ስንት የተዋጣላቸው ዶክተሮች እንዳዩትና ለምን ያህል ጊዜ የቆዳ ቀዶ ጥገና እንዳደረገ አላውቅም:: ነገር ግን ይህን ወጣት በእነዚህ ወራት መሃል አጽንቶ ያቆመው ዶክተሮቹ የሰጡት ገለጻ ሳይሆን፣ እንደሚድን የሰጡት ተስፋ ነበር:: ተስፋው ያ ነበር:: ተስፋውን ያጸናለት ደግሞ በጎኑ የቆሙለት የቤተሰቦቹና የወዳጆቹ ፍቅር ነበር:: የእግዚአብሔር ፍቅር በእነዚህ ሰዎች ውስጥ አልፎ ደረሰው:: ዛሬ ተሽሎት ለእግዚአብሔር ክብርን ይሰጣል::

እምነት (ቁ. 1)፣ ተስፋ (ቁ. 2) እና ፍቅር (ቁ. 5) እነዚህ ተጠቃለው ለአማኙ በመከራው እንዲታገሥ ያደርጉታል:: ትዕግሥት ደግሞ፣ አማኙ በባሕሪው እንዲያድግና በሳል የእግዚአብሔር ልጅ እንዲሆን ያደርገዋል (ያዕ. 1:1-4)::

*ረ) ከሚመጣው ቁጣ መዳን* (5:9-10) - ጳውሎስ ክርክሩ ከትንሽ ወደ ትልቅ ነበር:: እግዚአብሔር ጠላቶቹ ሳለን ካዳነን፣ አሁን ደግሞ ልጆቹ ስለሆንን የበለጠ ያድነናል:: ወደፊት የሚመጣ ቁጣ አለ፣ ነገር ግን እውነተኛ አማኞችን ይህ ፈተና አያገኛቸውም (1ኛ ተሰ. 1:9-10፣ 5:8-10):: ጳውሎስ ይቀጥልና ክርስቶስ በሞቱ ይህን ያህል ካደረገልን፣ አሁን ደግሞ በመንግሥተ ሰማይ ስለ እኛ እየማለደ የቱን ያህል ያደርግልን ይሆን! «ስለ በደላችን አልፎ ተሰጠ» (4:25):- «እኛን ስለማጽደቅ ተነሣ»:: ሕያው ሆኖ ስለሚኖር፣ ለዘለዓለም ድነናል (ዕብ. 7:23-25)::

ኑዛዜ ተናዛዡ እስካልሞተ ድረስ አይሠራም:: ሕግ አስፈጻሚ አካልም ኑዛዜው እንደሚገባ መፈጸሙንና ውርስ መከፋፈሉን ያያል:: ነገር ግን ሕግ አስፈጻሚው አካል ራስ ወዳድ ሆኖ ርስቱን ለራሱ መውሰድ ቢፈልግስ? ርስቱን ለመስረቅ ሕጉን የሚያጣምምበትን መንገድ ይፈልጋል::

ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ የተናዘዘልን ሲሆን፣ ኑዛዜውም የተጻፈው በደሙ ነው:: «ይህ ጽዋ ስለ እናንተ በሚፈሰው በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው» (ሉቃስ 22:20):: ኑዛዜው እንዲተገበር ሞተ፣ በኑዛዜው መሠረት ርስቱን ለማካፈል ደግሞ ከሞት ተነሥቶ ወደ ሰማይ ዐረገ:: ስለሆነም፣ «በሕይወት በመኖሩ ድነናል::»

*ሰ) ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅ* (5:11)- «ስርየት» የሚለው ቃል «መታረቅ፣ ከእግዚአብሔር ጋር እንደገና መወዳጀት» ማለት ነው:: ይህ አሳብ በቁጥር 10 ላይም ተጠቅሷል:: በሮሜ 1:18-32 ላይ ጳውሎስ ሰዎች በእግዚአብሔር ላይ ጦርነት በማወጃቸው፣ ለዘለዓለም መኮነን እንደሚገባቸው ገልጾልናል:: ነገር ግን እግዚአብሔር በሰው ልጆች ላይ ጦርነት አላወጀም:: በዚያ ፋንታ ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር እንዲታረቁ የሰላም መልእክተኛ አድርጎ ልጁን ላከው (ኤፌ. 2:11-18)::

ሰባቱን የጽድቅ በረከቶች መመዘን በክርስቶስ ያለንን ደኅንነት ምን ያህል እርግጠኛ መሆኑን ያሳያል። በሕግ ሳይሆን በጸጋ ያለፈውን፣ የአሁኑንና የወደፊቱን ነገራችንን የሚያበጅ ደኅንነት አግኝተናል። ክርስቶስ ስለ እኛ ሞተ፤ ስለ እኛ ሕያው ሆኖ ይኖራል፤ ክርስቶስ ይመጣልናል! ሃሌሉያ፣ እንዴት ድንቅ አዳኝ ነው!

## 2. የጽድቃችን መሠረት (5:12-21)

እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የሚያድነው እንዴት ነው? ክርስቶስ በመስቀል ላይ በውክልና እንደሞተልን እናውቃለን፣ ነገር ግን እንዴት በእኛ ፋንታ ሊሞት ይችላል?

ጳውሎስ እነዚህን ጥያቄዎች በዚህ ክፍል የመለሰ ሲሆን፣ የመልእክቱም እምብርት ይኸው ነው። እነዚህን ቁጥሮች ለመረዳት፣ ስለ ጠቅላላ ክፍሉ ያለውን እውነት ልናውቅ ይገባል። በመጀመሪያ፣ አንድ የምትለዋን ቃል ድግግሞሽ አስተውሉ። አሥራ አንድ ጊዜ ተጠቅሷል። ቁልፍ አሳቡ ከአዳምና ከክርስቶስ ጋር ያለንን አንድነት ለማሳየት ነው። በሁለተኛ ደረጃ፣ ነገሠ የሚለውን ቃል አስተውሉ። አምስት ጊዜ ተደጋግሟል። ጳውሎስ ሁለት ሰዎችን- አዳምና ክርስቶስን አይቷል፣ ሁለቱም የሚገዙት ግዛት አላቸው። በመጨረሻም፣ ይልቅ የሚለው ቃል አምስት ጊዜ መደጋገሙን ተመልከቱ። ይህም በአዳም ካጣነው ይልቅ በኢየሱስ ክርስቶስ ያገኘነው እንደሚበልጥ የሚያመለክት ነው!

በአጭሩ፣ ይህ ክፍል አዳምና ክርስቶስ በንጽጽር የቀረቡበት ነው። አዳም በአሮጌው ፍጥረት ሁሉ ላይ ሥልጣን ተሰጥቶት ነበር፣ ነገር ግን ኃጢአትን በመሥራቱ ሥልጣኑን አጣ። ከአዳም ኃጢአት የተነሣ፣ ሰዎች ሁሉ በሞት ፍርድ ሥር ሆኑ። ክርስቶስ ደግሞ በአዲስ ፍጥረት ላይ ንጉሥ ሆኖ መጣ (2ኛ ቆሮ. 5:17)። በመስቀል ላይ በመታዘዙ፣ ጽድቅንና ጻድቅነትን አመጣ። በዚህም ክርስቶስ አዳም ያጠፋውን ማቃናት ብቻ

ሳይሆን፣ ከዚህ ይልቅ እኛን የእግዚአብሔር ልጆች አደረገን:: «ይልቅ» የሚለውን ቃል ጳውሎስ በሮሜ 5:1-11 አብራርቶታል::

ተጠራጣሪ ሰዎች፣ «በአንድ ሰው አለመታዘዝ እግዚአብሔር ዓለምን በሙሉ መኮነኑ ተገቢ ነውን?» ብለው ይጠይቃሉ:: መልሱ ደግሞ ተገቢ ብቻ ሳይሆን፣ ጥበብንና ቸርነትን የተሞላ ውሳኔ ነው የሚል ይሆናል:: እግዚአብሔር እያንዳንዱን ሰው እንደገና ቢፈትነው፣ ውጤቱ ያው አለመታዘዝ ይሆናል:: ከሁሉም በጣም አስፈላጊው፣ በአንድ ሰው (አዳም) ምክንያት የሰው ዘር ሁሉ ቢኮነንም፣ *በአንድ ሰው (ኢየሱስ ክርስቶስ) አማካኝነት ዓለሙን ሁሉ ማዳን ችሏል!* ሁላችንም በሥጋ የአዳም ዘር (ጥንተ አብሶ) ስላለን፣ *ሥራው* እኛንም ይነካካናል (በተጨማሪ ዕብ. 7:9-10 ላይ የዝርያን (ራስ) ምሳሌ ይመልከቱ):: የወደቁት መላእክት ዘሮች ስላልሆኑ አይድኑም:: በግል ኃጢአትን ሠርተዋል፣ በግልም ፍርድን ተቀብለዋል:: ምትክ ሆኖ ፍርዳቸውን ተቀብሎ የሚያድናቸው የለም:: የሰው ዘር ራስ በሆነው በአዳም ምክንያት ጠፍተን ነበርን፣ ነገር ግን የአዲሱ ፍጥረት ራስ በሆነው በክርስቶስ መዳን እንችላለን:: የእግዚአብሔር ዕቅድ ቸርነትንና ጥበብን የተሞላ ነበር::

ከአዳም ጋር በሥጋ መወገናችን እንዴት ይታወቃል? የሚለው ጥያቄ መመለስ አለበት:: መልሱ በሮሜ 5:12:14 ይገኛል፣ አሳቡም እንደሚከተለው ነው:- ሰዎች ሁሉ እንደሚሞቱ እናውቃለን:: ሞት ደግሞ ሕግን ያለ መታዘዝ ውጤት ነው:: ከአዳም እስከ ሙሴ ሕግ አልነበረም፣ ነገር ግን ሰዎች ይሞቱ ነበር:: ለጅምላ ውጤት መንሥኤውም እንዲሁ ጅምላ ይሆናል:: ለመሆኑ ምክንያቱ ምን ነበር? አንድ ነገር ብቻ ነው ሊሆን የሚችለው:- እርሱም የአዳም አለመታዘዝ ነው:: አዳም ኃጢአትን በሠራ ጊዜ:- ሙት ሆነ:: ዝርያዎቹ ሕግ ባይሰጥም እንኳ ሞቱ (ዘፍጥ. 5):: መደምደሚያው:- አሁን የሞቱት በአዳም ኃጢአት እንዲሆን ያሳያል:: «ሁሉ ኃጢአትን ስላደረጉ» (ቁ. 12) የሚለው «ሁሉም በአዳም ኃጢአትን አድርገዋል» ማለቱ ነው:: ሰዎች የሚሞቱት አሁን በሚሠሯቸው የኃጢአት

ፍሬዎች አይደለም፤ ቢሆንማ ኖሮ፣ ምንም የማያውቁ ሕፃናት አይሞቱም ነበር (ሮሜ 9:11):: ሰዎች የሚሞቱት የአዳም ዘር ፍሬ ስለሆኑ ነው፣ «ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ» ይላልና (1ኛ ቆሮ. 15:22)::

የክፍሉን አጠቃላይ እውነቶች በተመለከተ በቂ ግንዛቤ ካገኘን፣ ጳውሎስ በአዳምና በክርስቶስ መካከል ማለትም የአዳምን ኃጢአትና የክርስቶስ በመስቀል ላይ የመታዘዝ ሥራ በንጽጽር እንመርምር::

ሀ) *የአዳም ሕግ መጣስ ከክርስቶስ ነፃ ስጦታ ጋር ተነጻጽሯል* (5:15)- አዳም በመተላለፉ፣ ብዙ ሰዎች ሞተዋል፤ በክርስቶስ መታዘዝ የእግዚአብሔር ጸጋ ለብዙዎች ሕይወትን አበዛ:: በቁጥር 12 እና 18 ያለው «ሁሉ» የሚለው ቃል፣ «ሰዎች ሁሉ» ማለቱ ነው:: «ይልቅ» እንዳልነው የክርስቶስን ጸጋ ለሰዎች ያመጣው ሥጋዊ ሕይወት ብቻ ሳይሆን፣ መንፈሳዊና የተትረፈረፈ ሕይወትም ነው:: ክርስቶስ ሞትን ስላሸነፈ፣ «በክርስቶስ» ሆነው የሞቱትን አካል ያስነሣል:: ነገር ሁሉ እዚህ ላይ ቢያቆም ኖሮ፣ የአዳምን ኃጢአት ብቻ ቀልብሶ ይቀር ነበር:: ነገር ግን «ከዚህ ይልቅ» ለሚያምኑበት ሁሉ፣ የዘለዓለማዊና የተትረፈረፈ ሕይወትን ሰጠ (ዮሐ. 10:10)::

ለ) *የአዳም ኃጢአት ከክርስቶስ መታዘዝ ጋር ሲነጻጸር* (5:16)- የአዳም ኃጢአት ፍርድንና ኩነኔን አመጣ፤ ክርስቶስ በመስቀል ላይ የሠራው ሥራ ግን ጽድን አስገኘ:: አዳም ኃጢአትን በሠራ ጊዜ ኃጢአተኛ ተብሎ ተኮነነ:: አንድ ኃጢአተኛ በክርስቶስ ሲያምን ግን፣ በክርስቶስ ጻድቅ ሆኖ ይቆጠርና ይጸድቃል::

ሐ) *ሁለቱ «ንግሥናዎች» ተነጻጽረዋል* (5:17)- በአዳም ያለመታዘዝ ሞት ነገሠ:: ዘፍጥረት ምዕራፍ 5 ላይ ያለውን የአዳምን ትውልድ መጽሐፍ በማንበብ «ሞተም» የሚለውን ቃል ከበድ ያለ ድግግሞሽ አስተውሉ:: በቁጥር 14 ላይ «ከአዳም እስከ ሙሴ» የነበሩት ሰዎች የሞቱት የተገለጠ የእግዚአብሔርን ሕግ በመጣስ ምክንያት እንዳልሆነ ጳውሎስ የሕግን አለመጠቀስ

በማሳሰብ ይሟገታል። «የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው» (ሮሜ 6:23)። ኃጢአት በሰዎች ሕይወት ስለነገሠ (ሮሜ 5:21)፣ ሞትም እንዲሁ ነግሦ ነበር (ቁ. 14 እና 17)።

ነገር ግን በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ አዲስ መንግሥት እንገባለን፡- «የእግዚአብሔር መንግሥት ጽድቅና ሰላም በመንፈስ ቅዱስም የሆነ ደስታ ናት እንጂ መብልና መጠጥ አይደለችምና» (ሮሜ 14:17)። «በእምነት የጸደቅን ሆነናል፣ ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም አለን፣ ስለዚህም በእግዚአብሔር የክብር ተስፋ እንደሰታለን። እኛ እንደነገሥን አስተውሉ! «በአንዱ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በሕይወት ይነግሣሉ» ተብሏልና (5:17)።

መ) *ሁለቱ «አንድ ድርጊቶች» ሲነጻጸሩ* (5:18-19)- አዳም ኃጢአትን እያከታተለ አልፈጸመም። እግዚአብሔር አዳምን በአንድ ነገር ሲፈትነው ወደቀ። ይህ «ሕግ መጣስና» አለመታዘዝ ሆኖ ተቆጠረ። «ሕግ መጣስ» ማለት «መተላለፍ፣ ኬላን ያለፍቃድ ማቋረጥ» የማለት ያህል ነው። አዳም የት ድረስ መሄድ እንዳለበት እግዚአብሔር ለአዳም ቢነግረውም፣ አዳም ግን ከተባለው ወሰን አልፎ ለመሄድ ወሰነ። «እግዚአብሔር አምላክም ሰውን እንዲህ ብሎ አዘዘው፡- ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ፤ ነገር ግን መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ፤ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና።» (ዘፍጥ. 2:16-17)።

ከአንድ ሰው «መተላለፍ» የሚነጻጸረው የአንድ ሰው «ጽድቅ»፣ ማለትም የክርስቶስ የመስቀል ላይ የጽድቅ ሥራ ነው። በቁጥር 19 ላይ ጳውሎስ «በአንዱ መታዘዝ» ብሎ ይናገራል (ፊልጵ. 5-12ን ይመልከቱ)። የክርስቶስ የመስቀል ላይ መሥዋዕትነት ያመጣው «ጽድቅን» ብቻ ሳይሆን፣ ሕይወታችንን ለማጽደቅም ጭምር ነው። ጻድቅ ተደርጎ መቆጠር በእግዚአብሔር ፊት ያለንን ስፍራ የሚያሳይ ምንም ኃጢአት እንዳልሠራን የሚገልጽ የሕግ ቃል ብቻ ሳይሆን፣ በአንድ የአኗኗር ዓይነት በሕይወታችን ይታያል። በቁጥር 18 ላይ ያለው «ሕይወታችንን ማጽደቅ» የሚለው ቃል በቁጥር 19 «ብዙዎች

ጻድቃን ይሆናሉ» ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ነው:: በሌላ አነጋገር ጽድቃችን ከክርስቶስ ጋር የመጣበቃችን ውጤት ነው:: ይህም ኅብረት ለእግዚአብሔር የሚታዘዝን አዲስ የጽድቅ ሕይወት ያስገኛል:: የአዳም ወገን በመሆናችን ኃጢአተኞች ሆንን፤ የክርስቶስ ወገን በመሆናችን ደግሞ «በሕይወት እንድንነግሥ» አስቻለን::

*ሠ) ሕግና ጸጋ ተነጻጽረዋል* (5:20-21):: «ሕግ ገባ»፤ ጸጋ እግዚአብሔር በኋላ ላይ ከዕቅዱ መካከል አሾልኮ ያስገባው ነገር ሳይሆን፣ በመጀመሪያው በእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ የነበረው ነው:: እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን የደረሰላቸው በጸጋው ነው፤ ከአባቶች ጋር የነበረው ግንኙነት በጸጋው ነው፤ እስራኤልን ያያት በጸጋው ነው:: እግዚአብሔር ሕግን በሙሴ በኩል የሰጠው ጸጋውን በሕግ ለመተካት ሳይሆን፣ የሰው ልጅ ጸጋ እንደሚያሻው ለመግለጥ ነው:: ሕግ ጊዜያዊ ነው፣ ጸጋ ግን ዘለዓለማዊ ነው::

ሕግ የሰውን ኃጢአት ሲያገንነው፣ የእግዚአብሔር ጸጋ እጅግ አብልጦ በዛ:: የእግዚአብሔር ጸጋ ለሰው ኃጢአት መፍትሔ ከመስጠት በላይ ነው:: ኃጢአትና ሞት አሁንም በዓለም ላይ ቢነግሡም፣ የእግዚአብሔር ጸጋ በክርስቶስ ጽድቅ በኩል ነግሷል:: የክርስቲያን አካል ለሞት የተገዛ በመሆኑ አሮጌው ባሕሪው ኃጢአት እንዲያደርግ ይፈትነዋል፤ ነገር ግን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የክርስቶስ *መንግሥት* አካል ስለሆነ «በሕይወት *መንገሥ*» ይችላል::

በሁለቱ «*መንግሥታት*» መካከል የሚደረገውን ግጭት በተመለከተ አንድ የብሉይ ኪዳን *ታሪክ* ግንዛቤ ያስጨብጠናል:: እግዚአብሔር ሳዖል የእስራኤል ንጉሥ እንዳይሆን ንቆ ዳዊትን ቀባው:: ዳዊትን *ያመኑ* በመጨረሻ የመንግሥቱ ሰላምና ደስታ ተካፋይ ሆኑ:: ሳዖልን *ያመኑ* ደግሞ መጨረሻቸው ኃፍረትና ሽንፈት ሆነ::

እንደ ዳዊት፣ ኢየሱስ ክርስቶስ በእግዚአብሔር የተቀባ ንጉሥ ነው:: እንደ ሳዖል፣ ሰይጣን ደግሞ ነፃ ሆኖ በዓለም ላይ በመሥራት ሰዎች ከእርሱ ጋር እንዲወግኑ ልባቸውን ይፈልጋል:: ኃጢአትና ሞት አዳም ገዢ በነበረበት «አሮጌው ፍጥረት» የነገሡ ሲሆን፣ ጸጋና ጽድቅ ግን ክርስቶስ ገዢ በሆነበት «በአዲሱ ፍጥረት» ነግሠዋል:: ለጌታ ስንሸነፍ «በሕይወ ላይ እንነግሣለን::»

በቁጥር 14፣ አዳም «ይመጣ ዘንድ ላለው ለእርሱ አምሳሉ ነውና» ተብሎ ተጠርቷል:: አዳም የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ፣ ወይም ጥላ ነበር:: አዳም ምድራዊ ሲሆን፣ ኢየሱስ ግን ከሰማይ የመጣ ጌታ ነው (1ኛ ቆሮ. 15:47):: አዳም የተፈተነው በውበትና በፍቅር ተከብቦ በዔድን ገነት ነው፤ ኢየሱስ ግን የተፈተነው በምድረ በዳ እና በጭከና በመስቀል ላይ ሲሞት በጥላቻ ተከብቦ ነው:: አዳም ሌባ በመሆኑ ከገነት ተባረረ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ወደ ሌባው ዞሮ፣ «ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ» አለ (ሉቃስ 23:43):: ብሉይ ኪዳን «የአዳም ትውልድ መጽሐፍ» ሲሆን (ዘፍጥ. 5:1)፣ ፍጻሜውም መርገም ነው (ሚል. 4:6):: አዲስ ኪዳን ግን «የኢየሱስ ክርስቶስ ትውልድ መጽሐፍ» ነው (ማቴ. 1:1)፣ ፍጻሜውም መርገም የሌለበት ነው (ራእ. 22:3)::

«አዳማዊ» መሆናችሁ ከእናንተ ቁጥጥር ውጭ በሆነው የመጀመሪያ ልደት የመጣ በመሆኑ ምንም ማድረግ አትችሉም:: ነገር ግን በአዳም ውስጥ ሳላችሁ በክርስቶስ በሰማያዊ ስፍራ የሚያስቀምጣችሁን ከሰማይ የሆነውን አዲስ ውልደት (ሁለተኛ ልደት) በመለማመድ «የክርስቶስ» መሆን ትችላላሁ:: ኢየሱስ «ዳግመኛ ልትወለዱ ያስፈልጋችኋል» ያለው ለዚህ ነው (ዮሐ. 3:7)::

# ሮሜ 6:1-23

እንግዲህ ምን እንላለን? ጸጋ እንዲበዛ በኃጢአት ጸንተን እንኑርን? አይደለም:: ለኃጢአት የሞትን እኛ ወደ ፊት እንዴት አድርገን በእርሱ እንኖራለን? ወይስ ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደ ተጠመቅን አታውቁምን? እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደ ተነሣ እንዲሁ እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ፣ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን::

ሞቱንም በሚመስል ሞት ከእርሱ ጋር ከተባበርን ትንሣኤውን በሚመስል ትንሣኤ ደግሞ ከእርሱ ጋር እንተባበራለን፤ ከእንግዲህስ ወዲያ ለኃጢአት እንዳንገዛ የኃጢአት ሥጋ ይሻር ዘንድ አሮጌው ሰዋችን ከእርሱ ጋር እንደ ተሰቀለ እናውቃለን፤ የሞተስ ከኃጢአቱ ጸድቆአልና:: (ሮሜ 6:1-7)

ብልቶቻችሁንም የዓመፃ የጦር ዕቃ አድርጋችሁ ለኃጢአት አታቅርቡ፣ ነገር ግን ከሙታን ተለይታችሁ በሕይወት እንደምትኖሩ ራሳችሁን ለእግዚአብሔር አቅርቡ፣ ብልቶቻችሁንም የጽድቅ የጦር ዕቃ አድርጋችሁ ለእግዚአብሔር አቅርቡ:: (ሮሜ 6:13-14)::

የኃጢአት ባሪያዎች ሳላችሁ ከጽድቅ ነፃ ነበራችሁና:: እንግዲህ ዛሬ ከምታፍሩበት ነገር ያን ጊዜ ምን ፍሬ ነበራችሁ? የዚህ ነገር መጨረሻው ሞት ነውና:: አሁን ግን ከኃጢአት አርነት ወጥታችሁ ለእግዚአብሔርም ተገዝታችሁ፣ ልትቀደሱ ፍሬ አላችሁ፤ መጨረሻውም የዘላለም ሕይወት ነው:: የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነውና የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን የዘላለም ሕይወት ነው:: (ሮሜ 6:20-23)::

# 5

# ለመኖር መሞት

በፍርድ ሥርዓት መሃል ጠበቃ ቆሞ፣ «ክቡር ፍርድ ቤት፣ ይህን እቃወማለሁ!» ይላል:: በሮም የነበሩ ክርስቲያኖችም የጳውሎስ መልእክት ሲነበብ ሲሰሙ፣ አሳባቸውን እንዳወቀባቸው ስለሚያስቡ ለመቃወም ይፈልጉ ይሆናል:: ከምዕራፍ 6-8 ጳውሎስ በእምነት የመጽደቅን አስተምህሮ ይመክታል:: ሦስት ተቃሞዎች ሊነሡ እንደሚችሉ ገምቷል:- 1) «ኃጢአት ስናበዛ ጸጋ አብልጦ ከበዛ የበለጠ ጸጋ እንድናገኝ አብዝተን ኃጢአት እንሥራ » (6:1-14)፣ 2) «ከሕግ በታች ካልሆንን እንግዲያውስ እንዳሻን እንኑር» (6:15-7:6)፤ እና 3) «የእግዚአብሔርን ሕግ ኃጢአተኛ አድርገሃል» (7:7-25) የሚሉት ናቸው::

እነዚህ ተቃውሞዎች አንባቢዎቹ ሕግንም ሆነ ጸጋን በሚገባ እንዳልተገነዘቡ ያሳያሉ:: በአንድ በኩል ሕግ አጥባቂነት በሌላ በኩል ደግሞ የኃጢአት ፈቃድ (ሊቸንሳ) በመስጠት ወደ ሁለት ጽንፍ አለቅጥ ተጉዘዋል:: ጳውሎስ ጻድቅ ሆኖ የመቆጠርን አስተምህሮ ሲያስረዳ አብሮ ቅድስናንም አብራርቷል:: እንዴት በድል እንደምንኖር (ምዕራፍ 6)፣ እንዴት በነጻነት እንደምንኖር (ምዕራፍ 7)፣ የእኛ ዋስትናችንን (ምዕራፍ 8) አስመልክቶ ተናግሯል:: ከሥጋ፣ ከሕግና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ስለሚኖረን ኅብረትም በስፋት ተናግሯል:: በምዕራፍ 6 በኃጢአት ላይ ድልን ለማግኘት ሦስት መመሪያዎችን ሰጥቷል::

## 1. እወቁ (6:1-10)

በቁጥር 1:6 እና 9 ላይ «ማወቅ» የሚለው ቃል ርቢ ተደጋግሞ መጠቀስ ጳውሎስ አንድን አስተምህሮ እንድናውቅለት መፈለጉን ያመለክታል:: የክርስትና ሕይወት ከክርስቲያናዊ አስተምህሮ ጋር የተያያዘ ነው፤ የተግባራችን መሠረቱ አስተምህሮ ነው:: ሰይጣን አንድን ክርስቲያን ከእውቀት ጎዳና ካወጣ ፍሬ አልባ ያደርገዋል::

የጳውሎስ ትምህርት መሠረታዊ እውነት አማኞች ከክርስቶስ ጋር በሞቱ፣ በቀብሩና በትንሣኤው መተባበራቸው ነው። ከአዳም ጋር በኃጢአትና በፍርድ እንደ ተባበርን፣ አሁን ደግሞ ከክርስቶስ ጋር በጽድቅና ጻድቅነት እንተባበራለን። ሮሜ 5:12 ላይ ጳውሎስ «ኃጢአቶች» የሚለውን ትቶ «ኃጢአት» እያለ አሳቡን አቅርቧል። ከውጤቱ ይልቅ ወደ ሥረ መሠረቱ፣ ከፍሬውም ይልቅ ወደ ሥሩ አምርቷል። ኢየሱስ ክርስቶስ የሞተው ለኃጢአታችን ብቻ ሳይሆን፣ ለኃጢአትም በመሆኑም፣ እኛም አብረነው ሞተናል። ምናልባትም የሚከተለው ንጽጽር ይህን የበለጠ ያብራራልናል።

| ሮሜ 3:21-5:21 | ሮሜ 6-8 |
|---|---|
| ምትክ- ስለ እኔ ሞተ | መተባበር -አብሬው ሞቻለሁ |
| ለኃጢአቴ ሞተ | ለኃጢአት ሞተ |
| የኃጢአትን ዋጋ ከፈለ | የኃጢአትን ጉልበት ሰበረ |
| ጻድቅ ሆኖ መቆጠር- | ጽድቅ - ለእኔ ጽድቅ |
| መቀደስ - | የሕይወቴ አካል ሆነ |
| በሞቱ መዳን | በሕይወቱ ድኛለሁ |

በሌላ አባባል በእምነት የሚገኝ ጽድቅ በእኔና በእግዚአብሔር መካከል ያለ ሕጋዊ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን፣ ሕያው ኅብረትም ነው። «ሕይወትን ለማጽደቅ» ነው (ሮሜ 5:18)። «እኔ በክርስቶስ ነኝ» ከእርሱ ጋርም እተባበራለሁ። ስለዚህ በክርስቶስ የሆነው ሁሉ ለእኔም ሆኗል። ሲሞት፣ ሞቻለሁ። ሲነሣም፣ ተነሥቻለሁ። አሁን ከእርሱ ጋር በሰማያዊ ስፍራ ተቀምጫለሁ ! (ኤፌ. 2:1-10፤ ቆላ. 3:1-3 ተመልከቱ)። ከክርስቶስ ጋር ካለው ሕያው ኅብረት የተነሣ፣ አንድ አማኝ ከኃጢአት ጋር የሚኖረው ግንኙነት አዲስ ይሆናል።

ሀ) *ለኃጢአት ሞቷል* (6:2-5)- ጳውሎስ የተጠቀመበት ምሳሌ ጥምቀትን ነው። የግሪኩ ቃል ሁለት ትርጉም አለው:- 1) አንድ

ቀጥታ ትርጉም- መጥለቅ ወይም መስጠም የሚለው ሲሆን፣ 2) ምሳሌያዊ ትርጉም - መተባበር የሚሉት ናቸው:: የሁለተኛው ምሳሌ ሊሆን የሚችለው 1ኛ ቆሮንቶስ 10:2 ይሆናል፣ «ሁሉም ሙሴን ይተባበሩ ዘንድ በደመናና በባሕር ተጠመቁ::» የእስራኤል ሕዝብ የቀይ ባሕርን ሲሻገሩ ከመሪያቸው ከሙሴ ጋር ተባብረዋል::

ጳውሎስ ይህንን አንቀጽ ሲጽፍ ቀጥተኛውንና ምሳሌያዊውን ትርጓሜ ከግምት አስገብቷል:: የአንባቢዎቹን የውኃ ጥምቀት በመጠቀም፣ በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ከክርስቶስ ጋር መተባበራቸውን አሳስቧቸዋል:: ቁጥር 3 ላይ ያለው «ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን» የሚለው፣ በ1ኛ ቆሮ. 12:13 ላይ «በአንድ መንፈስ አንድ አካል እንሆን ዘንድ» ካለው ጋር ተመሳሳይ ነው:: በውኃ ጥምቀትና በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት መካከል ልዩነት አለ (ዮሐ. 1:33):: ኃጢአተኛ በክርስቶስ ሲያምን ወዲያውኑ የእግዚአብሔር ቤተሰብ በመሆን የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ ይቀበላል:: ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆኑን በቆርኔሌዎስ ቤት የጴጥሮስን ስብከት ሲሰሙ የተፈጸመው ነው (የሐዋ. 10:34-48):: እነዚህ ሰዎች በክርስቶስ ሲያምኑ ወዲያውኑ መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ:: ወዲያውም ተጠመቁ:: «በእርሱ የሚያምን ሁሉ የኃጢአትን ሥርየት ይቀበላል» የሚለው የጴጥሮስ ቃል የሚያስፈልጋቸውን ተስፋ ሰጣቸው:: አመኑ - ዳኑም!

ታሪክ አዋቂዎች እንደሚናገሩት የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን የጥምቀት ሥርዓት በማጥለቅ ነበር:: አማኙ በውኃ ውስጥ ሲጠልቅና ሲወጣ የሞት፣ የቀብርና የትንሣኤ ምሳሌ ይሆናል:: የአማኙ በጥምቀት መጥለቅ (ጳውሎስ በሮሜ 6 እንደገለጸው) አማኙ በሞት፣ በቀብርና በትንሣኤ ከክርስቶስ ጋር መተባበሩን ያመለክታል:: በውስጥ የምንለማመደውን ለመግለጽ የምንጠመቅበት ውጫዊ ሥርዓት ነው:: ጳውሎስ በዚህ ስፍራ በውኃ መጠመቅ «በክርስቶስ እንዲሆኑ ያስችላቸዋል» ማለቱ አይደለም፣ ምክንያቱም ባመኑ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ይህን

ፈጽሞታልና። መጥለቃቸው መንፈስ ቅዱስ በሕይወታቸው የሠራውን ሥራ የሚገልጽ ነው። መንፈስ ቅዱስ በክርስቶስ ሞት፣ ቀብርና ትንሣኤ እንዲተባበሩ አድርጎአቸዋልና።

ይህም አማኙ ስለ ኃጢአት አዲስ ዕድገት ምልክት ይኖረዋል ማለት ነው። «ለኃጢአት ሙት ነው።» «ከክርስቶስ ጋር ተሰቅዬአለሁ» (ገላ. 2:20)። ስካራም ሰው ሲሞት፣ አካላዊ ስሜቱም ስለሚሞት በመጠጥ አይፈተንም። የአልኮል መጠጥን ማሽተት፣ መቅመስ ወይም መሻት አይችልም። በኢየሱስ ክርስቶስ ለኃጢአት ስለሞትንም «በኃጢአታችን ለመቀጠል አንፈልግም።» ለኃጢአት መሞት ብቻ ሳይሆን፣ በክርስቶስ ሕያዋንም ሆነናል። ከሞት ስለተነሣን፣ በትንሣኤው ኃይል እንኖራለን። «በአዲስ ሕይወት» እንመላለሳለን። ምክንያቱም በእርሱ ሕይወት እንካፈላለንና። «ከክርስቶስ ጋር ተሰቅዬአለሁ. . . የምኖረው» (ገላ. 2:20)።

ይህ ድንቅ የሆነ መንፈሳዊ እውነት በአልዓዛር የትንሣኤ ተአምር የበለጠ ተብራርቷል (ዮሐ. 11)። ኢየሱስ በቢታንያ ሲደርስ አልዓዛር በመቃብር ውስጥ አራት ቀን ስላሳለፈ ለመሞቱ ምንም ጥያቄ የለውም። በኢየሱስ ክርስቶስ በቃሉ ኃይል («አልዓዛር ውጣ!») ኢየሱስ ወዳጁን ከሙታን አስነሥቶታል። ነገር ግን አልዓዛር በመቃብር በር ላይ ቆሞ ሲታይ፣ በጨርቅ ተጠምጥሞ ነበር። «በአዲስ ሕይወት» እንዲመላለስ ተነሥቷል፣ ኢየሱስ «ፍቱትና ይሂድ!» ብሎ አዘዛቸው። በዮሐንስ 12 ላይ አልዓዛር ከጌታ ጋር በማዕድ ዙሪያ ተቀምጦ ኅብረት ያደርግ ነበር። አልዓዛር ሞተ- ከሙታን ተነሣ- በአዲስ ሕይወት ሊኖር ነፃ ወጣ- ከክርስቶስ ጋር ተቀመጠ- እነዚህ መንፈሳዊ እውነታዎች በኤፌሶን 2:1-10 የተገለጸውን የእኛን ማንነትም የሚያሳዩ ናቸው።

ብዙ ክርስቲያኖች «መሃል ሰፋሪዎች» ናቸው። ኑሮአቸው በግብጽና በከነዓን መካከል ነው፣ ድነዋል ግን ገና አልረኩም። የሚኖሩት በስቅላትና በትንሣኤው መሃል ነው፣ በመስቀሉ

ያምናሉ ነገር ግን ወደ ትንሣኤው ኃይልና ክብር አልገቡም:: ቁጥር 5 ከክርስቶስ ጋር ያለን ኅብረት ወደፊት ስንሞት ትንሣኤ እንዳለን ያስረዳል:: ቁጥር 4 ደግሞ የትንሣኤውን ኃይል ዛሬውኑ እንደምንካፈል ያስተምራል:: «እንግዲህ ከክርስቶስ ጋር ከተነሣችሁ፣ ክርስቶስ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦ ባለበት በላይ ያለውን እሹ፤ በላይ ያለውን አስቡ እንጂ በምድር ያለውን አይደለም» (ቆላ. 3:1-3)::

አንድ አማኝ ከክርስቶስ ጋር ስለተባበረ ለኃጢአት ያለው አመለካከት በመለወጡ አውቆ ኃጢአትን አያደርግም:: የአማኙ አሮጌ ሰው አልፏልና፤ ነገር ግን በአዲስ ሕይወት ተነሥቷል:: አልዓዛር በከፈን ተጠቅልሎ ወደ መቃብር ለመውረድ እንደማይፈልግ ሁሉ፣ አማኝም ወደ ኃጢአት ኑሮ ለመመለስ አይፈልግም:: በመቀጠልም ጳውሎስ ሁለተኛውን ማስረጃ ያቀርባል:-

ለ) *ኃጢአትን አያገለግልም* (6:6-10) - ኃጢአት በባሕርይው ኃይለኛ ገዢ ነው:: ስለሆነም በሰው አካል ውስጥ በፈቃዱ የሚታዘዝለትን ይፈልጋል:: *ሥጋችን* በባሕሪው ኃጢአተኛ አይደለም፤ ገለልተኛ ነው:: በኃጢአት ወይም በእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር መሆን ይችላል:: ነገር ግን የወደቀ የሰው ባሕርይ በመለወጣችን ወቅት ካልተቀየረ ለኃጢአት እጁን በመስጠት እንድንጠቃና እንዲቆጣጠረን በር ይከፍታል:: ጳውሎስ ይህንን ችግር ሲገልጠው «በእኔ ማለት በሥጋዬ በጎ ነገር እንዳይኖር አውቃለሁና፤ ፈቃድ አለኝና፣ መልካሙን ግን ማድረግ የለኝም» (ሮሜ 7:18)::

በዚህ ስፍራ አንድ ትልቅ እውነት ቀርቧል- አሮጌው ሰው ከክርስቶስ ጋር ተሰቅሏል:: ስለሆነም *ሥጋችን* በኃጢአት ቁጥጥር ሥር ሊወድቅ አይገባውም:: በቁጥር 6 ላይ ያለው «ይሻር» የሚለው ቃል ፈጽሞ መጥፋቱን የሚያመለክት ሳይሆን፣ «እንዳይሠራ መደረጉን» ለማመልከት ነው:: ይሄው ቃል በሮሜ 7:2 ላይ «ተፈትታለች» በሚለው ቃል ተተርጉሞ እናገኘዋለን:: አንድ ሴት ባሏ ቢሞት ስለ ባልዋ ከሆነው ሕግ ተፈትታ ዳግመኛ

ማግባት ትችላለች:: ይህም ሴቲቱ ከባልዋ ጋር የነበራትን ኅብረት መቀየሯን ያሳያል:: ሕጉ አለ፣ ነገር ግን ባልዋ በመሞቱ በሴቲቱ ላይ ምንም ሥልጣን የለውም::

ኃጢአት ሊገዛን ይፈልጋል:: በአሮጌው ሰውነታችን ላይ ተንጠላጥሎ የሰውነታችንን ክፍሎች ሊቆጣጠር ይፈልጋል:: ነገር ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ለኃጢአት ሞተናል:: በዚህም አሮጌው ሰውነታችን ተሰቅሏል፣ ይሠራ ዘንድ ዐቅም የለውም:: ጳውሎስ በዚህ ስፍራ የሕይወት ልምዱን እያካፈለ ሳይሆን፣ እውነታን እያስቀመጠ ነው:: እውነተኛው ልምምድ ወደ ኋላ ላይ ይመጣል:: ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል መሞቱን ታሪክ ዘግቧል:: አማኞችም ከእርሱ ጋር መሞታቸውን ታሪክ ይመሰክራል፤ «የሞተ ከኃጢአቱ ጸድቆአልና» (ቁ. 7):: የጳውሎስ ከሳሾች እንደሚሉት «ኃጢአትን ለማድረግ ነፃ መውጣት» ሳይሆን፤ «ከኃጢአት ነፃ» መሆን ነው::

ኃጢአትና ሞት በክርስቶስ ላይ ሥልጣን የላቸውም:: እኛም «በክርስቶስ» ስለሆንን፣ ኃጢአትና ሞት በእኛ ላይ ሥልጣን የላቸውም:: ኢየሱስ ክርስቶስ የሞተው «ስለ ኃጢአት» ብቻ ሳይሆን፣ «ለኃጢአትም» ነው:: የኃጢአትን ቅጣት ለመክፈል ብቻ ሳይሆን፣ የኃጢአትን ኃይልም ሰብሮታል:: የዚህ ሥልጣን ጉዳይ ወደ ሮሜ 5:12-21 መልሶ ይመልስልናል:: በዚህ ስፍራ ጳውሎስ የኃጢአትና የሞትን «ንጉሥነት» እና ስለ ጸጋ ተናግሯል:: በክርስቶስ «በሕይወት እንነግሣለን» (5:17) ስለሆነም ኃጢአት እንደገና አይቆጣጠረንም::

አሁን መጠየቅ ያለበት ትልቁ ጥያቄ፣ «የታሪክን እውነታ (ሐቅ) አምናለሁ፤ ነገር ግን ይህን በየቀኑ በሕይወቴ ለመለማመድ ምን ማድረግ አለብኝ?» የሚለው ነው:: ይህም ወደ ሁለተኛው የጳውሎስ አንኳር ነጥብ ይመራናል::

## 2. ቁጠሩ (6-11)

«ቁጠሩ» የሚለው ቃል በአዲስ ኪዳን 41 ጊዜ የተጠቀሰ ሲሆን፣ 19 ጊዜ የተጠቀመበት በሮሜ መልእክት ውስጥ ነው::

ትርጓሜውም ራስን እንደ አንድ ነገር አድርጎ ማሰብ ማለት ነው።

«ራስን መቁጠር» ማለት ራሳችንን በአንድ ሰው ቦታ ማስቀመጥ ማለት ሲሆን፣ እግዚአብሔር በቃሉ የተናገረው እውነት በሕይወታችሁም እውነት መሆኑን ማመን ማለት ነው።

ጳውሎስ ለአንባቢዎቹ የነገራቸው ለኃጢአት እንደ ሞቱ፣ ወይም ይህን በሙላት እንዲገነዘቡ ሳይሆን፣ የእግዚአብሔርን ቃል ተቀብለው የራሳቸው እንዲሆን አድርገው እንዲቆጥሩ ነው። «ራስን እንደ መቁጠር» በሥራ የሚገለጥ እምነት ነው። ልክ የባንክ ቼክ ላይ እንደ መፈረም ነው- ባንክ ውስጥ ገንዘብ እንዳለን ካመንን ቼኩ ላይ ፈርመን ገንዘቡን መውሰድ ነው። መቁጠር ተስፋን ለመቀበል ማወጅ ሳይሆን፣ በእውነታው ላይ እርምጃ መውሰድ ነው። እግዚአብሔር ለኃጢአት ሙት እንድንሆን አላዘዘንም። እርሱ ለኃጢአት ሞተን ለእግዚአብሔር እንድንኖር ነገሮናል። በዚህ እውነት ላይ እርምጃ እንድንወስድ ግን ያዘናል። እርምጃ ባንወስድም እንኳ፣ የተናገረው ሁሉ እውነት ሆኖ ይቀራል።

የጳውሎስ የመጀመሪያ መመሪያ «ማወቅ» በአእምሮ ዙሪያ ሲያጠነጥን፣፣ ሁለተኛውና «ቁጠሩ» የሚለው ቃል ደግሞ የሚያተኩረው በልባችን ላይ ነው። ሦስተኛው ትምህርቱ ደግሞ ፈቃዳችንን የሚዳስስ ነው።

## 3. አቅርቡ (6:12-23)

«አቅርቡ» የሚለው ቃል 5 ጊዜ ያህል የተጠቀሰ ሲሆን (ቁጥር 13፣16 እና 19)፣ ትርጉሙም «ራስን ለመሥዋዕትነት ማቅረብን» ይወክላል። እንደ ሮሜ 12:1 ከሆነ የአማኞች ሥጋ ለእግዚአብሔር ክብር በጌታ ፊት «ሕያው መሥዋዕት» ሊሆን ይገባዋል። የብሉይ ኪዳን መሥዋዕቶች የሞቱ መሥዋዕቶች ነበሩ። ጌታ አንዳንዶቻችንን እንድንሞትለት ይጠይቀን ይሆናል፣ ነገር ግን ሁላችንም ለእርሱ እንድንኖርለት ይሻል።

*ሀ) እንዴት ነው የምናቀርበው?* (6:12-13)- ይህ ክርስቶስ ለእኛ ያደረገውን ባወቅነው መሠረት የምንፈጽመው ፈቃዳችን ነው። በስሜታዊነት ተነድተን የምናደርገው ሳይሆን፣ በማስተዋል የሚፈጸም ጉዳይ ነው። በእነዚህ ቁጥሮች ያሉትን ግሦች ማስተዋል ጠቃሚ ነው። ወጥ ትርጉሙ «ስለዚህ ክፉ መሻቱን ትፈጽሙ ዘንድ በሚች ሥጋችሁ ላይ ኀጢአት እንዲነግሥበት አታድርጉ። ብልቶቻችሁን የክፋት መሣሪያ አድርጋችሁ ለኀጢአት አታቅርቡ፤ ይልቁንስ ከሞት ወደ ሕይወት እንደ ተሻገሩ ሰዎች አድርጋችሁ ራሳችሁን ለእግዚአብሔር አቅርቡ» (ሮሜ 6:12-13፣ አ.መ.ት) ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ራሳችንን እንዴት እንደምናቀርብ በሮሜ 12:1 ላይ ተገልጿል።

በአማኝ ሕይወት ውስጥ ሥጋችንን በሙላት ለኢየሱስ ክርስቶስ የምናቀርብበት አንድ የመጨረሻ ወቅት አለ። ይህም ወደ ፊት ራሳችንን አሳልፈን የምንሰጥበት እርከን የለም ማለት አይደለም። ምክንያቱም ይኖራል። ከክርስቶስ ጋር አብረን በተጓዝን ቁጥር ኅብረታችንም ሥር የሰደደ ይሆናል። ነገር ግን የመጀመሪያውን እርምጃ ሳንራመድ ቀጣዩን ደረጃ መራመድ አንችልም። በሮሜ 12:1 ላይ ያለው ግሥ በሮሜ 6:13 ካለው ጋር የተቆራኘ ነው- አንድ ጊዜ ራሳችሁን ለእግዚአብሔር አቅርቡ። ለመጨረሻ ጊዜ በሙላት ለእርሱ በመገዛታችን ላይ የተመሠረተ ቢሆንም፣ እርግጠኞች ለመሆን በየዕለቱ ራሳችንን እናስገዛለን።

እግዚአብሔር ሥጋችሁን ለምን ይፈልጋል? በመጀመሪያ፣ የአማኝ ሥጋ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነው፣ እግዚአብሔር ለራሱ ክብር ሊያውለው ይፈልጋል (1ኛ ቆሮ. 6:19-20፤ ፊልጵ. 1:20-21)። ጳውሎስ የአማኞች ሥጋ የእግዚአብሔር መሣሪያ እንደሆነ ጽፏል (ሮሜ 6:13)። እግዚአብሔር የሥጋችንን ብልቶች የሚፈልገው መንግሥቱን ሊገነባበትና ጠላቱን ሊዋጋበት ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ በሥጋቸው ተጠቅሞ ዓላማውን እንዲያሳካ ለእግዚአብሔር ሥጋቸውን ስለፈቀዱ ሰዎች ይናገራል።

እግዚአብሔር የሙሴን በትር ተጠቅሞ ግብፅን ድል ነሥቷል። የዳዊትን ወንጭፍ ተጠቅሞ ፍልስጥኤማውያንን ደምስሷል። የነቢያትን አንደበት ተጠቅሟል። የጳውሎስ የተሰጡ እግሮች ወንጌልን ይሰብክ ዘንድ ከአገር ወደ አገር ወስደውታል። የሐዋርያው ዮሐንስ ዓይኖች ወደፊት ሊሆን ያለውን ራእይ አይተዋል፣ ጆሮዎቹ የእግዚአብሔርን መልእክት ሰምተዋል፣ ጣቶቹ ደግሞ እኛ ዛሬ የምናነበውን መጽሐፍ ጽፈዋል።

ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱስ የሥጋ ብልቶች ለኃጢአት ሲውሉ ማንበብ ትችላላችሁ። የዳዊት ዓይኖች የባልንጀራውን ሚስት አይተዋል፤ ሕሊናው ክፉ ሴራ ጠንስሷል፤ እጆቹም የሴትየዋ ባል በግፍ ይገደል ዘንድ ትእዛዙን ፈርመዋል። መዝሙር 51ን ስታነቡ ሙሉ ማንነቱ በኃጢአት ተከልሷል፡ ዓይኖቹ (ቁ. 3)፣ አእምሮው (ቁ. 6)፣ ጆሮዎቹ (ቁ. 8)፣ ልቡ (ቁ. 10)፣ ከናፍርቶቹና አንደበቱ (ቁ. 14-15)። ከበደሌ ፈጽሞ እጠበኝ ያለው ለካ ወድዶ አይደለም? (ቁ. 2)።

*ለ) ለምን እናቀርባለን?* (6:14-23)- የራሳችንን የምናቀርብበትን ምክንያት መውደድ (ቁ. 14-15)፣ ነጻነት (ቁ. 16-20) እና ፍሬ (ቁ. 22-23)፣ የተባሉት ሦስት ቃላት ይጠቀልሉታል።

1) *መውደድ* (6:14-15)- ራሳችንን ለእርሱ የምናቀርበው ከእግዚአብሔር ጸጋ የተነሣ ነው። ጳውሎስ እንዳስረገጠው የምንድነው በሕግ አይደለም ከሕግ በታችም አንኖርም። በጸጋ መዳናችን የኃጢአትን በር አይከፍትልንም፤ ነገር ግን እንድንታዘዝ በቂ ምክንያት ሆኖናል። ሕግና ኃጢአት መንታ ሆነው ይጓዛሉ። «የሞት መውጊያ ኃጢአት ነው፤ የኃጢአትም ኃይል ሕግ ነው» (1ኛ ቆሮ. 15:56)። ከጸጋ በታች እንጂ ከሕግ በታች አለመሆናችን፣ የኃጢአትን ኃይል ያከስሰዋል።

2) *ነጻነት* (6:16-20) - የጌታና የባሪያው ምሳሌ ግልጽ ነው። ራሳችሁን ለምታስገዙበት ለዚያ ባሪያ ናችሁ። ከመዳናችሁ በፊት የኃጢአት ባሪያዎች ነበራችሁ። አሁን ግን የክርስቶስ በመሆናችሁ፣ ከአሮጌው የባርነት ኑሮ ተላቅቃችሁ የክርስቶስ

አገልጋዮች ሆናችኋል፡፡ ቁጥር 19 እንደሚናገረው ቀድሞ ለኃጢአት ባሪያዎች አድርጋችሁ ራሳችሁን እንዳቀረባችሁ ሁሉ እንዲዚሁም ለጌታ አቅርቡ ይላል፡፡ አንድ ጓደኛዬ በአንድ ወቅት እንዲህ አለኝ፣ «ልክ ኃጢአተኛ እንደነበርሁ ሁሉ ቅዱስ መሆን እፈልጋለሁ!» ከመለወጡ በፊት «የኃጢአተኞች አለቃ» ስለነበረ ምን ለማለት እንደፈለገ ገብቶኛል፡፡

ያልዳነ ሰው ከጽድቅ- ነፃ ነው (ቁ. 20)፡፡ ነገር ግን የኃጢአት እስራቱ እያደር ወደ ጠለቀ ባርነት ይከተውና ትክክለኛውን ነገር ለማድረግ እጅግ ይከብደዋል፡፡ አባካኙ ልጅ የዚህ ጥሩ ምሳሌ ነው (ሉቃስ 5:11-24)፡፡ ቤት ሳለ ነጻነቱን ፈለገና ቤቱን ጥሎ ራሱን ለማስደሰት ኮበለለ፡፡ ነገር ግን እንቢተኝነቱ ለባሰ ባርነት ዳረገው፡፡ ለክፋ ምኞት ባሪያ ነበር፡፡ በዚያው ለክፉ ሥራ ተገዛ፣ በመጨረሻም አሳማ ሲጠብቅ የተዋጣለት ባሪያ ሆነ፡፡ ራሱን ማግኘት ቢፈልግም ራሱን ግን ፈልጎ አጣው፡፡ ነጻነት ብሎ ያሰበው የባርነት ወለል ሆነ አገኘው፡፡ እውነተኛ ነጻነትን ያገኘው ወደ ቤቱ ተመልሶ ራሱን ለአባቱ ሲያቀርብ ነበር፡፡

3) ፍሬ (6:21-23)- አንድን ጌታ ካገለገላችሁ ደመወዝ መጠባበቃችሁ አይቀርም፡፡ ኃጢአት ደመወዝን ትከፍላለች- እርሱም ሞት ነው፡፡ እግዚአብሔርም ደመወዝን ይከፍላል- ይህም ቅድስናና የዘለዓለም ሕይወት ነው፡፡ ባለፈው ኑሮአችን የምናፍርበትን ፍሬ አፈራን፡፡ በክርስቶስ ባገኘነው አዲሱ ሕይወት ለሕይወታችን ደስታን የሚሰጥና እግዚአብሔርን የሚያከብር ፍሬን አፈራን፡፡ ብዙ ጊዜ ቁጥር 23ን ላልዳኑ ሰዎች እንጠቅሰዋለን፡፡ እውነት ነው ይመለከታቸዋል፡፡ ነገር ግን ይህ ቃል ለዳኑትም መልእክት አለው፡፡ (ለነገሩማ ይህ መልእክት የተጻፈው ለክርስቲያኖች ነበር፡፡) «ሞት የማይገባው ኃጢአት አለ» (1ኛ ዮሐ. 5:17)፡፡ «በእናንተ ዘንድ የደከሙና የታመሙ ብዙዎች አሉ፣ አያሌዎችም አንቀላፍተዋል» (1ኛ ቆሮ. 11:30)፡፡ ለምሳሌ፣ ሳምሶን ራሱን ለሥጋ ምኞት አሳልፎ ሰጠ፣ ውጤቱም ሞት ነበር (ይሁዳ 16)፡፡ አንድ አማኝ ሥጋውን ለጌታ ለማስገዛት እምቢ ካለ፣ ነገር ግን ለኃጢአት ካዋላቸው በአባቱ ለመቀጣት

ተቃርቧል፣ ቅጣቱም ሞት ነው። (ዕብ. 12፡5-11ን በተለይ የቁጥር 9ን ማብቂያ ይመልከቱ)።

እነዚህን ሦስት ትእዛዛት በዕለታዊ ኑሮአችን ልናስተውላቸው ይገባናል። ከክርስቶስ ጋር መሰቀላችሁንና ለኃጢአት መሞታችሁን እወቁ። ይህ በሕይወታችሁ እውን እንደሆነ ቁጠሩ። ለክብሩ እንዲጠቀምበት ሥጋችሁን ለጌታ አቅርቡ።

አሁን እነዚህን እውነቶች አውቃችኋል፣ በሕይወታችሁ እውነት እንደሆኑ ቁጠሩ፣ በመጨረሻም ራሳችሁን ለእግዚአብሔር አቅርቡ።

# ሮሜ 7፡1-25

ወንድሞች ሆይ፣ ሕግን ለሚያውቁ እናገራለሁና ሰው ባለበት ዘመን ሁሉ ሕግ እንዲገዛው አታውቁምን? ያገባች ሴት ባልዋ በሕይወት ሲኖር ከእርሱ ጋር በሕግ ታስራለችና ባልዋ ቢሞት ግን ስለ ባል ከሆነው ሕግ ተፈትታለች፡፡ ስለዚህ ባልዋ በሕይወት ሳለ ለሌላ ወንድ ብትሆን አመንዝራ ትባላለች፤ ባልዋ ቢሞት ግን ከሕጉ አርነት ወጥታለችና ለሌላ ወንድ ብትሆን አመንዝራ አይደለችም፡፡

እንዲሁ፣ ወንድሞቼ ሆይ፣ እናንተ ደግሞ በክርስቶስ ሥጋ ለሕግ ተገድላችኋል፤ ለእግዚአብሔር ፍሬ እንድናፈራ፣ እናንተ ለሌላው፣ ከሙታን ለተነሣው፣ ለእርሱ ትሆኑ ዘንድ፡፡ በሥጋ ሳለን በሕግ የሚሆን የኃጢአት መሻት ለሞት ፍሬ ሊያፈራ በብልቶቻችን ይሠራ ነበርና፤ አሁን ግን ለእርሱ ለታሰርንበት ስለ ሞትን፣ ከሕግ ተፈትተናል፣ ስለዚህም በአዲሱ በመንፈስ ኑሮ እንገዛለን እንጂ በአሮጌው በፊደል ኑሮ አይደለም፡፡

እንግዲህ ምን እንላለን? ሕግ ኃጢአት ነውን? አይደለም፤ ነገር ግን በሕግ ባይሆን ኃጢአትን ባላወቅሁም ነበር፤ ሕጉ፡- አትመኝ ባላለ ምኞትን ባላወቅሁም ነበርና፡፡ (ሮሜ 7፡1-7)

እንግዲያስ መልካሙን አደርግ ዘንድ ስወድ በእኔ ክፉ እንዲያድርብኝ ሕግን አገኛለሁ፡፡ በውስጡ ሰውነቴ በእግዚአብሔር ሕግ ደስ ይለኛልና፣ ነገር ግን በብልቶቼ ከአእምሮዬ ሕግ ጋር የሚዋጋውንና በብልቶቼ ባለ በኃጢአት ሕግ የሚማርከኝን ሌላ ሕግ አያለሁ፡፡ እኔ ምንኛ ጐስቋላ ሰው ነኝ! ለዚህ ሞት ከተሰጠ ሰውነት ማን ያድነኛል? በኢየሱስ ክርስቶስ በጌታችን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን፡፡ እንግዲያስ እኔ በአእምሮዬ ለእግዚአብሔር ሕግ፣ በሥጋዬ ግን ለኃጢአት ሕግ እገዛለሁ፡፡ (7፡21-25)

## 6

# ክርስቲያኖችና ሕግ

በሰው ባሕሪ ውስጥ ያሉ አንዳንድ ነገሮች ወደ ጽንፈኝነት የሚመሩ ናቸው:: ክርስቲያኖችም ይህን በተመለከተ ድካም ስላለባቸው ነፃ አይደሉም:: አንዳንዶች፣ «በጸጋው ስለ ዳንን፣ እንደፈለግን ለመኖር ነጻነቱ አለን» ብለው በመከራከር የጽንፈኝነትን ፈቃድ ለመጠቀም ይፈልጋሉ::

ሌሎች፣ «ነገር ግን የእግዚአብሔርን ሕግ ቸል ልንል አንችልም» ሲሉ፣ «የዳንነው በጸጋ መሆኑን እርግጠኞች ነን፣ እግዚአብሔርን ለማስደሰት ግን ከሕግ በታች መኖር አለብን::» ይላሉ:: ይህ ከልክ ያለፈ *የጽንፈኝነት* (የወንጌል አጥባቂነት) መግለጫ ነው::

ለመጀመሪያዎቹ ወገኖች ጳውሎስ በምዕራፍ 6 መልስ ሰጥቷቸዋል፤ ለሁለተኛዎቹ ደግሞ በምዕራፍ 7 መልሶላቸዋል:: በዚህ ምዕራፍ «ሕግ» የሚለው ቃል 23 ጊዜ ተጠቅሷል:: በምዕራፍ 6፣ ጳውሎስ እንዴት መጥፎ ነገሮችን ማድረግ እንደምናቆም ነግሮናል፤ በምዕራፍ 7 ደግሞ እንዴት መልካም ነገሮችን ማድረግ እንደማንችል ነግሮናል:: «ጻድቅ ሆናችሁ የተቆጠራችሁት ሕግን በመጠበቅ አይደለም፣ ሕግን በመጠበቅም መቀደስ አትችሉም» እያለ ይሟገታል::

በክርስቲያናዊ ሕይወቱ በማደግ ላይ የሚገኝ ማንኛውም ክርስቲያን በሮሜ 6 እና 7 ላይ የሚገኘውን መንፈሳዊ ልምምድ በደንብ ይገነዘባል:: እንዴት «ማወቅ፣ መቁጠርና ማቅረብ» እንደሚቻል ከተማርን በኋላ በሥጋ ባሕርያት ላይ ድል ማግኘት ስንጀምር፣ የበለጠ መንፈሳዊ እንደሆንን ይሰማናል:: መለኪያችንን ከፍ አድርገን አሳባችንን ከግብ ለማድረስ ለጊዜው እንጥራለን:: *ከዚህ በኋላ ሁሉም* ነገር *ይፈርሳል!* ልባችንን ዘልቀን ስንመረምር መኖራቸውን የማናውቃቸውን ኃጢአቶች እናገኛለን:: ቅዱስ የሆነው የእግዚአብሔር ሕግጋት በአዲስ ኃይል ጠላት ሆኖ

ይነሣብንና ደግነት ከቶ ማድረግ እንደማንችል በማሰብ እንደነቃለን! ሳይታወቀንም፣ «ወግ አጥባቂ» ሆነን ስለ ኃጢአት ሕግና ስለ ራሳችን ማንነት እንማራለን።

ለመሆኑ «ወግ አጥባቂነት» ምንድን ነው? ራሳችንን ቅዱስ በማድረግ ሕግን በመታዘዝ እግዚአብሔርን ማስደሰት እንችላለን የሚል እምነት ነው። በምንሠራውም ሥራ መንፈሳዊነታችንን የምንለካበት «የአድርግ» እና «የአታድርግ» ዝርዝር ነው። የወግ አጥባቂነት ደካማ ጎን ትኩረቱ በኃጢአቶች ላይ (በብዛት) እንጂ በኃጢአት (የችግሩ መንሥኤ በሆነው) ላይ አይደለም። ውስጣዊውን ሳያይ ውጫዊውን አይቶ ይፈርዳል። ከዚህም በላይ፣ ወግ አጥባቂ የእግዚአብሔርን ሕግ ትክክለኛ ዓላማና የእግዚአብሔርን ሕግና የጸጋ ዝምድናም አይገነዘብም።

በመጋቢነት የአገልግሎት ዘመኔ፣ በከፍተኛ የቅድስና ደረጃ ለመኖር ሲጥሩ ስሜታዊና መንፈሳዊ ቁስለት የደረሰባቸውን ብዙ ሰዎች አማክሬአለሁ። የመከራቸውን ውጤት አይቻለሁ፡- ወይ አስመሳይ ይሆናሉ፣ አለበለዚያ ደግሞ ሙሉ በሙሉ ተራቁተው በቅድስና ለመኖር ያላቸውን መሻት ይጥላሉ። ወግ አጥባቂዎች ለሌሎች ሰዎች እጅግ የማይመቹ ጨቅጫቃ፣ ፍቅር የለሽና ይቅርታን የማያደርጉ ሆነው አይቻለሁ። ጳውሎስ አንባቢዎቹን ከዚህ አስቸጋሪና አደገኛ ልምምድ ማዳን ፈልጓል። በሮሜ 7፣ ሦስት ርእሰ ጉዳዮችን ዳስሷል። እነዚህን ተረድተን በሥራ ላይ ብናውላቸው ከወግ አጥባቂነት እንድናለን።

## 1. የሕግ ሥልጣን (7:1-6)

እነዚህ ቁጥሮች ጳውሎስ በሮሜ 6:15 ላይ የጀመረው ርእሰ ጉዳይ ቀጣይ ናቸው። «ከጸጋ በታች እንጂ ከሕግ በታች ስላልሆንን ኃጢአት እንሥራን?» አንድ ክርስቲያን ራሱን ለእግዚአብሔር እንዴት እንደሚያቀርብ ለመግለጽ ጳውሎስ የጌታና የባሪያን ምሳሌ ተጠቅሟል። በዚህ ምንባብ ደግሞ አማኙ ከኢየሱስ ክርስቶስ የጌታና የባሪያን ምሳሌ ተጠቅሟል። በዚህ ምንባብ ደግሞ አማኙ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር በመተባበሩ

ምክንያት አዲስ ኅብረት እንዳለው ለማስረዳት የባልና የሚስትን ኅብረት ተጠቀመ።

ምሳሌው ቀላል ቢሆንም፣ የሚያስተላልፈው መልእክት ግን ጥልቅ ነው። ወንድና ሴት ሲጋቡ፣ ትዳራቸው የሕይወት ዘመን ነው። ጋብቻ ሥጋዊ ጥምረት ሲሆን («ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ») (ዘፍጥ. 2:24)፣ ሊፈርስ የሚችለውም በአካላዊ ምክንያት ብቻ ነው። ከእነዚህ ምክንያቶች አንዱ ሞት ነው። (ማቴ. 5:31-34 እና 19:1-12 እንደሚያመለክተው ታማኝ አለመሆን ትዳርን እንደሚያበላሽ ቢታወቅም፣ ጳውሎስ ግን ይህንን ጉዳይ አላነሣም። በዚህ ስፍራ የሚናገረው ጋብቻንና ፍቺን በተመለከተ ለማወያየት ሳይሆን፣ ጋብቻን በመጠቀም አንድን እውነት ለማብራራት ፈልጎ ነው።)

በሕይወት እስካሉ ድረስ፣ ባልና ሚስት ለጋብቻ ሕግ ተገዥ ናቸው። ሴቷ ጥላ ሌላ ሰው ብታገባ፣ አመንዝራለች። ባሏ ቢሞት ግን፣ በሕይወት የለምና ሌላ ልታገባ ትችላለች። የጋብቻውን ጥምረት ያፈረሰውና ነጻነትን የሰጣት ሞት ነው።

ጳውሎስ ከቁጥር 4-6 ባለው ክፍል ሙግቱን ያጠናክራል። አማኝ ከሕግ ጋር ያለውን ኅብረት በተመለከተ ሁለት አስደናቂ እውነታዎችን ያብራራል።

*ሀ) ለሕግ ሞተናል* (7:4) - ጳውሎስ ምሳሌዎችን ያምታታው ይመስላል፣ ነገር ግን እንደዚህ አይደለም። ከመዳናችን በፊት («በሥጋ ሳለን») (ቁ.5)፣ እግዚአብሔር ሕግ ሥልጣን ሥር ነበርን። በሕግም ተፈርዶብን ነበር። በክርስቶስ ባመንንና ከእርሱ ጋር በተባበርን ጊዜ፣ ለሥጋ እንደሞትነው (6:1-10) *ለሕግም ሞተናል*። ሕግ አይደለም የሚሞተው፣ እኛ ነን።

ነገር ግን ጳውሎስ በጋብቻ ምሳሌ እንደገለጠው ከሆነ፣ የሞተው *ባልየው* ሲሆን ዳግመኛ ያገባችዋ ሚስት ናት። እኔና እናንተ በሚስቲቱ ብንመሰልና፣ ሕግ ደግሞ በባል ቢመሰል ኖሮ፣ ምሳሌው ከእኛ ጋር እንደሚገባው አይዛመድም ነበር። በምሳሌው ላይ ሴቷ ብትሞት ኖሮ፣ ዳግመኛ ለማግባት እንደገና ሕያው

መሆን አለባት:: ነገር ግን ጳውሎስ ማስተማር የፈለገው ይህንኑ ነው! በክርስቶስ ስናምን፣ ለሕግ ሞተናል፤ ሆኖም በክርስቶስ፣ ከሙታን ተነሥተን አዲስ ሕይወት ለመኖር ከክርስቶስ ጋር «ተጣምረናል»!

ዛሬም የእግዚአብሔር ሕግ ሰዎችን ስለሚገዛ፣ ሕግ አልሞተም:: እኛ ለሕግ ስለሞትን፣ በእኛ ላይ ሥልጣን የለውም:: ሆኖም እኛ «ሕግ የሌለን» ስላልሆንን፣ ከክርስቶስ ጋር በመተባበራችን በሕይወቱ እንካፈላለን፣ «በአዲስ ሕይወትም» እንመላለሳለን:: ሮሜ 8:4 ሙግቱን መጨረሻ ደረጃ ላይ ያደርሰዋል:- «እንደ መንፈስ ፈቃድ እንጂ እንደ ሥጋ ፈቃድ በማንመላለስ በእኛ የሕግ ትእዛዝ ይፈጸም ዘንድ ኃጢአትን በሥጋ ኰነነ::» በቀደመው የኃጢአት ኑሮአችን፣ «የሞትን ፍሬ» አፈራን፣ በአዲሱ የጸጋ ሕይወታችን ግን «ለእግዚአብሔር ፍሬን እናፈራለን::» «ለሕግ መሞት» ማለት ሕግን የሚጥስ ሕይወት እንመራለን ማለት አይደለም:: የመኖር መነሣሣትም ሆነ ግብረገባዊ ኃይል የሚመነጨው ከሕግ ሳይሆን፣ በእግዚአብሔር ጸጋ ከክርስቶስ ጋር በመተባበራችን ነው::

ለ) *ከሕግ አርነት ወጥተናል* (7:6) - ሕግ በሞተ ሰው ላይ ሥልጣኑን መጠቀም አይችልም የሚለው መደምደሚያ የአሳብ ፍሰትን የተከተለ መቋጫ ነው:: ሞት ማለት አርነት ነው (ሮሜ 6:9-10ን ተመልከቱ):: ነፃ የወጣነው እንድናገለግል ነው:: የክርስትና ሕይወት ነፃ ወጥቶ ዐመፀኛ መሆን ማለት አይደለም:: ለሕግ የሞትነው «ከክርስቶስ ጋር እንድንጣመር ነው::» ከሕግ አርነት የወጣነው ክርስቶስን ለማገልገል ነው:: ይህ እውነት ጳውሎስ አስተምሯል ተብሎ የተከሰሰበትን ሕገወጥነት መሠረተ ቢስ ያደርገዋል::

ክርስቲያናዊ አገልግሎት ድሮ ከኖርንበት የኃጢአት ኑሮ የሚለየው በምንድን ነው? አንደኛው፣ ጌታን ለመታዘዝና ለማገልገል ስንተጋ መንፈስ ቅዱስ ያበረታናል:: ሕግ፣ የማድረግን ጉልበት አልሰጠንም:: የእግዚአብሔር ሕግ በምስክር

ጽላቶች ላይ ተጽፎ ለሰዎች ይነበብ ነበር። በጸጋው ግን የእግዚአብሔር ቃል በልባችን ተጽፏል (2ኛ ቆሮ. 3:1-3)። «በአዲስ ሕይወት እንመላለሳለን» (ሮሜ 6:4)፤ «በአዲስ መንፈስ» እናገለግላለን። ስለሆነም፤ አማኝ ከሕግ ሥልጣን ሥር አይደለም።

## 2. የሕግ አገልግሎት (7:7-13)

የጳውሎስ ተቃዋሚዎች ዝግጁ ነበሩ! «የማያስፈልገን ከሆነ ሕግ ምን ጥቅም አለው? ለመሆኑ ትምህርትህ ሕግን እንደ ኃጢአት የቆጠረው ለምንድን ነው?» ይህንን ተቃውሞ ሲመልስ ጳውሎስ ዛሬም እንኳ ያለውን የሕግን አገልግሎት አብራርቷል።

*ሀ) ሕግ ኃጢአትን ይገልጣል* (7:7) - «ኃጢአትም በሕግ ይታወቃልና» (ሮሜ 3:20)። «ሕግ በሌለበት መተላለፍ የለም» (ሮሜ 4:15)። ሕግ እንደ መስታወት ውስጣዊ ሰውነታችንን ገልጦ ምን ያህል እንደቆሸሽን የሚያሳየን ነው (ያዕ. 1:22-25)። ማስተዋል ያለብን ጳውሎስ እንደ ምሳሌ ያቀረበው ግድያን፣ ስርቆትን ወይም ዝሙትን ሳይሆን፣ *መጎምዠትን* ነው። ይህ የዐሥርቱ ትእዛዛት መጨረሻ ሲሆን፣ ከዘጠኙ ሕጎች የሚለየው በውስጣችን የምንፈጽመው በመሆኑ ነው። መጎምዠት ሌሎችን ሕግጋት እንድንጥስ ይነዳናል! በውስጣችን የሚፈጸም ኃጢአት በመሆኑ ብዙ ሰዎች አያስተውሉትም፤ ነገር ግን የእግዚአብሔር ሕግ ያጋልጠዋል።

ማርቆስ 10:17-27 ላይ የተጠቀሰው የሀብታም ሰው ታሪክ ሕግ የሰውን ኃጢአት እንደሚገልጥና አዳኝም እንደሚያስፈልጋቸው የሚያሳይ ጥሩ ምሳሌ ነው። ይህ ወጣት ከውጭ ሲታይ በባሕርይው ጥሩ ይመስላል፤ ነገር ግን በውስጡ ያለውን ኃጢአት ተጋፍጦት አያውቅም። ኢየሱስ ለዚህ ሰው ስለ ሕግ የነገረው እንዲድንበት ሳይሆን፤ ወጣቱ የራሱን ኃጢአተኝነት ስላላስተዋለ ነው። እርግጥ ነው፤ ዝሙትን አላደረገም፤ ማንንም አልዘረፈም፤ በሐሰት አልመሰከረም፤ ወላጆቹንም አላሳፈረም፤ ነገር ግን ጎምዥቶ ያውቅ ይሆን?

ኢየሱስ ወጣቱ ያለውን ሸጦ ለድሆች እንዲያካፍል ሲነግረው፣ ሰውየው በኀዘን ጥሎት ሄደ:: «አትመኝ» የሚለው ትእዛዝ ምን ዓይነት ኃጢአተኛ እንደነበረ ገለጠለት! በኃጢአቱ ከመጸጸት ይልቅ፣ ሳይለወጥ ክርስቶስን ጥሎት ሸሸ::

ለ) *ሕግ ኃጢአትን ይቀሰቅሳል* (7:8-9)- ጳውሎስ የተሰጠ ፈሪሳዊ ስለነበርና ከመለወጡ በፊት ሕግን ሲፈጽም ይተጋ ስለነበር፣ እነዚህን ቁጥሮች ለመረዳት ብዙ አንቸገርም:: (ጳውሎስ ከመለወጡ በፊት ስለነበረው ሕይወት ፊልጵ. 3:1-11 እና ገላ. 1ን አንብብ):: «የኃጢአት ኃይል ሕግ» መሆኑን በልባችሁ መያዝ አለባችሁ (1ኛ ቆሮ. 15:56):: ኃጢአታዊ ባሕርይ ስላለን፣ ማግኔት (መግነጢስ) ብረትን እንደሚስብ ሁሉ ሕግም የኃጢአት ባሕርያችንን ይቀሰቅሳል::

ሰው በባሕርይው በተሰጠው ሕግ ላይ ማመፅን ይወዳል:: አንድ ጊዜ በቺካጎ ከተማ ሲንከን መናፈሻ ቆሜ ሳለሁ ቀለም የተቀቡ አግዳሚ ወንበሮች ላይ፣ «እባካችሁ አትንኩ» የሚል ጽሑፍ ተጽፎ ነበር:: ነገር ግን ብዙ ሰዎች ሆን ብለው ጠጋ በማለት ቀለሙን ሲነኩት ተመለከትሁ! ለምን? ጽሑፉ (ምልክቱ) እንዳይነኩ ይነግራቸው የለም! አንድ ልጅ ወደ ውኃ እንዳይጠጋ ብትነግሩት፣ ቶሎ የሚያደርገው ያንኑ ነው:: ለምን? «ስለ ሥጋ ማሰብ በእግዚአብሔር ዘንድ ጥል ነውና ለእግዚአብሔር ሕግ አይገዛምና፣ መገዛትም ተስኖታል» (ሮሜ 8:7)::

በራሳቸው ሕግና ደንብ ለመኖር የሚተጉ ወግ አጥባቂ አማኞች የበለጠ ችግርና ኃጢአት እንደሚያመጣባቸው ይገነዘባሉ:: በገላትያ የነበሩት አማኞች አጉል ወግ አጥባቂ ነበሩና፣ እጅግ ብዙ ችግር ገጥሟቸው ነበር:: «ነገር ግን እርስ በርሳችሁ ብትነካከሱና ብትበላሉ እርስ በርሳችሁ እንዳትጠፋፉ ተጠንቀቁ::» (ገላ. 5:15):: ወግ አጥባቂነታቸው ኃጢአተኝነታቸውን አበዛው እንጂ የበለጠ መንፈሳዊ አላደረጋቸውም! ለምን? ሕግ በባሕርይው ለኃጢአት ይገፋፋልና ነው::

ሐ) *ፊደል ይገድላል* (7:10-11)- «ሕያው ሊያደርግ የሚቻለው ሕግ ተሰጥቶ ቢሆንስ በእውነት ጽድቅ ከሕግ በሆነ ነበር» (ገላ. 3:21)። ሕግ ግን ሕይወትን ሊሰጥ አይችልም፡- ኃጢአተኛው ግን በደለኛ እንደሆነና በኩነኔ ውስጥ እንዳለ ያሳየዋል። ይህም ወግ አጥባቂ ክርስቲያኖችና ቤተ ክርስቲያናት የማያድጉትና መንፈሳዊ ፍሬ የማያፈሩት ለዚህ እንደሆነ ያስረዳል። የሚኖሩት በሕግ ነው፣ ፊደል ደግሞ ይገድላል። በራሷ «የመንፈሳዊነት መለኪያ» የምትታበይና እነዚህን መስፈርቶች በራሷ ኃይል ለማሟላት የምትጥር ቤተ ክርስቲያን ሙት ናት። ብዙ ጊዜ የዚህች ዓይነት ቤተ ክርስቲያን አባላት እርስ በርሳቸው እየተነካካሱ ውጤቱ ጠብ ይሆናል። በመጨረሻም ቤተ ክርስቲያኗ ተከፋፍላ አባሎቿ ቁጡና መራራ ይሆናሉ።

አዲስ ክርስቲያን ሲያድግ፣ በክርስትና ሕይወት ያሉ አስተምህሮችን ያገኛል። መጻሕፍትን በማንበብ፣ ሥልጠና በመውሰድ፣ ስብከቶችን በማዳመጥ በቂ መረጃ ይኖረዋል። ካልተጠነቀቀ መሪውን ተከትሎ እርሱ የሚያስተምረውን እንደ ሕግ ይቆጥራል። የዚህ ዓይነቱ ልምምድ የወግ አጥባቂነት አንዱ ገጽታ ሲሆን፣ መንፈሳዊ ዕድገትን ይገድላል። ማንም የሰው አስተማሪ የክርስቶስን ቦታ ሊተካ አይችልም። የቱም መጽሐፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ዕኩያ አይሆንም። ሰዎች መረጃ ሊሰጡን ይችላሉ፣ መንፈሳዊ እውነታን እንድንረዳ የሚያደርገን ግን መንፈስ ቅዱስ ነው። መንፈስ ቅዱስ ልቦናችንን ያበራልንና ያስችለናል፤ ሰዎች ግን ይህን ሊያደርጉ አይችሉም።

መ) *ሕግ የኃጢአትን ክፋት ይገልጣል* (7:12-13)- ያልዳኑ ሰዎች ኃጢአት መኖሩን ቢያውቁም፣ የኃጢአትን መጥፎነት ግን አይረዱም። ብዙ ክርስቲያኖችም የኃጢአትን እውነተኛ ባሕርይ አይገነዘቡም። ኃጢአታችንን «ስሕተት» ወይም «ድካም» ብለን እንሸፋፍናለን፤ እግዚአብሔር ግን ኃጢአት ክፋት ወይም ወንጀል መሆኑን እንድናይ በማስቻል ኃጢአታችንን ይኮንናል። የኃጢአትን ክፋት እስክንረዳ ድረስ፣ ኃጢአትን በመቃወም የድል ኑሮ መኖር አንችልም።

እዚህ ላይ የምናየው የጳውሎስ ሙግት ድንቅ ነው:- 1ኛ) ሕግ ክፉ አይደለም- «ቅድስት፣ ጻድቅትም በጎም ናት»፤ 2ኛ) ሕግ ኃጢአትን ይገልጣል፣ ለኃጢአት የሚገድለን ኃጢአትን በመጠቀም ነው፣ ሕግ እነዚህ ውጤቶች ካሉት፣ መሃል ላይ የተበላሸ ነገር መኖር አለበት፤ 3ኛ) መደምደሚያ:- ክፉው ኃጢአት በጎ የሆነውን ሕግ በመጠቀም እንዲህ ዓይነት አሰቃቂ ውጤት ማምጣቱን ተመልከቱ:: ኃጢአት በእርግጥ «እጅግ በጣም ሲበዛ ክፉ ነው»:: ችግሩ ያለው ሕጉ ጋ ሳይሆን፣ ከራሴ ክፉ ባሕርይ ነው:: ይህም በዚህ ምዕራፍ ለምናየው ሦስተኛ ርእሰ ጉዳይ መንገድ ያዘጋጃል::

## 3. የሕግ አቅም ማጣት (7:14-25)

ጳውሎስ ሕግ ሊሠራ የሚገባው ምን እንደሆነ ካብራራ በኋላ፣ ሕግ ሊሠራ የማይችለውን ደግሞ ይገልጣል::

*ሀ) ሕጉ ሊለውጣችሁ አይችልም* (7:14)- የሕግ ባሕርይ በአራት ቃላት ተገልጧል:- ቅድስት፣ ጻድቅት፣ በጎና መንፈሳዊ:: ሕግ ቅድስትና ጻድቅት መሆኑን ማንም አይክድም፣ ምክንያቱም የሕጉ ምንጭ ቅዱስና፣ በሚናገረውም ሆነ በሚያደርገው ሁሉ በፍጹም ጻድቅ የሆነው አምላክ ነው:: ሕግ በጎ ነው:: የእግዚአብሔርን ቅድስና ገልጦ፣ አዳኝ እንደሚያስፈልገን ያሳየናል::

ሕግ «መንፈሳዊ» ነው ሲል ምን ማለቱ ነው? ትርጉሙ ሕግ መንፈሳዊ የሆነውን የሰው ውስጣዊ ማንነት የሚመረምር ሲሆን፣ ውጫዊ የሆኑ እርምጃዎችንም ይነካል:: በዘጸአት ለመጀመሪያ ጊዜ ሕግ ሲሰጥ፣ ትኩረቱ በውጫዊ ሥርዓት ላይ ነበር:: ነገር ግን ሙሴ በዘዳግም መጽሐፍ ሕጉን በድጋሚ ሲያስተምረው፣ ሕግ ያለውን ማእከላዊነትና ከሰው ልብ ጋር ስላለው ኅብረት ትኩረት ሰጥቶታል:: ይህም መንፈሳዊነት በዘዳግም 10:12-13 ሰፍሯል:: በዘዳግሞ «ፍቅር» የሚለው ቃል መደጋገም፣ የሕግ ጥልቅ ትርጓሜ ከውስጣዊ ሰውነት ጋር

የተዛመደ መሆኑን ያሳያል (ዘዳግ. 4:37፤ 6:4-6፤ 10:12፤ 11:1፤ 30 :6፣16፣20)::

ፍጥረታችን ሥጋዊ ነው፤ የሕግ ባሕርይ ግን መንፈሳዊ ነው:: ይህም የበፊቱ ባሕርያችን እንዲህ ዓይነት ምላሽ ለምን ለሕግ እንደሚሰጥ ያብራራል:: ከላይ እንደተገለጸው፣ «አሮጌው ሰዋችን ሕግን አያውቅም፣ አዲሱ ሰዋችን ደግሞ ሕግ አያሻውም::» ሕግ አሮጌውን ሰዋችንን ማደስ አይችልም፤ አሮጌው ሰዋችን ምን ያህል ክፉ መሆኑን ግን ያሳያል:: ከሕግ በታች መኖር የሚሻ አማኝ አሮጌውን ሰው ይቀሰቅሰዋል እንጂ አያጠፋውም::

ሐ) *ሕግ በጎ ነገር ለማድረግ አያስችልም* (7:15-21) - ጳውሎስ በዚህ ምንባብ ኃጢአት በእኛ ውስጥ እንደሚኖር ሦስት ጊዜ ጠቅሷል (ቁ. 14፣18፣20):: ይህንን ሲል ስለ አሮጌው ሰዋችን መናገሩ ነበር:: መንፈስ ቅዱስ በእኛ መኖሩ እውነት ነው:: በምዕራፍ 8 ጳውሎስ ሕግ ሊያደርግ የማይችለውን በመሥራት የእግዚአብሔር መንፈስ የድል ኑሮ እንድንኖር እንዴት እንደሚያስችለን ገልጧል::

በዚህ ክፍል የተገለጡት ተውላጠ ስሞች ጸሐፊው ራሱ ችግር እንደገጠመው ያሳያሉ:: ይህ ማለት ክርስቲያኑ ሁለት የተከፋፈለ ሰውነት አለው ማለት አይደለም፣ ምክንያቱም የለውምና:: ደኅንነት ሰውን ሙሉ ያደርገዋል:: ነገር ግን የአማኙ አእምሮ፣ ፈቃድና ሥጋ በአሮጌው ሰው ወይም በአዲሱ ሰው ባሕርይ ማለትም በሥጋ ወይም በመንፈስ ቁጥጥር ሥር ሊውል እንደሚችል ያመለክታል:: ዐረፍተ ነገሩ እንደሚያመለክተው አማኝ ሁለት ዓይነት ችግሮች አሉት:- 1) የሚወደውን በጎ ነገር አያደርግም፣ 2) የማይወደውን ክፉ ነገር ያደርጋል::

እንዲህ ማለት ጳውሎስ ራሱ የእግዚአብሔርን ሕግ መተላለፉን ማቆም አቅቶት ቀጣፊ፣ ሌባና ነፍሰ ገዳይ ሆኗል ማለት ነውን? በፍጹም አልሆነም! ጳውሎስ የሚናገረው የእግዚአብሔርን ሕግ መጠበቅ አለመቻሉንና ለመፈጸም ጥረት

ሲያደርግ ደግሞ በውስጡ አሁንም ክፋት መኖሩን ለመግለጽ ነው:: ምንም ይሥራ ምን፣ ሥራው አሁንም ኃጢአት ነበረበት:: የቻለውን ያህል እንኳን አድርጎ ሳለ፣ «እንዳላተረፈ አገልጋይ» (ሉቃስ 17-10) መሆኑን መቀበል ነበረበት:: «እንግዲያስ መልካሙን አደርግ ዘንድ ስወድ፣ በእኔ ክፉ እንዲያድርብኝ ሕግን አገኛለሁ» (ሮሜ 7:21):: ይሄ በምዕራፍ 6 ካየነው የተለየ ችግር ነው:: እዚያ ላይ የተጠቀሰው ችግር «መጥፎ ነገር ማድረግን እንዴት ማቆም እችላለሁ?» ሲሆን፣ እዚህ ጋ ያለው ችግር ደግሞ «እንዴት በጎ ነገርን ማድረግ እችላለሁ?» የሚለው ነው::

ሕግ አጥባቂው፣ «ሕግን ጠብቁ ከዚያም በኋላ በጎ ነገር ማድረግና ጥሩ ሕይወት መኖር ትችላላችሁ» ይላል:: ነገር ግን ሕግ ማድረግ የሚችለው ኃጢአትን መግለጥ፣ ለኃጢአት መገፋፋትና የኃጢአትን ክፉነት ማሳየት ነው! በውስጤ በሕግ ላይ የሚነሣ ባሕርይ ስላለ፣ ሕግን ለመታዘዝ አልችልም:: በጎ የሠራሁ ቢመስለኝም እንኳ፣ ክፋት በውስጤ እንዳለ አውቃለሁ:: ሕግ ጥሩ ነው፣ እኔ ግን በፍጥረቴ መጥፎ ነኝ! ስለሆነም፣ ወግ አጥባቂው ተሳስቷል:- ሕግ በጎ ነገር እንሠራ ዘንድ አያስችለንም::

ሐ) *ሕግ ነፃ ሊያወጣችሁ አይችልም* (7:21-24) - አማኝ ወደ ኋላ ጎትቶ በቀንበሩ ውስጥ ሊያስቀረው የሚፈልግ አሮጌ ማንነት አለው:: ክርስቲያኑም ለራሱ፣ «ካለፈው ኃጢአቴ ነፃ እወጣለሁ!» ይላል:: «ከአሁን በኋላ ይህንን ደግሜ ላደርግ ወስኛለሁ» ይላል:: ከዚያስ ምን ይሆናል? የፈቃዱን ኃይልና ያለውን ጉልበት ሁሉ ይጠቀምና ለጊዜው ይሳካለታል፤ ነገር ግን ባልጠበቀው ሁኔታ ዳግመኛ ይወድቃል:: ለምን? ከአሮጌው ባሕርይው መገላገል የፈለገው በሕግ ሲሆን፣ ሕግ ደግሞ ከአሮጌው ማንነታችን አርነት ሊያወጣን አይችልም:: ከሕግ በታች ለመሆን ስትጥሩ፣ አሮጌው ሰዋችሁን እያበረታችሁት ነው፤ ምክንያቱም «የኃጢአት ኃይል ሕግ ነውና» (1ኛ ቆሮ. 15:56):: እንድንረታ ኃይል የሚሰጠን ነገር በመሆን ፋንታ ሕግ እንደ መግነጢስ ወደ ተለያዩ ኃጢአቶችና ብክለቶች ይስበናል:: ውስጣዊ ማንነታችን

በእግዚአብሔር ሕግ ቢደሰትም [መዝ. (119):35]፣ አሮጌው ማንነታችን ግን ሕግን በማፍረስ ይረካል:: ከሕግ በታች ያለ አማኝ መድከሙ፣ ተስፋ መቁረጡና በመጨረሻም መረታቱ አያስደንቅም! ምርኮኛ ሆኖአልና «ጎስቋላ» ነው (የግሪኩ ቃል በጦርነት ተረትቶ የደከመን ሰው ያመለክታል):: ጥሩ ሕይወት ለመኖር ያለህን ጉልበትህን ሁሉ ጨርሰህ፣ የኋላ ኋላ የሠራኸው ሁሉ ብቃት እንደሌለው ከማወቅ የከፋ «ጉስቁልና» ምን አለ!

ነፃ መውጣት ይቻል ይሆን? በሚገባ! «ነፃ የሚያወጣኝ ኢየሱስ ክርስቶስ ስላለኝ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ!» አማኙ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር በመተባበሩ፣ ለሕግ ሞቷልና በሕግ ሥልጣን ሥር አይኖርም:: ነር ግን የመንፈስ ቅዱስን ኃይል በመቀበል ለእግዚአብሔር ሕያው ሆኖ ይኖራል::የዚህ ድል ማብራሪያ በምዕራፍ 8 ተሰጥቷል::

የምዕራፉ የመጨረሻ ዐረፍተ ነገር፣ አማኝ የተከፋፈለ ሁለት ሕይወት እንዳለው፣ ማለትም በሥጋው ኃጢአት እየሠራ በአእምሮው ደግሞ እግዚአብሔርን እንደሚያገለግል አያመለክትም:: ይህ ማለት እኮ *ሥጋው በአንድ ጊዜ* በሁለት መንገድ እየተሠራበት ነው ማለት ነው:: ይህ ደግሞ ፈጽሞ አይቻልም:: አማኝ በሥጋውና በመንፈሱ መካከል ትግል መኖሩን ያውቃል (ገላ. 5:16-18)፣ ነገር ግን ከሁለት አንዱ ሌላውን እንደተቆጣጠረ ያውቃል::

ጳውሎስ በ«አእምሮዬ» ሲል «የሥጋ» ተቃራኒ የሆነውን (ቁ. 18) «ውስጣዊ ሰውነቱን» (ቁ. 22) ማለቱ ነው:: ይህንን አሳብ በሮሜ 8:5-8 አስፍቶ አቅርቦታል:: አሮጌው ሰዋችን አንድም በጎ ነገር ማድረግ አይችልም:: መጽሐፍ ቅዱስ ስለ አሮጌው ሰው የሚናገረው ሁሉ አሉታዊ ነው:- «በጎ ነገር እንዳይኖር» (7:18) ይላልና:: «ሥጋ ምንም አይጠቅምም» (ዮሐ. 6:63)፤ «በሥጋም የማንታመን» (ፊልጵ. 3:3) ይላልና:: በሥጋ ብርታት የምንታመን ከሆነ፣ እግዚአብሔርን ማገልገልም ሆነ ማስደሰት፣ እንዲሁም በጎ ነገር ማድረግ አንችልም:: ነገር ግን ራሳችንን

ለመንፈስ ቅዱስ ብናቀርብ፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመሙላት የሚያስፈልገንን ኃይል እናገኛለን። ሥጋ ከእግዚአብሔር ጋር በውጊያ ላይ ስለሆነ፣ የእግዚአብሔርን ሕግ ማገልገል አይችልም። መንፈስ ግን ለእግዚአብሔር ሕግ መታዘዝ ይችላል! ስለዚህ፣ በጎ ለማድረግ ምሥጢሩ ራስን ለመንፈስ ቅዱስ ማቅረብ ነው።

ጳውሎስ «ለእግዚአብሔር ፍሬ እንድናፈራ» (ቁ. 4) ሲል ፍንጭ ሰጥቶናል። ለአሮጌው ማንነታችን ሙት እንደሆንነው ለሕግም እንደዚሁ ሙታን ነን። ነገር ግን ከክርስቶስ ጋር ተባብረን በክርስቶስ ሕያዋን ስለሆንን፣ ለእግዚአብሔር ፍሬን እናፈራለን። እግዚአብሔርን በሚገባ እንድናገለግል ያስቻለን ከክርስቶስ ጋር መተባበራችን ነው። «ስለ በጎ ፈቃዱ መፈለግንም ማድረግንም በእናንተ የሚሠራ እግዚአብሔር ነው።» (ፊልጵ. 2:13)። ይህም በሮሜ 7:18 ላይ የነበረውን የጳውሎስን ችግር ይፈታዋል። «በጎ ፈቃድ አለኝና መልካሙን ግን ማድረግ የለኝም።»

አሮጌው ሰዋችን ሕግን አያውቅም፣ አዲሱ ማንነታችን ደግሞ ሕግ አያስፈልገውም። ወግ አጥባቂነት አዲሱን ባሕርይ እያሳዘነ አሮጌውን ማንነት ስለሚቀሰቅስ አማኙን ጎስቋላ ያደርገዋል! ወግ አጥባቂ የኋላ ኋላ ውጫዊ ድርጊቱ ተቀባይነት ያለው፣ ውስጣዊ አስተሳሰቡ ግን ፍጹም የረከሰ ፈሪሳዊ ይሆናል። ኢየሱስ ፈሪሳውያኑን «በውጭ አምረው የሚታዩ በውስጥ ግን የሙታን አጥንት ርኩሰትም ሁሉ የተሞሉ በኖራ የተለሰኑ መቃብሮች» ማለቱ አያስደንቅም (ማቴ. 23:27)። ለመሆኑ ምን ያህል ጎስቋላ እንደ ሆናችሁ ትገነዘባላችሁ?

ወደፊት የሚመጣው የተሻለ ይሆናል! የሚቀጥለው ምዕራፍ ክፉን ለማሸነፍ መልካሙን ለማፍራት መንፈስ ቅዱስን የሚሠራውን ሥራ ይገልጣል።

# ሮሜ 8:1-39

እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኵነኔ የለባቸውም። በክርስቶስ ኢየሱስ ያለው የሕይወት መንፈስ ሕግ ከኃጢአትና ከሞት ሕግ አርነት አውጥቶኛልና። ከሥጋ የተነሣ ስለደከመ ለሕግ ያልተቻለውን፣ እግዚአብሔር የገዛ ልጁን በኃጢአተኛ ሥጋ ምሳሌ በኃጢአትም ምክንያት ልኮ አድርጎአልና፤ እንደ መንፈስ ፈቃድ እንጂ እንደ ሥጋ ፈቃድ በማንመላለስ በእኛ የሕግ ትእዛዝ ይፈጸም ዘንድ ኃጢአትን በሥጋ ኰነነ። (ሮሜ 8:1-4)

ነገር ግን ኢየሱስን ከሙታን ያስነሣው የእርሱ መንፈስ በእናንተ ዘንድ ቢኖር፣ ክርስቶስ ኢየሱስን ከሙታን ያስነሣው እርሱ በእናንተ በሚኖረው በመንፈሱ፣ ለሚሞተው ሰውነታችሁ ደግሞ ሕይወትን ይሰጠዋል።

እንግዲህ፣ ወንድሞች ሆይ፣ ዕዳ አለብን፣ እንደ ሥጋ ፈቀድ ግን እንኖር ዘንድ ለሥጋ አይደለም። እንደ ሥጋ ፈቃድ ብትኖሩ ትሞቱ ዘንድ አላችሁና፤ በመንፈስ ግን የሰውነትን ሥራ ብትገድሉ በሕይወት ትኖራላችሁ። በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ ሁሉ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና። አባ አባት ብለን የምንጮኽበትን የልጅነትን መንፈስ ተቀበላችሁ እንጂ እንደ ገና ለፍርሃት የባርነትን መንፈስ አልተቀበላችሁምና። የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ያ መንፈስ ራሱ ከመንፈሳችን ጋር ይመሰክራል። ልጆች ከሆንን ወራሾች ደግሞ ነን፤ ማለት የእግዚአብሔር ወራሾች ነን፣ አብረንም ደግሞ እንድንከበር አብረን መከራ ብንቀበል ከክርስቶስ ጋር አብረን ወራሾች ነን። (ሮሜ 8:11-17)

ሞት ቢሆን፣ ሕይወትም ቢሆን፣ መላእክትም ቢሆኑ፣ ግዛትም ቢሆን፣ ያለውም ቢሆን፣ የሚመጣውም ቢሆን፣ ኃይላትም ቢሆኑ፣ ከፍታም ቢሆን፣ ዝቅታም ቢሆን፣ ልዩ ፍጥረትም ቢሆን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን ካለ ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን እንዳይችል ተረድቼአለሁ። (ሮሜ 8:38-39)

# 7

# ነጻነትና ፍጻሜው

ጥር 6 ቀን 1941 (እ.ኤ.አ) ፕሬዚደንት ፍራንክሊን ዴላኖ ሩዝቬልት በአውሮፓ የነበረውን ጦርነት አስመልክተው ለጉባኤው ንግግር አደረጉ። ከተናገሩት አብዛኛው ዛሬ ተረስቷል። ነገር ግን በንግግራቸው መደምደሚያ ላይ «ዓለም በአራቱ አስፈላጊ ነጻነቶች ላይ ተመሥርታ ማየት» እንደሚናፍቁ ተናገሩ። አራቱ ነጻነቶቹም:- የመናገር ነጻነት፣ የአምልኮ ነጻነት፣ ከአጉል መሻት ነጻነትና ከፍርሃት ነጻነት ናቸው። እነዚህ ነጻነቶች በዓለም ዙሪያ ሙላታቸውን ባያገኙም ቃሎቹን አሁንም እናስታውሳቸዋለን።

ሮሜ 8 የክርስቲያን «የነጻነት ዐዋጅ» ነው። ጳውሎስ በዚህ ስፍራ አራቱን ነጻነቶች ከክርስቶስ ጋር በመተባበራችን እንዳገኘ ናቸው አስፍሯል። ይህንን ምዕራፍ ስናነብ የምንገነዘበው፣ 19 ጊዜ ለተጠቀሰው ለመንፈስ ቅዱስ ትኩረት እንደተሰጠ ነው። «የጌታም መንፈስ ባለበት በዚያ አርነት አለ» (2ኛ ቆሮ. 3:17)።

## 1. ከፍርድ ነፃ ነን - ኩነኔ የለብንም (8:1-4)

ሮሜ 3:20 ስለ ኩነኔ መንሥኤ ለመናገር «ይህም» (አ.መ.ት) የሚለውን ቃል ሲጠቀም፣ ሮሜ 8:1 ደግሞ ከኩነኔ ነፃ የመሆናችንን ነገር ለመግለጽ «ስለዚህ» የሚለውን ቃል ይጠቀማል (አ.መ.ት)። ይህም የሚገርም እውነት ሲሆን፣ የተዋጣለት የሙግት መደምደሚያ ነው። የዚህ ድንቅ ዋስትና መሠረቱ «በኢየሱስ ክርስቶስ» የሚለው ሐረግ ነው። በአዳም ምክንያት ኩነኔ ነበረብን። በክርስቶስ ግን ከኩነኔ ነፃ ነን።

ይህ ክፍል «ስሕተት የለባቸውም» ወይም «ድክመት የለባቸውም» ወይም «ኃጢአት የለባቸውም» አይልም። ክርስቲያኖች ይሳሳታሉ፣ ይደክማሉ፣ ኃጢአትም ያደርጋሉ። አብርሃም ስለሚስቱ ዋሽቷል፣ ዳዊት አመንዝሯል፣ ጴጥሮስም

በሰይፍ ሰው ለመግደል ሞክሯል:: ስለ ኃጢአታቸው ቢቀጡም፣ ኩነኔ ግን አልነበረባቸውም::

ሕግ ይኮንናል:: አማኝ ደግሞ ከሕግ ጋር አዲስ ግንኙነት ስላለው ሊኮነን አይችልም:: ጳውሎስ ስለ አማኝና ሕግ ሦስት ነገሮችን የተናገረ ሲሆን፣ ሁሉም ሲደመሩ ኩነኔ የለባቸውም ይሆናሉ::

ሀ) *ሕግ የራሱ ሊያደርጋችሁ አይችልም* (8:2)- ከኃጢአትና ከሞት ሕግ አርነት ወጥታችኋል:: አሁን የመንፈስ ሕይወት አላችሁ:: በክርስቶስ ወደ አዲስ ክበብ ገብታችኋል (ተሻግራችኋል) «የኃጢአትና የሞት ሕግን» ጳውሎስ በሮሜ 7:7-25 ገልጾታል:: ሕግ ከአሁን በኋላ ሊዳኛችሁ አይችልም:: ለሕግ ስለሞታችሁ (ሮሜ 7:4)፣ ከሕግ ነፃ ወጥታችኋል (ሮሜ 8:2)::

ለ) *ሕጉ ሊኮንናችሁ አይችልም* (8:3) - ለምን? ምክንያቱም እናንተ ልትቀበሉት የነበረውን ፍርድ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሆኖ ተቀብሏል:: ሕግ ይኮንናል እንጂ ማዳን አይችልም:: ነገር ግን እግዚአብሔር ልጁን የላከው እንዲያድነንና ሕግ ሊሠራው የማይችለውን እንዲፈጽም ነው:: ኢየሱስ እንደ መልአክ ሆኖ አልመጣም:: ሰው ሆኖ ነው የመጣው:: «ኃጢአተኛ *ሥጋ* ለብሶ» አልመጣም:: እንደ ሰው በኃጢአተኛ *ሥጋ* አምሳል መጣ:: በ*ሥጋ*ው ኃጢአታችንን በመስቀል ላይ ተሸከመ::

አንድ ሰው በሠራው ወንጀል ሁለት ጊዜ ሊወነጀል አይገባውም የሚል አንድ ሕግ አለ:: ኢየሱስ ክርስቶስ የኃጢአታችሁን ዋጋ ስለ ከፈለላችሁና እናንተም «በክርስቶስ» በመሆናችሁ እግዚአብሔር አይኮንናችሁም::

ሐ) *ሕግ አይገዛችሁም* (8:4) - አማኝ የጽድቅ ኑሮ የሚኖረው በሕግ ኃይል ሳይሆን፣ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ነው:: ሕግ ኃጢአትን ገልጦ ይኮንነዋል እንጂ፣ ቅድስናን ሊያፈራ አይችልም:: ነገር ግን በውስጣችሁ ያለው መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር በሕጉ የጠየቀው ጽድቅ በመንፈስ ኃይል በእናንተ

ተፈጽሟል። በመንፈስ ቅዱስ ሕይወት፣ አርነትና (8:2) ደስታን አግኝታችኋል (ሮሜ 8:4)።

ሕግ አጥባቂው በራሱ ብርታት የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ለመፈጸም ሲሞክር ይወድቃል። በመንፈስ የተሞላ ክርስቲያን ራሱን ለጌታ ሲያቀርብ፣ በመንፈስ ቅዱስ በሕይወቱ የሚሠራውን ቅድስና ይለማመዳል። «ስለ በጎ ፈቃዱ መፈለግንም ማድረግንም በእናንተ የሚሠራ እግዚአብሔር ነው» (ፊልጵ. 2:13)። ይህ እውነት ነው እንደ ክርስቲያን ወደምንለማመደው ሁለተኛ ነጻነት የሚመራን።

## 2. ከሽንፈት አርነት እንወጣለን- *ዕዳ የለብንም* (8:5-17)

«እንግዲህ፣ ወንድሞች ሆይ፣ *ዕዳ* አለብን፣ እንደ *ሥጋ ፈቃድ* ግን እንኖር ዘንድ ለ*ሥጋ* አይደለም» (ሮሜ 8:12)። ለአሮጌው ሰዎችን *ዕዳ* የለብንም። አማኝ በድል መኖር ይችላል። በዚህ ክፍል ሦስት የተለያዩ እርከኖች እንዳሉ በመግለጹ፣ እያንዳንዱ አማኝ በከፍተኛው እርከን ላይ እንዲኖር ጳውሎስ ያበረታታል።

*ሀ) «መንፈስ የላችሁም»* (8:5-8) በዚህ ክፍል ጳውሎስ *ሥጋ*ዊና *መንፈሳዊ* ክርስቲያኖችን እየገለጸ ሳይሆን፣ የዳኑትንና ያልዳኑትን እያነጻጸረ ነው። አራት ንጽጽሮች ቀርበዋል።

1) *በሥጋ - በመንፈስ* (8:5)። ያልዳነ ሰው የእግዚአብሔር መንፈስ ስለሌለው (ሮሜ 8:9)፣ ለ*ሥጋ*ውና በ*ሥጋ* ይኖራል። አእምሮው የሚያስበው *ሥጋን* ስለሚያረካ ነገር ብቻ ነው። ነገር ግን ክርስቲያኑ የእግዚአብሔር መንፈስ በውስጡ ስላለ፣ የሚኖረው *ፈጽሞ* አዲስ በሆነ ክበብ ውስጥ ነው። ይህ ግን ያልዳነው ሰው *መቼም* ቢሆን በጎ ነገር ማድረግ አይችልም ወይም አማኝ ክፉ ነገርን አይፈጽምም ማለት አይደለም። ትርጉሙ የሚያመለክተው ሕይወታቸው ለየቅል መሆኑን ነው። አንዱ ለ*ሥጋ*፣ ሌላኛው ደግሞ ለመንፈሱ ይኖራል።

2) *ሞት- ሕይወት* (8:6)። ያልዳነው ሰው በ*ሥጋ* ሕያው ቢሆንም፣ በመንፈስ *ሙት* ነው። ውስጣዊ ማንነቱ ስለ

እግዚአብሔር ነገር ሙት በመሆኑ፣ ለመንፈስ ምላሽ አይሰጥም:: የግብረገብ ሰውና ሃይማኖተኛ ሊሆን ይችላል፤ መንፈሳዊ ሕይወት ግን የለውም:: «በክርስቶስ ኢየሱስ የሕይወት መንፈስ ያሻዋል» (ሮሜ 8:2)::

3) *ከእግዚአብሔር ጋር ውጊያ- ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም* (8:6-7):: ሮሜ 7ን ስናጠና፣ አሮጌው ሰዋችን በእግዚአብሔር ላይ እንደሚያምጽና ራሱን ለእግዚአብሔር ሕግ እንደማያስገዛ አይተናል:: በክርስቶስ ያመኑት «ከእግዚአብሔር ጋር ሰላምን» ሲፈጥሩ (ሲያጣጥሙ) (ሮሜ 5:1)፣ ያልዳኑት ደግሞ ከእግዚአብሔር ጋር በውጊያ ላይ ናቸው:: «ለክፉዎች ሰላም የላቸውም ይላል እግዚአብሔር» (ኢሳ. 48:22)::

4) *ራስን ማስደሰት - እግዚአብሔርን ማስደሰት* (8:8):: «በሥጋ» መሆን ማለት ከክርስቶስ ውጭ ሆኖ መጥፋት ማለት ነው:: ያልዳነ ሰው ራሱን ለማስደሰት የሚኖር ሲሆን፣ እግዚአብሔርን ለማስደሰት ማሰቡ እንኳ ያጠራጥራል:: የኃጢአት ሥር ራስ ወዳድነት ነው:: «የእኔ ፈቃድ» እንጂ «የአንተ ፈቃድ» ይሁን አይደለም::

አለመዳንና የመንፈስ በሕይወት አለመኖር በሕይወት እጅግ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ መኖር ማለት ነው:: ሰው በዚህ ሁኔታ ሆኖ መቆየት የለበትም:: በክርስቶስ በማመን ወደሚቀጥለው እርከን መጓዝ ይችላል::

ለ) *«የእግዚአብሔር መንፈስ አላችሁ»* (8:9-11)- «እናንተ ግን የእግዚአብሔር መንፈስ በእናንተ ዘንድ ቢኖር፣ በመንፈስ እንጂ በሥጋ አይደላችሁም» (ሮሜ 8:9):: የመለወጣችን ማረጋገጫ መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን ኖሮ የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ሲመሰክርልን ነው (ሮሜ 8:10):: ሥጋችሁ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ይሆናል (1ኛ ቆሮ. 6:19-20):: በኃጢአት ምክንያት ሥጋችን ለሞት የተሰጠ ቢሆንም (ጌታ እስካልመጣ ድረስ)፣ ዛሬ መንፈስ ለሥጋችን ሕይወት በመስጠት እግዚአብሔርን እንድናገለግል ያስችለናል:: ብንሞትም እንኳ

መንፈስ ቅዱስ እያንዳንዱን አማኝ ስላተመው፣ ሥጋ አንድ ቀን ከሞት ይነሣል (ኤፌ. 1:13-14)::

መንፈስ ቅዱስ በሕይወታችሁ መኖር ሲጀምር የሚያመጣው ለውጥ የሚደንቅ ነው:: አዲስ ሕይወትን ትለማመዳላችሁ፣ በሥጋችሁም እንኳ ሳይቀር ወደ አዲስ ልምምድ ይወስዳችኋል:: ዲ. ኤል. ሙዲ እንዴት እንደተለወጡ ሲናገሩ እንዲህ ብለዋል፣ «ወደ አዲስ ዓለም ገባሁ:: በሚቀጥለው ቀን ፀሐይ የበለጠ ደመቀች:: የወፎቹም ዜማ ከበፊት ይልቅ ጣመኝ:: ዛፎች በክረምት ጊዜ የረገፉ ቅርንጫፎቻቸውን ለደስታ ዘረጉ:: ፍጥረት ሁሉ ሰላም ሆኖ ነበር::» በክርስቶስ ያለ ሕይወት የተትረፈረፈ ሕይወት ነው::

ነገር ግን እስካሁን ያየናቸው ዝግጅቶች ሲሆኑ ሦስተኛ እርከን አለ::

*ሐ) «መንፈስ ወርሷችኋል»* (ሮሜ 8:12-17)- እኛ መንፈስ ስላለን ብቻ በቂ አይደለም፤ መንፈስ እኛን ሊወርሰንም ያስፈልጋል:: የተትረፈረፈው የድል ሕይወት በክርስቶስ በኩል የእኛ የሚሆነው በዚህ ጊዜ ብቻ ነው:: ሥጋችን ለሕይወታችን ከችግር በቀር ያመጣልን ነገር ስለሌለ፣ የሥጋ ዕዳ የለብንም:: ክርስቶስን ባመንን ጊዜ በኃጢአታችን የወቀሰን፣ ክርስቶስን የገለጠልንና የዘለዓለም ሕይወት ያካፈለን መንፈስ ቅዱስ በመሆኑ የእርሱ ዕዳ አለብን:: እርሱ «የሕይወት መንፈስ» ስለሆነ፣ ክርስቶስን እንድንታዘዝና ክርስቶስን እንድንመስል ያስችለናል::

ነገር ግን እርሱ የሞት መንፈስም ነው:: የሰውነታችንን የኃጢአት ሥራ (የክፋት ተግባር) «እንድንገድል» ያስችለናል:: የሥጋችንን ብልቶች ለመንፈስ ቅዱስ ስናቀርብ (ሮሜ 6:12-17)፣ የክርስቶስን ሞትና ትንሣኤ በሕይወታችን ይገልጠዋል:: የሥጋን ነገር ገድሎ የመንፈስን ነገር በውስጣችን ያፈራል::

መንፈስ ቅዱስ «ልጅነትን የሚሰጥ መንፈስ ነው» (8:14-17):: መንፈስ ቅዱስ እኛን የእግዚአብሔር ልጆች ያደርገናል:: ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የምንገባው በመወለድ ነው::

የእግዚአብሔር ቤተሰብ ለመሆን እንደተወለድን ወዲያውኑ፣ ልጁ ያደርገናል:: የበኩር ልጅ የሚገባውንም ቦታ ሕፃን ልጅ መሄድ፣ መናገር ውሳኔ ማሳለፍ ወይም የቤተሰቡን ሀብት መውሰድ አይችልም:: ነገር ግን አማኝ በተወለደበት ቅጽበት፣ እነዚህን ሁሉ ማድረግ ይችላል::

መራመድ ይችላል «በመንፈስ ይመራል» (8:14):: የዚህ ቃል ግሥ «በፈቃደኝነት መመራት»ን ያመለክታል:: ራሳችንን ለመንፈስ ስናቀርብ፣ እርሱ ዕለት ዕለት በቃሉ ይመራናል:: በሕግ ቀንበር ሥር ስላልሆንን፣ እርምጃ ለመውሰድ አንፈራም:: የመንፈስ አርነት ስላለን ክርስቶስን ለመከተል ነፃ ነን:: አማኝ «አባ አባት» ብሎ መጮህ ይችላል (8:15):: አዲስ የተወለደ ሕፃን ቀና ብሎ ለአባቱ ሰላምታ ቢሰጠው አያስገርምም:: በመጀመሪያ፣ መንፈስ «አባ አባት» ይላልና (ገላ. 4:6)፣ ከዚያም እኛ እግዚአብሔርን «አባ አባት» እንለዋለን:: («አባ» ማለት «አባቴ» የሚል የቁልምጫ አባባል ነው::)

ሕፃን በባንክ ቼክ ላይ መፈረም አይችልም፣ ነገር ግን የእግዚአብሔር ልጅ በእምነት የእግዚአብሔር ወራሽና ከክርስቶስም ጋር አብሮ ወራሽ በመሆኑ መንፈሳዊ ሀብትን መውረስ ይችላል (8:17):: መንፈስ ከቃሉ ያስተምረናል፣ ከዚያም የእግዚአብሔርን ሀብት በእምነት እንቀበላለን:: «የልጅነትን መንፈስ ማግኘት»ና በሕይወታችን ሲሠራ ማየት ምን ያህል ያስደስታል::

አማኝ መረታት የለበትም:: ራሱን ለመንፈስ አቅርቦ በእምነት አሮጌውን ሰው ይረታዋል:: የሕይወት መንፈስ ኃይልን ያስታጥቀዋል:: የሞት መንፈስ ደግሞ ሥጋን እንዲያሸንፍ ያስችለዋል:: የልጅነት መንፈስ ይህን አበልጽጎ ወደ እግዚአብሔር ፈቃድ ይመራዋል::

## 3. ተስፋ ከመቁረጥ ነፃ ያወጣናል- መሰናክል የለም (8:18-30)

ጳውሎስ በዚህ ክፍል መከራንና ሥቃይን ዳስሷል። ይህንን ክፍል በተሻለ መንገድ ለመረዳት፣ ሦስቱን «መቃተት» መመልከት አስፈላጊ ነው።

*ሀ) ፍጥረት ይቃትታል* (8:18-22)- እግዚአብሔር ፍጥረቱን በፈጸመ ጊዜ ሁሉም መልካም ነበር (ዘፍጥ. 1:31)፤ ነገር ግን ዛሬ ፍጥረት ይቃትታል። መከራና ሞት አለ፣ ሥቃይ አለ። ይህ ሁሉ ደግሞ የአዳም ኃጢአት ውጤት ነው። ፍጥረት በራሱ ችግር ኖሮበት አይደለም። የፍጥረትን መታወክ ለመግለጽ ጳውሎስ የተጠቀመባቸውን ቃላት አስተውሉ። ሥቃይ (ቁ. 18)፣ ከንቱነት (ቁ. 20)፣ ባርነት (ቁ. 21)፣ ጥፋት (ቃ. 21) እና መከራ (ቁ. 22) ናቸው። ነገር ግን ይህ መቃተት ዋጋ ቢስ አይደለም። ጳውሎስ ይህን በምጥ ላይ ካለች ሴት ጋር አንጻጽሮታል። ሕመም ይኖራል፣ ነገር ግን ልጁ ሲወለድ ሥቃዩ ያከትማል። አንድ ቀን ፍጥረት አርነት ይወጣና የከበረ ፍጥረት ስለሚሆን፣ የፍጥረት መቃተት ያከትማል! አማኝ ዛሬ በሚያየው መከራ ላይ አትኩሮት አይኖረውም። የነገን ክብር ያያል (ቁ. 18፤ 2ኛ ቆሮ. 4:15-18)። የዛሬው የምጥ ባርነት በነገ የክብር ነጻነት ይለወጣል።

*ለ) እኛ አማኞች እንቃትታለን* (8:23-25)- የምንቃትትበት ምክንያት «የመንፈስ በኩራት» ስለቀመስን ሲሆን፣ ይህም የመጭው ክብር ቅምሻ ነው። ሰላዮቹ በተመለሱ ጊዜ እስራኤላውያን የከነዓንን በኩራት እንደቀመሱ (ዘኁል. 13:23-27)፣ እኛ ክርስቲያኖች በመንፈስ አገልግሎት የመንግሥተ ሰማያትን በረከት ቀምሰናል። ይህም ጌታን ልናየው እንድንናፍቅ፣ አዲስ አካልን ለመቀበልና ከእርሱ ጋር እየኖርን ለዘለዓለም እንድናገለግለው ያደርጋል። ክርስቶስ ሲመጣ፣ የሚኖረንን የሥጋችንን መዋጀት እየጠበቅን እንኖራለን (ፊልጵ. 3:20-21)። ይህም በተለወጥን ጊዜ ያገኘነው የእግዚአብሔር

ልጅነት ከፍተኛው ደረጃ ላይ መድረስ ሲሆን፣ የልጅነት መንፈስ የልጅነትን ሥልጣን ሰጥቶ ከእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ እንድንቆም አስቻለን። ክርስቶስ ሲመለስ ወደ ሙሉ ርስታችን እንገባለን።

እስከዚያው፣ በተስፋ እንጠባበቃለን። «በተስፋ ድነናልና» (8:24)። የምን ተስፋ? «. . . የተባረከውን ተስፋችንን እርሱም የታላቁን የአምላካችንንና የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር መገለጥ. . .» ነው (ቲቶ 2:13)። የሚሻለው ገና ወደ ፊት ይመጣል! አማኝ በዚህ ዓለም መከራና ሥቃይን ሲያይ ተስፋ አይቆርጥም። ጊዜያዊው መከራ አንድ ቀን የክብር መግቢያ እንደሚሆን ያውቃል።

*ሐ) መንፈስ ቅዱስ ይቃትታል* (8:25-30)- እግዚአብሔር ስለ ሕዝቡ መከራ ግድ ይለዋል። ኢየሱስ በምድር ላይ በሥጋ ሲኖር ኃጢአት በሰዎች ላይ ያደረሰውን ችግር አይቶ ቃትቷል (ማር. 7:34፤ ዮሐ. 11:33-38)። ዛሬም መንፈስ ቅዱስ ድካማችን፣ ሸክማችንና መከራችን እየተሰማው ከእኛ ጋር ይቃትታል። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ከመቃተት የበለጠ ነገር ያደርጋል። ሁልጊዜ የእግዚአብሔርን አሳብ አናውቅም። ሁልጊዜም እንዴት እንደምንጸልይ አናውቅም፣ ነገር ግን በመከራ ፊንታ የእግዚአብሔርን አሳብ እንድናውቅ መንፈስ ስለ እኛ ይማልዳል። መንፈስ «ድካማችንን ያግዛል»።

እግዚአብሔር በዓለም ላይ እንደሚሠራ እና ፍጹም የሆነ ዕቅድ ለሕይወቱ እንዳለው ስለሚያውቅ (8:28)፣ አማኝ በመከራና በፈተና ሊዝል አይገባውም (8:29)። እግዚአብሔር በዕቅዱ ሁለት ዓላማዎች አሉት፡- እነርሱም የእኛ በጎ መሆንና የእርሱ ክብር ናቸው። በመጨረሻም፣ ኢየሱስን እንድንመስል ያስችለናል። ከሁሉ የሚልቀው ደግሞ የእግዚአብሔር ፈቃድ መከናወኑ ነው። ሥራውን የጀመረው ከዘለዓለም እኛን በክርስቶስ በመረጠን ጊዜ ነው (ኤፌ. 1:4-5)። አንድ ቀን ልጁን እንድንመስል አስቀድሞ ወሰነ። ቅድመ-ውሳኔ ለዳኑት ሰዎች ብቻ ነው። እግዚአብሔር

አስቀድሞ ሰዎችን ለኩነኔ መርጦአል የሚል ትምህርት አልተማርንም:: የሚኮነኑት በክርስቶስ ለማመን አሻፈረኝ በማለታቸው ነው (ዮሐ. 3:18-21):: የመረጣቸውን ጠራቸው (2ኛ ተሰ. 2:13-14ን ተመልከቱ)፣ ለጥሪው ምላሽ ሲሰጡ አጸደቃቸው፣ ከዚያም አከበራቸው:: ይህ የሚያሳየን አማኝ በክርስቶስ የከበረ መሆኑን ነው (ዮሐ. 17:22):: የዚህ ክብር መገለጥ ደግሞ የጌታን መመለስ ይጠባበቃል (ሮሜ 8:21-23)::

የእግዚአብሔርን ክብር ተካፍለን እያለ፣ እኛ ክርስቲያኖች ተስፋ የምንቆርጠውና የምንዝለው ለምንድን ነው? የዛሬው መከራችን ክርስቶስ ሲመለስ የበለጠ ክብርን ያጎናጽፈናል!

## 4. ከፍርሃት ነፃ ወጥተናል- መለየት የለም (8:31-39)

ኩነኔ የማይኖርብን ከእግዚአብሔር ጽድቅ ስለምንካፈል እና ሕግ ሊኮንነን ስለማይችል ነው:: *ሥጋን አሸንፈን ለእግዚአብሔር* እንድንኖር የእግዚአብሔር መንፈስ ስላለን ዕዳ የለብንም:: ተስፋ መቁረጥም የለም:: ምክንያቱም የተባረከ ተስፋችን በሆነው በክርስቶስ መመለስ የእግዚአብሔርን ክብር እንካፈላለንና:: የእግዚአብሔርን ፍቅር ስለምንለማመድ መለየት የለም:- «ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል?» (ሮሜ 8:35)::

የዚህ የመጨረሻ ክፍል አጽንኦት የአማኞችን ዋስትና በተመለከተ ነው:: በክርስቶስ ፍቅር ስለተጠበቅን ትናንትን፣ ዛሬንና ነገን ልንፈራ አይገባንም:: በአማኝና በጌታ መካከል መለያየት አለመኖሩን ለማስረዳት ጳውሎስ አምስት ሙግቶችን አቅርቧል::

*ሀ) እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው (8:31)-* እግዚአብሔር አብ ከእኛ ጋር መሆኑን ለመግለጽ ልጁን ልኳል (8:32):: ወልድም ከእኛ ጋር ነው (8:34)፣ መንፈስ ቅዱስም ከእኛው ጋር ነው (8:26):: እግዚአብሔር ሁሉ ነገር ለበጎ እንደሚሆንልን አድርጓል (8:28):: በማንነቱና በአቅርቦቱ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው:: አንዳንድ ጊዜ እንደ ያዕቆብ እናለቅሳለን፣ «ልጅ አልባ አስቀራችሁኝ» (ዘፍጥ. 42:36)፣ ነገር ግን ሁሉ ነገር ለበጎ

ይሆንልናል:: መቋጫው ግልጽ ነው:- «እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ፣ ማን ይቃወመናል?»

አማኝ በእያንዳንዱ ቀን እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር እንደሆነ በመረዳት መኖር አለበት:: ከእርሱ መልካም ነገርን ለመቀበል የግድ በፈተና ቢያልፉም አፍቃሪ አባታቸው የሚበጀውን ስለሚመኝላቸው፣ መፍራት አያስፈልጋቸውም:: «ለእናንተ የማስባትን አሳብ እኔ አውቃለሁ፤ ፍጻሜና ተስፋ እሰጣችሁ ዘንድ የሰላም አሳብ ነው እንጂ የክፉ ነገር አይደለም» (ኤር. 29:11)::

*ለ) ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶአል* (8:32)- እዚህ ላይ ሙግቱ ከአነስተኛ ወደ ታላቅ ነው:: ኃጢአተኞች ሳለን እግዚአብሔር ምርጡን ከሰጠን፣ አሁንማ ልጆቹ ስንሆን የሚያስፈልገንን ሁሉ አይሰጠንምን? ኢየሱስም መሥጋትና መፍራት ሞኝነት መሆኑን ለሕዝቡ ለማስረዳት ሲሞክር ይህን ሙግት ተጠቅሟል:: እግዚአብሔር ለወፎችና ለበጎች እንዲሁም ለሜዳ አበባ ግድ ይለዋል:: ለእኛማ በእርግጥ የበለጠ ያስብልናል:: እግዚአብሔር የእርሱ ከሆኑት ጋር ያለው ተዛምዶ ሕግን የተመረኮዘ ሳይሆን፣ በቀራንዮ ጸጋው ላይ የተመሠረተ ነው:: እግዚአብሔር የራሱ ለሆኑት ሁሉ ሁሉን በነፃ ይሰጣል::

*ሐ) እግዚአብሔር አጽድቆናል* (8:33) - ይህም በክርስቶስ ውስጥ ጻድቅ አድርጎ ቆጥሮናል ማለት ነው:: ሰይጣን ሊከሰን ይወድዳል (ራእይ 12:10፤ ዘካ. 3:1-7)፣ ነገር ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ጻድቅ ሆነን እንቆማለን:: እኛ በክርስቶስ የተመረጥን፣ በክርስቶስ ተቀባይነትን ያገኘን የእግዚአብሔር ምርጦች ነን:: እርሱ ራሱ ስላጸደቀን እግዚአብሔር እኛን አይከስሰንም:: እርሱ የሚከስሰን ከሆነ የሰጠን ደኅንነት ዋጋ ቢስ ነው:: እኛ አሁንም በኃጢአታችን አለን ማለት ነው::

የጽድቅን ትርጉም መረዳት ለልባችን ሰላምን ያመጣል:: እግዚአብሔር አንድን ያመነ ኃጢአተኛ ጻድቅ ብሎ ሲጠራው ዐዋጁ መቼም ቢሆን አይለወጥም:: የክርስትና ልምምዳችን ከተን

ወደ ቀን ሊቀያየር ይችላል፣ ጽድቃችን ግን አይለወጥም። እኛ ራሳችንን እንከስ ይሆናል፣ ሰዎችም ሊከሱን ይችላሉ፤ እግዚአብሔር ግን ወደ ፍርድ ወንበር ወስዶ ፈጽሞ አይከሰንም። ኢየሱስ የኃጢአትን ዋጋ ስለ ከፈለ፣ እኛ ተጠብቀናል።

*መ) ክርስቶስ ስለ እኛ ይማልዳል* (8:34)- እጥፍ ምልጃ አማኙን በክርስቶስ ዋስትና ይሰጠዋል። *መንፈስ ይማልዳል* (8:26-27)፣ የእግዚአብሔር ልጅም ይማልድልናል (8:34)። ለእኛ የሞተልን ያው ጌታ አሁን በሰማያት ይማልድልናል። ሊቀ ካህናችን በመሆኑ ፈተናን መወጣት የምንችልበትን ጸጋና ጠላትን የምንረታበትን ጉልበት ይሰጠናል (ዕብ. 4:14-16)። ጠበቃችን ስለሆነና፣ ኃጢአታችንን ይቅር ብሎ ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ኅብረት ያድሳል (1ኛ ዮሐ. 1:9-2:2)። ምልጃ ማለት ኢየሱስ ክርስቶስ በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት እኛን ወክሎ ስላለ ራሳችንን መወከል አያሻንም ማለት ነው።

በሮሜ 5:9-10 ባለው ክፍል ጳውሎስ የምልጃን አገልግሎት ጠቁሟል። የዳንነው በሞቱ ብቻ ሳይሆን በሕይወቱም ነው። «ስለ እነርሱም ሊማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራልና ስለዚህ ደግሞ በእርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል» (ዕብ. 7:25)። ጴጥሮስ በጌታ ላይ ኃጢአት ሠርቶ ነበር፣ ነገር ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ኃጢአቱ ተፋቀለት ኅብረቱም ታደሰለት። «ስምዖን ስምዖን ሆይ፣ እነሆ፣ ሰይጣን እንደ ስንዴ ሊያበጥራችሁ ለመነ፤ እኔ ግን እምነትህ እንዳይጠፋ ስለ አንተ አማለድሁ» (ሉቃስ 22:31-32)። ስለ እያንዳንዳችን ይማልዳል ይህም አገልግሎቱ እያንዳንዳችን ዋስትና ያለን ስለመሆኑ ያረጋግጥልናል።

*ሠ) ክርስቶስ ይወድደናል* (8:35-39)- ከቁጥር 31-34 ጳውሎስ እግዚአብሔር እንደማይተወን አረጋግጧል። ነገር ግን እኛ ልንተወው እንችላለን? ከዚያስ? ጳውሎስ ይህንን ችግር በዚህ በመጨረሻው ክፍል ከክርስቶስ ፍቅር ሊለየን የሚችል ምንም ነገር እንደ ሌለ ያብራራል።

ለመንፈሳዊ ዕድገታችን የሚያስፈልጉን ስለሆነ ብሎ (ሮሜ 5:3-5) እግዚአብሔር ከሕይወት ውጣ ውረዶች አያስጠልለንም:: በሮሜ 8:28 እንደተናገረው የሕይወት ውጣ ውረዶች ለበጎ እንደሚሆኑልን እንጂ እንደማያጠፉን አረጋግጦልናል:: ለራሳችን በጎነትና ለራሱ ክብር ሲል እግዚአብሔር ፈተናን ይፈቅዳል:: ስለ እርሱ ብለን ፈተናን እንታገሳለን (8:36):: ይህንን በማድረጋችን እግዚአብሔር የሚተወን ይመስላችኋል? በፍጹም! ይልቁንም በሕይወት ፈተና ስናልፍ የበለጠ ይጠጋናል::

በተጨማሪም፣ የምናሸንፍበትን ኃይል ይሰጠናል (ቁ. 37):: በክርስቶስ «ከአሸናፊዎች እንበልጣለን::» በድል ላይ ድልን ይሰጠናል:: ሕይወትንም፣ ሞትንም፣ ያለውንም፣ የሚመጣውንም አንፈራም:: ምክንያቱም ኢየሱስ ክርስቶስ ይወድደናል፣ ድልንም ይሰጠናል:: ይህ የተስፋ ቃል በእኛ ጥረት ላይ የተመሠረተ አይደለም፣ «እንዲህ ብታደርጉ፣ እንዲህ አደርጋለሁ» አላለም:: ይህ ዋስትናችን የጸና እውነት ነው:: እኛ የክርስቶስ ስለሆንን ዋስትናው የራሳችን መሆኑን እናውቃለን:: ከእርሱ ፍቅር ምንም ሊለያችሁ አይችልም:: እመኑና በእርሱ ሐሴት አድርጉ!

የዚህ አስደናቂ ምዕራፍ ግምገማ ክርስቲያን ሙሉ በሙሉ ባለድል መሆኑን ያሳያል:: ክርስቶስ ስለሞተልን ከፍርድ ነፃ ነን:: የእርሱም ጽድቅ አለን:: ክርስቶስ በመንፈሱ በእኛ ውስጥ ስለሚኖርና በሕይወቱ ስለምንካፈል፣ ከሽንፈት ነፃ ነን:: ክርስቶስ ስለሚመጣና በክብሩ ስለምናካፈል ከተስፋ መቁረጥ አርነት ወጥተናል:: ክርስቶስ ስለሚማልድልንና ከእርሱ ፍቅር ሊለየን የሚችል ማንም ስለሌለ፣ ከፍርሃት ነፃ ነን::

ኩነኔ የለብንም! ዕዳ የለብንም! ተስፋ አንቆርጥም! ከእርሱ አንለይም!

እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ፣ ማን ይቃወመናል?

# ሮሜ 9:1-33

ብዙ ኀዘን የማያቋርጥም ጭንቀት በልቤ አለብኝ ስል በክርስቶስ ሆኜ እውነትን እናገራለሁ፣ አልዋሽምም ሕሊናዬም በመንፈስ ቅዱስ ይመሰክርልኛል:: በሥጋ ዘመዶቼ ስለ ሆኑ ስለ ወንድሞቼ ከክርስቶስ ተለይቼ እኔ ራሴ የተረገምሁ እንድሆን እጸልይ ነበርና:: እነርሱ እስራኤላውያን ናቸውና፣ ልጅነትና ክብር ኪዳንም የሕግም መሰጠት የመቅደስም ሥርዓት የተስፋውም ቃላት ለእነርሱ ናቸውና፤ ከእነርሱም ክርስቶስ በሥጋ መጣ፣ እርሱም ከሁሉ በላይ ሆኖ ለዘላለም የተባረከ አምላክ ነው፤ አሜን :: (ሮሜ 9:1-5)

ነገር ግን፣ አንተ ሰው ሆይ፣ ለእግዚአብሔር የምትመልስ ማን ነህ? ሥራ ሠሪውን:- ስለ ምን እንዲህ አድርገህ ሠራኸኝ ይለዋልን? ወይም ሸክላ ሠሪ ከአንድ ጭቃ ክፍል አንዱን ዕቃ ለክብር አንዱንም ለውርደት ሊሠራ በጭቃ ላይ ሥልጣን የለውምን? ነገር ግን እግዚአብሔር ቍጣውን ሊያሳይ ኃይሉንም ሊገልጥ ወዶ፣ አስቀድሞ ለክብር ባዘጋጃቸው በምሕረት ዕቃዎች ላይ የክብሩን ባለጠግነት ይገልጥ ዘንድ፣ ለጥፋት የተዘጋጁትን የቁጣ ዕቃዎች በብዙ ትዕግሥት ከቻለ፣ እንዴት ነው? የምሕረቱ ዕቃዎችም ከአይሁድ ብቻ አይደሉም፣ ነገር ግን ከአሕዛብ ደግሞ የጠራን እኛ ነን:: (9:20-24)

እንግዲህ ምን እንላለን? ጽድቅን ያልተከተሉት አሕዛብ ጽድቅን አገኙ፣ እርሱ ግን ከእምነት የሆነ ጽድቅ ነው፤ እስራኤል ግን የጽድቅን ሕግ እየተከተሉ ወደ ሕግ አልደረሱም:: ይህስ ስለ ምንድር ነው? በሥራ እንጂ በእምነት ጽድቅን ስላልተከተሉ ነው፤

እነሆ፣ በጽዮን የእንቅፋት ድንጋይና የማሰናከያ ዓለት እኖራለሁ በእርሱም የሚያምን አያፍርም፤ ተብሎ እንደ ተጻፈ በእንቅፋት ድንጋይ ተሰናከሉ:: (ሮሜ 9:30-33)

# 8

## እግዚአብሔር ተሳሳተን?

ጳውሎስ ስለ ደኅንነት የጀመረውን ትምህርት አቋርጦ በሦስት ምዕራፎች ስለ እስራኤል ሕዝብ ጉዳይ መጻፉ እንግዳ ነገር ይመስላል:: ስለ ዶክትሪን (አስተምህሮ) የሚያስተምረውን ምዕራፍ 8ን እንደ ጨረሰ በሕይወት ስለማዛመድ ወደሚናገረው ከምዕራፍ 12-15 ወዳለው ክፍል ለምን በቀጥታ አላለፈም? ሮሜ 9-11 በጥንቃቄ ካጠናነው የእስራኤል ሕዝብ ጉዳይ በድንገት ጣልቃ አለመግባቱን ይገልጥልናል:: ጳውሎስ በእምነት ስለ መጽደቅ ላቀረበው ማረጋገጫ ይሄ አስፈላጊ ክፍል ነው::

ጳውሎስ በአይሁዳውያን ዘንድ የሚታየው እንደ ከሃዲ ነበር:: አሕዛብን አገልግሏል:: ከሙሴ ሕግ ነፃ ስለመውጣትም አስተምሯል:: በተለያዩ ምኩራቦች ሰብኮ ችግር ተፈጥሯልና በሮም የነበሩት አማኞች የጳውሎስን ዝና መስማታቸው ጥርጥር የለውም:: በእነዚህ ምዕራፎች ጳውሎስ ለእስራኤላውያን ያለውን ፍቅርና ለደኅንነታቸው ያለውን ጉጉት አሳይቷል :: ይህንን ያደረገበት በራሱ የግል ምክንያት ሊሆን ይችላል::

ነገር ግን አስተምህሮው ምክንያት ነበረው:: ጳውሎስ በሮሜ 8 ላይ አማኝ በኢየሱስ ክርስቶስ የተጠበቀ መሆኑንና የእግዚአብሔርም ምርጫ እንደሚጸና ሙግቱን አቅርቧል (8:28-30):: ነገር ግን አንዱ፣ «አይሁዳውያንስ? በእግዚአብሔር ተመርጠው ነበር፤ አሁን ግን እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን እየገነባ አይሁድን ችል ብሏቸዋል:: እግዚአብሔር ለእስራኤል የገባውን ተስፋ ጥሎታልን» ብሎ ይጠይቃል:: በሌላ አባባል የእግዚአብሔር ባሕርይ አደጋ ላይ የወደቀ ይመስላል:: እግዚአብሔር ለአይሁድ ለሰጠው ቃል ኪዳን ታማኝ ካልሆነ፣ ለቤተ ክርስቲያን መታመኑንስ በምን እናውቃለን?

በምዕራፍ 9 የተገለጠው የእስራኤል መመረጥ አስቀድሞ ሲሆን፣ ምዕራፍ 10 ላይ ደግሞ እስራኤል እግዚአብሔርን

መግፋቷን ያትትና በምዕራፍ 11 ላይ የእስራኤልን የወደፊት የመታደስ ዘመን ይናገራል:: በዓለም ላይ ያለፈ፣ የአሁንና የወደፊት ታሪክ ያላት ብቸኛ አገር እስራኤል ነች:: ምዕራፍ 9 ላይ ጳውሎስ በምዕራፍ 9 እግዚአብሔር የእስራኤል የኋላ ታሪክ የእግዚአብሔርን በጎ ባሕርያት የሚገልጥ እንደሆነ በመግለጽ በተለይ አራቱን ባሕርያቱን ጠቅሷል:- ታማኝነቱን (ቁ. 1-13)፣ ጽድቁን (ቁ. 14-18)፣ ፍትሑን (ቁ. 19-29)፣ ጸጋውን (ቁ. 30-33):: በደንብ ካስተዋላችሁ እነዚህ ዋና ዋና ክፍሎች ጳውሎስ ከጠየቃቸው ሦስት ጥያቄዎች ጋር ይጣጣማሉ:- እነርሱም «በእግዚአብሔር ዘንድ ዐመፃ አለ ወይ?» (ቁ. 14):: «እንግዲህ ስለ ምን እስከ አሁን ድረስ ይነቅፋል?» (ቁ. 19) እና «እንግዲህ ምን እንላለን?» (ቁ. 30)::

## 1. የእግዚአብሔር ታማኝነት (9:1-13)

ጳውሎስ ከሚያስደስተው ከምዕራፍ 8 ኀዘን ወደ ተሞላው ወደ ምዕራፍ 9 መራመዱ ግልጽ ነው:: ክርስቶስን ሲያይ ተደሰተ፤ የጠፉትን እስራኤላውያንን ሲያይ ደግሞ አለቀሰ:: እንደ ሙሴ (ዘጸ. 32:30-35) ስለ እስራኤል መዳን ራሱ የተረገመ ይሆን ዘንድ ፈቃደኛ ነበር:: ይሄ ጳውሎስ ምን ዓይነት ሰው ነው? ስላልዳኑት ከመንግሥተ ሰማይ መጉደልን እንኳ መረጠ (9:3)፤ ስለጠፉትም ሲል ሲዖል መውረድን ፈቀደ::

ጭብጡ እግዚአብሔር እስራኤልን የመምረጡ ጉዳይ ሲሆን፣ በመጀመሪያ የዳሰሰው የመመረጣቸውን በረከት ነው (ቁ. 4-5):: እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ልጆቹ አድርጎ መርጦአቸዋል (ዘጸ. 4:22-23):: በመገናኛ ድንኳንና በቤተ መቅደስ ክብሩን አሳይቷቸዋል (ዘጸ. 40:34-38፣ 1ኛ ነገ. 8:10-11):: ሙሴ በሲና ተራራ ላይ ያየው ክብር በእስራኤል መካከል ኖረ (ዘጸ. 24:16-17):: እግዚአብሔር ቃል ኪዳኑን ለእስራኤል ሰጠ፣ በመጀመሪያ ለአብርሃም፣ ከዚያም ተጨማሪ ቃል ኪዳኖችን ለሙሴና ለዳዊት ሰጠ:: ፖለቲካዊ፤ ማኅበራዊና ሃይማኖታዊ ሕይወት የሚያስተዳድር ሕግ የሰጣቸው ሲሆን፣ በታዘዙት

መሠረት እንደሚባርካቸው ዋስትና ነበራቸው:: በመገናኛው ድንኳንና በቤተ መቅደስ እንዲያገለግሉት «የእግዚአብሔርን አገልግሎት» ሰጣቸው:: የተስፋ ቃልንና አባቶችን ሰጣቸው:: የዚህ ሁሉ በረከት ዓላማ ኢየሱስ ክርስቶስ በእነርሱ በኩል ወደ ዓለም እንዲመጣ ነው:: (ቁ. 5 ኢየሱስ አምላክ መሆኑን እንደሚያስረግጥ አስታውሉ::) እነዚህ ሁሉ በረከቶች ለእስራኤል በነፃ የተሰጡ ሲሆን፣ ለሌሎች አሕዛብ ግን አልተሰጡም ነበር::

እነዚህ ሁሉ በረከቶች ቢኖሩም እስራኤል ግን አልተሳካላትም:: መሢሑ በመጣ ጊዜ እስራኤላውያን ገፉት፣ ሰቀሉትም:: ጳውሎስ ራሱ አሳዳጅ ስለነበረ፣ ይህን ከእርሱ በተሻለ መልኩ የሚያውቅ አይኖርም:: የእስራኤል መውደቅ የእግዚአብሔርን ቃል ይሽራልን? መልሱ «በፍጹም! የሚል ነው:: ሰዎች በቃሉ ላይ የፈለጋቸውን ቢያደርጉም፣ እግዚአብሔር ግን ታማኝ ነው»:: በዚህ ስፍራ ጳውሎስ የእስራኤልን የመመረጥ ምክንያት ያብራራል::

ሀ) *በሥጋ የዘር ሐረግ አልነበረም* (9:6-10) - በሮሜ 2:25-29 እንዳየነው፣ በሥጋ የአብርሃም ዘር በሆኑና በመንፈስ የአብርሃም ልጆች በሆኑት መካከል ልዩነት እንዳለ አይተናል:: አብርሃም ሁለት ልጆች ነበሩት፣ እስማኤልና (ከአጋር) ይስሐቅ (ከሣራ):: እስማኤል የበኩር ልጅ ስለሆነ፣ መመረጥ ነበረበት:: ነገር ግን እግዚአብሔር የመረጠው ይስሐቅን ነበረ:: ይስሐቅና ርብቃ ዔሣውና ያዕቆብ የተባሉ ሁለት መንትያ ልጆች ነበሯት:: የመጀመሪያ ልጅ በመሆኑ ዔሣው መመረጥ ሲገባው፣ እግዚአብሔር የመረጠው ግን ያዕቆብን ነበረ:: በተለይ ዔሣውና ያዕቆብ እንደ ይስሐቅና እስማኤል የተወለዱት ከሁለት እናቶች ሳይሆን፣ የአንድ እናት የአንድ አባት ልጆች ነበሩ:: የእግዚአብሔር ምርጫ በሚታይ ነገር ላይ የተመሠረተ አይደለም:: ስለዚህ የአብርሃም የሥጋ ዘር የሆኑት እስራኤላውያን የእግዚአብሐርን ቃል ቢገፉ፣ የእግዚአብሔርን ምርጫ ከንቱ አያደርገውም::

ለ) *በሰው ጥረት አይደለም* (9:11-13) - ሕፃናቱ ከመወለዳቸው አስቀድሞ እግዚአብሔር ያዕቆብን መረጠ። ልጆቹ በጎ ወይም ክፉ አላደረጉም፣ የእግዚአብሔር ምርጫ በባሕርያቸው ወይም በፀባያቸው ላይ የተመረኮዘ አልነበረም። ቁጥር 13 ከሚልክያስ 1:2-3 የተወሰደ ሲሆን፣ የሚያወሳውም ስለ እስራኤልና ስለ ኤዶም ነው እንጂ ስለ ኃጢአተኛ ግለሰቦች አይደለም። ዮሐ. 3:16 እንደሚያመለክተው እርሱ ኃጢአተኞችን ይወዳል። ምንባቡ የሚናገረው ስለ አንድ አገር መመረጥ እንጂ ስለ ግለሰቦች አይደለም። እግዚአብሔር እስራኤልን የመረጠው በሰው ጥረት ላይ ተመሥርቶ ስላልነበረ፣ አለመታዘዛቸው የእግዚአብሔርን የምርጫ ዓላማ ከንቱ አያደርገውም። ሕዝቡ ታማኞች ባይሆኑም እንኳ እግዚአብሔር ታማኝ ነው።

## 2. የእግዚአብሔር ጽድቅ (9:14-18)

እግዚአብሔር አንዱን መርጦ ሌላውን መተዉ ዐመፀኛ መሆኑን የሚያመለክት ይመስላል። «በእግዚአብሔር ዘንድ ዐመፃ አለ ወይ?» ብሎ ጳውሎስ ጠይቋል። ራሱ «አይደለም» ብሎ መልስ ይሰጣል። ቅዱስ እግዚአብሔር ዐመፅ ያደርጋል ማለት የማይታሰብ ነገር ነው። ምርጫ የጸጋ ጉዳይ ነው። እግዚአብሔር ነገርን ሁሉ እንደ ጽድቃችን ቢሰጠን ኖሮ፣ ማንም አይድንም ነበር። ጳውሎስ ዘጸአት 33:19 ጠቅሶ የእግዚአብሔር ምሕረትና ርኅራኄ የሚቀጥሉት እንደ ሰው ፈቃድ ሳይሆን፣ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን አሳይቷል። ሁላችንም ምሕረት ሳይሆን፣ ፍርድ የተገባን ነበርን። ዘጸአት 33 የሚናገረው ሙሴ በተራራው ላይ ሕግጋተ እግዚአብሔርን ሲቀበል እስራኤላውያን ስለማመንዘራቸው ነው። ሕዝብ ሁሉ መሞት ሲገባቸው፣ እግዚአብሔር የቀሰፈው ግን 3000 ሰዎችን ብቻ ነው። ያልሞቱት ቅዱሳን ስለሆኑ ወይም የሞቱት ከእነርሱ የባሱ ክፉና ርኩሳን ስለሆኑ ሳይሆን፣ በምሕረቱና በጸጋው ነው።

ጳውሎስ ዘጸአት 9:16 በመጥቀስ ፈርዖንን እንደ ምሳሌ አቅርቧል። ሙሴ አይሁድ ነበር፣ ፈርዖን ደግሞ አረማዊ፣ ነገር

ግን ሁለቱም ኃጢአተኞች ነበሩ። ሁለቱም ነፍሰ ገዳዮች ነበሩ። ሁለቱም የእግዚአብሔርን ተአምራት አይተዋል። ሙሴ ሲድን፣ ፈርዖን ግን ጠፋ። እግዚአብሔር ፈርዖንን ያስነሣው ክብሩንና ኃይሉን ሊገልጥ ነው። ሙሴን ደግሞ የማረው ሕዝቡን እስራኤልን ነፃ እንዲያወጣ ነው። ፈርዖን ገዥ ነው፣ ሙሴ ደግሞ ባሪያ ነበር። ነገር ግን የእግዚአብሔርን ምሕረትና ርኅራኄ የተለማመደው ሙሴ ነው- ምክንያቱም እግዚአብሔር እንዲህ እንዲሆን ፈቀደ። እግዚአብሔር ሉዓላዊ ስለሆነ በሥራውና በአደራረጉ እንደ ፈቀዱና እንደ ዓላማው ያደርጋል። ነገሩ የጽድቅ ጉዳይ ሳይሆን፣ ልዑል የሆነው የእግዚአብሔር ፈቃድ ጉዳይ ነው።

እግዚአብሔር ቅዱስ ነውና ኃጢአትን ሊቀጣ ይገባዋል። ነገር ግን እግዚአብሔር አፍቃሪና ኃጢአተኞችን ለማዳን መሻት ያለው አምላክ ነው። ሰው ሁሉ ቢድን፣ ቅድስናውን መካዱ ነው፤ ሰው ሁሉ ቢጠፋ ደግሞ፣ ፍቅሩን ሊክድ ነው። መፍትሔው የእግዚአብሔር ሉዓላዊ ምርጫ ነው።

አንድ ጊዜ አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ሴሚናሪ ፕሮፌሰር እንዲህ አለኝ፣ «የእግዚአብሔርን ምርጫ ለማብራራት ስትሞክር፣ አእምሮህን ታጣለህ፤ ብትክደው ደግሞ፣ ነፍስህን ታጣለህ!»

እግዚአብሔር እስራኤልን መርጦ ግብፅን ኮነነ፣ ሉዓላዊ፣ ዓላማው ይህ ነበርና። እግዚአብሔር ጻድቅ ስለሆነ፣ ምሕረቱን በምን መንገድ እንደሚሰጥ ማንም ሊጠይቅ አይችልም።

ይህን ክፍል ስንጨርስ ስለ ፈርዖን ልብ «መደንደን» እንነጋገራለን (ቁ. 18)። «የልብ መደንደን» ሂደት ከዘጸአት 7-14 ድረስ 15 ጊዜ ተጠቅሷል። አንዳንድ ጊዜ ፈርዖን ልቡን እንዳደነደነ ተነግሮናል (ዘጸ. 8:15፣19፣32)፣ በሌላ ጊዜ ደግሞ እግዚአብሔር የፈርዖንን ልብ እንዳደነደነ ተጽፎአል (ዘጸ. 9:12፤10:1፣20፣27)። ቃሉን በማወጅና ኃይሉን በመግለጥ ፈርዖን ንስሐ እንዲገባ ዕድል ቢሰጠውም፣ እርሱ ግን እግዚአብሔርን በመቋቋም ልቡን አደነደነ። ችግሩ ያለው በእግዚአብሔር ዘንድ

ሳይሆን፣ በፈርዖን ላይ ነው:: በረዶን የሚያቀልጥ የፀሐይ ብርሃን ሸክላን ያደርቃል:: እግዚአብሔር ፈርዖንን በንስሐ ገብቶ እንዲያምን ዕድል ስለሰጠው፣ እግዚአብሔር ዐመፀኛ አልነበረም::

## 3. የእግዚአብሔር ፍትሕ (9:19-29)

የእግዚአብሔር ሉዓላዊነት ሌላ ችግር የሚፈጥር ይመስላል:: «እግዚአብሔር ሉዓላዊ ከሆነ፣ ማን ሊቋቋመው ይችላል? የሚቋቋመው ካለ ደግሞ እንዴት ሊዳኝ ይችላል?» ይህ እግዚአብሔር በሰው ዘር ታሪክ ውስጥ ስለ ፍትሐዊ አሠራሩ የሚጠየቅ የቆየ ጥያቄ ነው::

በቺካጐ ጎዳና በራሪ መንፈሳዊ ወረቀቶችን ስበትን የሆነውን አስታውሳለሁ:: አብዛኛዎቹ ሰዎች ትራክቶችን በምሥጋና የተቀበሉኝ ሲሆን፣ አንዱ ግን ጭምድድ አድርጎ የውኃ አሸንዳ ውስጥ ወረወረው:: የትራክቱ ስም «እግዚአብሔር እንድታውቃቸው የሚፈልገው አራት ነገሮች» የሚል ነበር::

ሰውየው፣ «እግዚአብሔር እንዲያውቃቸው የምፈልገው ጥቂት ነገሮች አሉ» አለ:: «በዚህ ዓለም ለምን ብዙ ኀዘንና ሰቆቃ ኖረ? ሀብታሞች በነጻነት ሲመላለሱ ምስኪኖች ለምን ይሠቃያሉ?» ብሎ በንቀት ገላመጠኝና፣ «እግዚአብሔር አለ ብለህ አትንገረኝ! እግዚአብሔር ካለ በዓለም ላይ ከኖሩ ኃጢአተኞች ትልቁ እርሱ ነው!» አለና በንቀት ጀርባውን ሰጥቶኝ ከሕዝቡ ጋር ተቀላቀለ::

እግዚአብሔር በባሕርይው ፍጹም እንደሆነ እናውቃለን:: «የምድር ሁሉ ፈራጅ በቅን ፍርድ አይፈርድምን?» (ዘፍጥ. 18:25) እግዚአብሔር ዓመፅን ሲያደርግ ወይም ዐመፀኛ ዓላማና ፈቃድ እንዳለው ፈጽሞ የማይታሰብ ነው:: አንዳንድ ጊዜ ግን እንዲህ የሚያደርግ ይመስላል:: ለሙሴ ምሕረትን አደረገ፣ በፈርዖን ላይ ግን ፈረደበት:: ይህ ትክክል ነውን? እስራኤልን መረጠ፣ ሌሎቹን አሕዛብ ተዋቸው:: ይህ ልክ ነውን? ጳውሎስ ለዚህ ክስ ሦስት መልሶችን ሰጥቷል::

*ሀ) ለእግዚአብሔር የምንመልስ እኛ ማን ነን?* (9:19-21)- ይህ ሥነ - አመክንዮአዊ ነው። እግዚአብሔር ሠሪያችን ከሆነ፣ እኛ ደግሞ ሸክላዎች ነን። እግዚአብሔር ከእኛ ይልቅ ጥበበኛ ስለሆነ፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ልናርም ወይም ልንቋቋም መሞከራችን ሞኝነት ነው። (የዚህ ምንባብ ማጣቃሻ ኢሳ. 45:9 ነው።) ሸክላ ሕይወት የለውም፣ በሠሪው እጅም ላይ ተጽዕኖ ማሳደር አይችልም። ስሜት፣ እውቀትና ፈቃድ ስላለን ከፈለግን እግዚአብሔርን ልንቃወመው እንችላለን። (ኤርምያስ 18ን አንብቡ)። ነገር ግን አንድ ሰው ሙሴን ወይም ፈርዖንን እንዲሆን የሚወስነው እግዚአብሔር ነው። ሙሴም ሆነ ፈርዖን እንዲሁም ማንኛውም ሰው ወላጆችን መምረጥ፣ የሚወለድበትን ቦታና ጊዜ መምረጥ ወይም ምን ዓይነት ቁመና እንደሚኖረው መምረጥ፣ አይችልም። እነዚህ ነገሮች በእግዚአብሔር እጅ መሆናቸውን ማመን አለብን።

ነገር ግን፣ ይህ መሆኑ ከተጠያቂነት አያድነንም። ፈርዖን ስለ እውነተኛው አምላክ የመማር ትልቅ ዕድል ነበረው። ነገር ግን ማመፅ ፈለገ። ጳውሎስ ይህንን እውነት የጠቀሰው የሚያስተምረው ጭብጥ መለኮታዊ ሉዓላዊነት እንጂ የሰው ተጠያቂነት ስለሆነ አይደለም። ውስኑ አእምሮአችን ሁለቱንም በሙላት ባይረዳም፣ አንዱ ሌላኛውን አይክድም።

*ለ) እግዚአብሔር የራሱ ዓላማ አለው* (9:22-24)- እግዚአብሔር እንደ ፈርዖን ያለውን ጨካኝ እያየ ይደሰታል ማለት አይደለም። እግዚአብሔር ለሙሴ «የሕዝቤን መከራ በእውነት አየሁ. . . ጩኸታቸውን ሰማሁ ሥቃያቸውን አውቃለሁ» (ዘጸ. 3:7) አለው። ይህ የሚያመለክተው እግዚአብሔር ለፈርዖን ዕድል መስጠቱን ነው (2ኛ ጴጥ. 3:9)። በቁጥር 22 ላይ እግዚአብሔር ፈርዖንን የቁጣ ዕቃ አድርጎ አልመረጠውም። እግዚአብሔር ሰዎችን የሚያዘጋጃቸው ለክብር ነው (ቁ. 23)። ነገር ግን ኃጢአተኞች ራሳቸውን ለፍርድ ያዘጋጃሉ። በሙሴና በእስራኤል እግዚአብሔር የምሕረቱን ባለጠግነት ገለጠ። በፈርዖንና በግብፅ ላይ ደግሞ ኃይሉንና

ቁጣውን ገለጠ:: ማናቸውም ምሕረት የተገባቸው ስላልሆኑ፣ እግዚአብሔር በዐመፅ ሊከሰስ አይችልም::

በፍጻሜውም የእግዚአብሔር ዓላማው በቤተ ክርስቲያኑ አይሁድንና አሕዛብን (ቁ. 24) ለመፍጠር ነው:: ዛሬ አማኞች በእግዚአብሔር ጸጋ «የምሕረት ዕቃዎች» ሆነው ለክብር እየተዘጋጁ ሲሆን፣ ይህም እውነት ሮሜ 8:29-30 ያለውን ክፍል ያስታውሰናል::

*ሐ) ይህ ሁሉ በትንቢት ተነግሯል* (9:25-29)- በመጀመሪያ ጳውሎስ ሆሴዕ 2:23ን ጠቅሶ፣ እግዚአብሔር አይሁድን ትቶ አሕዛብን እንደሚጠራ ያውጃል:: ቀጥሎ ሆሴዕ 1:10ን አጣቅሶ፣ እነዚህ አዲስ ሕዝቦች የእግዚአብሔር ሕዝብ እና «የሕያው እግዚአብሔር ልጆች» ተብለው እንደሚጠሩ ያረጋግጣል:: ኢሳይያስ 10:22-23ን ጠቅሶ፣ አብዛኛው እስራኤላዊ ፍርድን እንደሚቀበል ቅሬታዎቹ ግን እንደሚድኑ ያሳያል:: ቁጥር 28 ምናልባትም የሚናገረው እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ ስደትንና ፍርድን ስለሚፈጽምበት ስለ መከራው ዘመን ይመስላል:: ቅሬታዎች ብቻ ናቸው ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር ሲመለስ ወደ መንግሥቱ የሚገቡት:: ነገር ግን ዛሬ ከዚህ የምንማረው ነገር ግልጽ ነው:: የሚያምኑት በጣም ጥቂት አይሁድ ብቻ ሲሆኑ፣ እነርሱም ከአሕዛብ ጋር «በእግዚአብሔር የተጠሩ» (ቁ. 24) ይባላሉ:: የመጨረሻው ጥቅስ ከኢሳይያስ 1:9 የሚያወሳ ሲሆን፣ አጽንኦት የሚሰጠው የሚያምኑትን ቅሬታዎች በሚያድነው እግዚአብሔር ጸጋ ላይ ነው::

አሁን ታዲያ፣ ይህ ሁሉ የሚያስረግጠው ምንድን ነው? እግዚአብሔር አንዳንዶቹን አድኖ በሌሎቹ ላይ መፍረዱ ዐመፀኛ አያደርገውም፤ በብሉይ ኪዳን ከዘመናት በፊት የተነገሩትን ትንቢቶች ወደ ፍጻሜ እያመጣ ነውና:: ቃሉን ባይጠብቅ ኖሮ ዐመፀኛ ይሆን ነበር:: እነዚህ ትንቢቶች እንደሚያሳዩት የእግዚአብሔር ምርጫ አሕዛብ እንዲድኑ አስችሎአቸዋል:: ይህ የእግዚአብሔር ጸጋ ነው:: ከግብጽ ባርነት ነፃ በወጡበት ጊዜ እግዚአብሔር አሕዛብን ትቶ አይሁድን የመረጠው፣ በአይሁድ

በኩል አሕዛብን ለማዳን ነው:: የእስራኤል ሕዝብ ፈቃዱን ተቃወሙ፣ ይህ ግን ዓላማውን እንዲያጥፍ አላደረገም:: የአይሁድ ቅሬታዎች አመኑ፣ የእግዚአብሔም ቃል ተፈጸመ::

እስካሁን፣ ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ታማኝነት፣ ጽድቅና ፍትሐዊነት በማሳየት የእግዚአብሔርን ባሕርይ ትክክለኝነቱን እንደሚገልጽ እያስረዳ ነው:: እስራኤላውያን ባይቀበሉም፣ የእግዚአብሔርን ምርጫ ሊገቱት አልቻሉም:: ነገር ግን እርሱ ለባሕርይውና ለዓላማው እውነተኛ መሆኑን አረጋገጠ እንጂ::

## 4. የእግዚአብሔር ጸጋ (9:30-33)

ጳውሎስ በመቀጠል ከመለኮታዊ ሉዓላዊነት ወደ ሰው ተጠያቂነት አመራ:: ጳውሎስ «የተመረጡና» «ያልተመረጡ» ከማለት ይልቅ በእምነት ላይ አጽንኦት መስጠቱን አስተውሉ:: እዚህ ላይ የተምታታ ነገር ያለ ይመስላል- አይሁድ ጽድቅን ፈለጉ ነገር ግን አላገኙም:: አሕዛብ ግን ሳይፈልጉት አገኙት! ምክንያቱም ምንድን ነው? እስራኤላውያን መዳን የፈለጉት በሥራ እንጂ በእምነት ስላልነበረ ነው:: «በጸጋ የሚገኝን ጽድቅ» ተቃውመው «በሕግ ጽድቅ» እግዚአብሔርን ሊያስደስቱ ፈለጉ:: አሕዛብ ለመዳን እንደ እስራኤላውያን መሆን እንዳለባቸው አይሁዳውያን ቆጠሩ:: ነገር ግን አይሁድ ለመዳን ዝቅ ብለው እንደ አሕዛብ መሆን አለባቸው:: «ልዩነት የለምና፤ ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋል የእግዚአብሔርም ክብር ጐድሎአቸዋል» (ሮሜ 3:22-23):: የተሰጣቸውን ዕድል ወደ ክርስቶስ እንዲመራቸው በማድረግ ፈንታ (ሮሜ 9:1-5)፣ ክርስቶስን ምትክ አድርገው ተጠቀሙበት::

ነገር ግን የእግዚአብሔርን ጸጋ ካየን፣ የእስራኤል አለማመን የአሕዛብ መዳን ሆነ! የጳውሎስ የመጨረሻው ጥቅስ የተወሰደው ከኢሳይያስ 28:16 ነው:: ይህም ክርስቶስ የደኅንነት ዓለት መሆኑን ይናገራል [መዝ. (118):22 ይመልከቱ::] እግዚአብሔር ክርስቶስ የመሠረት ድንጋይ እንዲሆን ሰጠን:: ነገር ግን እስራኤል አልተቀበለውምና የማሰናከያ ዓለት ሆነ:: በዚህ ዓለት ላይ «በመቆም» ፋንታ እስራኤል ወደቀች (ሮሜ 11:11)፤ ነገር

ግን እንደምናየው ውድቀታቸው አሕዛብ በእግዚአብሔር ጸጋ እንዲድኑ አስቻለ።

ምን ዓይነት ጽድቅ እንደምንሻ መወሰን አለብን። ለመዳን በሥራችንና በባሕርያችን ነው የምንመካው ወይስ በክርስቶስ ብቻ ነው የምንታመነው? እግዚአብሔር ሰዎችን በአወላለዳቸው ወይም በባሕርያቸው ላይ ተመርኩዞ አያድናቸውም። «በእምነት አማካኝነት በጸጋው» (ኤፌ. 2:8-9) ያድናቸዋል። ጥያቄው ከእግዚአብሔር ምርጦች መካከል መሆን ያለመሆናችን አይደለም። ይህ በእግዚአብሔር ብቻ የሚታወቅ ምሥጢር ነው። እርሱ ደኅንነትን በእምነት ሰጥቶናል። ይህም ዕድል የተሰጠው «ለሚፈልግ» ሁሉ ነው (ራእ. 22:17)። በክርስቶስ ካመንን በኋላ ከተመረጡት መሃል ለመሆናችን ምስክርና ማስረጃ ይኖረናል (ኤፌ. 1:4-14፣ 1ኛ ተሰ. 1:1-10)። በመጀመሪያ ግን በእርሱ ታምነን የመንግሥተ ሰማያትን ዋስትና የሚሰጠውን ጽድቁን በእምነት መቀበል ያሻናል።

ከመለኮታዊ ሉዓላዊነት ከሰው ተጠያቂነት ጋር የተያያዙ ብዙ ምሥጢሮች መኖራቸውን ማንም አይክድም። ሁለቱም ከእግዚአብሔር ስለሚመጡና የዕቅዱም አካል ስለሆኑ፣ ከሁለቱ አንዱን እንድንመርጥ እግዚአብሔር ጠይቆን አያውቅም። እርስ በርሳቸው አይመካከሩም፣ ይተጋገዛሉ እንጂ። ሁለቱ ባንድ ላይ እንዴት እንደሚጓዙ አለመረዳታችን አብረው የመሄዳቸውን እውነት አይቃረንም። አንድ ሰው ቻርልስ ስፐርጀንን እንዴት አድርጎ መለኮታዊ ሉዓላዊነትንና የሰውን ተጠያቂነት እንደሚያስታርቅ ቢጠይቀው፣ «በጭራሽ ወዳጆችን ለማስታረቅ አልሞክርም!» ሲል መልሶለታል።

ነገር ግን የዚህ ምዕራፍ ጣልቃ መግባት ግልጽ ነው። ይህም የእስራኤል ክርስቶስን አለመቀበል የእግዚአብሔርን ታማኝነት አያስቀርም። ሮሜ 9 ሮሜ 8ን አይሽርም። እግዚአብሔር አሁንም ታማኝ፣ ጻድቅ፣ ትክክልና ቸር ሲሆን፣ ዓላማውንና ቃል ኪዳኑን እንደሚፈጽም ልንታመንበት እንችላለን።

# ሮሜ 10:1-21

ወንድሞች ሆይ፣ የልቤ በጎ ፈቃድና ስለ እስራኤል ወደ እግዚአብሔር ልመናዬ እንዲድኑ ነው። በእውቀት አይቅኑ እንጂ ለእግዚአብሔር እንዲቀኑ እመሰክርላቸዋለሁና። የእግዚአብሔርን ጽድቅ ሳያውቁ የራሳቸውንም ጽድቅ ሊያቆሙ ሲፈልጉ፣ ለእግዚአብሔር ጽድቅ አልተገዙም። የሚያምኑ ሁሉ ይጸድቁ ዘንድ ክርስቶስ የሕግ ፍጻሜ ነውና።

ሙሴ ከሕግ የሆነውን ጽድቅ የሚያደርገው ሰው በእርሱ በሕይወት እንዲኖር ጽፎአልና።

ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ በአፍህ ብትመሰክር እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህና፤ ሰው በልቡ አምኖ ይጸድቃልና በአፉም መስክሮ ይድናልና። መጽሐፍ፦ በእርሱ የሚያምን ሁሉ አያፍርም ይላልና። በአይሁዳዊና በግሪክ ሰው መካከል ልዩነት የለምና፤ አንዱ ጌታ የሁሉ ጌታ ነውና፣ ለሚጠሩትም ሁሉ ባለ ጠጋ ነው፤ የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናልና።

እንግዲህ ያላመኑበትን እንዴት አድርገው ይጠሩታል? ባልሰሙትስ እንዴት ያምናሉ? ያለ ሰባኪስ እንዴት ይሰማሉ? መልካሙን የምሥራች የሚያወሩ እግሮቻቸው እንዴት ያማሩ ናቸው ተብሎ እንደ ተጻፈ ካልተላኩ እንዴት ይሰብካሉ?

9

# የተዛባ ጽድቅ

የዚህ ምዕራፍ ጭብጥ እስራኤል አሁን እግዚአብሔርን የመግፋቷ ጉዳይ ነው፡፡ ጳውሎስ ከመለኮታዊ ሉዓላዊነት (ምዕራፍ 9) ወደ ሰው ተጠያቂነት ያመራል፡፡ ባለፈው ምዕራፍ (ሮሜ 9:30-33) የጽድቅን ጭብጥ ካስተዋወቀ በኋላ የእስራኤልን የእምቢታ ሦስት ገጽታዎች ያብራራል፡፡

## 1. ያልተቀበሉበት ምክንያት (10:1-13)

እስራኤል እንደ ሕዝብ የመሢሑን መምጣት በጉጉት እየጠበቁ ሊቀበሉት የተዘጋጁ እንደነበሩ አድርጋችሁ ታስቡ ይሆናል፡፡ ለዘመናት የብሉይ ኪዳን ትንቢቶችን ያውቃሉ፤ ሕጉንም ሲሠሩበት ኖረዋል፣ እርሱም ወደ ክርስቶስ እንዲመራቸው የተሰጠ እንደ «ሥራ መሪ» ነበር (ገላ. 3:24)፡፡ እግዚአብሔር ሕዝቡን ሊያዘጋጅ ፈልጓል፣ ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስ በመጣ ጊዜ አልተቀበሉትም፡፡ «የእርሱ ወደ ሆነው መጣ፣ የገዛ ወገኖቹም አልተቀበሉትም» (ዮሐንስ 1:11)፡፡ እርግጥ ነው፣ መምጣቱን ሲጠባበቁ የነበሩት ቅሬታዎች ነበሩ፣ ለምሳሌ ስምዖንና ሐና (ሉቃስ 2:25-38)፤ ነገር ግን አብዛኛው ሕዝብ ክርስቶስ ሲመጣ ዝግጁ አልነበረም፡፡

ይህን አሳዛኝ ነገር እንዴት መግለጽ እንችላለን? እስራኤላውያን መሢሑን ያልተቀበሉበትን ብዙ ምክንያቶች ጳውሎስ አቅርቧል፡፡

*ሀ) ደኅንነት እንደሚያስፈልጋቸው አልተሰማቸውም* ( 10:1) - ጳውሎስ ከሕዝቡ ጋር ተስማምቶ ወንጌልን ተቃውሞ ኢየሱስን እንደ አታላይ የቆጠረበት ጊዜ ነበር፡፡ እስራኤላውያን ደኅንነት የሚያስፈልጋቸው አይሁድ ሳይሆኑ አሕዛብ ብቻ እንደሆኑ ቆጠሩ፡፡ በብዙ ምሳሌዎቹ እነዚህን የተሳሳቱ አሳቦች ኢየሱስ አንድ በአንድ አንሥቶአቸዋል፡- ታላቁ ወንድም (ሉቃስ 15:11-32) እና ፈሪሳዊው (ሉቃስ 18:9-14) ሁለት ምሳሌዎች ናቸው፡፡ እስራኤላውያን ከሮም ነፃ የሚወጡበት የፖለቲካ አርነት

ቢፈልጉም፣ መንፈሳዊ ደኅንነት እንደሚያስፈልጋቸው ግን አልተረዱም ነበር::

*ለ) ለእግዚአብሔር ይቀኑ ነበር* (10:2)- እስራኤላውያን ከባቢሎን ምርኮ መልስ ከጣዖት አምልኮ ተፈውሰው ነበር:: በምኩራብና በቤተ መቅደስ እውነተኛው አምላክ ይመለክና ይገለግል ነበር:: እውነተኛው ሕግ በትምህርት ይሰጥ ነበር:: አይሁድ ከቅናታቸው የተነሣ «የእግዚአብሔርን ሕግ አሻሽለው» የራሳቸውን ትውፊት በማከል ከሕጉ ጋር እኩል አደረጓቸው:: ጳውሎስ ለሕግና ለትውፊት ቀናተኛ ነበር (የሐዋ. 26:1-11፤ ገላ. 1:13-14)

ቅናታቸው ግን በእውቀት ላይ የተመሠረተ አልነበረም፤ ብርሃን የሌለበት ሙቀት ነበረ:: ዛሬም ብዙ የሃይማኖት ሰዎች ተመሳሳይ ስሕተት ይፈጽማሉ:: መልካም ሥራቸውና መንፈሳዊ ድርጊታቸው ከመዳን እንደሚያርቋቸው ሳይገነዘቡ፣ ደኅንነት የሚሰጧቸው ይመስላቸዋል:: በእርግጥ አብዛኞዎቹ ቅንና የተሰጡ ናቸው፣ ነገር ግን ቅንነትና መሰጠት ነፍስን አያድንም:: «ይህም የሕግን ሥራ በመሥራት ሥጋ የለበሰ ሁሉ በእርሱ ፊት ስለማይጸድቅ ነው» (ሮሜ 3:20)::

*ሐ) ኩሩና ራሳቸውን ያጸደቁ ነበሩ* (10:3) - ስላልሰሙ ሳይሆን፣ ለመማር ባለመፍቀዳቸው፣ እስራኤላውያን ስለ እግዚአብሔር ጽድቅ የማያውቁ ነበሩ:: ዕድል ከማጣት የሚመጣ አለማወቅ ቢኖርም፣ እስራኤላውያን ግን ለመዳን በጣም ብዙ ዕድል ነበራቸው:: በራሳቸው እልከኝነት የመጣ እውነትን የመቃወም ባሕርይ ኖሮባቸው ለእግዚአብሔር አይገዙም:: በመልካም ሥራቸውና በጽድቃቸው ስለታመኑ፣ ኃጢአተኝነታቸውን አምነው አዳኙን አልታመኑበትም:: ጌታን ከመገናኘቱ በፊት ጳውሎስም ተመሳሳይ ስሕተት ፈጽሟል (ፊልጵ. 3:1-11)::

ሮበርት ሙሬይ ማክቼኒ የተባለ አንድ የእግዚአብሔር ሰው፣ መንፈሳዊ ጽሑፎችን ሲያድል በጥሩ ሁኔታ ልብስ ለለበሰች ሴት

ሰጣት፡፡ ሴትየዋም በንቀት አየችውና፣ «ጌታው፣ ማን እንደሆንኩ አታውቅም!» አለችው፡፡

እርሱም በእርጋታ፣ «የእኔ እመቤት፣ የፍርድ ቀን መጥቷል፣ በዚያ ቀን ማንነትዎ ዋጋ የለውም!» አላት፡፡

*መ) የራሳቸውን ሕግ አልተገነዘቡም* (10:4-13) – የአይሁድ እምነት የሚጠቁመው የመሢሑን መምጣት፣ መሥዋዕቶቻቸውን፣ ክህነትን፣ የቤተ መቅደስ አገልግሎትን፣ የሃይማኖት ሥርዓትን እና ቃል ኪዳንን ነው፡፡ ሕጋቸው ኃጢአተኛ መሆናቸውንና አዳኝ እንደሚያስፈልጋቸው ነግሮአቸዋል፡፡ ሕጉ ወደ ክርስቶስ እንዲያመጣቸው ከመጽሐፍ ይልቅ (ገላ. 3:24) ሕግን እያመለኩ አዳኙን አልተቀበሉትም፡፡ ሕግ መንገድ ጠቋሚ ምልክት ነበረ፡፡ ነገር ግን ወደ ፍጻሜ አያደርሳቸውም፡፡ ሕግ ጽድቅን ወደሚሰጥ አዳኝ ይመራል እንጂ ጽድቅን አይሰጥም፡፡

ክርስቶስ «የሕግ ፍጻሜ ነው»፣ በሞቱና በትንሣኤው ለሚያምኑበት የሕግን አገልግሎት ቋጭቷልና፡፡ ክርስቲያኖችን በተመለከተ ሕግ ተፈጽሟል፡፡ የሕግ ጽድቅ በአማኝ ውስጥ የተፈጸመው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ነው (ሮሜ 8:4)፤ ነገር ግን የሕግ ገዥነቱ አክትሟል (ኤፌ. 2:15 እና ቆላ. 2:14ን ይመልከቱ፡፡) «ከጸጋ በታች እንጂ ከሕግ በታች አይደላችሁምና» (ሮሜ 6:14)፡፡

አንባቢዎቹ የራሳቸውን ሕግ በቅጡ እንዳልተገነዘቡት ለማስረዳት ጳውሎስ ከብሉይ ኪዳን ጠቀሰላቸው፡፡ በዘሌዋውያን 18:5 ብትታዘዙ፣ ትኖራላችሁ የሚለውን የሕግን ዓላማ በመጥቀስ ጀመረ፡፡

«ታዝዘናል እኮ!» ብለው ይሟገታሉ፡፡

ጳ ሎስ ሲመልስም፣ «በውጫዊ ሥርዓት ታዝዛችሁ ይሆናል፣ ነገር ግን በልባችሁ አላመናችሁበትም» ብሎ ይመልሳል፡፡ ቀጥሎ ዘዳግም 30:12-14ን ጠቅሶ ለምንባቡ ጥልቅ

መንፈሳዊ ትርጓሜ ሰጠ። የሙሴ መልእክት ፍሬ ነገር «ትእዛዝ» (ዘዳግ. 30:11) ሲሆን፣ የሚያመለክተውም የእግዚአብሔርን ቃል ነው። በዚህ ክፍል እስራኤላውያን ሕግ እንደተብራራላቸውና ከአጠገባቸውም ስላልራቀ የእግዚአብሔርን ሕግ አለመታዘዝ እንደማይችሉ ገልጾላቸዋል። ሙሴ ሕግን ከልባቸው እንዲቀበሉ ገፋፍቷቸዋል (ዘዳግ. 5:29፤6:5-12፤ 13:3 እና 30:6 ይመልከቱ)። በዘዳግም አጽንኦት የተሰጠው ለውስጣዊ (መንፈሳዊው) ነገር ለልብ ነው እንጂ ለውጫዊው የመታዘዝ ሥርዓት አይደለም።

ጳውሎስ የዚህን መንፈሳዊ ተግሣጽ ግንዛቤ አስጨብጦናል። «የትእዛዛት» ወይም «ቃል» ትርጉሙ «ክርስቶስ፣ የእግዚአብሔር ቃል» እንደሆነ አድርጎ አይቶታል። ስለሆነም «ክርስቶስን» «በትእዛዛት» ፋንታ ተክቶታል። የእግዚአብሔር የደኅንነት መንገድ አስቸጋሪና የተወሳሰበ እንዳልሆነም ነግሮናል። ክርስቶስን ለማግኘት ወደ መንግሥተ ሰማይ ወይም ወደ ሙታን መንደር መሄድ የለብንም። እርሱ ያለው አጠገባችን ነው። በሌላ አባባል የክርስቶስን ወንጌል- የእምነትን ቃል ማንም ሰው ማግኘ ት ይችላል። ኃጢአተኛው ለመዳን አስቸጋሪ ሥራ መሥራት የለበትም። ማድረግ የሚገባው በክርስቶስ ማመን ብቻ ነው። በአይሁድ ከናፍርት ላይ ያለው ቃል የእምነት ቃል ነው። የሚያነቡትና የሚደግሙት ሕግ ወደ ክርስቶስ ያመለክታል።

በዚህ ስፍራ ጳውሎስ ከኢሳይያስ 28:16 ደኅንነት *በእምነት* መሆኑን ለማሳየት ጠቅሷል። «በእርሱ የሚያምን አያፍርም።» ይህንን ቃል በሮሜ 9:33 ላይ ቀደም ብሎ ጠቅሶታል። በሮሜ 10:9-10 ላይ ደኅንነት *በእምነት* መሆኑን በግልጽ አስቀምጧል- በልባችን አምነን የእግዚአብሔርን ጽድቅ ተቀብለን የክርስቶስን ጌትነት በግልጽ እና ሳናፍር እንናገራለን።

የጳውሎስ የመጨረሻው ጥቅስ የተወሰደው ከኢዩኤል 2:32 ሲሆን፣ ደኅንነት ለሰው ሁሉ እንደሆነ ይናገራል:- «የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል።» በፍርድ «ልዩነት እንደሌለ» ጳውሎስ

አረጋግጧል (ሮሜ 3:20-23)። አሁን ደግሞ በደኅንነት «ልዩነት እንደሌለ» ያረጋግጣል። አንድ አይሁድ በሕግ በኩል ልዩ ጽድቅ ከማግኘት ይልቅ እንደኮነናቸው አሕዛብ ኃጢአተኛ ሆኖ ተቆጠረ።

ሙሉው ክፍል የሚያተኩረው «የሕግን ጽድቅ» እና «የእምነት ጽድቅ» በሚመለከት ነው። ንጽጽሮቹ እንደሚከተለው ተጠቃልለው ቀርበዋል።

| *የሕግ ጽድቅ* | *የእምነት ጽድቅ* |
|---|---|
| ለአይሁድ ብቻ | «ለማንም» |
| በሥራ የተመሠረተ | በእምነት ብቻ የሚገኝ |
| የራስ ጽድቅ አያድንም | የእግዚአብሔር ጽድቅ ደኅንነት ያስገኛል |
| ጌታን ለመታዘዝ ይጥራል | ጌታን ይጣራል |
| ወደ ትዕቢት ይገፋል | እግዚአብሔርን ያከብራል |

ጳውሎስ እስራኤል የእግዚአብሔርን ጽድቅ የገፉችባቸውን ምክንያቶች ካብራራ በኋላ፣ ወደሚቀጥለው የርእሱ ገጽታ ያመራል።

## 2. ላለመቀበላቸው መፍትሔ (10:14-17)

ይህ ምንባብ ለቤተ ክርስቲያን የሚስዮናዊ መርሐ ግብር ሲውል ይታያል፣ ትክክልም ነው፣ በቀዳሚነት ግን ተፈጻሚነቱ ለእስራኤል ሕዝብ ነው። የማያምኑ አይሁድ ሊድኑ የሚችሉበት ብቸኛ መንገድ የጌታን ስም በመጥራት ነው። ከመጥራታቸው በፊት ግን ሊያምኑ ያስፈልጋቸዋል። ለአይሁድ የደኅንነት መንገድ የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑንና የእስራኤል መሢሕ መሆኑን ማመን ማለት ነው። እንዲሁም በመሢሑ ሞትና ትንሣኤ ማመን ማለት ነው (ሮሜ 9:9-10)። ነገር ግን በሰሚው ሰው ልብ ውስጥ እምነት የሚፈጥረው እርሱ ስለሆነ ቃሉን መስማት አለባቸው (ቁ. 17)።

ይህ ከሆነ የቃሉ የምሥራች መላክ አለበት፡፡ ቃሉን የሚልከው ደግሞ ጌታ ነው፡፡ በዚህ ነጥብ ጳውሎስ ቃሉን ለእግዚአብሔር ሲሰብክ እንዴት እንደ ተጠራ እያስታወሰ ሳይሆን አይቀርም (የሐዋ. ሥራ 13:1-3)፡፡

በሮሜ 10:15 ላይ የተጠቀሱት ጥቅሶች ከኢሳይያስ 52:7 እና ናሆም 1:15 ላይ ይገኛሉ፡፡ ከናሆም የተጠቀሰው ስለ አሦር መንግሥት መደምሰስ የሚናገር ሲሆን፣ እነርሱ በአይሁድ የተጠሉ ጠላቶቻቸው ነበሩ፡፡ ዋና ከተማቸው ነነዌ ስትሆን፣ ከናሆም 150 ዓመታት በፊት እግዚአብሔር ዮናስን የላከበት ክፋት የተሞላች ከተማ ናት፡፡ እግዚአብሔር በትዕግሥት ነነዌን የጎበኛት ሲሆን፣ አሁን ግን የፍርድ መምጫው ደርሷል፡፡ መልእክተኛ ወደ አይሁድ ይዞ የመጣው ይህንን «የምሥራች» ነው፡፡ እግሮቹን የተዋቡ ያደረገለትም የምሥራቹ ነው፡፡

ኢሳይያስ ይህን ትንቢት የተጠቀመበት ክርስቶስ ተመልሶ የክብር መንግሥቱን ሲመሠርት («አምላክሽ ነግሦአል» ኢሳ. 52:7-10ን አንብቡ፡፡) እንደሚፈጸም በማሰብ ነው፡፡ እግሮቹ የተዋቡለት መልእክተኛ እግዚአብሔር የእስራኤልን ጠላት እንደ መታና መሢሑ ከኢየሩሳሌም ሆኖ እንደሚገዛ ያውጃል፡፡

ነገር ግን ጳውሎስ ይህን ክፍል ጠቅሶ ለአሁን ጊዜ ተጠቀመበት:- መልእክተኛው የወንጌል መልእክተኛ ሲሆን፣ የምሥራቹን ዛሬ ወደ እስራኤል ያደርሳል፡፡ «ሰላም» የተባለው «ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም» (ሮሜ 5:1) ሲሆን፣ ይህን ሰላም ክርስቶስ በአይሁድና በአሕዛብ መካከል የፈጠረው አካል በሆነችው አንድ ቤተ ክርስቲያን አማካኝነት ነው (ኤፌ. 2:13-17)፡፡ ለእስራኤል ክርስቶስን አለመቀበል መፍትሔው የወንጌልን ቃል ሰምቶ በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ነው፡፡

የጳውሎስ ቀጣዩ ጥቅስ የተወሰደው ከኢሳይያስ 53:31፣ ሲሆን፣ ሁሉም የእግዚአብሔርን ቃል የሚቀበሉት እስራኤላውያን ያለመሆናቸውን ያረጋግጣል፡፡ ይህ ጥቅስ በብሉይ ኪዳን ስለ መሢሑ ከተነገሩ ትንቢቶች መካከል አንዱ ነው፡፡

የአይሁድ ሊቃውንት ኢሳይያስ 53 ከመሢሑ ይልቅ ለእስራኤል እንደተነገረ ያስባሉ። ነገር ግን ቀደምት መምህራን የሕዝቡን ኃጢአት ተሸክሞ ስለ ሕዝቡ ኃጢአት የሚሠቃየውን መሢሕ እንደሚያመለክት ነው ያዩት (የሐዋ. 8:26-40)። በኢሳይያስ ዘመን የነበሩ ሰዎች ልክ እንደ ዘመናችን ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል አያምኑም ነበር። ዮሐ. 12:37- 41 ኢሳይያስ 53:1ን ጠቅሶ ሕዝቡ የክርስቶስን ተአምራት አይተው ለማመን እምቢ እንዳሉ ለመግለጽ ተጠቅሞበታል። ስለማያምኑ፣ ፍርድ በላያቸው መጥቷልና ማመንም አይችሉም።

በክርስቶስ ማመን የእምነት ብቻ ሳይሆን፣ የመታዘዝም ጉዳይ መሆኑን አስተውሉ። በክርስቶስ አለማመን እግዚአብሔርን አለመታዘዝ ነው። እግዚአብሔር «በየቦታቸው ንስሐ ይገቡ ዘንድ ሰዎችን ያዛል» (የሐዋ. ሥራ 17:30)። ሮሜ 6:17 «እምነት»ና «መታዘዝን» በእኩልነት ፈርጇቸዋል። እውነተኛ እምነት ፈቃድን ነክቶ የተለወጠ ሕይወትን ያስገኛል።

የቤተ ክርስቲያንን የወንጌል ሥርጭት አገልግሎት ማሳነስ የለብንም። ይህ ምንባብ በቅድሚያ ከእስራኤላውያን ጋር የተዛመደ ቢሆንም፣ በዓለም ዙሪያ ሁሉ ለጠፉት ነፍሳት የሚሆን ነው። የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ስም እስካልጠሩ ድረስ አይድኑም። ካላመኑ ደግሞ መጥራት አይችሉም። እምነት በመስማት ነው። ስለዚህ መልእክቱን መስማት አለባቸው። እንዴት ይሰማሉ? መልእክተኛ መልእክት ይዞ ወደ እነርሱ መሄድ አለበት። ይህ ደግሞ እግዚአብሔር መልእክተኛን ጠርቶ መልእክተኛው መላክ አለበት ማለት ነው። ያማሩ እግሮች ያሉት መልእክተኛ መሆን እንዴት ያለ መታደል ነው!

ይህንን ምዕራፍ በመጻፍ ላይ ሳለሁ፣ ስልኬ አቃጨለና ከቤተ ክርስቲያናችን ነጋዴዎች አንዱ አንድ ሰው ወደ ክርስቶስ መምጣቱን ነገረኝ። የደወለልን ሰው ከጥቂት ዓመታት በፊት የጎላ መንፈሳዊ ችግር ስለነበረበት ልረዳው ችዬአለሁ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በቢሮው ከሚሠሩት ሰዎች ጭምር ብዙ ሰዎችን ወደ ክርስቶስ መርቷል። የደወለበት ምክንያት ግን ክርስቲያን ጓደኛው

አንድ ወዳጁን ወደ ጌታ የመራበትን ተአምር ለመንገር ሲሆን፣ ይህም የምስክርነት ሰንሰለት ለሦስት ዓመታት ያህል እንደቀጠለ ይገኛል:: ጓደኛዬ ያማሩ እግሮች አሉትና በሄደበት ሁሉ የወንጌል የምሥራች ለሰዎች ይናገራል::

አንዳንዶቻችን ይህንን የምሥራች ባለንበት ቦታ ስናሰራጭ፣ ሌሎች ደግሞ ወደ ሩቅ ስፍራ ለማድረስ ይላካሉ:: የተዘጉ ጥቂት በሮች ቢኖሩም፣ ከዚህ በፊት ያልነበሩ ብዙ የወንጌል በሮች ዛሬ ተከፍተዋል:: የምንሠራባቸው የተሻሉ መሣሪያዎች ደግሞ አሉ:: የቅርብ ወዳጄና የሚስዮናዊነት አስተማሪዬ የሆነው ዶክተር ኢ. መየርስ ሃሪስን፣ ቤተ ክርስቲያን ለምን ወንጌል መልእክተኞችን መላክ እንዳለባት አራት ምክንያቶችን ያቀርባሉ:- (1) *ከላይ የተሰጠን ትእዛዝ* - «ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ» (ማር. 16:15)፤ (2) *ከሥር ያለው ጩኸት* - «ወደ አባቴ ቤት እንድትሰደው» (ሉቃስ 16:27)፤ (3) *በውጭ የሚሰማው ጥሪ* - «ተሻገርና እርዳን» (የሐዋ. ሥራ 16:9)፤ እና (4) *በውስጣችን ያለው ግድ ስለሚለን* - «የክርስቶስ ፍቅር ግድ ይለናል» (2ኛ ቆሮ. 5:14)::

ጳውሎስ ያቀረበው እስራኤል ደኅንነትን የተጋፈጠችበት ሁኔታ ሦስተኛው ገጽታ የሚከተለው ነው::

## 3. ያለ መቀበላቸው ውጤት (10:18-21)

ሦስት ውጤቶች ያሉ ሲሆን፣ እያንዳንዳቸው በብሉይ ኪዳን ማጣቀሻዎች የተደገፉ ናቸው::

*ሀ) እስራኤል በደለኛ ናት* (10:18)- ምናልባት አንድ ሰው ጳውሎስ እንዲህ ብሎ ይሞግተው ይሆናል:- «እስራኤል መስማቷን በምን ታውቃለህ?» ምላሹም መዝሙር 19:4 ሲሆን፣ ጥቅሱ አጽንኦት የሰጠው እግዚአብሔር ራሱን በዓለም ላይ ስለመግለጡ ነው:: እግዚአብሔር ራሱን በፍጥረት ውስጥ ገልጧል (መዝ. 19:1-6)፣ እንዲሁም በቃሉ ውስጥ ገልጧል (መዝ. 19:7-11):: «የፍጥረት መጽሐፍ» እና «የመገለጥ መጽሐፍ» አብረው የሚሄዱ ሲሆን፣ ሁለቱም የእግዚአብሔርን ክብር ያውጃሉ:: እስራኤል እነዚህን መጻሕፍት በማግኘቷ

ተጠቅማለች:: በዚህም እግዚአብሔር በፍጥረት ውስጥ ሲሠራ አይታለች:: የተጻፈውንም የእግዚአብሔር ቃል ተቀብላለች:: እስራኤል ሰምታለች፣ ነገር ግን አላስተዋለችም:: ኢየሱስ አንዳንድ ጊዜ ለሕዝቡ፣ «የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ!» ማለቱ አያስደንቅም::

*ለ) መልእክቱ ወደ አሕዛብ ሄደ (10:19-20)* – እንዴት የሚደንቅ ጸጋ ነው! እስራኤል መሢሑን አልቀበልም ስትል፣ እግዚአብሔር አሕዛብ ይድኑ ዘንድ ወንጌል ላከላቸው:: ይህም ሙሴ በዘዳግም 32:21 አስቀድሞ የተናገረው ነው:: ይህንን እውነት ጳውሎስ ከዚህ በፊት በሮሜ 9:22-26 ላይ ጠቅሶታል:: እግዚአብሔር ወንጌልን ለአሕዛብ የላከበት አንዱ ምክንያት፣ አይሁድን እንዲያስቀኑ ብሎ ነው (ሮሜ 10:19፤ 11:11):: ወንጌል ለአይሁድም ሆነ ለአሕዛብ የጸጋ አዋጅ ነው:: ኢሳይያስም እግዚአብሔር አሕዛብን እንደሚያድን ተንብዮአል (ኢሳ. 65:1)::

አዲስ ኪዳንን ስታጠኑት፣ «በመጀመሪያ ለአይሁድ» የሚለው የዘመቻው መርህ እንደሆነ ታገኛላችሁ:: ኢየሱስ አገልግሎቱን የጀመረው በአይሁድ ነው:: ደቀ መዛሙርቱን ለመጀመሪያ ጊዜ ለአገልግሎት ሲልካቸው ለአሕዛብና ለሳምራውያን እንዳይሰበኩ ነግሯቸዋል (ማቴ. 10:1-6):: ከትንሣኤው በኋላ ግን በኢየሩሳሌም ቆይተው አገልግሎታቸውን እንዲጀምሩ አዘዛቸው (ሉቃስ 24:46-49፤ የሐዋ. 1:8):: በሐዋርያት ሥራ የመጀመሪያዎቹ 7 ምዕራፎች አገልግሎታቸው ለአይሁድ ወይም ደግሞ ወደ ይሁዲነት ለገቡ አሕዛብ ብቻ ነበረ:: ነገር ግን ሕዝቡ (አይሁድ) እስጢፋኖስን በድንጋይ ወግረው ከገደሉት በኋላ፣ ስደት ሲነሣ እግዚአብሔር ወንጌልን ለሳምራውያን (የሐዋ. 8:1-8)፣ ከዚያ በኋላ ለአሕዛብ ላከላቸው (የሐዋ. 10)::

ጴጥሮስ ወንጌልን ይዞ ወደ አሕዛብ በሄደበት ጊዜ አይሁድ አማኞች ደንግጠው ነበር (ዮሐ. 11:1-18):: ነገር ግን አይሁድም ሆኑ አሕዛብ እግዚአብሔር በክርስቶስ በማመን እንደሚድኑ ያስረዳውና የላከው ራሱ መሆኑን ገለጸላቸው:: ነገር ግን የወግ አጥባቂዎቹ አይሁድ ተቃውሞ በማየሉ በጉዳዩ ላይ ለመወያየት

ስብሰባ መቀመጥ ነበረባቸው፡፡ የጉባኤው ዘገባ በሐዋርያት ሥራ 15 ላይ ይገኛል፡፡ በጉባኤው መዝጊያ ላይ አይሁድም ሆኑ አሕዛብ የሚድኑት በክርስቶስ በማመን በመሆኑ፣ አንድ አሕዛብ ክርስቲያን ከመሆኑ በፊት ወደ ይሁዲነት መግባት እንደማያስፈልገው ገለጹ፡፡

*ሐ) እግዚአብሔር አሁንም የሕዝቡን መመለስ ይናፍቃል* (10:21) – ይህ ጥቅስ የተወሰደው ከኢሳይያስ 65:2 ላይ ነው፡፡ «ቀኑን ሁሉ» የሚለው እስከ አሁን ድረስ ያለውን «የመዳን ቀን» ወይም የምንኖርበትን የጸጋ ዘመን ያመለክታል፡፡ እስራኤል እንደ ሕዝብ ስትለይ፣ አንዳንድ አይሁድ ድነዋል፣ እየዳኑም ነው፡፡ «ቀኑን ሁሉ» የሚለው ሐረግ ጳውሎስ እሥረኛ ሆኖ በሮም ያሉትን አይሁድ ስላገለገለበት ሁኔታ እንድናስብ ያደርገናል፡፡ «ከጥዋት ጀምሮ እስከ ማታ» ጳውሎስ ቅዱሳት መጻሕፍትን እያብራራ ኢየሱስ መሢሕ መሆኑን በመግለጽ ሊያሳምናቸው ጥረት አድርጓል (የሐዋ. 28:23)፡፡ እግዚአብሔር የማይታዘዙት ሕዝቡ ወደ እርሱ እንዲመለሱ በጳውሎስ አማካይነት ቀኑን ሁሉ የፍቅር እጆቹን ዘርግቶላቸዋል፡፡ እግዚአብሔር አሕዛብን መውደዱ ለአይሁድ ያለውን ፍቅሩን አልቀነሰበትም፡፡

እግዚአብሔር እኛ የምሥራቹን ለአይሁድና ለአሕዛብ እንድናሰራጭ ይፈልጋል፡፡ የጳውሎስን እጆችና እግሮች እንደተጠቀመ ሁሉ በእኛም መጠቀም ይችላል፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ኢየሩሳሌም አልቅሶ በእጆቹ ሕዝቡን ሊሰበስብ ናፍቋል፡፡ ይልቁንም እነዚያን እጆቹን ለአይሁድም ለአሕዛብ በሞተበት በፈቃደኝነት በመስቀል ላይ ዘርግቶአቸዋል፡፡ እግዚአብሔር ታጋሽ ነው፡፡ «ነገር ግን ሁሉ ወደ ንስሐ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፉ ወዶ ስለ እናንተ ይታገሣል» (2ኛ ጴጥ. 3:9)፡፡

እግዚአብሔር ለእስራኤል ያለው ትዕግሥት ይሟጠጥ ይሆን? ይህ ሕዝብ የወደፊት ተስፋ አለው? የሚቀጥለው ምዕራፍ እንደሚያሳይን ከሆነ፣ አዎን አለው፡፡

# ሮሜ 11:1-36

እንግዲህ፡- እግዚአብሔር ሕዝቡን ጣላቸውን? እላለሁ:: አይደለም፤ እኔ ደግሞ እስራኤላዊና ከአብርሃም ዘር ከብንያምም ወገን ነኝና:: እግዚአብሔር አስቀድሞ ያወቃቸውን ሕዝብ አልጣላቸውም:: መጽሐፍ ስለ ኤልያስ በተጻፈው የሚለውን፣ በእግዚአብሔር ፊት እስራኤልን እንዴት እንደሚከስ፣ አታውቁምን? ጌታ ሆይ፣ ነቢያትህን ገደሉ፣ መሠዊያዎችህንም አፈረሱ፤ እኔም ብቻዬን ቀረሁ፣ ነፍሴንም ይሹአታል:: ነገር ግን አምላካዊ መልስ ምን አለው? ለበአል ያልሰገዱትን ሰባት ሺህ ሰዎች ለእኔ አስቀርቼአለሁ:: (ሮሜ 11:1-4)

እንግዲህ፡- እኔ እንድገባ ቅርንጫፎች ተሰበሩ ትል ይሆናል:: መልካም፤ እነርሱ ከአለማመን የተነሣ ተሰበሩ አንተም ከእምነት የተነሣ ቆመሃል:: ፍራ እንጂ የትዕቢትን ነገር አታስብ:: እግዚአብሔር እንደ ተፈጠሩት ለነበሩት ቅርንጫፎች የራራላቸው ካልሆነ ለአንተ ደግሞ አይራራልህምና:: እንግዲህ የእግዚአብሔርን ቸርነትና ጭከና ተመልከት፤ ጭከናው በወደቁት ላይ ነው፣ በቸርነቱ ግን ጸንተህ ብትኖር የእግዚአብሔር ቸርነት በአንተ ላይ ነው፤ ያለዚያ አንተ ደግሞ ትቈረጣለህ:: እነዚያም ደግሞ በአለማመናቸው ጸንተው ባይኖሩ በዛፉ ውስጥ ይገባሉ፤ እግዚአብሔር መልሶ ሊያገባቸው ይችላልና:: አንተ በፍጥረቱ የበረሃ ከነበረ ወይራ ተቈርጠህ እንደ ፍጥረትህ ሳትሆን በመልካም ወይራ ከገባህ፣ ይልቁንስ እነዚያ በፍጥረታቸው ያሉት ቅርንጫፎች በራሳቸው ወይራ እንዴት አይገቡም?

ወንድሞች ሆይ፣ ልባሞች የሆናችሁ እንዳይመስላችሁ ይህን ምሥጢር ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ፤ የአሕዛብ ሙላት እስኪገባ ድረስ ድንዛዜ በእስራኤል በአንዳንድ በኩል ሆነባቸው፤(ሮሜ 11:19-25)

# 10

# እግዚአብሔርና ያልተቋጨው የእስራኤል ነገር

ሰዎች ለዘመናት የእስራኤል ጉዳይ እንቆቅልሽ ሆኖባቸዋል:: የሮማውያን መንግሥት ለአይሁድ እምነት እውቅና ቢሰጥም፣ ነገር ግን ያን «ክፉ የሃይማኖት ክፍል» ይለው ነበር:: ታዋቂው የታሪክ ተመራማሪ አርኖልድ ቶይንቢ እስራኤልን «ከቅሪተ አካል ሥልጣኔ» ጋር ፈርጇታል:: ስለ እስራኤል ምን ማለት እንደሚችል ግራ ገብቶት ነበር:: በአንዳንድ ምክንያቶች የእስራኤል ታሪክ ለእርሱ የታሪክ ዘገባ አመቺ አልነበረም::

ጳውሎስ በሮሜ 11 ላይ እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር ነገሩን እንዳልጨረሰ ለማሳየት ሙሉ ምዕራፉን ተጠቅሟል:: ይህንን ምዕራፍ ለዘመናችን ቤተ ክርስቲያን ልናውለው አይገባም፣ ምክንያቱም ጳውሎስ የእስራኤልን ሕዝብ የወደፊት ዕጣ ፈንታ እያብራራ ነው:: አይሁድ በእግዚአብሔር ዕቅድ ስፍራ እንዳላቸው ማስረጃ ለመስጠት አምስት ምስክሮችን ጠርቷል

## 1. ጳውሎስ ራሱ (11:1)

«እግዚአብሔር ሕዝቡን ጣላቸውን? እላለሁ:: አይደለም፤ እኔ ደግሞ እስራኤላዊ ነኝና::» እግዚአብሔር ሕዝቡን ቢጥላቸው ኖሮ፣ የሐዋርያው የጳውሎስን መለወጥ የምንገልጽበት ምንም መንገድ አይኖርም ነበር::

የመለወጡ እውነታ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ሦስት ጊዜ መቅረቡ እጅግ ጠቃሚ ነው (ምዕራፍ 9:22፣26):: ሉቃስ በእነዚህ ምዕራፎች ደጋግሞ የጻፈው የጳውሎስን ታሪክ ለማግነን አይደለም:: ሦስት ጊዜ ተደጋግሞ የተጻፈው የጳውሎስ መለወጥ ለወደፊት የእስራኤል ሕዝብ መመለስ እንደ ምሳሌ ሆኖ እንዲያገለግል ነው:: ጳውሎስ ራሱን፣ «እንደ ጭንጋፍ ለምሆን» ብሎ ጠርቷል (1ኛ ጴጥ. 15:8):: በ1ኛ ጢሞቴዎስ 1:16 እግዚአብሔር እንዳዳነው ለመግለጽ የሚከተለውን ጽፏል፣ «የዘላለምን ሕይወት ለማግኘት በእርሱ ያምኑ ዘንድ ላላቸው

ሰዎች ምሳሌ እንድሆን፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ዋና በምሆን በእኔ ላይ ትዕግሥቱን ሁሉ ያሳይ ዘንድ፣ ምሕረትን አገኘሁ::»

የጳውሎስ የመለወጡ ትረካ ዛሬ እኛ ከምንለማመደው ደኅንነት ጋር ትንሽም ቢሆን ምስስል አለው:: ማንኛችንም ክርስቶስን በክብሩ አላየነውም፣ ከመንግሥተ ሰማይ ሲናገርም ድምፁን አልሰማንም:: በሰማይ ብርሃኑ አልታወርንም፤በመሬት ላይም አልተዘረጋንም:: ታዲያ የጳውሎስ መለወጥ «ሞዴል» የሚሆነን እንዴት ነው? ኢየሱስ ክርስቶስ መንግሥቱን ሊያጸና ሲመለስ እስራኤል እንዴት እንደምትድን የሚያሳይ ምሳሌ ነው:: የእስራኤልን የወደፊት መታደስና ደኅንነት በተመለከተ በዘካርያስ 12:10-13:1 ላይ በዝርዝር ተጽፏል:: ሲመለስ ሕዝብ ሁሉ ያዩታል (ዘካ. 14:4፤ የሐዋ. 1:11፤ ራእ. 1:7)፣ መሢሐቸውም ለመሆኑ እውቅና ይሰጡታል፣ ንስሐም ገብተው ይቀበሉታል:: ይህም የጠርሴሱ ጳውሎስ በደማስቆ መንገድ ክርስቲያኖችን ሲያሳድድ ካጋጠመው ተሞክሮ ጋር ተመሳሳይ ይሆናል (የሐዋ. 9)::

ጳውሎስ ራሱን እንደ መጀመሪያ ምስክር የቆጠረው በዚህ ነው:: የእርሱ መዳን እስራኤል ተስፋ እንዳላት ማስረጃ አይሆንም:: ይልቁንም፣ ጠቃሚው ነገር እርሱ የዳነበት መንገድ ነው::

## 2. ነቢዩ ኤልያስ (11:2-10)

እስራኤላውያን በእግዚአብሔር የተመረጡ ሕዝብ ናቸው፤ አስቀድሞ አውቋቸዋል፣ ወይም መርጧቸዋልና፣ የእርሱ ናቸው:: አብዛኛዎቹ እስራኤላውያን ክርስቶስን ባለመቀበላቸው እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ያለው ግንኙነት ለመጠናቀቁ ማስረጃ አይሆንም:: ኤልያስ በዘመኑ ሕዝቡ ሁሉ ከእግዚአብሔር እንደተለዩ አስቦ ነበር (1ኛ ነገ. 19ን አንብቡ):: ነገር ግን የእውነተኛ አማኞች ቅሬታዎች እንደነበሩ ኤልያስ ተረዳ:: የቀረው ታማኝ አይሁድ እርሱ ብቻ እንደሆነ አሰበ፤ ነገር ግን 7000 የሚሆኑ ታማኝ አይሁዶች እንደነበሩ ተገነዘበ::

ጳውሎስ ስለ እነዚህ «ቅሬታዎች» ከኢሳይያስ 10:22-23 በመውሰድ በሮሜ 9:27 ላይ ጠቅሶታል:: ድፍን የእስራኤል ሕዝብ ለጌታ ታማኝ የሆነበት ጊዜ አልነበረም:: እግዚአብሔር በአብርሃም የተፈጥሮ ልጆቹና በመንፈስ ልጆቹ በሆኑት መካከል ልዩነትን ያደርጋል (ሮሜ 2:25-29):: አይሁድ ተገርዘው በኪዳን መካፈላቸው የደኅንነታቸው ዋስትና አይሆንም:: እንደ አብርሃም የእግዚአብሔርን ጽድቅ ለመቀበል በእርሱ ሊያምኑ ይገባቸዋል (ሮሜ 4:1-5)::

እነዚህ ቅሬታዎች የዳኑት በጸጋ እንጂ በሥራ አለመሆኑን አስተውሉ (11:5-6):: ከሮሜ 9:30-33 ጋር ያለውን ተመሳሳይነት ተመልከቱ:: አንዱ ሌላውን ስለሚሽረው ጸጋና ሥራን መቀላቀል አይቻልም:: የእስራኤል ትልቁ መሻት ሁልጊዜ በመልካም ሥራ እግዚአብሔርን ለማስደሰት መሞከር ነበር (ሮሜ 9:30-10:4):: ልክ ዛሬ ራሳቸውን ጻድቅ አድርገው በዘመናችን እንደሚቆጥሩት፣ ሰዎች ሕዝቡ ለክርስቶስ ጽድቅ ራሳቸውን ላለማስገዛት ዓመፁ::

ቅሬታዎቹ ከዳኑ፣ እግዚአብሔር ሕዝቡን እንዳልተወ ማስረጃ ሲሆን፣ ታዲያ ሌሎቹስ ምን ሆኑ? ልባቸውን አደንድነው ነበር («ታውረው» ነበር የሚለው የተሻለ ትርጉም ነው (ቁ. 7):: እውነትን ባለመቀበላቸው፣ እንደ ፈርዖን ልባቸው በድንዳኔ ተሞላ:: ጳውሎስ አነጋገሩን ለመደገፍ ኢሳይያስ 29:10ን፣ ዘዳግም 29:4ን ጠቀሰ:: አረማዊ ገዥ በእግዚአብሔር ላይ ልቡን ማደንደኑን ብናስብም፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ ግን እንዲህ ያደርጋል ብለን አናስብም::

ቁጥር 9 እና 10 የተወሰዱት ከመዝሙር (69):22-23 ላይ ነው:: ይህ መዝሙር ስለ መሢሕ ከሚናገሩት ምንባቦች መሃል አንዱ ሲሆን፣ በአዲስ ኪዳንም ብዙ ጊዜ ተጠቅሷል:: በተለይ ቁጥር 4፣9፣21 እና 22ን አስተውሉ:: «ማዕዳቸው ወጥመድና አሽክላ» ማለት በረከታቸው ወደ ሸክምና ፍርድ ተለወጠባቸው:: ለእስራኤል የሆነባቸው ይኸው ነው:- መንፈሳዊ በረከቶቻቸው

ወደ ክርስቶስ ሊመሯቸው ሲገባ፣ ከክርስቶስ የሚያርቁ ወጥመድ ሆኑባቸው:: ሃይማኖታዊ ሥርዓቶቻቸው ለእውነተኛው የደኅንነት ሕይወት ምትክ ሆኑባቸው:: ዛሬም ቢሆን ሰዎች በሃይማኖት ልምምዶችና ሥርዓቶች ላይ ተደግፈው በእነዚህ ሁሉ የተገለጠውን ክርስቶስን ማመን ሲሳናቸው ተመሳሳይ ስሕተት መፈጸማቸው የአደባባይ እውነት ነው::

ጳውሎስ በግልጽ እንዳስቀመጠው የእስራኤል ልብ ማደንደን ፍጻሜ ወይም የመጨረሻቸው አለመሆኑ፣ እግዚአብሔር አሁንም ለእስራኤል ተስፋ እንዳለው ማስረጃ ነው:: «የአሕዛብ ሙላት እስኪገባ ድረስ ድንዛዜ በእስራኤል በአንዳንድ በኩል ሆነባቸው» (ሮሜ 11:25):: በኤልያስ ዘመን እንደሆነው፣ ዛሬም የሚያምኑ የአይሁድ ቅሬታዎች መኖራቸው፣ እግዚአብሔር አሁንም ለሕዝቡ ዕቅድ እንዳለው ማስረጃ ነው:: ጳውሎስ እንደ ኤልያስ «እኔ ብቻዬን ቀርቻለሁ!» ብሎ የኤልያስን ስሕተት አልደገመም:: በእግዚአብሔር ያመኑ የእስራኤል ቅሬታዎች እንዳሉ አውቋል::

## 3. አሕዛብ (11:11-15)

በሮሜ 2:1-3 ላይ ጳውሎስ በአሕዛብ በመጠቀም የአይሁድን በደለኝነት ያስረዳ ሲሆን፣ አሁን ደግሞ የወደፊቱን የእስራኤልን መታደስ ለማስረዳት በአሕዛብ ተጠቅሟል:: ሥነ አመክንዮአዊው አቀራረቡም የሚያስገርም ነው:: አይሁድ ወንጌልን ባልተቀበሉ ጊዜ፣ እግዚአብሔር ወደ አሕዛብ ላከው፣ እነርሱም አምነው ዳኑ:: በእስራኤል ሦስት አሳዛኝ ክስተቶች ተፈጸሙ:- ሕዝቡ *ወደቀ* (ቁ. 11)፣ *በደለኛ ሆነ* (ቁ.12፣ መሸነፋቸው)፣ በመጨረሻም *ተጣሉ* (ቁ. 15):: ከእነዚህ ቃላት የትኛውም ስለ እስራኤል የመጨረሻ ፍርድ አይናገርም:: የሚገርመው ነገር በእስራኤል መጣል ወንጌል ወደ አሕዛብ መምጣቱ ነው:: እግዚአብሔር አሕዛብ እንደሚድኑ ተናግሮ ነበር (ሮሜ 9:25-26)፣ ቃሉንም ጠብቋል:: ለአይሁዶችስ የገባውን ቃል አይጠብቅምን?

በደንብ ማወቅ ያለብን በብሉይ ኪዳን ለአሕዛብ የተሰጡት ቃሎች በሙሉ ከእስራኤል «ማንሠራራት» ማለትም ወደ መንግሥቷ ከመግባቷ ጋር የተያያዙ ናቸው:: ኢሳይያስ 11 እና 60 ላይ ያሉት ትንቢቶች አሕዛብ የእስራኤልን መንግሥት እንደሚካፈሉት ግልጽ አድርገዋል:: ነገር ግን እስራኤል «አልቆመችም»፣ *ወደቀች እንጂ!* ታዲያ እግዚአብሔር አሕዛብን ምን ያድርጋቸው? እግዚአብሔር መንገድን ቀየሰ:: ይኸውም ቤተ ክርስቲያንን መትከሉ ነው:: ያመኑ አይሁድ አሕዛብም በክርስቶስ አንድ ናቸው (ኤፌ. 2:11-22):: በኤፌሶን 3 ላይ ይህንን አዲስ መርሐ ግብር ጳውሎስ «ምሥጢር» ብሎ ጠርቶታል:: ትርጉሙም ከብሉይ ኪዳን ያልተገለጠው «የተቀደሰ ምሥጢር» ማለት ነው:: ታዲያ እግዚአብሔር የእስራኤልን መንግሥት ጉዳይ ትቶታል ማለት ነው? በፍጹም አልተወም! እግዚአብሔር ለእስራኤል ያለውን ዓላማ የሚፈጽምበት ዘመን እስኪመጣ ድረስ፣ ለጊዜው እስራኤል ወደ ጎን ገለል ተደርጋለች::

ጳውሎስ እንደገለጸው ከሆነ፣ አሕዛብ ለእስራኤል በጣም ቁልፍ አገልግሎት አላቸው:: ዛሬ ዛሬ የዳኑት አሕዛብ በክርስቶስ ካገኙት መንፈሳዊ ባለጠግነት የተነሣ እስራኤላውያን «እንዲቀኑ» ያነሣሷቸዋል (ሮሜ 10:19 ይመልከቱ):: ክርስቲያኖች በክርስቶስ «ሁሉም መንፈሳዊ በረከት ሲኖራቸው» (ኤፌ. 1:3)፣ እስራኤል ግን በዘመናችን መንፈሳዊ ኪሳራ ደርሶባታል (አንድ ያልዳነ አይሁድ አንድ ቤተ ክርስቲያን ጎራ ቢል፣ እኛ ያለንን ለማግኘት ይቀና ይሆን? ወይስ እንዲሁ ይነሳሳ ይሆን?»

እስራኤል ወደ ፊት ተስፋ አላት:: ጳውሎስ ይህንኑ «ሙላት» ና (ቁ. 12) «መመለሳቸው» (ቁ. 15) እያለ ይጠራዋል:: በዘመናችን፣ እስራኤል በመንፈሳዊ ነገሯ ወድቃለች፣ ነገር ግን ክርስቶስ ሲመለስ፣ እንደገና ታንሰራራለች:: ዛሬ እስራኤል በእግዚአብሔር ተጥላለች፣ ነገር ግን አንድ ቀን ተቀባይነት ታገኛ ለች:: እግዚአብሔር እንደሚመልሳቸው ከሕዝቡ ጋር የገባውን ኪዳን አያጥፍም (እግዚአብሔር የተስፋ ቃሉን ከፀሐይ፣ ጨረቃና ከዋክብት ጋር ያያይዘዋል፣ ኤር. 31:35-37ን ይመልከቱ:)

## 4. አባቶች (11:16-24)

ጳውሎስ የወደፊቱን ካየ በኋላ፣ የእስራኤልን መንፈሳዊ ጥፋት ለማሳየት እንደገና ወደ ቀድሞው ዘመን ተመለሰ:: ገና ከመጀመሪያው እስራኤላውያን ከእግዚአብሔር የተለዩ ልዩ ሕዝብ ነበሩ:: እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር ያለውን ነገሩን እንዳልጨረሰ ለማሳየት ጳውሎስ ሁለት ምሳሌዎችን ተጠቀመ::

ሀ) *ቡሆ* (11:16)- ይህ ጥቅስ የተወሰደው ከዘኁልቁ 15:17-21 ነው:: የመጀመሪያው ቡሆ ለእግዚአብሔር የሚሰጠው ሁሉም የእግዚአብሔር መሆኑን ለማሳየት ነው:: ይህ በመከር በዓል ጊዜ ሁሉም መከር የእግዚአብሔር እንደሆነ ለማሳየት (ዘሌዋ. 23:9-4) ካህኑ የበኩራቱን ነዶ ለእግዚአብሔር ከሚወዘውዝበት ሥርዓት ጋር ተመሳሳይ ነው:: መሠረተ አሳቡ እግዚአብሔር ጥቂቱን ከተቀበለው፣ ሁሉንም ይቀድሳል የሚል ነው::

ይህንን ከእስራኤል ታሪክ ጋር ካዛመድነው፣ የጳውሎስ አሳብ ይገባናል:: እግዚአብሔር የሕዝቡ መሥራች የሆነውን አብርሃምን ከተቀበለ፣ ዘሩንም ለራሱ ይለያቸዋል:: እግዚአብሔር ሌሎች አባቶችን ማለትም ይስሐቅና ያዕቆብንም ቢሆን ኃጢአታቸውንና ውድቀታቸውን አልፎ ተቀብሏቸዋል:: ከዚህ የምንረዳው እግዚአብሔር የቀረውን ሊጥ ይቀበላል ማለት ነው:: እነርሱም የእስራኤል ሕዝብ ናቸው::

ለ) *የወይራ ዛፍ* (11:16 -24) - ይህ የእስራኤል ሕዝብ ተምሳሌት ነው (ኤር. 11:16-17፤ ሆሴዕ 14:4-6):: ጳውሎስ የሚናገረው አንድ አማኝ ከእግዚአብሔር ጋር ስላለው ግንኙነት ሳይሆን፣ እስራኤል በእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ ስላላት ድርሻ ነው:: የዛፍ ሥር ዛፉን ይደግፋል:: ይህም እስራኤልን የመሠረቱት የአባቶች ተምሳሌት ነው:: እግዚአብሔር ቃል ኪዳኑን ያደረገው ከአብርሃም፣ ከይስሐቅና ከያዕቆብ ጋር በመሆኑ፣ ሊክዳቸው ወይም ሊለውጣቸው አይችልም:: እስራኤልን ዛሬም እንኳ ያቆማት እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባው ቃል ነው::

አብዛኛዎቹ አይሁድ አላመኑም:: ጳውሎስ እነርሱን እንደ ተገነጠሉ የዛፍ ቅርንጫፎች አድርጎ ሥሏቸዋል:: ነገር ግን አንድ አስደናቂ ነገር ተመልክቷል:- ሌሎች ቅርንጫፎች በተቆረጠው ቦታ ገብተው የዛፉን ሕይወት ሲጋሩ አይቷል:: እነዚህ ቅርንጫፎች አሕዛብ ናቸው:: በቁጥር 24 ላይ ጳውሎስ ይህ ሂደት «ከፍጥረት ሕግ ውጭ» መሆኑን ተናግሯል:: አብዛኛውን ጊዜ በጥሩ ሁኔታ ያደገ ቅርንጫፍ ከበረሃ ዛፍ ላይ ተጣብቆ ሕይወቱን ቢጋራም የረባ ፍሬ አያፈራም:: ነገር ግን በዚህ ክፍል፣ ወደ መልካሙ ዛፍ ሲገቡ የምናያቸው «የበረሃ ወይራ» (አሕዛብ) ናቸው:: «መዳን ከአይሁድ ነውና» (ዮሐ. 4:22)::

የወይራን ዛፍ በተፈጥሮው ካሉትና ተብትበው ከተጣበቁት ቅርንጫፎች ጋር የቤተ ክርስቲያን ምሳሌ አድርገን ከወሰድነው ትልቅ ስሕተት ነው:: በቤተ ክርስቲያን «ልዩነት የለም»፤ አማኞች ሁሉ «በኢየሱስ ክርስቶስ አንድ ናቸው» (ገላ. 3:28):: እግዚአብሔር የክርስቶስን አካል አይሁድና አሕዛብ ብሎ በመከፋፈል አያይም:: የወይራ ዛፍ የሚያመለክተው አይሁድና አሕዛብ በእግዚአብሔር መርሐ ግብር ያላቸውን ግንኙነት ነው:: «የቅርንጫፎቹ መሰበር» «የመውደቃቸው» (ቁ. 11)፣ «የመሸነፋቸው» (ቁ. 12) እና «የመጣላቸው» (ቁ. 18) ከሚሉት ቃላት ጋር ተመጣጣኝ ነው:: ምሳሌው የአንድን አማኝ የዘላለም ዕጣ ፈንታ እንደሚያመለክት ማሰብ ጳውሎስ ሊያስተላልፍ የፈለገውን እውነት መቆልመም ነው::

ጳውሎስ አሕዛብ ለእስራኤል እንዲገድዳቸው እንጂ ባገኙት አዲስ መንፈሳዊ ደረጃ /አቋም እንዳይታበዩ አስጠንቅቋቸዋል (11:18-21):: አሕዛብ በእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ የገቡት በእምነት እንጂ፣ በሠሩት መልካም ሥራ አይደለም:: ጳውሎስ በዚህ ስፍራ ላይ የሚናገረው ስለ አንድ አማኝ ወይም ስለሌላው ተሞክሮ ሳይሆን ስለ አሕዛብ በጥቅሉ ነው::

በመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት መሠረት የምታምን የአሕዛብ ቤተ ክርስቲያን ወደ ኋላ ከማፈግፈጓ የተነሣ «ልትቆረጥ»

እንደምትችል መነገሩን ማስተዋሉ ጠቃሚ ነው:: 1ኛ ጢሞቴዎስ 4፣ 2ኛ ጢሞቴዎስ 3ና 2ኛ ተሰሎንቄ 2 እንደሚያመለክቱት በመጨረሻው ዘመን ቤተ ክርስቲያን ከእውነተኛ እምነት እንደምትርቅ ይናገራሉ:: *ወደ ኋላ ለተመለሰችው እስራኤል ተስፋ ቢኖርም፣ ላፈገፈገችው ቤተ ክርስቲያን ግን ተስፋ የለም!* ለምን? በወይራ ሥር ምክንያት እግዚአብሔር ለአባቶች ቃሉን ሲጠብቅ፣ ባለማመናቸው ምክንያት ደግሞ ለአሕዛብ የገባውን ቃል ያጥፋል::

እስራኤል ከእግዚአብሔር እውነት የቱንም ያህል ብትኮበልልም፣ ሥሮቹ አሁንም ጥሩ ናቸው:: እግዚአብሔር አሁንም «የአብርሃም አምላክ የይስሐቅ አምላክ የያዕቆብም አምላክ ነው» (ማቴ. 22:23፣ ዘጸ. 3:6):: ለእነዚህ አባቶች ቃሉን ይጠብቃል:: ይህ ማለት የወይራ ዛፉ እንደገና በጤናማ ሁኔታ ይበቅላል ማለት ነው::

## 5. ራሱ እግዚአብሔር (11:25-36)

ጳውሎስ የመጨረሻ ምስክርነቱን ለማጠቃለያ አቀይቶታል:: የእግዚአብሔር ባሕርይና ሥራው በወደፊቱ የእስራኤል ዕጣ ፈንታ ላይ ጣልቃ መግባቱን አስረግጧል:: ሰዎች ስለ ትንቢት ያላቸው ትርጓሜ ቢለያይም፣ ማወቅ ያለባቸው ይህ ክፍል የሚናገረው *የእግዚአብሔር ሕዝብ* ስለሆኑት እስራኤላውያን መሆኑን ነው::

*ሀ) የእግዚአብሔር ጊዜ* (11:25)- በእስራኤል የተፈጸመው የእግዚአብሔር ዕቅድ አካል ሲሆን፣ እግዚአብሔር የሚሠራውን ያውቃል:: የእስራኤል መታወር (መደንደን፣ ቁ. 27) ከፊልና ጊዜያዊ እንጂ፣ የመጨረሻዋ ወይም የፍጻሜዋ አይደለም:: እስከ መቼ ይሆን? መልሱ፣ «የአሕዛብ ሙላት እስኪገባ ድረስ» (ቁ. 25):: ለእስራኤል (ቁ.12) እንዲሁም ለአሕዛብ «ሙላት» አላቸው:: ዛሬ፣ እግዚአብሔር በጸጋው አሕዛብን እየጎበኘ ለስሙ መጠሪያ የሚሆን ሕዝብ እያወጣ ነው (የሐዋ. 15:12-14):: አንዳንድ አይሁድ ቢድኑም፣ ይህ ዘመን እግዚአብሔር በቅድሚያ

አሕዛብን የሚጎበኝበትና ቤተ ክርስቲያኑን የሚያንጽበት ነው:: ይህ ዘመን ሲጠናቀቅና የአሕዛብ ሙላት ሲደርስ፣ እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር ያለውን ጉዳይ እንደገና ይጀምራል::

ሮሜ 11:25 በመጽሐፍ ቅዱስ ጠቃሚ ከሆኑትና «እስከ. . . .» ጥቅሶቹ መካከል አንዱ ነው:: ማቴዎስ 23:32-39፤ ሉቃስ 21:24 ና መዝሙር (110):1ን በተጨማሪ ይመልከቱ:: እግዚአብሔር ዘመኑን እንደሚያውቅና ፈቃዱን ለመሙላት ፈጽሞ እንደማይዘገይ ይህ ቃል ዋስትናን የሚሰጥ ነው::

ለ) *የእግዚአብሔር ተስፋ* (11:26)- በዚህ ቦታ የሚገኘው ጥቅስ የተወሰደው ከኢሳይያስ 59:20-21 ላይ ሲሆን፣ ሙሉ አሳቡን ለማግኘት ኢሳይያስ 60ን ማንበብ ይገባችኋል:: እግዚአብሔር ሕዝቡን ሲያድን ቃል ገብቷል፣ ቃሉንም ይጠብቃል:: ይህን ምንባብ አንዳንድ ግለሰቦች በወንጌል አማካኝነት ስለሚያገኙት ደኅንነት ነው የሚናገረው ብለው ይተረጉሙታል፣ በእኔ መረዳት ግን ነቢዩ ስለ አገር አቀፍ ለውጥ አስቦ የተናገረው ይመስለኛል:: «እስራኤል ሁሉ ይድናል» ሲል በዚህ ዓለም የኖረ አይሁድ ሁሉ ይድናሉ ማለቱ ሳይሆን፣ መድኃኒታችን ሲመለስ በሕይወት የሚኖሩ አይሁድ ያዩታል፣ ይቀበሉታል፣ ይድናሉ ማለቱ ነው:: ዘካርያስ 12-13 ሙሉውን ዝርዝር ጽፏል:: ለእኔ እንደሚመስለኝ በብሉይ ኪዳን ካሉት ትንቢቶች ውስጥ ስለ እስራኤል ብሔራዊ መታደስ የሚናገሩ፣ እኛም መንፈሳዊነታቸውን ጠብቀን ለዛሬይቱ ቤተ ክርስቲያን ልንጠቀምባቸው የምንችል እጅግ ብዙ ዝርዝሮች አሉ::

*ሐ) የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን* (11:27-28)- ይህ ከኢሳይያስ 59 የተወሰደው ተከታይ ጥቅስ ነው:: ትኩረቱ ግን እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር ስላደረገው ቃል ኪዳን ነው:: እግዚአብሔር እስራኤልን የመረጣት በሠራችው መልካም *ሥራ* እንደ ሽልማት ሳይሆን፣ እንዲሁ በጸጋው ነው (ዘዳግ. 7:6-11 እና 9:1-6):: ሕዝቡ ስለ ደግ *ሥራው* ካልተመረጠ፣ ስለ ኃጢአቱ ሊገፋ ይችላልን? «ምርጫ» ማለት ጸጋ እንጂ ለተሠራው መልካም

ሥራ የሚመጥን ሽልማት አይደለም። ለወንጌል ካላቸው ጥላቻ የተነሣ፣ የአይሁድ ሕዝብ የአሕዛብ አማኞች ጠላቶች ናቸው። ነገር ግን የአይሁድ ሕዝብ ለእግዚአብሔር «ስለ አባቶች ተወዳጆች ናቸው»። እግዚአብሔር ለአብርሃም፣ ለይስሐቅና ለያዕቆብ የገባውን ቃል አያጥፍምና።

*መ) የእግዚአብሔር ባሕርይ* (11:29) - «እኔ እግዚአብሔር ነኝ፣ አልለወጥም» (ሚል. 3:6)። «ሐሰትን ይናገር ዘንድ እግዚአብሔር ሰው አይደለም፣ ይጸጸትም ዘንድ የሰው ልጅ አይደለም።» (ዘኁል. 23:19)። እግዚአብሔር ለእስራኤል ያለው ስጦታና እግዚአብሔር እስራኤልን መጥራቱ ሊቀለበስ ወይም ሊለወጥ አይችልም። ካልሆነማ እግዚአብሔር በእውነት ፍጹም የሆነውን ባሕርይውን ሊቃረን ነው። እስራኤል በተሰጣት ስጦታ አለመደሰት ወይም እንደ ተመረጠ ሕዝብ አለመኖሯ ይህንን እውነት አይፍቀውም። ሰዎች ያሻቸውን ቢያደርጉም እግዚአብሔር ግን ስለ ራሱና ስለ ቃሉ ሲል ዝንፍ ሳይል ይኖራል። «የማያምኑ ቢኖሩ አለማመናቸው የእግዚአብሔርን ታማኝነት ያስቀራልን?» (ሮሜ 3:3)።

*ሠ) የእግዚአብሔር ጸጋ* (11:30-32) -- «ከአለመታዘዛቸው የተነሣ ምሕረት እንዳገኛችሁ» ይላል ጳውሎስ። «እንዲሁ በተማራችሁበት ምሕረት እነርሱ ደግሞ ምሕረትን ያገኙ ዘንድ።» ጳውሎስ በተደጋጋሚ አሕዛብ እስራኤልን በቅናት የማነሣሣት ግዴታ እንዳለባቸው ላመኑት አሕዛብ ያሳስባቸዋል (ሮሜ 10:19፤11:1፣14)። የእስራኤል ድንዳኔ «በከፊል» ነው (ቁ.25)፣ ይህም አንዳንድ አይሁድ በግለሰብ ደረጃ ይድናሉ ማለት ነው። እግዚአብሔር «ሁሉን ባለመታዘዝ» ዘግቶታል- አይሁድም አሕዛብም በጸጋ መዳን የሚችሉበትን ዕድል እንዲያገኙ «ልዩነት የለምና»። እግዚአብሔር ዛሬ በጸጋውና በምሕረቱ አይሁድን ማዳን ከቻለ፣ ወደፊት እንዴት አያድናቸውም?

ማስታወስ ያለብን ነገር እግዚአብሔር አይሁድን የመረጠው አሕዛብን ለማዳን መሆኑን ነው። «በአንተ የምድር አሕዛብ ሁሉ

ይባረካሉ»፣ የሚለው ቃል እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባለት ቃል ነው (ዘፍጥ. 12፡1-3)። አሳዛኙ ጉዳይ ግን እስራኤል ተለይታ ለአሕዛብ ይህን እውነት ለማካፈል አለመቻሏ ነው። እስራኤላውያን አሕዛብ ይድኑ ዘንድ አይሁድ መሆን እንደሚገባቸው አሰቡ። ነገር ግን እግዚአብሔር አይሁድም አሕዛብም የጠፉና በኩነኔ ሥር ያሉ መሆናቸውን ተናገረ። ይህም እግዚአብሔር ሁሉንም በክርስቶስ የመስቀል ላይ መሥዋዕትነት በምሕረቱ ሊያድናቸው ይችላል ማለት ነው።

*ረ) የእግዚአብሔር ጥበብ* (11፡33-36)- እግዚአብሔር ለአይሁድና ለአሕዛብ ያለውን ታላቅ ዕቅድ ካሰላሰለ በኋላ፣ ጳውሎስ ማድረግ የቻለው ነገር ምስጋና ማቅረብ ነው። አንዱ እንደተናገረው «ሥነ መለኮት ቡራኬ ሆነ!» የእስራኤልን ውድቀት ለዓለም ደኅንነት መለወጥ የሚችል ጥበበኛ የሆነው እግዚአብሔር ብቻ ነው! ዕቅዱ ሊጨናገፍ ወይም ዓላማው ሳይፈጸም ሊቀር አይችልም። ሰው የጌታን ልብ በሙላት ሊያውቀው አይችልም። የበለጠ መንገዱን ባጠናን ቁጥር የበዛ ምስጋናን እናቀርባለን። እግዚአብሔር የሚያደርገውን እንደማያውቅ ቆጥረን የእስራኤልን ሕዝብ ዕቅዱን እንዳከላሸበት በመገመት አሳባችንን እንቋጭን? በፍጹም! እግዚአብሔር ጠቢብ ነውና የማይሟላ ዕቅድ አይነድፍም። እስራኤል ይገዛት ዘንድ ፈቃደኛ ስላልሆነች፣ እርሱ በጉልበቱ ገዛት!

ጳውሎስ አምስት ምስክሮችን ሰብስቧል፣ እነርሱም ተስማምተዋል፡- እስራኤል ወደፊት ተስፋ አላት። እስራኤል «ከውድቀቷ » ስታገግምና ወደ «ሙላቷ» ስትገባ፣ ዓለም የእግዚአብሔርን ጸጋ ባለጠግነት ከዚህ በፊት አይታ በማታውቀው መልኩ ትለማመዳለች። ኢየሱስ ክርስቶስ ተመልሶ በዳዊት ዙፋን ሲቀመጥና በመንግሥቱ ሲገዛ፣ እስራኤል «ትታረቅና» «ተቀባይነት ታገኛለች»፣ ይህም ልክ እንደ ትንሣኤ ይሆናል!

# ሮሜ 12:1-13:14

እንግዲህ፣ ወንድሞች ሆይ፣ ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ፣ እርሱም ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው። የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍጹምም የሆነው ነገር ምን እንደ ሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ።

እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ የእምነትን መጠን እንዳካፈለው፣ እንደ ባለ አእምሮ እንዲያስብ እንጂ ማሰብ ከሚገባው አልፎ በትዕቢት እንዳያስብ በመካከላችሁ ላለው ለእያንዳንዱ በተሰጠኝ ጸጋ እናገራለሁ። (ሮሜ 12:1-3)።

ፍቅራችሁ ያለ ግብዝነት ይሁን። ክፉውን ነገር ተጸየፉት፤ከበጎ ነገር ጋር ተባበሩ፤ በወንድማማች መዋደድ እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ፤ እርስ በርሳችሁ ተከባበሩ፤ ለሥራ ከመትጋት አትለግሙ፤ በመንፈስ የምትቃጠሉ ሁኑ፣ ለጌታ ተገዙ፤ በተስፋ ደስ ይበላችሁ፣ በመከራ ታገሡ፤ በጸሎት ጽኑ፤ ቅዱሳንን በሚያስፈልጋቸው እርዱ፤ እንግዶችን ለመቀበል ትጉ።

የሚያሳድዱአችሁን መርቁ፣ መርቁ እንጂ አትርገሙ። (ሮሜ 12:9-14)

ነፍስ ሁሉ በበላይ ላሉት ባለ ሥልጣኖች ይገዛ። ከእግዚአብሔር ካልተገኘ በቀር ሥልጣን የለምና፤ያሉትም ባለ ሥልጣኖች በእግዚአብሔር የተሾሙ ናቸው። ስለዚህ ባለ ሥልጣንን የሚቃወም የእግዚአብሔርን ሥርዓት ይቃወማል፤ የሚቃወሙትም በራሳቸው ላይ ፍርድን ይቀበላሉ። ገዦዎች ለክፉ አድራጊዎች እንጂ መልካም ለሚያደርጉ የሚያስፈሩ አይደሉምና። ባለ ሥልጣንን እንዳትፈራ ትወዳለህን? መልካሙን አድርግ ከእርሱም ምስጋና ይሆንልሃል፤ ለመልካም ነገር ለአንተ የእግዚአብሔር አገልጋይ ነውና። በከንቱ ግን ሰይፍ አይታጠቅምና ክፉ ብታደርግ ፍራ ቍጣውን ለማሳየት ክፉ አድራጊውን የሚበቀል የእግዚአብሔር አገልጋይ ነውና። ስለዚህ ስለ ቍጣው ብቻ አይደለም ነገር ግን ስለ ሕሊና ደግሞ መገዛት ግድ ነው። (ሮሜ 13:1-5)

# 11

## እውነተኛ ግንኙነት ማለት እውነተኛ አኗኗር ነው

በመልእክቶቹ ሁሉ፣ ጳውሎስ አስተምህሮቱን የደመደመው በተግባር የሚተረጎምበትን መንገድ በመዘርዘር ነው። በክርስትና ሕይወት አስተምህሮና ተግባር እጅ ለእጅ ተያይዘው የሚጓዙ ናቸው። እምነታችን እንዴት እንደምንኖር ይወስነናል። የጳውሎስን የአስተምህሮ ዝርዝር መገንዘቡ ብቻ በቂ አይደለም። የተማርነውን በሕይወት በመተርጎም፣ በእግዚአብሔር ቃል እንደምንታመን በዕለት ኑሯችን መግለጽ ይገባናል።

የዚህ ክፍል ፍሬ ነገር *ኅብረት/ግንኙነት* ነው። «አንጻራዊ ሥነ መለኮት» የሚለው ቃል አዲስ ቢሆንም፣ አሳቡ ግን አዲስ አይደለም። ከእግዚአብሔር ጋር የተስተካከለ ኅብረት ካለን፣ የሕይወታችን ክፍል ከሆኑት ሰዎች ጋርም ተገቢ ግንኙነት ይኖረናል። «ማንም:- እግዚአብሔርን እወዳለሁ እያለ ወንድሙን ቢጠላ ሐሰተኛ ነው» (1ኛ ዮሐ. 4:20)።

### 1. ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖረን ኅብረት (12:1-2)

መልእክቱ ውስጥ ይህ አራተኛው «እንግዲህ» ነው። ሮሜ 3:20 ስለ ኩነኔ «ይህም» ተብሎ የተተረጎመው ሲሆን፣ ዓለም ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት በደለኛ መሆኑን እያወጀ ነው። ሮሜ 5:1 ላይ «እንግዲህ» የሚለው ጽድቅን ሲያመለክት፣ ሮሜ 8:1 ላይ ያለው ዋስትናን ያመለክታል። በሮሜ 12:1 ላይ «እንግዲህ» ራስን አሳልፎ መስጠትን ሲወክል፣ ይህም ጳውሎስ በዚህ ክፍል ያነሣቸው ግንኙነቶች መሠረት ነው።

እውነተኛ መስጠት ምንድን ነው? ጳውሎስ በዚህ ስፍራ እንደገለጸው ክርስቲያናዊ መስጠት ሦስት እርከኖች አሉት።

*ሀ) ሰውነታችሁን ለእግዚአብሔር ትሰጣላችሁ* (12:1)- በክርስቶስ ከማመናችን በፊት ሰውነታችንን ለኃጢአት ደስታና ዓላማ ተጠቅመንበታል። ነገር ግን አሁን የእርሱ ስለሆንን፣

ሰውነታችንን ለክብሩ ልንጠቀምበት እንፈልጋለን:: የእግዚአብሔር መንፈስ በውስጡ ስለሚኖር፣ የክርስቲያን ሰውነት የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነው (1ኛ ቆሮ. 6:19-20፤ ሮሜ 8:9):: ክርስቶስን በሥጋችን ማክበርና የማጉላት ልዩ መብት ተሰጥቶናል (ፊልጵ. 1:20-21)::

ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም ሥጋ እንደለበሰ ሁሉ፣ በእኛም አልፎ የእግዚአብሔርን ሥራ እንዲሠራ ሰውነታችንን ለክርስቶስ አሳልፈን መስጠት ይገባናል:: የአካላችንን ክፍሎች (ብልቶች) «የጽድቅ ዕቃ» (ሮሜ 6:13) አድርገን ለመንፈስ ቅዱስ በመስጠት ለእግዚአብሔር ሥራ ጥቅም ላይ እንዲውል መፍቀድ አለብን:: የብሉይ ኪዳን መሥዋዕቶች ሙት መሥዋዕት ነበሩ:: ነገር ግን እኛ ሕያው መሥዋዕት ነን::

በመጽሐፍ ቅዱስ ሁለት ዓይነት «ሕያው መሥዋዕቶች» ያሉ ሲሆን፣ ትርጉማቸውን መረዳቱ ይጠቅመናል:: የመጀመሪያው ይስሐቅ ነው (ዘፍጥ. 22)፤ ሁለተኛው ደግሞ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: ይስሐቅ በፈቃዱ ራሱን በመሠዊያው ላይ በማኖሩ ለእግዚአብሔር ፈቃድ በመታዘዙ ሊሞት ነበር፣ ነገር ግን ጌታ በግ ልኮ በእርሱ ምትክ እንዲሞት አደረገ:: ይስሐቅ «ሞተ» ማለትም ለራሱ ፈቃድ ሞተ፣ ራሱን ለእግዚአብሔር ፈቃድ አሳልፎ ሰጠ:: ከመሠዊያው ሲነሣ፣ ይስሐቅ ለእግዚአብሔር ክብር «ሕያው መሥዋዕት» ነበር::

ለአባቱ ፈቃድ በመታዘዝ መሥዋዕት ሆኖ ሞቷልና፣ ፍጹም የሆነ «የሕያው መሥዋዕት» ምሳሌአችን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: ነገር ግን ከሞት ተነሥቶአል:: ዛሬም በሰውነቱ የቀራንዮን ቁስል ተሸክሞ «ሕያው መሥዋዕት» ሆኖ በመንግሥተ ሰማይ ይኖራል:: በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት ሊቀ ካህናችን ነው (ዕብ. 4:14-16)፣ ጠበቃችንም ነው (1ኛ ዮሐ. 2:1)::

«አቅርቡ» የሚለው ግሥ ትርጉሙ «ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ አቅርቡ» ማለቱ ነው:: ሙሽራውና ሙሽራይቱ በሠርጋቸው ቀን

አንዳቸው ለአንዳቸው እንደሚሰጣጡ፣ ሰውነታችን ለጌታ በሙላት እንድንሰጥ ያዛል፡፡ በሰውነታቸው ላይ የሚሠሩትን የሚወስነው ይህ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ያደረጉት መሰጠት ነው፡፡ ስለዚህ መሰጠት ጳውሎስ ሁለት ምክንያቶችን ሰጥቷል፡- (1) እግዚአብሔር ለእኛ ላደረገው ሁሉ ምላሽ ነው - «እንግዲህ ወንድሞች ሆይ. . . በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ» እና (2) ይህ መሰጠት «ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችን ነው» ወይም መንፈሳዊ አምልኮአችን ነው፡፡ ይህም በእያንዳንዱ ቀን ሰውነታችንን ለጌታ ስናቀርብ በአምልኮ ውስጥ ነን ማለት ነው፡፡

*ለ) ልባችሁን ስጡት* (12:2) - ዓለም ልባችሁን መቆጣጠር ስትፈልግ፣ እግዚአብሔር ደግሞ ልባችሁን ሊያድሰው ይፈልጋል (ኤፌ. 4:17-24 እና ቆላ. 3:1-11ን ይመልከቱ)፡፡ *መታደስ* የሚለው ይህ ቃል በማቴዎስ 17:2 ላይ እንደተገለጸው ሙሉ *መለወጥን* ያመለክታል፡፡ «ፊቱም እንደ ፀሐይ በራ ልብሱም እንደ ብርሃን ነጭ ሆነ» ከሚለው ቃል ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ከውስጥ የሚመነጭ ለውጥን ያመለክታል፡፡ ዓለም ልባችሁን መቀየር ስለምትፈልግ፣ ከውጭ ግፊት ታደርጋለች፡፡ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ልባችሁን ለመለወጥ ኃይልን ከውስጣችሁ ያፈልቃል፡፡ ዓለም አሳባችሁን ከተቆጣጠረችው የኃይሏ ተቀባይ ትሆናላችሁ፤ እግዚአብሔር አሳባችሁን የሚቆጣጠረው ከሆን ግን ኃይሉን አስተላላፊ ትሆናላችሁ፡፡

እግዚአብሔር ልቦናችንን ለውጦ ቃሉን በመጠቀም መንፈሳዊ ልቦና እንዲኖረን ያደርጋል፡፡ የእግዚአብሔርን ቃል በማሰላሰል በልባችሁ እየያዛችሁ የውስጥ ሰውነታችሁ አካል ስታደርጉት እግዚአብሔር ልቦናችሁን የበለጠ መንፈሳዊ ያደርገዋል፡፡

*ሐ) ፈቃዳችሁን ስጡት* (12:2) — ልባችሁ ሰውነታችሁን ሲቆጣጠር፣ ፈቃዳችሁ ደግሞ ልቦናችሁን ይገዛል፡፡ ብዙ ሰዎች ፈቃዳቸውን «በፈቃዳቸው ኃይል» ሊቆጣጠሩት ይሞክራሉ፣ ነገር ግን አብዛኛውን ጊዜ አይችሉም፡፡ ይህ በሮሜ 7:15-21 የተዘገበው የጳውሎስ ተሞክሮ ነው፡፡ ፈቃዳችንን አሳልፈን ስንሰጥ፣ የእርሱ

ኃይል ፈቃዳችንን አሸንፎ ድል አድራጊ ክርስቲያኖች እንድንሆን የፈቃዱን ኃይል ይሰጠናል።

ፈቃዳችንን ለእግዚአብሔር የምናስገዛው እንደሚገባ በመጸለይ ነው። በጸሎት ጊዜአችን ፈቃዳችንን ለእግዚአብሔር አሳልፈን በመስጠት፣ «የእኔ ፈቃድ ሳይሆን የአንተ ፈቃድ ይሁን» እያልን ነው። ስለ ሁሉም ነገር መጸለይ የሚገባን ሲሆን፣ እግዚአብሔር ደግሞ ነገርን ሁሉ በራሱ መንገድ እንዲሠራ እንፍቀድለት።

ለብዙ ዓመታት በእያንዳንዷ ቀን ሰውነቴን ለጌታ በማስረከብ ለመጀመር ሞክሬያለሁ። ቃሉን አጠናና ልቤን ለውጦ አስተሳሰቤን ለአዲሱ ቀን እንዲያዘጋጅልኝ እተዋለሁ። በመቀጠልም እጸልይና የቀኑን ዕቅዶቼን ለእርሱ አቅርቤ እንደወደደ እንዲያደርግ እተውለታለሁ። በተለይ ስለሚያበሳጩኝና ስለሚያስጨንቁኝ ነገሮች እጸልያለሁ። ሁልጊዜም ያየኛል። ከእግዚአብሔር ጋር የሠመረ ግንኙነት እንዲኖረን፣ ሰውነታችንን፣ ልቦናችንንና ፈቀዳችንን ለእርሱ በማቅረብ ቀኑን እንጀምር።

## 2. ከሌሎች አማኞች ጋር የሚኖረን ኅብረት (12:3-16)

ጳውሎስ የጻፈው በሮም ለሚገኙ የአንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባሎች ነው። እርስ በርስ የሚኖራቸውን ኅብረት በአንድ አካል ላይ እንደሚገኙ ብልቶች በመመሰል ገልጾላቸዋል። (ተመሳሳይ ምሳሌ በ1ኛ ቆሮንቶስ 12 ላይና ኤፌሶን 4:7-16 ላይ ተጠቅሷል። ፍሬ ነገሩ እያንዳንዱ አማኝ የክርስቶስ አካል ሕያው ክፍል (ብልት) ሲሆን፣ እያንዳንዱም የሚሠራው ልዩ መንፈሳዊ ተግባር አለው። እያንዳንዱ አማኝ ስጦታ (ስጦታዎች) አለው። እነርሱንም አካሉን ለመገንባትና ሌሎች የአካሉን ብልቶች ፍጹም ለማድረግ ይጠቀምባቸዋል። በአጭሩ አንዳችን ለአንዳችን የተገባን ነን። እርስ በርሳችን አገልግሎት እንሰጣጣለን። አንዳችን ለአንዳችንም አስፈላጊዎች ነን። በክርስቶስ አካል ውስጥ ለመንፈሳዊ አገልግሎትና ዕድገት አስፈላጊው ነገር ምንድን ነው?

*ሀ) በቅንነት ሕይወትን መፈተሽ* (12:3) - እያንዳንዱ ክርስቲያን መንፈሳዊ ስጦታዎቹን በመለየት በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን፣ በራሱ ሕይወት ወይም በሌሎች ክርስቲያናት ምስክርነት ስጦታው ምን እንደሆነ ለማወቅ መሞከር ክፋት የለውም:: ስሕተት የሚሆነው ስለ ራሳችን የተሳሳተ ግምት ሲኖረን ነው:: በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከፍተኛ ችግር የሚደርሰው አንድ አማኝ ራሱን ከፍ በማድረግ ሊሠራው የማይቻለውን ለማድረግ ሲሞክር ነው:: (አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ሰዎች ከመጠን ባለፈ ሁኔታ ራሳቸውን ዝቅ ያደርጋሉ፣ ይህም ከላይ ያየነው ተቃራኒ ሲሆን፤ ሁለቱም ስሕተቶች ናቸው)::

ያገኘናቸው ስጦታዎች የመጡት በእግዚአብሔር ጸጋ ምክንያት ነው:: በእምነት ልንቀበላቸውና በሥራ ላይ ልናውላቸው ይገባል:: የዳንነው «በጸጋው በእምነት» ነው (ኤፌ. 2:8-9)፣ ስለዚህም «በጸጋው በእምነት» ልንኖርና ልናገለግል ይገባናል:: ስጦታዎቻችን ከእግዚአብሔር ስለሆኑ፣ ልንኩራራ አይገባም፤ ማድረግ የሚገባን ስጦታውን ተቀብለን ስሙን ለማክበር ማዋል ነው:: (1ኛ ቆሮንቶስ 15:10 ስለ ጳውሎስ ስጦታ የቀረበውን ምስክርነት ይመልከቱ)::

በአንድ ወቅት ስለ ስጦታቸው የተለያየ አመለካከት ካላቸው ሁለት ሰዎች ጋር አገልግያለሁ:: አንደኛው ስጦታውን አሳንሶ የሚያይና የማይጠቀምባቸው ሲሆን፣ ሌላኛው ደግሞ በሌለው ስጦታ የሚኩራራ ነበር:: ሁለቱም የትዕቢት በደል ነበረባቸው፣ ምክንያቱም ሁለቱም የእግዚአብሔርን ጸጋ አላመሰገኑም፣ የሚገባውን ክብርም አልሰጡትም:: ሙሴም እግዚአብሔር በጠራው ጊዜ ተመሳሳይ ስሕተት ሠርቷል (ዘጸ. 4:1-13):: አማኞች ስጦታቸውን ሳያውቁ በእምነት ሲቀበሉአቸውና ለእግዚአብሔር ክብር ሲጠቀሙባቸው፣ እግዚአብሔር በድንቅ ሁኔታ ይባርካቸዋል::

*ለ) በታማኝነት መተባበር* (12:4-8) - እያንዳንዱ አማኝ ልዩ ስጦታ አለው፣ እግዚአብሔር ደግሞ እነዚህን ስጦታዎች

የሰጠበት ምክንያት፣ አጥቢያ አካሉ በተገቢው መንገድ ሚዛኑን በጠበቀ መንገድ ማዕከላዊነቷን ጠብቃ እንድታድግ ነው:: ነገር ግን እያንዳንዱ አማኝ ስጦታውን በእምነት መለማመድ መቻል አለበት:: የአገልግሎታችንን ፍሬ እኛ ላናየው እንችል ይሆናል:: ጌታ ግን ያየዋል፤ ይባርከዋልም:: «ማበረታታት» ልክ እንደ ስብከትና ማስተማር ሁሉ መንፈሳዊ አገልግሎት መሆኑን አስተውሉ:: መስጠትና ምሕረትን ማድረግም ጠቃሚ ስጦታዎች ናቸው:: ለአንዳንድ ሰዎች እግዚአብሔር የማስተዳደር ወይም የመግዛትን ስጦታ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሰጥቷቸዋል:: ምንም ዓይነት ስጦታ ቢኖረን፣ ለእግዚአብሔር የተሰጠና ለቤተ ክርስቲያን ጥቅም የሚውል ሊሆን ይገባዋል::

በቤተ ክርስቲያን ከሌሎች ስጦታዎች በላይ አንድ ስጦታ ላይ ብቻ ትኩረት ሲሰጥ እንዴት ያሳዝናል:: «ሁሉ ሐዋርያት ናቸውን? ሁሉስ ነቢያት ናቸውን? ሁሉስ አስተማሪዎች ናቸውን? ሁሉስ ተአምራት ይሠራሉን? ሁሉስ የመፈወስ ስጦታ አላቸውን? ሁሉስ በልሳኖች ይናገራሉን? ሁሉስ ይተረጉማሉን?» (1ኛ ቆሮ. 12:29-30):: ለሁሉም ጥያቄዎች መልሱ የለም በፍጹም ነው! ለአንድ ክርስቲያን የራሱን ስጦታ አግንኖ የሌሎችን ማጣጣል ስጦታዎቹ የተሰጡበትን ዓላማ መሳት ነው:- ለክርስቶስ አካል ተሰጥተዋልና:: «ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን መግለጥ ለእያንዳንዱ ለጥቅም ይሰጠዋል» (1ኛ ቆሮ. 12:7)::

መንፈሳዊ ስጦታዎች ለግንባታ የምንጠቀምባቸው መሣሪያዎች ናቸው እንጂ፣ መጫወቻ አሻንጉሊት ወይም መዋጊያ የጦር መሣሪያዎች አይደሉም:: በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የነበሩት አማኞች፣ መንፈሳዊ ስጦታዎችን አላግባብ እየተጠቀሙ አገልግሎታቸውን አፈራረሱት:: መንፈሳዊ ስጦታዎችን ለቤተ ክርስቲያን ግንባታ በማድረግ ፋንታ የመንፈሳዊ ከፍታ ቁንጮ አድርገው ይወስዷቸው ነበር:: ለመንፈሳዊ ስጦታዎች ከፍተኛ ትኩረት በመስጠታቸው መንፈሳዊ ጸጋን አጡ:: የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ቢኖራቸውም፣

የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ የሆኑት ፍቅር፣ ደስታና ሰላም ግን አልነበሯቸውም (ገላ. 5:22-23)።

*ሐ) የፍቅር ተሳትፎ* (12:9-16)- በዚህ ክፍል ስጦታው ያላቸው ሰዎች ሊኖራቸው ስለሚገባ ባሕርይ አጽንኦት ይሰጣል። መንፈሳዊ ስጦታን መንፈሳዊ ባልሆነ መንገድ መጠቀም ይቻላል። ጳውሎስ ተመሳሳይ አሳብ «የፍቅር ምዕራፍ» እየተባለ በሚታወቀው በ1ኛ ቆሮንቶስ 13 ላይ አንሥቷል። ፍቅር አማኞች ሁሉ በጤናማ መልኩ ተስማምተው እንዲሠሩ የሚያስችል የመንፈሳዊ አካል አንቀሳቃሽ ሞተር ነው። ይህ ፍቅር በግብዝነት የተሞላ አይደለም (ቁ. 9)፤ ትሑት ነው እንጂ ትዕቢተኛ አይደለም (ቁ. 10)። «በወንድማማች መዋደድ» ማለት እያንዳንዱ ባልንጀራው ከራሱ ይልቅ እንዲሻል በትሕትና ይቍጠር» ማለት ነው (ፊልጵ. 2:1-4)።

ክርስቶስን ማገልገል ማለት በአብዛኛው ሰይጣናዊ ተቃውሞ ያለባቸው ተስፋ የሚያስቆርጡ ቀናትን ያዘለ ነው። ስለሆነም ጳውሎስ አንባቢዎቹ የሚያገለግሉት ጌታን እንጂ ሰዎችን ስላልሆነ፣ ያላቸውን መንፈሳዊ ጽናት አጥብቀው እንዲይዙ ያስጠነቅቃቸዋል። ሕይወት አስቸጋሪ ስትሆን፣ ክርስቲያን ቅናቱ እንዲያረጅ መፍቀድ የለበትም። «በመንፈስ የምትቃጠሉ ሁኑ፤ ለጌታ ተገዙ፤ በተስፋ ደስ ይበላችሁ፤ በመከራ ታገሡ፤ በጸሎት ጽኑ» (ሮሜ 12:12)።

በመጨረሻም፣ ጳውሎስ የሌሎችን ስሜት እንዲካፈሉ ያሳስባቸዋል። ክርስቲያናዊ ኅብረት ከመተቃቀፍና ከመጨባበጥ ያለፈ ነው። የሌሎችን ሸክምና በረከት አብሮ በመጋራት ሁላችንም ጌታን በማክበር አብረን የምናድግበት ነው። ክርስቲያኖች እርስ በርሳቸው ካልተግባቡ ጠላቶቻቸውን እንዴት ሊፋለሙ ይችላሉ? ትሕትናና ለማካፈል ፈቃደኛ መሆን አካሉን በሚያገለግሉ ክርስቲያኖች የሚታዩ ምልክቶች ናቸው። ጌታችን ተራ ሰዎችን አገልግሎ እነርሱም በደስታ ሰምተውታል (ማርቆስ 12:37)። አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን «በኑሮአቸው ሻል ያሉትን»

ብቻ ለማቀፍ ከወሰነች ከክርስቲያናዊ የአገልግሎት መሥመር ትለያለች።

## 3. ከጠላቶቻችን ጋር የሚኖረን ግንኙነት (12:17-21)

እግዚአብሔርን መታዘዝ የሚፈልግ አማኝ ጠላቶችን ያፈራል። ጌታችን በምድር ላይ ሲያገለግል ጠላቶች ነበሩት። ጳውሎስና ሐዋርያት በተጓዙበት ቦታ ሁሉ ሥራቸውን የሚቃወሙ ጠላቶች ነበሩባቸው። ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ሲያስተምር የከፉ ጠላቶቻቸው የገዛ ቤተሰቦቻቸው ሊሆኑ እንደሚችሉ ነግሯቸዋል (ማቴ. 10:36)። የሚያሳዝነው ግን አንዳንድ አማኞች ጠላቶችን የሚያፈሩት ፍቅርና ትዕግሥት ስለጎደላቸው እንጂ፣ በምስክርነታቸው ታማኞች ስለሆኑ አይደለም። «የመስቀል ዕንቅፋት» (ገላ. 5:11፤6:12-15) በመሆን እና አሰናካይ ክርስቲያን በመሆን መካከል ልዩነት አለ።

ክርስቲያን በእግዚአብሔር እየዘበተ፣ በራሱ ሊበቀል ሊነሣሣ አይገባም። ክፉን ስለ ክፋት መመለስ ወይም ደግን በደግነት መመለስ ብዙ ሰዎች የሚኖሩት ኑሮ ነው። ክርስቲያን ግን ከዚህ ከፍ ባለ እርከን (ደረጃ) መኖር መቻል አለበት። ለክፉ ደግሞ በጎ መመለስ መቻል አለበት። በመጀመሪያ ዝንባሌያችን ለመልሶ ማጥቃት ቢያነሣሣንም ፍቅር ያስፈልገናል። እምነትም ያሻናል-በዚህም እግዚአብሔር በሕይወታችን ፈቃዱን እንደሚሞላና በሚጎዱን ሰዎች ላይ ፈቃዱን እንደሚፈጽም እንድናምን ያስችለናል። ለእግዚአብሔር «ቁጣ» ጊዜ ልንሰጥ ይገባናል (ዘዳግም 32:35)።

አንድ ወዳጄ የሆነ ሰው አንድ ሰባኪ በሬዲዮ ስለ እርሱ መጥፎ ብቻ ሳይሆን እውነት ያልሆኑ ነገሮችንም ሲናገር አዳመጠ። በጣም በመናደዱ እርሱም መልስ ሊሰጥ ሲያቅድ ሌላ ሰባኪ፣ «አታድርግ። ራስህን የምትመለከት ከሆነ፣ ጌታ ስለ አንተ አይዋጋም። በጌታ እጅ ላይ ተወው» አለው። ያ ወዳጄ ምክሩን ተቀብሎ ለጌታ ሲተው ጌታ ካሰው (ተበቀለለት)።

በሮሜ 12:20 ላይ ያለው ምክር በማቴዎስ 5:44-48 ላይ ክርስቶስ የተናገረውን ያስታውሰናል:: እነዚህ ቃላት ለማንበብ ቀላል ቢሆኑም፣ ለመተግበር ግን ከባድ ናቸው:: ለጠላቶቻችን ደግነትን ለማሳየት ስንሞክር እግዚአብሔር ፍቅር እንዲሰጠን ልንጸልይ ይገባናል:: አጋጣሚውን ተጠቅመው ያጠቁን ይሆን? አምርረው ይጠሉን ይሆን? ጌታ ብቻ ነው የሚያውቀው:: የእኛ ድርሻ ራሳችንን መከላከል ሳይሆን፣ ጌታን መታዘዝና ውጤቱን ለእርሱ መተው ነው:: ጳውሎስ ምሳሌ 25:21-22ን ጠቅሶ በጌታ ስም በክፉ ፋንታ መልካም ነገርን እንድንመልስ ይገፋፋናል:: «የእሳት ፍም» ማለቱ ምናልባት ለክፋታቸው መልካም ነገርን ስንመልስ፣ ጠላቶቻችን የሚያልፉበትን የኀፍረት ስሜት መግለጹ ይሆናል::

እንደ እግዚአብሔር ልጅነታችን ለክፋት መልካምነትን ለመመለስ በሚያስችለው ከፍታ ላይ መሆን ያስፈልገናል:: ማንም ሰው በደግ ነገር ፋንታ መልካም ነገርን፣ ለክፋት ደግሞ ክፋትን መመለስ ይችላል:: ክፋትን የምናሸንፍበት ብቸኛው መንገድ መልካም ነገርን በማድረግ ነው:: በክፋት ፋንታ ክፋትን መመለስ፣ በእሳት ላይ ቤንዚን እንደ መጨመር ነው:: ጠላቶቻችን የተለወጡ ባይሆኑም፣ እኛ ግን የእግዚአብሔርን ፍቅር በውስጣችን እየተለማመድንና በጸጋው እያደግን ነው::

## 4. ከመንግሥት ጋር የሚኖረን ግንኙነት (13:1-14)

እግዚአብሔር ሦስት ተቋማትን መሥርቷል:: ቤተሰብ (ዘፍጥ. 2:18-25)፣ መንግሥት (ዘፍጥ. 9:1-17) እና ቤተ ክርስቲያን (የሐዋ. 2):: ጳውሎስ የሮሜን መልእክት የጻፈው በሮማውያን ግዛት እምብርት ላይ ለነበሩት አማኞች ነው:: በዚያን ጊዜ ታላቁ ስደት አልነበረም፣ ነገር ግን በመንገድ ላይ ነበረ:: ክርስትና እንደ አይሁድ የሃይማኖት ክፍል ተወስዶ ነበር፤ የአይሁድ ሃይማኖት ደግሞ በሮም ፍቃድ ነበረው:: ነገር ግን ክርስቲያኖች ለነገሥታቱ (ለዓፄዎች) በታማኝነት መታዘዝ የማይችሉበት አስቸጋሪ ዘመን እየመጣ ነበር:: ዕጣን በመሠዊያው ላይ አፍስሶ «ቄሣር አምላክ ነው» ማለትና መቀበል አይችሉም ነበር::

በዘመናችን፣ *በክርስቶስ ስም* ዐመፅንና ብጥብጥን የሚያስተምሩ ሰዎች አሉ! ክርስቲያን መሆን ሕግን አለመታዘዝ፣ በመንግሥት ላይ ማመፅና ሰዎች ሁሉ በዓይናቸው ፊት መልካም መስሎ የታያቸውን መሥራት እንዲችሉ መፍቀድ መሆኑን እንድናምን ይፈልጋሉ:: ጳውሎስ ይህንን አሳብ በዚህ ምዕራፍ ክርስቲያን ለምን ለሕግና ለመንግሥት መታዘዝ እንዳለበት አራት ምክንያቶችን በመዘርዘር ያከሽፈዋል::

ሀ) *ከፍርድ ለመዳን* (13:1-4)- የዓለምን መንግሥታት ያቋቋመው እግዚአብሔር ነው:: (የሐዋ. ሥራ 17:24-28 ይመልከቱ):: ይህም በግፍ ስለሚፈጽሙት ኃጢአታቸው ኃላፊነት አለበት ማለት ሳይሆን፣ እንዲያስተዳድሩ ሥልጣኑ የተሰጣቸው ከእግዚአብሔር መሆኑን ለማመልከት ነው:: ናቡከደነፆር በግድ መማር የተገባው ይህን ነበር:: (ዳንኤል 4 በተለይ ቁጥር 17፣25 እና 32 ይመልከቱ):: ሕግን መቃወም ከእግዚአብሔር በዓለም ላይ የተመሠረተውን መንግሥት አለመቀበል ሲሆን፣ ይህም የሚያስከትለው ፍርድን ነው::

ገዥዎች ሰይፍ የታጠቁት ፍርድን ለማስፈጸም ሲሆን፣ ይህም ሕይወትን እስከ ማጥፋት ይደርሳል:: እግዚአብሔር ሰዋዊ መንግሥትን ያቋቋመበት ምክንያት ሰው ኃጢአተኛ ስለሆነና በላዩ ላይ ሥልጣን ያለው አካል መኖር ስላለበት ነው:: እግዚአብሔር ለመንግሥታት ሰይፍን ያስታጠቃቸው ሲሆን፣ በዚህ ሥልጣናቸው ለመቅጣት እንዲሁም ለመግደል እንዲችሉ ነው:: በዘፍጥረት 9:5-6 ዐይንን ስለ ዐይን ፍርድ ተፈቅዶአል፤ እንዲቆምም አልተደረገም:: መንግሥት በእግዚአብሔር ስለተሾመ ምንም እንኳን ሥልጣን ላይ ያለውን ሰው ባናከብርም፣ ሥልጣኑን ልናከብር ይገባናል::

ጳውሎስ በአገልግሎቱ ሕይወቱን ለማዳንና አገልግሎቱን ለመቀጠል የሮምን ሕግ ከአንድ ጊዜ በላይ ተጠቅሞበታል:: በሐዋርያት ሥራ የተጠቀሱት መቶ አለቃዎች በባሕሪያቸው የተመሰገኑና የተመሠከረላቸው ነበሩ:: የመንግሥት ሠራተኞች

አማኞች ባይሆኑም፣ መንግሥትን ያቋቋመው እግዚአብሔር ስለሆነ፣ «የእግዚአብሔር አገልጋዮች ናቸው»::

*ለ) ስለ ሕሊናችን ስንል* (13:5-7)- አሁን ምክንያቶቻችንን ትንሽ ከፍ እናድርግ:: ማንኛውም ዜጋ ቅጣትን ፈርቶ ሕግን ሊታዘዝ ይችል ይሆናል:: ክርስቲያን ግን መታዘዝ ያለበት ከሕሊና የተነሣ ነው:: መንግሥት በሕሊናችን ጣልቃ መግባት ከጀመረ ግን፣ ክርስቲያን ከሰዎች ይልቅ እግዚአብሔርን መታዘዝ አለበት (የሐዋ. 5:29):: ነገር ግን፣ ሕጉ ትክክል ከሆነ፣ ክርስቲያን ስለ በጎ ሕሊናው ሊታዘዘው ይገባል (1ኛ ጢሞ. 1:5፣19፤3:9፤4:2፤ እና የሐዋ. 24:16)::

ቁጥር 7 ቀረጥን፣ ግብርንና ክብርን መስጠት እንዳለብን ያዘናል:: ቀረጥን ባንከፍል ሕጉን፣ ባለሥልጣናትንና ጌታን አላከበርንም ማለት ነው:: ይሄ ደግሞ የአማኙን ሕሊና ይጎዳል ገንዘቡ ስለሚውልበት ሁኔታ ብዙ የማንስማማ ቢሆንም፣ ገንዘቡን ባለመክፈላችን ከሕሊናችን ጋር ልንጋጭ አይገባንም::

*ሐ) ስለ ፍቅር ብለን* (13:8-10) -- ጳውሎስ ከመንግሥት ባለሥልጣናት በተጨማሪ ሌሎች ሰዎችንም በመጨመር የኃላፊነት አድማሳችንን ያሰፋዋል:: «እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ» የሚለው የክርስትና ሕይወት መሠረታዊ መርሆ ነው:: ክርስቶስ የሰጠን አዲስ ትእዛዝ ነው (ዮሐ. 13:34):: ፍቅርን በተግባር ስናውል፣ ተጨማሪ ሕግ አያሻንም፣ ምክንያቱም ፍቅር ሁሉን ይሸፍናል:: ሌሎችን ከወደድናቸው፣ በእነርሱ ላይ ኃጢአት አንሠራም:: ዐሥርቱ ትእዛዛት በአዲስ ኪዳን በብዛት ያልተጠቀሱበትን ምክንያት ይህ ያስረዳል:: በነገራችን ላይ ሰንበትን ማክበር በመልእክቶች ውስጥ በአዲስ ኪዳን ፈጽሞ አልተጠቀሰም:: እንደ አማኝነታችን የምንኖረው ከጸጋ በታች እንጂ ከሕግ በታች አይደለም:: እግዚአብሔርንና ሌሎችን ለመታዘዝ የሚያነሣሣን በልባችን ያለው የክርስቶስ ፍቅር ነው::

«ለማንም ዕዳ አይኑርባችሁ» የሚለው የክርስቲያኖች ገቢና ወጪን በማስመልከት ነውን? አንዳንድ ሰዎች ይህንን በማመን

ባለዕዳ መሆን ኃጢአት ነው ይላሉ:: በቻይና ሚስዮናዊ የነበረው ሃድሰን ቴይለር በዚህ ጥቅስ ላይ ተመሥርቶ ጨርሶ አይበደርም ነበር:: ቻርልስ ስፐርጀን የተባለው ታላቁ የባፕቲስት ሰባኪም እንዲሁ ያምን ነበር:: ሆኖም፣ መጽሐፍ ቅዱስ መበደርንና ሌሎች ትርፍ የሚያስገኙ ሕጋዊ የገንዘብ ግብይቶችን አይከለክልም:: መጽሐፍ ቅዱስ የሚከለክለው ከፍተኛ ወለድን፣ ወንድሞችን መበዝበዝንና ዕዳን አለመክፈልን ነው (ዘጸ. 22:25-27ንና ነህምያ 5:1-11ን ይመልከቱ):: ማቴዎስ 25:27 እና ሉቃስ 19:23 እንደሚያመለክቱት በባንክ ማስቀመጥም ሆነ ትርፍ ለሚያስገኝ ተግባር ገንዘብን ማዋል ስሕተት እንዳልሆነ ይናገራል:: ማንም ሰው ቢሆን አላስፈላጊ ዕዳ ውስጥ መዘፈቅ ወይም ሊሠራው የማይችለውን ውል መፈጸም የለበትም:: «አትስረቅ» ሮሜ 13:8ን ሙሉ በሙሉ ከገንዘብ ጋር ከሚያያዙ ሕጋዊ ግዴታዎች ቃሉን ትንሽ የተለጠጠ ያደርገዋል እላለሁ::

በዚህ ክፍል፣ ጳውሎስ የችግር ሁሉ ምንጭ በሆነው በሰው ልብ ላይ ትኩረት አድርጓል:: የሰው ልብ ኃጢአተኛ በመሆኑ፣ እግዚአብሔር መንግሥታትን አቋቋመ:: የሰው ልብ በሕግ ሊለወጥ አይችልም:: የሰው ልብ ራስ ወዳድ ስለሆነ፣ ሊለወጥ የሚችለው በእግዚአብሔር ጸጋ ብቻ ነው::

*መ) ለኢየሱስ ብለን* (13:11-14) – ሕግን የምንታዘዝበትን ምክንያት በተመለከተ፣ ረጅም ርቀት ተጉዘናል:: ከሕሊናችን ፍርሃት እስከ ፍቅር፣ ከዚያም ለኢየሱስ ክርስቶስ ስንል እስከሚለው ደርሰናል:: አጽንዖት የሚሰጠው በክርስቶስ ዳግም ምጽአት ላይ ነው:: ሲመለስ እንደ አገልጋዮቹ፣ ታማኝ ሆነን መገኘት እንፈልጋለን:: መዳናችን ሊፈጸም ተቃርቧል! ንጋቱ ወገግ እያለ ነው! ስለዚህ ተዘጋጁ!

በጌታ ምጽአት ብርሃን ጳውሎስ ብዙ ተግሣጾችን ሰጥቷል:: የመጀመሪያው፣ «ንቁ!» ሲሆን፣ ከ1ኛ ተሰሎንቄ 5:1-11 እና ማቴዎስ 25:1-13 ጋር አያይዙት:: ሁለተኛው፣ «ንጹ!» ሲሆን፣ ጌታ ሲመለስ ቆሻሻ ልብስ ለብሰን መገኘት አንፈልግም (1ኛ

ዮሐንስ 2:28-3:3)። ክርስቲያን የሚለብሰው የብርሃንን ጋሻ ነው እንጂ፣ የጨለማውን ሥራ አይደለም። በኃጢአት በሚገኝ ደስታ በዓለማዊነት ውስጥ አይዘፈቅም። በመጨረሻም፣ ጳውሎስ ሲገሥጽ፣ «አደጉ» ብሏል (ቁ. 14)። ኢየሱስን «መልበስ» ማለት የበለጠ እርሱን በመምሰል ለዕለት ኑሮአችን የሚያስፈልገንን ከእርሱ በእምነት መቀበልን ያሳያል። እንደምንበላው ምግብ መጠን እናድጋለን። ለዚህ ነው እግዚአብሔር የኃጢአት ተፈጥሮአችንን እንዳንመግብ የሚያስጠነቅቀን። ኃጢአተኛውን ተፈጥሮ (ሥጋ) ብዙ ከመገብነው፣ እንወድቃለን። በሚያረሰርሰው መንፈስ ቅዱስ ውስጣችንን ከመገብነው ደግሞ፣ ስኬታማ እንሆናለን።

በሌላ አባባል፣ ክርስቲያን ምርጥ ዜጋ ሊሆን ይገባዋል። ክርስቲያኖች ሁልጊዜ በፖለቲካ ወይም በፓርቲዎች ላይስማሙ ይችላሉ። ነገር ግን ሁሉም የሰው መንግሥት እንደሚያስፈልግ ይስማማሉ።

# ሮሜ 14:1-15:7

በእምነት የደከመውንም ተቀበሉት፣ በአሳቡም ላይ አትፍረዱ። ሁሉን ይበላ ዘንድ እንደ ተፈቀደለት የሚያምን አለ፣ ደካማው ግን አትክልት ይበላል። የሚበላ የማይበላውን አይናቀው፤ የማይበላውም በሚበላው አይፍረድ፣ እግዚአብሔር ተቀብሎታልና። (ሮሜ 14:1-3)

ከእኛ አንድ ስንኳ ለራሱ የሚኖር የለምና፣ ለራሱም የሚሞት የለም፤ በሕይወት ሆነን ብንኖር ለጌታ እንኖራለንና፣ ብንሞትም ለጌታ እንሞታለን። እንግዲህ በሕይወት ሆነን ብንኖር ወይም ብንሞት የጌታ ነን። ስለዚህ ነገር ሙታንንም ሕያዋንንም ይገዛ ዘንድ ክርስቶስ ሞቶአልና ሕያውም ሆኖአልና።

አንተም በወንድምህ ላይ ስለ ምን ትፈርዳለህ? ወይስ አንተ ደግሞ ወንድምህን ስለ ምን ትንቃለህ? ሁላችን በክርስቶስ ፍርድ ወንበር ፊት እንቆማለንና ። (ሮሜ 14:7-10)

በራሱ ርኩስ የሆነ ነገር እንደ ሌለ በጌታ በኢየሱስ ሆኜ አውቄአለሁ ተረድቼአለሁም፤ ነገር ግን ምንም ርኩስ እንዲሆን ለሚቈጥር ለእርሱ ርኩስ ነው። ወንድምህንም በመብል ምክንያት የምታሳዝን ከሆንህ እንግዲህ በፍቅር አልተመላለስህም። ክርስቶስ ስለ እርሱ የሞተለትን እርሱን በመብልህ አታጥፋው። እንግዲህ ለእናንተ ያለው መልካም ነገር አይሰደብ፤ የእግዚአብሔር መንግሥት ጽድቅና ሰላም በመንፈስ ቅዱስም የሆነ ደስታ ናት እንጂ መብልና መጠጥ አይደለችምና። (ሮሜ 14:14-17)

እኛም ኃይለኞች የሆንን የደካሞችን ድካም እንድንሸከም ራሳችንንም ደስ እንዳናሰኝ ይገባናል። እያንዳንዳችን እንድናንጸው እርሱን ለመጥቀም ባልንጀራችንን ደስ እናሰኝ። ክርስቶስ ራሱን ደስ አላሰኘምና፤ ነገር ግን፡- አንተን የነቀፉበት ነቀፋ ወደቀብኝ ተብሎ እንደ ተጻፈ ሆነበት። (ሮሜ 15:1-3)

# 12

# ክርስቲያኖች በማይስማሙበት ጊዜ

መለያየት በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል ትልቅ ችግር ሆኖ የኖረ ጉዳይ ነው። በብሉይ ኪዳን እንደተዘገበው የእርስ በርስ ጦርነትና የቤተሰብ አለመግባባት በእስራኤል ሕዝብ መካከል የነበረ ሲሆን፣ በአዲስ ኪዳን የተጠቀሱት አብያተ ክርስቲያናትም መከፋፈል ይታይባቸው ነበር። በቆሮንቶስ የነበሩት ክርስቲያኖች በመሪዎች ምርጫ ተለያይተው፣ ከአባላቱ አንዳቸው ሌላውን እስከ መክሰስ ደርሰዋል (1ኛ ቆሮ. 1:10-13፤ 6:1-8)። በገላትያ የነበሩ ቅዱሳንም እርስ በርሳቸው «ይነካከሱና ይበላሉ» ነበር (ገላ. 5:15)፣ በኤፌሶንና ቆላስይስ የነበሩት ቅዱሳንም ስለ ክርስቲያናዊ አንድነት ጥቅም ማሳሰቢያ አስፈልጓቸው ነበር (ኤፌ. 4:1-3፤ ቆላ. 2:1-2)። በፊልጵስዩስ በነበረችው ቤተ ክርስቲያንም ሁለት ሴቶች ባለመግባባታቸው ሳቢያ ቤተ ክርስቲያኗ ልትከፋፈል እንደነበር እናያለን (ፊልጵ. 4:1-3)። ዘማሪው፣ «ወንድሞች በኅብረት ቢቀመጡ፣ እነሆ፣ መልካም ነው፣ እነሆም ያማረ ነው» [መዝ. (133):1-2] ያለው ለዚህ ነው።

የአንዳንዶቹ ችግሮች መንሥኤ በቤተ ክርስቲያን ያሉት አማኞች የነበሩበት ሁኔታ የተለያየ በመሆኑ ምክንያት ነው። አይሁድ ለምሳሌ የዳኑት ለመርሳት ከሚያስቸግር የሕግ ወግ አጥባቂነት ሕይወት ነው። አሕዛብ ደግሞ ስለሚበላና ስለማይበላ እንስሳ ወይም ስለ በዓል ቀናት ተጨንቀው ተጠበው አያውቁም። በታሪክ ውስጥ የመጀመሪያው የነበረው የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ፣ የተወያየው ክርስቲያን ከሕግ ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት ጉዳይ ነበር (የሐዋ. 15)።

በሮም የነበሩት አማኞችም ስለ ተለዩ አመጋገቦችና ስለ ተለዩ የበዓላት ቀናት በመካከላቸው መለያየት ነበር። አንዳንዶቹ ሥጋ መብላት ኃጢአት ስለ መሰላቸው፣ አትክልት ብቻ ይበሉ ነበር። አንዳንዶች የአይሁድ በዓላትን አለመጠበቅ ኃጢአት ይመስላቸው

ነበር:: እያንዳንዱ ክርስቲያን የተረዳውን ለራሱ ቢጠብቅ ምንም ችግር ባልተፈጠረ ነበር:: ነገር ግን እርስ በርሳቸው መፈራረድና መነቃቀፍ ጀመሩ:: አንደኛው ቡድን ሌላኛው በፍጹም መንፈሳዊ እንዳልሆነ ደመደመ::

የሚያሳዝነው ዛሬም በዘመናችን ግልጽ ያልሆኑና ለእያንዳንዱ አማኝ ትክክል ወይም ስሕተት ያልሆኑ ነገሮች አሉ:: አንዳንድ ልምምዶች ትክክል እንዳልሆኑ እናውቃለን፣ ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ስለሚኮንናቸው ነው:: ሌሎች ደግሞ ትክክል የሆኑ አሉ፣ ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ እንድንጠብቃቸው ያዘናልና:: ነገር ግን በቅዱሳት መጻሕፍት በግልጽ ብያኔ ባልተሰጠባቸው ጉዳዮች ላይ ተጨማሪ ምሪት ያስፈልገናል:: ጳውሎስ ለዚህ ምሪት አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን ሰጥቷል:: አማኞች በጣም መሠረታዊ ባልሆኑ ጉዳዮች ላይ ባይስማሙም፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንድነታቸውን ጠብቀው መኖር እንሚችሉ አብራርቷል:: ለአንባቢዎቹ ሦስት ምክሮችን ሰጥቷቸዋል::

## 1. እርስ በርሳችሁ ተቀባበሉ (14:1-12)

እንደምታዩት ይህ ክፍል ጀምሮ የሚጨርሰው በዚህ ምክር ነው (ሮሜ 15:7):: ጳውሎስ የሚናገረው «በእምነት ለበረቱት» ሲሆን፣ እነርሱም በክርስቶስ ያገኙትን መንፈሳዊ አርነት ተረድተው የምግብ ወይም የቅዱስ ቀናት ወግ አጥባቂ ሕጎች (ደንቦች) ባሪያ አልነበሩም:: «በእምነት ደካማዎቹ» ደግሞ ያልበሰሉት አማኞች ሲሆኑ፣ ምን እንደሚመገቡና መቼ እንደሚያመልኩ ሕጎችን ለመጠበቅ ግዴታ እንዳለባቸው ያስቡ ነበር:: ብዙ ሰዎች የበሰሉ ክርስቲያኖች ትእዛዛትን ቀጥ ብለው የሚከተሉ እንደሆኑ አድርገው ቢያስቡም ነገሩ ግን እንዲህ አይደለም:: በሮም ጉባኤ ደካማ ክርስቲያን የተባሉት፣ ከሕግ ጋር የተጣበቁና በጌታ ባገኙት ነጻነት የማይደሰቱበት ናቸው:: ደካማ ክርስቲያን የተባሉት ጠንካራ ክርስቲያኖች በተባሉት ላይ ይፈርዱባቸው ስለነበር፣ ብርቱዎቹ ክርስቲያኖች ደካማዎቹን ይንቋቸው ነበር::

«እርስ በርሳችሁ ተቀባበሉ» የሚለው የጳውሎስ የመጀመሪያው ምክር ሲሆን፣ መቀባበል ያስፈለገበትንም አራት ምክንያቶች ዘርዝሯል:-

ሀ) *እግዚአብሔር ተቀብሎናል* (14:1-3)- ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስላለው ክርስቲያናዊ ኅብረት መመዘኛውን ማውጣት የጌታ እንጂ የእኛ ኃላፊነት አይደለም:: ሰው ሠራሽ አጥሮችን በራሳችን ልምምድ ላይ ተመሥርተን ማውጣቱ፣ ከእግዚአብሔር ቃል አልፈን መሄዳችንን ያመለክታል:: እግዚአብሔር ስለተቀበለን፣ እርስ በርሳችን ልንቀባበል ይገባናል:: በእነዚህ ነገሮች መከራከር፣ መፈራረድ ወይም መጠላላት አይገባንም:: ምናልባትም ቅዱስ አውግስጢኖስ፣ «በመሠረታዊው ጉዳይ አንድነት፣ መሠረታዊ ባልሆነው ነገር ነጻነት፤ በነገር ሁሉ ደግሞ ልግስና» በማለት ጉዳዩን በጥሩ ሁኔታ ገልጸውታል::

እግዚአብሔር ጴጥሮስ ለአሕዛብ ወንጌልን ይዞ እንዲሄድ ሲያዘው፣ ቤተ ክርስቲያኗ ጴጥሮስ ከእነዚህ አዲስ ክርስቲያኖች ጋር በጋራ በመመገቡ ኮነነችው (የሐዋ. 11:1-3):: ነገር ግን እግዚአብሔር አሕዛብን እንደ ተቀበለ በግልጽ ለማሳየት በበዓለ ኀምሳ ለአይሁድ አማኞች የሰጠውን መንፈስ ቅዱስ ለአሕዛብም ሰጣቸው (የሐዋ. 10:44-48፤11:15-18):: ጴጥሮስ ይህንን እውነት በዘላቂነት አልተከተለም:: በኋላ ላይ በአንጾኪያ ከነበሩ አሕዛብ ክርስቲያኖች ጋር ኅብረት ለማድረግ ባለመፈለጉ ጳውሎስ ገሥጾታል (ገላ. 2:11-13):: እግዚአብሔር ለጴጥሮስም ሆነ ለጳውሎስ የክርስቲያኖች ኅብረት መሠረቱ ምግብና የሃይማኖት ቀን ቆጠራ አለመሆኑን ገልጾላቸዋል::

በየቤተ ክርስቲያኑ ደካማና ብርቱ ክርስቲያኖች አሉ:: ብርቱዎቹ መንፈሳዊ እውነትን ተረድተው በሥራ ላይ ሲያውሉት፣ ደካማዎቹ ደግሞ ወደዚህ ብስለትና ነጻነት አልደረሱም:: ደካማ ብርቱውን መኮነን ወይም መንፈሳዊ እንዳልሆነ መቁጠር የለበትም:: ብርቱው ደግሞ ደካማውን ያልበሰለ ብሎ መጥራትም ሆነ መጥላት አይኖርበትም::

እግዚአብሔር ብርቱዎቹንም ደካማዎቹንም ተቀብሏቸዋል:: ስለዚህ እርስ በርሳቸው ሊቀባበሉ ይገባቸዋል::

*ለ) እግዚአብሔር የራሱን ጠብቆ ያቆያል (14:4)* - ብርቱው ክርስቲያን በደካማው የተኮነነ ሲሆን፣ ጳውሎስ ይህን ያወገዘበት ምክንያት ደካማው ክርስቲያን በእግዚአብሔር ቦታ ሆኖ በብርቱው ላይ መፍረድ እንደማይገባው ለማሳየት ነው:: ጌታችን እግዚአብሔር ነው፤ ክርስቲያን ደግሞ አገልጋይ ነው:: ይህንን ግንኙነት ማቃወስ ስሕተት ነው::

በክርስትና ሕይወታችን የምናገኘው ስኬታማነት በሌሎች ክርስቲያኖች አስተሳሰብ ወይም አቋም ስለማይደገፍ ልንበረታታ ይገባናል:: ፈራጁ እግዚአብሔር ነው፣ ሊያቆመንም የሚችለው እርሱ ነው:: «አገልጋይ» የሚለው ቃል የሚያመለክተው ክርስቲያኖች ለጌታ በመሥራት መትጋት እንዳለባቸው ሲሆን፤ በዚህ ምክንያት ሌሎች ክርስቲያኖች ላይ ለመፍረድ ወይም ሌሎችን ለመኮነን ጊዜ አይኖራቸውም:: ሰዎችን ለክርስቶስ የሚማርኩ የሌሎች ቅዱሳንን ሕይወት ከመፈተሽ የላቀ ሥራ አላቸው::

*ሐ) ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ ነው* ( (14:5-9)- «ጌታ» የሚለው ቃል በእነዚህ ቁጥሮች ብቻ ስምንት ጊዜ ተጽፎ ይገኛል:: ማንም ክርስቲያን በሌላ ክርስቲያን ሕይወት «እንደ እግዚአብሔር» ሊሆን አይችልም:: ልንጸልይ፣ ልንመክርና ልንገሥጽ እንችላለን፣ ነገር ግን የእግዚአብሔርን ቦታ ልንይዝ አንችልም:: ምግብን ወይም ቀንን «ቅዱስ» የሚያደርገው ምንድን ነው? ከጌታ ጋር ስናገናኘው ነው:: የተለዩ ቀናትን ቅዱስ አድርጎ የሚመለከት ሰው ይህን የሚያደርገው «ለጌታ» ነው:: እያንዳንዷን ቀን እንደተቀደሰች የሚያስብም «ለጌታ» ሲል ያደርገዋል:: ሥጋ የሚበላ ክርስቲያን ጌታን ያመሰግናል:: ሥጋን የሚተው ደግሞ «ለጌታ ሲል ይተዋል»:: «እያንዳንዱ በገዛ አእምሮው አጥብቆ ይረዳ» (ቁ.5) ማለቱ እያንዳንዱ ሰው የሚያደርገውን ለጌታ ብሎ

እንደሚያደርግ ይመልከት እንጂ እንዲያው ሚዛን በጎደለው ሁኔታ ወይም በአምሮት ሊሆን አይገባም።

በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት ያሉት አንዳንድ ልምምዶችና የምንሰጣቸው ደረጃዎች ወግን የተከተሉ እንጂ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደሉም። «ሰይጣን በአየር ላይ ሥልጣን ያለው አለቃ» ስለሆነ የክርስቲያን ሬድዮን ጣቢያ የሚቃወሙ የተሰጡ ክርስቲያኖች እንደነበሩ እናስታውሳለን። እንዲያውም አንዳንዶቻችን መጽሐፍ ቅዱስ የመተርጎምን ተግባር የቀጥተኛ ነት መመዘኛ ያደርጋሉ። ቤተ ክርስቲያን የደከመችውና የተከፋፈለችው ክርስቲያኖች ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲገዛ ስላልፈቀዱለት ነው።

ይህን እውነት በተመለከተ አንድ አስደናቂ ምሳሌ በዮሐንስ 21:15-25 ተሰጥቷል። ኢየሱስ ጴጥሮስን ወደ ቀድሞው የሐዋርያነት ሥልጣኑ መልሶታል። እንደገናም «ተከተለኝ» ብሎታል። ጴጥሮስ ኢየሱስን መከተል ጀመረ፣ ከዚያም ሌላ ሰው ሲከተለው ሰማ። እርሱም ሐዋርያው ዮሐንስ ነበረ።

ከዚያም ጴጥሮስ ኢየሱስን፣ «ጌታ ሆይ፣ ይህ ሰው ምን ያደርጋል?» ብሎ ጠየቀው።

የጌታን መልስ አስተውሉ:- «እስክመጣ ድረስ ይኖር ዘንድ ብወድስ ምን አገደህ? አንተ ተከተለኝ» አለው። በሌላ አበባል፣ «ጴጥሮስ፣ እኔን የሕይወትህ ጌታ ማድረግህን እርግጠኛ ሁን። የዮሐንስን ጉዳይ ለእኔ ተወው።» ማለት ነው። አማኞች መሠረታዊ ባልሆነ ጉዳይ ባለመስማማታቸው ሌሎች ክርስቲያኖችን ሲወቅሱ ስሰማ፣ በእግዚአብሔር ቃል የተከለከለ ከሆነ፣ «አንተን ምን ገዶህ? ክርስቶስን ተከተል! እርሱ ብቻ ጌታህ ይሁን!» እላለሁ።

ጳውሎስ አማኝ ከክርስቶስ ጋር ስላለው አንድነት አጽንኦት ሰጥቷል፣ «በሕይወት ሆነን ብንኖር ለጌታ እንኖራለንና ብንሞትም ለጌታ እንሞታለን» (ቁ. 8)። በመጀመሪያ ኃላፊነት ያለብን ለጌታ ነው። ክርስቲያኖች ለነቀፌታ ወደ ወንድማቸው

ከመሄዳቸው በፊት፣ በጸሎት ወደ ጌታ ቢቀርቡ ኖሮ፣ በቤተ ክርስቲያን የጠነከረ ኅብረት ይኖር ነበር።

*መ) ኢየሱስ ክርስቶስ ዳኛ ነው* (14፡10-12)- ጳውሎስ ደካማውን ክርስቲያን፣ «አንተም በወንድምህ ላይ ስለምን ትፈርዳለህ?» በማለት ይጠይቀዋል? የበረታውን ክርስቲያን ደግሞ፣ «አንተ ወንድምህን ስለምን ትንቃለህ?» ብሎ ይጠይቃል። ብርቱም ሆነ ደካማው ክርስቲያን በክርስቶስ የፍርድ ዙፋን ፊት ቀርበው በጌታ ይዳኛሉ እንጂ አንዳቸው አንዳቸውን አይዳኙም።

የክርስቶስ የፍርድ ወንበር፣ ክርስቲያኖች ሁሉ ስለ *ሥራ*ቸው በጌታ የሚፈርድባቸው ቦታ ነው። ክርስቶስ የኃጢአትን ዋጋ ስለ ከፈለና ኩነኔ ስለሌለብን የምንዳኘው ስለ ኃጢአታችን አይደለም (ሮሜ 8፡1)። «የፍርድ ወንበር» የሚለው የግሪኩ ቃል የሚያመለክተው በአትሌቲክስ ውድድር ወቅት ዳኞቹ የሚቀመጡበትን ቦታ ነው። አንድ ተወዳዳሪ ሕግ ሲጥስ ቢያዩት ወዲያውኑ ከጨዋታ ውጭ ያደርጉታል። በውድድሩም መጨረሻ ሽልማት የሚሰጡት ዳኞቹ ናቸው (1ኛ ቆሮ. 9፡24-27ን ይመልከቱ)። 1ኛ ቆሮ. 3፡10-15 ስለ ክርስቶስ የፍርድ ወንበር ሌላ *ሥዕል* ይሰጠናል። ጳውሎስ አገልግሎታችንን ከቤተ መቅደስ ግንባታ ጋር አወዳድሮታል። በርካሽ ቁሳቁስ ብንገነባ፣ እሳቱ ያቃጥለዋል። በውድና በጠንካራ ቁሳቁስ ብንሠራ ግን፣ *ሥራ*ችን የተዋጣ ይሆናል። *ሥራዎ*ቻችን ፈተናውን ካለፉ፣ ሽልማት እንቀበላለን። ከተቃጠሉ ግን፣ ሽልማቱን እናጣለን፣ ነገር ግን «በእሳት እንደሚድን» እንድናለን።

ክርስቲያን ለክርስቶስ የፍርድ ወንበር እንዴት መሰናዳት ይችላል? ኢየሱስ ክርስቶስን የሕይወቱ ጌታ በማድረግና በታማኝነት እርሱን በመታዘዝ ነው። በሌሎች ክርስቲያኖች ላይ በመፍረድ ፋንታ በሕይወታችን ሌላ ዳኛ ስላለ ክርስቶስ በፍርዱ ወንበር ክርስቶስን ለመገናኘት ራሳችንን እናዘጋጅ (ሉቃስ 12፡41-48ን፤ ዕብ. 13፡17ንና 1ኛ ዮሐ. 2፡28ን ይመልከቱ።)

በኃጢአታችን አለመከሰሳችን እግዚአብሔርን እንዳንታዘዝ ሊያበረታታን አይገባም:: በሕይወታችን የሚኖረው ኃጢአት ክርስቶስን እንደሚገባ እንዳናገለግለው የሚያደርገን ሲሆን፣ ሽልማታችንንም ያሳጣናል:: ሎጥ እንደ አጎቱ አብርሃም ከጌታ ጋር ስላልተጓዘ ምስክርነቱን በቤተሰቡ መሃል እንኳን ሳይቀር አጣ:: በመጨረሻው ፍርድ ሲመጣ ከእሳትና ዲን ቢድንም፣ ዕድሜ ልኩን የኖረለት ሀብት ግን ተቃጠለ:: «በእሳት እንደሚድን» ዳነ::

ጳውሎስ እያንዳንዳቸው ስለ ሌሎች ሳይሆን፣ ስለ ራሳቸው መልስ እንደሚሰጡ ገልጾላቸዋል:: የራሳቸው ነገር ጥሩ መሆኑን ማረጋገጥ ነበረባቸው:: ትኩረቱ የጌትነትን መርሆች በመግለጽ ላይ ሲሆን፣ ኢየሱስ ክርስቶስን የሕይወታችሁ ጌታ፣ እንዲሁም በሌሎችም ክርስቲያኖች ሕይወት ጌታ እንዲሆን ፍቀዱለት ይላቸዋል::

በእንግሊዝ አገር ከነበሩት ክርስቲያን ሰባኪዎች መካከል ቻርልስ ስፐርጀንና ዮሴፍ ፓርከር ኃያል የወንጌል ሰባኪዎች ነበሩ:: በአገልግሎታቸው ጅማሬ ላይ ኅብረት በማድረግ አንዳቸው በሌላኛው መድረክ ላይ ይሰብኩ ነበር:: ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን፣ ሳይስማሙ ቀሩና ነገራቸው በጋዜጣ ላይ መውጣት ጀመረ:: ስፐርጀን ቲያትር ያያልና መንፈሳዊ አይደለም ሲል ፓርከርን ከሰሰው:: የሚገርመው ደግሞ ስፐርጀን ደግሞ ብዙ ክርስቲያኖች የሚኮንኑትን ሲጋር ያጨስ ነበር:: ማንኛቸው ልክ ነበሩ? የተሳሳተውስ ማን ነበር? ምናልባት ሁለቱም ተሳስተዋል! በክርስትና ሕይወት አጠያያቂ በሆኑ ጉዳዮች ላይ እውነተኛ አማኞች ሳይነታረኩ ለመስማማት አይችሉምን? «እግዚአብሔር ከእኔ ጋር የማይስማሙ ሰዎችን እንደሚባርክ ተምሬአለሁ» ብሎ አንድ ወዳጄ ሲነግረኝ፣ እኔም ለራሴ ተማርኩ:: ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ ሲሆን፣ በራሱ አገልጋዮች እንደ ፈቀደ እንዲያደርግ እንፈቅድለታለን ማለት ነው::

## 2. እርስ በርሳችሁ ተናነጹ (14:13-23)

በመጀመሪያው ምክር ላይ ብናቆም፣ ክርስቲያኖች እርስ በርሳቸው ባሉበት ታግረው፣ ደካማውም ደካማ ሆኖ እንዲቀር የሚያስተምር ይመስላል:: ነገር ግን ይህ ሁለተኛው ምክር ነገሮችን በበለጠ ያብራራል:: አጽንኦቱ «በጌታና አገልጋይ» ላይ ሳይሆን፣ «በወንድማማችነት» ላይ ነው:: የወንድማዊ ፍቅር መርህ ነው:: እርስ በርሳችን ከተዋደድን፣ እርስ በርሳችን እንተናነጻለን፣ በእምነትም እርስ በርሳችን እናድጋለን:: አንባቢዎቹ ወንድሞቻቸውን እንዲረዱ ጳውሎስ ብዙ እውነታዎችን አካፍሏቸዋል::

*ሀ) የክርስቲያኖች ሕይወት አንዱ የሌላውን ይዳስሳል* (14:13-15)- እርስ በርሳችን አንዱ የሌላውን ሕይወት የሚለውጥበት መንገድ እንዳለ አስተውሉ:: ሌሎች እንዲሰናከሉ፣ እንዲያዝኑ ወይም እንዲጠፉ ልናደርግ እንችላለን:: ጳውሎስ ብርቱው ክርስቲያን ደካማውን ስለሚለውጥበት መንገድ ተናግሯል:: ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 8-9 ላይ፣ «ክርስቲያኖች ለጣዖት የተሠዋውን ሥጋ መብላት ይገባቸዋልን?» በሚለው ጥያቄ የነበረውን ችግር ተጋፍጦ ነበር:: በዚህ ቦታ ዕውቀትና ፍቅር አብረው መሥራት እንዳለባቸው አመልክቷል «እውቀት ያስታብያል ፍቅር ግን ያንጻል» (1ኛ ቆሮ. 8:1):: ብርቱው ክርስቲያን መንፈሳዊ ዕውቀት አለው፣ ነገር ግን ፍቅር ከሌለው፣ እውቀቱ ደካማዎቹን ክርስቲያኖች ይጎዳል:: እውቀት በፍቅር መርገብ አለበት::

ብዙ ጊዜ ሕፃናት በቁምሣጥን ውስጥ የተደበቀ ነገር ያለ ስለሚመስላቸው ጨለማን ይፈራሉ:: እናቱ ልጇን ምንም ክፉ ነገር በቤት ውስጥ እንደማያጋጥመው ታውቃለች:: ነገር ግን የእርሷ እውቀት በራሱ ለልጁ ይህንን ሊያረጋግጥለት ወይም ሊያጽናናው አይችልም:: ሕፃኑ ፍርሃትን እንዲያስወግድ ልትሞግቱት አትችሉም:: እናቱ በአልጋው ዳር ተቀምጣ በፍቅር ልጇን ስታዋራውና ሁሉም ነገር ሰላም እንደሆነ ስታረጋግጥለት

ያለፍርሃት እንቅልፍ ይወስደዋል:: እውቀት ከፍቅር ጋር ሲሆን ደካማው ሰው ጠንክሮ እንዲያድግ ይረዳዋል::

«በራሱ ርኩስ የሆነ ነገር የለም» ሲል ጳውሎስ ጽፏል (ቁ.14):: በራሱ ርኩስ የሆነ ምግብ፣ በራሱ ርኩስ የሆነ ቀን ወይም በራሳቸው ርኩስ የሆኑ ሕዝቦች የሉም:: (ጴጥሮስ ይህንን እንዴት እንደተማረ ለማየት የሐዋርያት ሥራ 10ን ይመልከቱ):: የአንድን ነገር ጥራት የሚወስነው፣ በሰው ላይ የሚደርሰው ተጽዕኖ ነው:: አንድ ሰው አንድን መጽሐፍ አንብቦ ላይረበሽ ይችላል:: ሌላው ደካማ ክርስቲያን ግን አንብቦ በኃጢአት ሊፈተን ይችላል:: ፍሬ ነገሩ «እንዴት ነው የሚለውጠኝ?» ሳይሆን «እኔ ይህን ባደርግ ወንድሜን ሊጎዳው ይችል ይሆንን?» መሆን አለበት:: ያሰናክለው ይሆን? የምወደውን ምግብ መመገቤ ቢያስደስተኝ ከወንድሜ ጉዳት ጋር ሲመጣጠን ይጠቅመኛልን? በፍጹም አይጠቅምም!

*ለ) ክርስቲያኖች የሚያስቀድሙት ነገር ሊኖር ይገባል (14:16-18)* - እንደ ድሮዎቹ ፈሪሳውያን እኛም ክርስቲያኖች ትንሹን ትልቅ አድርገን እንጠበባለን (ማቴ. 23:23-24):: ከመሠረታዊ የክርስትና እምነት አስተምህሮ ጋር ሲነጻጸሩ እዚህ ግባ በማይባሉ ነገሮች የተከፋፈሉ አብያተ ክርስቲያናትን አውቃለሁ:: ፒያኖው የት እንደሚቀመጥ ወይም እሁድ እሁድ ምን መመገብ እንዳለባቸውና በመሳሰሉ ጥቃቅን ነገሮች የተከፋፈሉ አብያተ ክርስቲያናት እንዳሉ ሰምቻለሁ:: «የእግዚአብሔር መንግሥት. . . መብልና መጠጥ አይደለችም» (ቁ. 17):: «መብል ግን ወደ እግዚአብሔር አያቀርበንም ባንበላም ምንም አይጎድለንም ብንበላም ምንም አይተርፈንም» (1ኛ ቆሮ. 8:8)::

ዘለዓለማዊው ጽድቅ፣ ሰላምና ደስታ በሕይወታችን ቀዳሚውን ስፍራ ሊይዙ ይገባል:: ለመሆኑ ከየት ይመጣሉ? በሕይወታችን ከሚሠራው ከመንፈስ ቅዱስ ይመጣሉ (ሮሜ 5:1-2ን ይመልከቱ):: እያንዳንዱ አማኝ ራሱን ለመንፈስ ቅዱስ ቢያቀርብ፣ እግዚአብሔርን የሚመስል ሕይወት ቢኖር በተራ

ነገር የሚጣሉ ክርስቲያኖች አይኖሩም ነበር። በቤተ ክርስቲያን ለሚኖረው ስምምነት የመንፈሳዊ ነገሮች መሠረታዊና ጥቃቅን ጉዳዮች ቅደም ተከተል አስፈላጊ ነው።

*ሐ) ክርስቲያኖች ለማደግ እርስ በርሳቸው መረዳዳት አለባቸው* (14:19-21) - ብርቱውና ደካማው ክርስቲያን ሁለቱም ሊያድጉ ይገባቸዋል። ብርቱው በፍቅር ሊያድግ ሲገባው፣ ደካማው ደግሞ በእውቀት ሊያድግ ይገባዋል። አንድ ወንድም በእምነት ቢደክም፣ አለመብሰሉን በፍቅር ልናስተናግድ ይገባናል። በእውነት ከወደድነው እንዲያድግ እንረዳዋለን። ለክርስቲያን ጥሬ ሆኖ መኖርም ሆነ ደካማ ሕሊና መያዝ ስሕተት ነው።

በቤታችን ውስጥ የሚፈጸሙ ነገሮች ይህንን የበለጠ እንድንረዳ ያግዙናል። አንድ ልጅ በቤት ውስጥ ሲወለድ፣ ሁሉም ነገር ይለዋወጣል። እናትና አባት መቀስና የመሳሰሉ አደገኛ ነገሮችን በየወንበሩ ላለማስቀመጥ ይጠነቀቃሉ። ልጁ እያደገ ሲሄድ ግን፣ የቤታቸውን ሥርዓት አስተካክለው እንደ አዋቂ ሰው ይቆጣጠሩታል። ልጅ መራመድ ሲማር መደናቀፉ አይቀሬ መሆኑ ተፈጥሮአዊ ነው። ነገር ግን አንድ ጎልማሳ በተደጋጋሚ ቢወድቅ፣ አንድ ችግር እንዳለበት እናውቃለን።

ለጋ ክርስቲያኖች ለማደግ የሚያበረታታቸው ከክፉ የሚጠብቃቸው ኅብረት ያስፈልጋቸዋል። ነገር ግን በዘመናቸው ሁሉ እንደ «ሕፃናት» ልንይዛቸው አንችልም። የከረሙት ክርስቲያኖች በፍቅርና በትዕግሥት እንዳይወድቁ ሊጠነቀቁላቸው ይገባል። ነገር ግን ለጋዎቹ ክርስቲያኖች «በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና እውቀት» ሊያድጉ ይገባቸዋል (2ኛ ጴጥ. 3:18)። በእምነት ሲጠነክሩ፣ ሌሎች አማኞች እንዲያድጉ ማገዝ ይችላሉ። የሰንበት ትምህርት ወይም የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት ትኩረት «ለሕፃናት ክርስቲያኖች» አገልግሎት ብቻ ከሆነ፣ እነዚህ ክርስቲያኖች እንዳያድጉ እያደረግን ሲሆን፣ የበሰሉት የቅዱሳን አገልግሎትንም እናሰናክላለን። ደካሞች ከብርቱዎች ሊማሩ የሚገባቸው ሲሆን፣

ብርቱዎች ደግሞ ደካሞችን ሊወዱ ይገባቸዋል:: ውጤቱም ለእግዚአብሔር ክብር ሰላምና ብስለት ይሆናል::

*መ) ክርስቲያኖች የራሳቸውን አሳብ በሌሎች ላይ በኀልበት መጫን የለባቸውም* (14:22-23) - የእምነት መሠረት በመሆናቸው አንዳንድ እውነቶችን ክርስቲያኖች ሊቀበሏቸው ይገባቸዋል:: ነገር ግን ከቅንነት የሚነሡ አለመስማማቶች ለኅብረታችን መመዘኛ መሆን የለባቸውም:: ስለ አንድ ነገር ከእግዚአብሔር ዘንድ እውነተኛ መረዳት ካገኛችሁ፣ ለራሳችሁ ጠብቁት እንጂ ሌሎች እንዲቀበሉ አታስገድዷቸው:: ማንም ክርስቲያን የሌላውን ክርስቲያን ጽኑ እምነት «ተውሶ» በክርስትና ሕይወቱ ታማኝ ሊሆን አይችልም:: «በእምነት» ይዞ ካልተገበራቸው በቀር ኃጢአትን እያደረገ ነው ያለው:: የሰውየው ያመነባቸው ነገሮች ያልበሰሉ ጥሬዎች ቢሆኑም እንኳ፣ ከሕሊናው ማፈንገጥ የለበትም:: ይህ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ላይ አደጋ ያደርስበታል:: ለምሳሌ፣ የበሰለ ክርስቲያን ጣዖት ምንም እንዳይደለ ያውቃል:: ለጋው ክርስቲያን ግን ከአረማውያን የጣዖት አምልኮ የተለወጠ በመሆኑ፣ አሁንም ጣዖታትን ይፈራል:: የበረታው አማኝ አዲሱን ክርስቲያን ለጣዖት የተሠዋን ሥጋ እንዲበላ ካስገደደው፣ ያልበሰለው ክርስቲያን በሕሊናው ችግር ስለሚገጥመው፣ የበለጠ ይደክማል:: (1ኛ ቆሮ. 8-9 ይመልከቱ::)

ሕሊና የሚበረታው በእውቀት ነው:: ነገር ግን እውቀት በፍቅር መርገብ አለበት:: ካልሆነ ግን፣ በመገንባት ፈንታ ያፈራርሰዋል:: «ምግብ ሁሉ ንጹሕ የመሆኑ» (ቁ. 14 እና 20) እውነት በራሱ ክርስቲያንን አያሳድገውም:: ነገር ግን ለጋዎቹ ክርስቲያኖች ይህንን እውነት በፍቅር ሲማሩ፣ ማደግና ጠንካራ ሕሊና ማዳበር ይችላሉ:: አማኞች የተለያየ እምነት ሊኖራቸው ቢችልም፣ በፍቅር ሊይዟቸው ይገባል::

## 3. አንዱ ሌላውን ያስደስት (15:1-7)

ጳውሎስ *ራስ ወዳድነትን* በተመለከተ ሲያስተምር ራሱን ከብርቱ ቅዱሳን ወገን ፈርጇል:: እውነተኛው የክርስቲያን ፍቅር ራስ ወዳድ አይደለም:: ይልቁንስ ለሌሎች ለማካፈልና ሌሎችን ለማስደሰት ይፈልጋል:: ለጋዎቹን ክርስቲያኖች ለመሸከምም ፈቃደኛ ነው:: በመንፈሳዊ ዕድገታቸው ሊያግዛቸው ይወዳል:: ኃጢአት ሲሠሩ አንታገሳቸውም፣ ነገር ግን እንዳይሠሩ እናበረታታቸዋለን!

ይህን በተመለከተ ታላቁ ምሳሌያችን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: እኛን ለማገልገል ትልቅ ዋጋ ከፍሏል:: ይህን ለማስረዳት ጳውሎስ መዝሙር (69):9ን ጠቅሷል:: ብርቱው ክርስቲያን የሆነን መብል ወይም መጠጥ በመተው ትልቅ መሥዋዕትነት እንደከፈለ ራሱን ይቆጥራልን? ከሆነ የእርሱን መሥዋዕትነት በክርስቶስ መሥዋዕትነት ይመዝን:: የትኛውም የምንከፍለው መሥዋዕትነት ቀራንዮን ሊስተካከል አይችልም::

የአንድ ሰው መንፈሳዊ ብስለት የሚገለጠው ክፉና ደጉን በመለየቱ ላይ ነው:: ሌሎች እንዲረዱ የራሱን መብት ለመተው ፈቃደኛ ነው:: ይህን የሚያደርገው ሌሎችን ለመባረክ እንጂ ሸክም ሆኖበት አይደለም:: አፍቃሪ ወላጆች ለልጆቻቸው መሥዋዕትነት እንደሚከፍሉ፣ የበሰለም አማኝ ለጋ ክርስቲያኖች በእምነት ያድጉ ዘንድ መሥዋዕትነትን ይከፍላል::

ጳውሎስ ሌሎችን የሚያስደስት ኑሮ ለመኖር የሚያስችሉትን ሁለት የመንፈሳዊ ኃይል ምንጮች:- የእግዚአብሔር ቃልና (ቁ. 4) ጸሎት (ቁ. 5-6) እንዲሆኑ አስረድቷል:: መናዘዝ ያለብን ነገር በልጆቻቸው ትዕግሥትን እንደሚያጡ ወላጆች በለጋ ክርስቲያኖች ላይ አንዳንድ ጊዜ ትዕግሥት ማጣታችን ነው:: ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል የሚያስፈልገንን «ትዕግሥትና ብርታትን» ሊሰጠን ይችላል:: ጳውሎስ ይህን መልእክት የቋጫው እርሱ ብቻ የሚሰጠውን መንፈሳዊ አንድነት ከእግዚአብሔር ዘንድ እንዲያገኙ ለአንባቢዎቹ በመጸለይ ነበር::

ይህ የሚያመለክተን የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ዋና ትኩረት በእግዚአብሔር ቃልና በጸሎት ላይ ሊሆን እንደሚገባ ነው:: በቤተ ክርስቲያን አንድነት ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ የደረሰው አደጋ የመጣው ሐዋርያት የእግዚአብሔርን ቃል ለማስተማርና ለመጸለይ ሌሎች ተግባራት ስለከለከሏቸው ነበር (የሐዋ. 6:1-7):: ሸክማቸውን የሚካፈሉ ሌሎች ሰዎችን ሲያገኙ ግን፣ ወደ ቀድሞው አገልግሎታቸው ተመልሰው ቤተ ክርስቲያን ስምምነትንና ዕድገትን ትለማመድ ጀመር::

የዚህ ውጤት፣ ለእግዚአብሔር ክብር መስጠት ነው (ቁ. 7):: መለያየትና አለመስማማት ክብሩን ይዘርፋሉ እንጂ፣ እግዚአብሔርን አያስከብሩም:: አብርሃም ለሎጥ የነገረው ቃል ዛሬም ለዘመናችን ሊውል ይችላል:- «እኛ ወንድማማች ነንና በእኔና በአንተ በእረኞችና በእረኞችህ መካከል ጠብ እንዳይሆን እለምንሃለሁ::» (ዘፍጥ. 13:8):: ጎረቤቶቻቸው ሁሉ ያዩ ነበር! አብርሃም እርሱና ሎጥ እውነተኛውን አምላክ ስለሚያመልኩ የተለዩ መሆናቸውን እነርሱ እንዲያዩ ፈልጓል:: በዮሐንስ 17 ጌታ ኢየሱስ ሲጸልይ፣ ለእግዚአብሔር ክብር ስለ ቤተ ክርስቲያን አንድነት ጸልዮአል (ዮሐ. 17:20-26)::

እርስ በርሳችሁ ተቀባበሉ፤ እርስ በርሳችሁ ተናነጹ፤ እንዲሁም አንዱ ሌላውን ያስደስት - ይህም ሁሉ ስለ እግዚአብሔር ክብር ይሁን::

# ሮሜ 15:8-16:27

ለአባቶች የተሰጠውን የተስፋ ቃል ያጸና ዘንድ፣ ደግሞም:- ስለዚህ በአሕዛብ መካከል አመሰግንሃለሁ ለስምህም እዘምራለሁ ተብሎ እንደ ተጻፈ፣ አሕዛብ ስለ ምሕረቱ እግዚአብሔርን ያከብሩ ዘንድ፣ ክርስቶስ ስለ እግዚአብሔር እውነት የመገረዝ አገልጋይ ሆነ እላለሁ:: ደግሞም:- አሕዛብ ሆይ፣ ከሕዝቡ ጋር ደስ ይበላችሁ ይላል:: ደግሞም:- እናንተ አሕዛብ ሁላችሁ፣ ጌታን አመስግኑ ሕዝቦቹም ሁሉ ይወድሱት ይላል:: ደግሞም:- እናንተ አሕዛብ ሁላችሁ፣ ጌታን አመስግኑ ሕዝቦቹም ሁሉ ይወድሱት ይላል:: ደግሞም:- ኢሳይያስ:- የእሴይ ሥር አሕዛብንም ሊገዛ የሚነሣው ይሆናል፤ በእርሱ አሕዛብ ተስፋ ያደርጋሉ ይላል:: የተስፋ አምላክም በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በተስፋ እንድትበዙ በማመናችሁ ደስታንና ሰላም ሁሉ ይሙላባችሁ::

እኔም ራሴ ደግሞ፣ ወንድሞቼ ሆይ፣ በበጎነት ራሳችሁ እንደ ተሞላችሁ፣ እውቀትም ሁሉ እንደ ሞላባችሁ፣ እርስ በርሳችሁም ደግሞ ልትገሠጹ እንዲቻላችሁ ስለ እናንተ ተረድቼአለሁ:: ነገር ግን አሕዛብ በመንፈስ ቅዱስ ተቀድሰው የተወደደ መሥዋዕት ሊሆኑ፣ ለእግዚአብሔር ወንጌል እንደ ካህን እያገለገልሁ፣ ለአሕዛብ የክርስቶስ ኢየሱስ አገልጋይ እሆን ዘንድ ከእግዚአብሔር በተሰጠኝ ጸጋ ምክንያት ተመልሼ ላሳስባችሁ ብዬ በአንዳንድ ቦታ በድፍረት ጻፍሁላችሁ:: (ሮሜ 15:8-16)

እንግዲህ እንደ ወንጌሌ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ተሰበከ፣ ከዘላለም ዘመንም የተሰወረው አሁን ግን የታየው በነቢያትም መጻሕፍት የዘላለም እግዚአብሔር እንደ አዘዘ ለእምነት መታዘዝ ይሆን ዘንድ ለአሕዛብ ሁሉ የታወቀው ምሥጢር እንደ ተገለጠ መጠን ሊያበረታችሁ ለሚችለው፣ ብቻውን ጥበብ ላለው ለእግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ እስከ ዘላለም ድረስ ክብር ይሁን፤ አሜን:: (16:25-27)

## 13

# ሰው በእንቅስቃሴ ላይ

በሮሜ መልእክት የመደምደሚያ ምዕራፎች ውስጥ ካሉት ቁልፍ ቃሎች መሃከል አንዱ «አገልግሎት» የሚለው ነው:: ይህን ጭብጥ ለማስረዳት ጳውሎስ ሦስት የግሪክ ቃላትን ተጠቅሟል:: በሮሜ 15:8፣ 25፣31 እና 16:1 ላይ አገልግሎት ወይም አገልጋይ የሚለውን ግልጽ ቃል ተጠቅሟል:: «ዲያቆን» የሚለው የአማርኛ ቃል የመጣው ከዚህ ነው:: በቁጥር 16 ና 27 ላይ «አገልጋይ» የሚለውን ቃል የተጠቀመ ሲሆን፣ ለሕዝብ አገልግሎት ወይም በቤተ መቅደስ የሚሰጥን አገልግሎት ያመለክታል:: በሮሜ 15:16 ላይ ግን በግሪኩ አዲስ ኪዳን በስተቀር በሌላ ቦታ ያልተጠቀሰን ቃል ተጠቅሟል:: ትርጓሜውም «የተቀደሰን ሥርዓት በክህነት ማገልገልን» ይወክላል::

በዚህ ክፍል፣ ጳውሎስ አራት የተለያዩ አገልግሎቶችን ገልጿል::

## 1. የኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎት ለአሕዛብ (15:8-13)

የአገልግሎት ምሳሌ ቁንጮ ምንጊዜም ኢየሱስ ክርስቶስ መሆን ይገባዋል:: «እኔ ግን በመካከላችሁ እንደሚያገለግል ነኝ» (ሉቃስ 22:27):: በመጀመሪያ ለማገልገል የመጣው በእስራኤል አማካይነት አሕዛብን ለማገልገል ነው:: በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያ አገልግሎት ጊዜ፣ የተከተሉት መመሪያ «መጀመሪያ ለአይሁድ» የሚለውን ነበር::

ለምሳሌ፣ መጥምቁ ዮሐንስ የመጣው ለመሲሑ ያዘጋጃቸው ዘንድ ለእስራኤል ሕዝብ ነበር:: ኢየሱስ አገልግሎቱን የጀመረው ለእስራኤል ሕዝብ ብቻ በመስጠት ነበር:: ሐዋርያትን በመጀመሪያው የወንጌል አገልግሎት ጊዜ ሲልካቸው፣ እንዲህ ብሎ አዘዛቸው፣ «በአሕዛብ መንገድ አትሂዱ፣ ወደ ሳምራውያንም ከተማ አትግቡ ይልቅስ የእስራኤል ቤት

ወደሚሆኑ ወደ ጠፉት በጎች ሂዱ እንጂ» (ማቴ. 10:5-6)። ትልቁ ትኩረት በእስራኤል ላይ ቢሆንም፣ አሕዛብ ግለሰቦችን አላገለገለም ማለት አይደለም፤ አንዳንድ አሕዛብን አገልግሏልና (ማቴ. 8:5-13 እና 15:21-28)።

ከትንሣኤው በኋላ ሐዋርያት አገልግሎታቸውን በኢየሩሳሌም ተቀምጠው እንዲጀምሩ አዘዛቸው (ሉቃስ 24:44-49)። በሐዋርያት ሥራ 1-7 ባለው ክፍል አገልግሎታቸው ያተኮረው በአይሁድና ወደ ይሁዲነት በገቡ ሰዎች ላይ ብቻ ነበር። ወንጌል ወደ ሰማርያ የሄደው በምዕራፍ 8 ላይ ሲሆን፣ ምዕራፍ 10 ላይ ደግሞ ወደ አሕዛብ እንደ ደረሰ እናነባለን። ከዚያም በጳውሎስ አገልግሎት በሮማ ግዛት ሁሉ ተዳረሰ (የሐዋ. 13:1-3)።

ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር መጥቶ በሞተ ጊዜ፣ እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለሌሎቹ የአይሁድ ሕዝብ አባቶች የሰጠውን ተስፋ አረጋገጠ (ሉቃስ 1:30-33፣ 46-55 እና 67-80 ይመልከቱ)። ከተሰጡት ተስፋዎች አንዳንዶቹ የተፈጸሙ ሲሆን፣ ብዙዎች ግን ወደ ምድር መጥቶ መንግሥቱን እስኪመሠርት ድረስ ይጠብቃሉ።

የእግዚአብሔር ትኩረት በአይሁድ ላይ መሆኑ ራስ ወዳድነት ነውን? አይደለም። ምክንያቱም በአይሁድ በኩል የምሥራቹን ወደ አሕዛብ ይልካል። የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች አይሁድ ነበሩ! «ደኅንነት ከአይሁድ ነው» (ዮሐ. 4:22)። በብሉይ ኪዳን ዘመን እግዚአብሔር እስራኤል አሕዛብን እንድታገለግል መረጣት። ነገር ግን በተቃራኒው እስራኤል የአመንዝራዎቹን አሕዛብ መንገድ በመከተሏ፣ መቀጣት ነበረባት። በአዲስ ኪዳን ዘመን እግዚአብሔር አይሁዳዊ አማኞች የምሥራቹን ለአሕዛብ እንዲያደርሱ የመረጣቸው ሲሆን፣ እነርሱም ታዘዙለት።

ጳውሎስ ከቁጥር 9 እስከ 12 ድረስ የጠቀሳቸው ተስፋዎች ያማረ ቅደም ተከተል አላቸው።

- አይሁድ በአሕዛብ መካከል እግዚአብሔርን አከበሩ

[ቁ. 9፣ ከመዝሙር (18):49 የተወሰደ]

- አሕዛብ ከአይሁድ ጋር ተደሰቱ

(ቁ. 10፣ ከዘዳግም 32:43 የተወሰደ)

- አይሁድና አሕዛብ በአንድነት እግዚአብሔርን አመሰገኑ::

[ቁ. 11፣ ከመዝሙር (117):1 የተወሰደ]

- ክርስቶስ በአይሁድና በአሕዛብ ላይ ገዥ ነው::

(ቁ. 12፣ ከኢሳ. 11:10 የተወሰደ)

ሮሜ 15:8 የወንጌላትና የሐዋርያት ሥራን ምዕራፎች ከ1-7 ያካትታል:: ሮሜ 15:9 በአሕዛብ መካከል የነበረውን የጳውሎስን የምስክርነት አገልግሎት ይገልጻል:: ሮሜ 15:10 አሕዛብ «ሕዝቡ» ከሆኑት አይሁድ ጋር እኩል ደረጃ ባገኙበት የሐዋርያት ሥራ 15 ጉባኤ ላይ ተግባራዊ ሆኗል:: ዛሬ አይሁድና አሕዛብ በአንድነት በቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔርን ያመሰግናሉ::

በቁጥር 12 መጨረሻ ላይ ተስፋን ሲያመለክት፣ በአንድ ወቅት አሕዛብ «ያለ ተስፋ ነበሩ» (ኤፌ. 2:12)፣ አሁን ግን በክርስቶስ ተስፋ አላቸው:: አማኞች ተስፋ ብቻ ሳይሆን፣ ደስታ፣ ሰላምና ኃይልም አላቸው (ቁ. 13)! ራሳቸውን ለእርሱ ሲሰጡ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ እነዚህን በረከቶች ያካፍላቸዋል::

አይሁድ ክርስቲያኖች ወንጌልን ወደ አሕዛብ ለማድረስ ታማኝ በመሆናቸው፣ ዛሬ የዓለም ሕዝቦች በክርስቶስ አዳኝነት የማመንን ዕድል አገኙ::

## 2. ጳውሎስ ለአሕዛብ የነበረው አገልግሎት (15:14-24)

የጳውሎስን የተለየ አገልግሎት ካልተገነዘብን፣ የእግዚአብሔርን የጸጋ መልእክት ብዙም ልናደንቅ አንችልም:: ጳውሎስ የአገልግሎቱን ባሕርያት ገልጿል::

*ሀ) የተቀበልነው በጸጋ ነው* (15:14-15)-- የጠርሴሱ ሳውል፣ አሳዳጁ መምህር በነበረበት ወቅት፣ ጳውሎስ ስለ እግዚአብሔር ጸጋ የሚያውቀው ነገር አልነበረም:: ቤተ ክርስቲያንን እያሳደደ ሊያጠፋት ፈለገ:: ጳውሎስ ኢየሱስ ክርስቶስን በደማስቆ መንገድ ላይ በተገናኘው ጊዜ (የሐዋ. 9)፣ የእግዚአብሔርን ጸጋ ተቀበለ:: ያዳነው የእግዚአብሔር ጸጋ ነው፣ የጠራውና ሐዋርያ ያደረገውም የእግዚአብሔር ጸጋ ነው (1ኛ ቆሮ. 15:8-11) «ስለ ስሙ በአሕዛብ ሁሉ መካከል ከእምነት የሚነሣ መታዘዝ እንዲገኝ ጸጋንና ሐዋርያነትን ተቀበልን» (ሮሜ 1:5):: በኤፌሶን 3 ላይ ጳውሎስ በአሕዛብ ዘንድ ያለውን አገልግሎቱን በሰፊው ተንትኗል::

*ለ) በወንጌል ላይ ያተኮረ ነበር (15:16)* - ከዚህ በፊት እንደተገለጸው ጳውሎስ በዚህ ክፍል ለአገልግሎት ሁለት ቃላትን ተጠቅሟል:: ነገር ግን ትኩረቱ በክህነት አገልግሎት ላይ ነው:: ጳውሎስ ለክርስቶስ ያሸነፋቸውን አሕዛብ፣ በመሠዊያ አጠገብ እንዳለ እንደ ካህን ራሱን ቆጥሮ በእግዚአብሔር ዘንድ ያቀርባቸዋል:: ለእግዚአብሔር ክብር «መንፈሳዊ መሥዋዕት» ነበሩ (1ኛ ጴጥ. 2:5ን ይመልከቱ):: ወንጌልን የመስበክ ተግባሩ እንኳ «የክህነት አገልግሎት ነበር»:: አገልግሎቱን በተመለከተ የዚህ ዓይነት ዕይታ ለአገልግሎታችን ክብርና የኃላፊነት ሸክምን ይሰጠናል:: ካህናት ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡት ምርጥ ምርጡን ብቻ እንደነበረ ማወቁ ጠቃሚ ነው (ሚል 1:6-14ን ይመልከቱ)::

በቃሉ አገልግሎት የሥላሴን ተካፋይነት አስተውሉ:: ጳውሎስ የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋይ ነው፣ ስለዚህ «የእግዚአብሔርን ወንጌል» ሰበከ:: አገልግሎቱን በቀደሰው በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ኃይል አገለገለ:: የጠፉትን ለኢየሱስ ክርስቶስ ለመማረክ ሥላሴን ማገልገል እንዴት ያለ መታደል ነው! እንዴትስ ያለ ኃላፊነት ነው! ነፍሳትን መማረክ የተቀደሰ ኃላፊነትና የክህነት አገልግሎት መሆኑን ማስታወስ አለብን:: ስለሆነም ጌታን በቤተ መቅደስ እንዳለ ካህን በመስጠት ልናገለግለው ይገባናል::

*ሐ) የተሠራው ለእግዚአብሔር ክብር ነው (15:17)* - «እንግዲህ ከእግዚአብሔር ዘንድ በሚሆን ነገር በክርስቶስ ኢየሱስ ትምክህት አለኝ»:: ጳውሎስ ስለ አገልግሎቱ እየፎከረ አይደለም:: ጌታ በሠራው ሥራ እየተመካ እንጂ:: ሐዋርያው የላቀ ዓላማ ስለነበረው ያገለገለውና የተሠቃየው የራሱን ስም ለመከተል አልነበረም:: ለኢየሱስ ክርስቶስ ክብርን ሊያመጣ ፈልጓል:: «እርሱም በሁሉም ፊተኛ ይሆን ዘንድ» (ቆላ. 1:18)::

*መ. የተሠራው በእግዚአብሔር ኃይል ነው* (15:18-19) - መንፈስ ቅዱስ ጳውሎስ ያገለግል ዘንድ ኃይልን አስታጠቀውና ምልክቶችና ድንቅ ነገሮችን ያደርግ ዘንድ አስቻለው:: እግዚአብሔር ጳውሎስ እንዲያከናውነው የፈቀደለት ተአምራት እርሱን ለሌሎች ይገልጥ ዘንድ «ምልክቶች» ነበሩ:: «የሚያስገርሙ» ስለነበሩ የሰዎችን አድናቆት ቀሰቀሱ:: ነገር ግን ሁልጊዜም ቢሆን ሕልማቸው ለወንጌል ስብከት በርን የመክፈት ነበር:: ተአምራት የሚከናወነው ለመልእክቱና ለመልእክተኛው ክብር ለመስጠት ነበር (ዕብ. 2:1-4)፣ ተአምራት በራሳቸው የጠፉትን ሊያድኑ አይችሉም:: በልስጥራን ጳውሎስ ያንን ሽባ ሲፈውሰው (የሐዋ. 14)፣ ወዲያው የተገለጠው አረማዊ ምላሽ ነበር:: ሰዎቹ ጳውሎስና በርናባስን አማልክት ናችሁ ብለው ሊያመልኳቸው ሞከሩ! ጳውሎስ ወንጌሉን በሰበከላቸው ጊዜ፣ በደስታ አልተቀበሉትም:: በመጨረሻም፣ ጳውሎስን በድንጋይ ወግረውት እንዲሞት ከአጥር ውጭ ጣሉት::

የእግዚአብሔር መንፈስ ጳውሎስ ቃሉን እንዲናገር ኃይልን ሰጠው፣ ዓላማውም «አሕዛብ እንዲታዘዙ ለማድረግ ነው» (ሮሜ 5:18):: ሐዋርያው የምሥራቹን የሰበከው «በቃልና በሥራ» ነበር:: እኛም ዛሬ «በቃላችንና በሥራችን» በዙሪያችን ላሉት የጠፉ ሰዎች የእግዚአብሔርን ፍቅር ልናካፍል እንችላለን:: የባሕርይ ለውጥ በራሱ ከመንፈስ ቅዱስ የፈውስ ተአምራት እኩል ዋጋ ያለው ነው::

*ሠ) እንደ እግዚአብሔር ዕቅድ ነበር* (15:20-24)- እግዚአብሔር ጳውሎስ እንዲከተለው የፈለገበት የተለየ ዕቅድ ነበረው:: ሌላ ሐዋርያ ሄዶ በሰበከበት እንዲሰብክ አልፈቀደለትም:: (ጴጥሮስ በሮም ያለችውን አብያተ ክርስቲያናት ላለመመሥረቱ፣ ወይም ሮም ላለመኖሩ አንዱ መረጃ ይሄ ሲሆን፤ ይሄ ባይሆን ኖሮ ጳውሎስን እዚያ ከመሄድ ያግደው ነበር::) «ከኢየሩሳሌም ጀምሮ እስከ እልዋሪቆን» (ቁ. 19) ድረስ 240 ኪሎ ሜትር ያህል ይሆናል:: የጉዞውን መዘግየትና በመንገድ ላይ የነበሩትን አደጋዎች ግምት ውስጥ በማስገባት (2ኛ ቆሮ. 11:26-27)፣ ጳውሎስ በወንጌል መልእክተኝነት አገልግሎቱ ያገኘውን ትልቅ ውጤት ልታደንቁ ትችላላችሁ:: በሌላ ሰው ሥራ መግባቱ ስሕተት ባይሆንም (ዮሐ. 4:38)፣ ፈር ቀዳጅ የሆነ የወንጌል አገልግሎት ወደ አዲስ ክልል መውሰድ የተሻለ ነው:: ጳውሎስ ለዚህ ዓይነቱ አገልግሎት ኢሳይያስ 52:15ን በመጥቀስ መለከታዊ ማረጋገጫን ጠቅሷል::

በሌሎች የሮማ ግዛቶች የነበረው አገልግሎቱ ጳውሎስ ሮምን በቶሎ እንዳይጎበኝ አድርጐት ነበር:: ጳውሎስ ወደ ሮም እንዳይሄድ ያደረገው የሰይጣን ተቃውሞ ወይም የሰው መሰናክል ገጥሞት ሳይሆን፣ በነበረበት ቦታ የጀመረውን አገልግሎት መጨረስ ግድ ስለሆነበት ነው:: በወንጌል ሥርጭት አገልግሎቱ ታማኝ ከመሆኑ የተነሣ፣ በዚያ ክፍል ያላገለገለበት ቦታ አልነበረም:: ይህም ጳውሎስ በዚያ አካባቢ ላሉ ግለሰቦች አንድ በአንድ መስክሯል ማለት ሳይሆን፣ ወንጌልን ወደነዚህ ቦታዎች በማድረስና ሊመሰክሩ የሚችሉ አብያተ ክርስቲያናትና ክርስቲያኖች ሥራውን እንዲቀጥሉ አድርጓል ማለት ነው:: ጳውሎስ ሌላ አገልግሎት ከመጀመሩ በፊት የጀመረውን ይጨርሳል፣ ይህም ለእኛ የወንጌል ሥርጭት አገልግሎት ጥሩ ምሳሌ ነው::

ጳውሎስ ለረጅም ዘመን ሲመኝ የነበረው ሮምን ጎብኝቶ ወደ ስፔን ለመሻገር ቢሆንም እዚያ ለመድረሱ ምንም መረጃ የለንም:: በትውፊት ደረጃ ወደ ስፔንና ብሪታንያ ከተፈታ በኋላ እንደሄደ

ቢነገርም፣ የቤተ ክርስቲያንን አፈ ታሪክ ብዙ ጊዜ ለማመን ያስቸግራል::

### 3. አሕዛብ ለአይሁድ የነበራቸው አገልግሎት (15:25-33)

ጳውሎስና ጓደኞቹ በግሪክ ከነበሩት የአሕዛብ አብያተ ክርስቲያናት በኢየሩሳሌም ይሠቃዩ ለነበሩት የአይሁድ ቅዱሳን የሚሆን ልዩ ስጦታ ተቀበሉ:: ስለዚህ ስጦታ አሰባሰብ ዝርዝር በ2ኛ ቆሮ. 8 እና 9 ቀርቧል:: ከዚህ ልዩ ስጦታ በስተኋላ ብዙ ግቦች ነበሩ:: በመጀመሪያ፣ ለአይሁድ ወንድሞቻቸው የአሕዛብ የፍቅር መግለጫ ነበር:: በሁለተኛ ደረጃ፣ የደኸዩት የአይሁድ አማኞች ከችግራቸው እንዲላቀቁ በጊዜው እጅግ ያስፈልጋቸው ነበረ:: በሦስተኛ ደረጃ፣ በቤተ ክርስቲያን አይሁድና አሕዛብን አንድ ለማድረግ ረድቷል:: ሁለቱንም ያያዘ ገመድ ነበር::

ጳውሎስ ይህንን ስጦታ ዕዳን እንደ መክፈል አድርጎ አይቶታል:: አሕዛብ መንፈሳዊ ሀበትን ከአይሁድ አግኝተዋል:: አሁን ደግሞ ብድራቸውን ለመመለስ ቁሳዊ ሀብትን ሰጡ:: ጳውሎስ ራሱን «ባለዕዳ» አድርጎ ቆጥሯል (ሮሜ 1:14):: እንዲሁም አሕዛብ ክርስቲያኖችን ለአይሁድ ባለዕዳ አድርጎ ቆጥሯቸዋል:: ምክንያቱም ለአሕዛብ የእግዚአብሔርን ቃልና የእግዚአብሔርን ልጅ የሰጧቸው አይሁዳውያን ነበሩ:: እኛም ክርስቲያኖች ስለ እስራኤል ግድ ሊለን ይገባል:: ዕዳችንንም ለመክፈል ለእስራኤል ልንጸልይ፣ ወንጌልን ልናካፍላቸውና በቁሳዊ ነገር ልንረዳቸውም ይገባል:: በተሰጠ የክርስቶስ ሕይወት ፀረ -እስራኤል አሳብ ቦታ የለውም::

ይህ ስጦታ የተከፈለ ዕዳ ሳይሆን፣ «ፍሬም» ነበረ (ሮሜ 15:28):: ጳውሎስ ከአብያተ ክርስቲያናት የዘረፈው አይደለም! እነዚያ አማኞች (ከአሕዛብ የሆኑት) ከጌታ ጋር ባላቸው አካሄድ የተገኘ ፍሬ ነው (ዮሐንስ 15:1-8ን ይመልከቱ)::

በቤተ ክርስቲያን የመንፈስ ቅዱስ ሕይወት ሲፈስ፣ መስጠት ችግር አይሆንም:: ጳውሎስ በ2ኛ ቆሮንቶስ 8:1-5፣ በመቄዶንያ አብያተ ክርስቲያናት የሆነውን የጸጋ ተአምር ገልጾታል::

ጳውሎስ ይህ ስጦታ በአይሁድ አማኞች ዘንድ ተቀባይነትን እያገኝ እንደሆነ ሰግቷል:: በኢየሩሳሌም በነበረችው እናት ቤተ ክርስቲያንና በሌሎች የሮማ ግዛቶች ባሉ አጥቢያ (እኅት) አብያተ ክርስቲያናት መካከል መንፈሳዊ ትስስርን መፍጠር ፈልጓል:: እንደ አጋጣሚ ለአሕዛብ የመጣውን የጸጋ ወንጌል የሚቃወሙና አሕዛብ ለመዳን ወደ ይሁዲነት መግባትና የአይሁድን ሕግ መቀበል አለባቸው የሚሉ ነበሩ:: (እነዚህ ሰዎች ጳውሎስ በሄደበት ሁሉ እየተከተሉ አብያተ ክርስቲያናቱን ሊነጥቁት ይሞክሩ ነበር:: የገላትያ መልእክት የተጻፈው ክፉውን ሥራቸውን ለመዋጋት ነበር::)

በቁጥር 30 ላይ ያለው «ከእኔ ጋር ትጋደሉ ዘንድ» የሚለው ቃል አንድ ስፖርተኛ በውድድር የቻለውን ሁሉ እንደሚያደርግ ዓይነት አሳብ አለው:: ይህ ተመሳሳይ ቃል በቆላስይስ 4:12 ላይ ኤጳፍራ በጸሎት እንደሚጋደል ለማሳየት ተጠቅሷል:: ይህ ቃል የምንፈልገውን ለማግኘት ከእግዚአብሔር ጋር መጋደል እንዳለብን አያመለክትም:: ነገር ግን ጸሎታችን በልባችን ቁምነገር የሌለበት ተራ ልምምድ ሊሆን እንደማይገባ ያመለክታል:: ነጻ ትግል የሚታገል ሰው ለትግሉ የሚያስፈልገውን ዓይነት ጠንካራ ስሜት ሊኖረን ይገባል!

## 4. አማኞች ለጳውሎስ የነበራቸው አገልግሎት (16:1-27)

እንዴት አስደናቂ ምዕራፍ ነው! በዚህ ውስጥ ጳውሎስ ቢያንስ የ26 ሰዎችን ስሞች ጠቅሶ፣ ለሁለት ስማቸው ላልተጠቀሱና በየቤቱ ለሚሰበሰቡ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ሰላምታ አቅርቧል:: መልእክቱን ሲቋጭም በቆሮንቶስ ሆኖ የሮሜን መልእክት በጻፈ ጊዜ ከእርሱ ጋር የነበሩትን ዘጠኝ ሰዎች ስም ጠቅሷል:: የዚህ ጥቅም ምንድን ነው? ይህ የሚያሳየው ጳውሎስ ነፍሳትን መማረክ ብቻ ሳይሆን፣ ወዳጅ ማፍራትንም እንደሚያውቅበት ነው:: ራሱን ገንጥሎ ለመኖር አልሞከረም:: በጌታ ወዳጆች ነበሩት፣ ያደንቃቸውም ነበር:: በግሉና በአገልግሎቱ ጠቃሚዎቹ ነበሩ:: የሰዎችን ታሪክ እንዳነበብኩት እግዚአብሔር የተጠቀመባቸው አብዛኞዎቹ አገልጋዮች ጓደኛ

ማፍራት የሚችሉ ነበሩ:: ራሳቸውን በወዳጆቻቸውና በአገልግሎት አጋሮቻቸው አማካኝነት አበዙ:: ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖሩ ብቸኛ አማኞች ቢኖሩም፣ እንደ እኔ መረዳት ግን አብዛኛዎቻችን አንዳችን ለአንዳችን እናስፈልጋለን:: በጎች ነንና፣ በጎች ደግሞ የሚሰማሩት በአንድነት ነው::

*ሀ) ሰላምታ ለወዳጆች* (16:1-16) - ሰላምታውን የጀመረው በፌቤን ሲሆን፣ እርሷም የክንክራኦስ ቤተ ክርስቲያን አባልና መልእክቱን ወደ ሮም ወዳሉ ቅዱሳን ያደረሰች ሴት ናት:: ከዚህ ቀደም ማንም መልእክተኛ እንደዚህ ዓይነት በጣም አስፈላጊ መልእክት አላደረሰም! ክንክራኦስ የቆሮንቶስ ወደብ ስትሆን፣ ምናልባትም ፌቤን ለክርስቶስ የተማረከችው ጳውሎስ ለአንድ ዓመት ተኩል በቆሮንቶስ በነበረ ጊዜ ሳይሆን አይቀርም:: «አገልጋይ» የሚለው ቃል ዲያቆንን ስለሚወክል፣ አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች ፌቤን ዲያቆን እንደነበረች ያምናሉ:: ይህ ሊሆን የሚችል ነገር ነው:: ምክንያቱም በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ሴቶች የታመሙትን በመጠየቅ፣ ወጣት ሴቶችን በማገዝና ድሃን በመርዳት ያገለግሉ ነበር:: ጳውሎስ እንደተናገረው ፌቤን ለእርሱና ለሌሎች ክርስቲያኖች ደጋፊ ነበረች:: ስለሆነም ቤተ ክርስቲያኗ እንድትረዳት ያበረታታል::

ከእያንዳንዱ ስም ጀርባ ያሉትን ታሪኮች ማወቅ ብንችል ኖሮ መልካም ነበር! ጵርስቅላና አቂላን በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ እናውቃቸዋለን (18:1-3፣ 18-19፣ 26):: የትና መቼ ነፍሳቸውን ለጳውሎስ ለሞት እንዳቀረቡ ባናውቅም፣ ስላደረጉ ግን እንደሰታለን! (1ኛ ቆሮ. 16:19ን እና 2ኛ ጢሞ. 4:19 ይመልከቱ):: ይህ በተጻፈበት ወቅት፣ በሮም የነበሩ ሲሆን፣ አንድ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ በቤታቸው ውስጥ ነበረች:: በዚህ ምዕራፍ ጳውሎስ ለብዙ ጉባኤዎች ሰላምታ አቅርቧል (ሮሜ 16:10-11፣ 14-15)::

አራት ሰዎች ደግሞ በጳውሎስ «ተወዳጆች» ተብለው ተጠርተዋል:: እነርሱም:- አጤኔጦን (ቁ.5)፣ ጵልያጦን (ቁ.8)

ሰንጣክን (ቁ. 9) እና ጠርሲዳ (ቁ. 12) ናቸው። በእስያ በመጀመሪያ የተለወጠው እርሱ በመሆኑ፣ ጳውሎስ አጤኔጦንን በተለይ ያስታውሰዋል። የእስጢፋኖስ ዘመድ ሳይሆን አይቀርም፣ ምክንያቱም በ1ኛ ቆሮንቶስ 16:15 ላይ እነዚህ ሰዎች «የአካያ በኩር ፍሬዎች» ተብለው ተጠርተዋልና።

አንዲራኒቆንና ዩልያን «ዘመዶቼ» ተብለው የተጠሩ ሲሆን፣ የጳውሎስ የሥጋ ዘመድ ወይም እንደ ጳውሎስ የብንያም ነገድ አይሁድ ሳይሆኑ አይቀሩም። በአንድ ወቅት ከጳውሎስ ጋር በወኅኒ ነበሩ። «ሐዋርያ» የሚለው ቃል ልክ እንደ ጳውሎስ ዐይነቱን የሐዋርያነት ሹመት የሚያመለክት ሳይሆን፣ የጌታ «መልእክተኞች» መሆናቸውን የሚያወሳ ነው። «ሐዋርያ» የሚለው ቃል ጠባብና ሰፊ ትርጓሜ አለው።

በቁጥር 13 የተጠቀሰው ሩፎን በማርቆስ 15:21 ላይ የተጠቀሰው ሊሆን ቢችልም፣ በእርግጠኝነት መናገር ግን አንችልም። ከሆነ ግን በቀሬንዮ የነበረው የስምዖን ልምምድ እርሱና ቤተሰቡ እንዲለወጡ አድርጓል ማለት ይቻላል። ጳውሎስና ሩፎን ዘመዳሞች አልነበሩም። «ለእኔና ለእርሱም እናት» ማለቱ የሩፎን እናት ለጳውሎስም እንደ እናት ነበረች ማለቱ ነው (ማር. 10:30 ይመልከቱ)።

ይህ ዝርዝር የሚያሳየው በጳውሎስ አገልግሎትና በአብያተ ክርስቲያናት አገልግሎት ሰዎች የተጫወቱትን ሚና ነው። ፌቤን ብዙዎችን ትረዳ ነበር። ጵርስቅላና አቂላ የጳውሎስ «ረዳትና» ስለ እርሱ «ነፍሳቸውን እንኳ ለሞት ያቀረቡ» ነበሩ። የአጤኔጦን መለወጥ በእስያ ላሉ ለሌሎች መዳን ሆነ። ማርያ «ብዙ ደከማለች»። አንዲራኒቆንና ዩልያን ከጳውሎስ ጋር ታስረዋል። አገልግሎታቸውን ለእግዚአብሔር ክብር ከፈጸሙ ከእነዚህ ቅዱሳን ሰዎች የተነሣ፣ እግዚአብሔርን ማመስገን ይገባል። እኛ ም ፈለጋቸውን እንከተል!

*ለ) የምናስወግዳቸው ጠላቶች* (16:17-20) – ሁሉም ሰው ከጳውሎስ ጋር ለወንጌል ሥርጭት እየሠራ አልነበረም።

በራሳቸው ግላዊ ምክንያት የተሳሳተ አስተምህሮ እያስተማሩ አብያተ ክርስቲያናትን የሚከፋፍሉ ነበሩ። ምናልባት እነዚህ ሰዎች ጳውሎስን እየተከተሉ በየአብያተ ክርስቲያኑ ሰዎችን ወደ ይሁዲነት የሚመልሱ ችግር ፈጣሪዎች ሳይሆኑ አይቀሩም (ፊልጵ. 3፡17-21ን ይመልከቱ)። እነዚህ ሰዎች እውነትን በመስበክ ፋንታ፣ የራሳቸውን ሃይማኖታዊ የትምህርት ነፋስ በሚያስትና በሚያማልል ንግግር ያስፋፉ ነበር። ዛሬም ተመሳሳይ ችግር ስላለ፣ ክርስቲያኖች ከሐሰተኛ አስተማሪዎች ሊጠነቀቁ ይገባል። ወደ ቤታችሁ በመጽሔት፣ በመጻሕፍትና በካሴት አማካይነት በመምጣት እውነትን እንደሚያስተምሩ ለማስረዳት ይሞክራሉ። ጳውሎስ ሁለት መመሪያዎችን ሰጥቷል፡- ለዩአቸው፣ ከዚያም አስወግዷቸው።

ይህ ለጌታ የምንታዘዝበትና ለሌሎች የምንመሰክርበት ነው። ፍሬ ነገሩ ወዳጅ ስለማፍራት አይደለም፣ ነገር ግን ጌታን ማስደሰትና ዘላቂ የሆነ ምስክርነትን ጠብቆ ማቆየት እንጂ። ቁጥር 20 እንደሚጠቁመው እነዚህ አስተማሪዎች የሚመጡት ከሰይጣን ሲሆን፣ እርሱ አንድ ቀን ሙሉ በሙሉ ይደመሰሳል።

*ሐ) ሊከበሩ የሚገባቸው ታማኝ አገልጋዮች* (16:21-24) – እንዴት የሚገርም የጀግኖች ዝርዝር ነው! ጢሞቴዎስ በሐዋርያት ሥራና በመልእክቶች ውስጥ ብዙ ጊዜ ተጠቅሷል። የጳውሎስ «የእምነት ልጅ» ነበረና በብዙ አስቸጋሪ ቦታዎች ከጳውሎስ ጋር ደክሟል (ፊልጵ. 2፡19-24 ይመልከቱ።) ሉቂዮስ አይሁድ ሲሆን፣ ኢያሶንና ሱሲጴጥሮስም አይሁዳዊ ናቸው። በዚህ ስፍራ የተጠቀሰው ኢያሶን ጳውሎስን በተሰሎንቄ ያዳነው ለመሆኑ ማስረጃ የለንም (የሐዋ. 17፡1-9)። ስለዚህ ኢያሶን ምናልባት አሕዛብ ሳይሆን አይቀርም።

ጤርጥዮስ ጳውሎስ እየነገረው መልእክቱን የጻፈው ሰው ነው። ጋይዮስ ደግሞ ጳውሎስ በቆሮንቶስ ሳለ፣ የኖረው በዚህ ሰው ቤት ነበር። 1ኛ ቆሮ. 1፡14 እንደሚናገረው ጳውሎስ ጋይዮስን ወደ ክርስቶስ የመራውና ያጠመቀው የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያንን በመሠረተበት ወቅት ነበር። ይህ ጥቅስ በዚህ ሰው

ቤት ውስጥ የሚሰበሰቡ አማኞች እንደ ነበሩ ያመለክታል:: ኤርስጦስ ደግሞ በከተማዋ ከፍተኛ ባለሥልጣን ሲሆን፣ ምናልባትም ገንዘብ ያዥ ሳይሆን አይቀርም:: በቆሮንቶስ ወንጌል ለባለሥልጣናትና ከታች ላለው ተራ ሕዝብ ተዳርሶ ነበር (1ኛ ቆሮ. 1:26-31፤ 6:9-11)::

ምናልባትም ቁ. 24 በጳውሎስ በራሱ የእጅ ጽሕፈት ሳይጻፍ አይቀርም:: ምክንያቱም በየመልእክቶቹ የጳውሎስ ማኅተም ይሄ ነበርና (2ኛ ተሰ. 3:17-18 ይመልከቱ)::

የመዝጊያ ቡራኬው ጳውሎስ በጻፋቸው መልእክቶች ካሉት ሁሉ ረጅሙ ነው:: ይህም ለአሕዛብ ያለውን ልዩ አገልግሎት ያንጸባርቃል:: «ምሥጢሩ» በእግዚአብሔር መርሐ ግብር የሚያምኑ አይሁድና አሕዛብን በቤተ ክርስቲያን አማካይነት አንድ አካል ማድረጉ ነው (ኤፌ. 3 ተመልከቱ):: ይህ የጳውሎስ ልዩ መልእክት ነበር:: ወደ ይሁዲነት የሚመለሱት ጳውሎስን የሚያሳድዱት በዚህ ልዩ መልእክት ምክንያት ሲሆን፣ ከይሁዲነት ጋር ተያይዘው የሚመጡ ጥቅማ ጥቅሞችንም ላለማጣት ይፈልጋሉ:: በሮም አብያተ ክርስቲያናት ያሉ አይሁድና አሕዛብ የእግዚአብሔርን መርሐ ግብር ማወቅ ነበረባቸው:: አንዳንዶቹን ጳውሎስ ከምዕራፍ 9 እስከ 11 ባለው ክፍል ገልጿቸዋል::

ክርስቲያኖች ጳውሎስ ይህንን ለምን እንደ ጻፈ ምክንያቱን በሚገልጠው እውነት ላይ የተመሠረቱ ሲሆን፣ በዚህም ለክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን ፈቃድ ገልጦ ክርስቲያኖቹ በዚህ እውነት ላይ ተመሥርተው እውነትን ላጠፉት እንዲያካፍሉ ያደርጋል:: ለነገሩማ እኛ ራሳችን የሌለንን ለሌሎች ማካፈል አንችልም::

ይህ ማለት ሮሜን ስናጠና መልእክቱ እኛን በእምነት የበለጠ ሊያየንና ክርስቶስን ለሌሎች በደስታ እንድናካፍል ሊያደርገን ይገባል:: ውጤቱም:- «ብቻውን ጥበብ ላለው ለእግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት እስከ ዘላለም ድረስ ክብር ይሁን!»

# የጥናት ጥያቄዎች
# ምዕራፍ አንድ

## ወደ ሮም ለመጓዝ መዘጋጀት

(ሮሜ 1:1-17)

1. በሮም የነበረችው ቤተ ክርስቲያን ሰዎች ልምምድ ምን ነበር?
2. የሮሜ መልእክት የመጣው ከየት ነበር?
3. የመጽሐፉ ጭብጥና ዓላማ ምንድን ነው?
4. «ተስማማ» የሚለው ርእስ «ጻድቅ በእምነት በሕይወት ይኖራል» ከሚለው ጥቅስ ጋር የሚዛመደው እንዴት ነው?
5. የጳውሎስ ሹመቶች ምን ነበሩ? ለአንድ ቤተ ክርስቲያን መልእክት ብትጽፉ ራሳችሁን የምታስተዋውቁት እንዴት ነው?
6. በሮሜ 1:8-15 ጳውሎስ ለአማኞች ግድ እንደሚለው የሚያሳዩ ማስረጃዎች ምን ምን ናቸው?
7. እኛ ለሌሎች ግድ እንደሚለን የምንገልጥባቸው ማስረጃዎች ምን ምንድን ናቸው?
8. በዚያ ጊዜ የሚኖር ሮማዊ እንዳያምን የነበሩበት መሰናክሎች ምን ምን ነበሩ?
9. ጳውሎስ በወንጌል አለማፈሩን ያሳየው እንዴት ነበር?
10. ወንጌል «የእግዚአብሔር ኃይል» የሆነው በምን መንገድ ነው?

# የጥናት ጥያቄዎች

## ምዕራፍ ሁለት

## እግዚአብሔር አሳልፎ ሲሰጥ

(ሮሜ 1:18 -3:20)

1. «በደለኛ ናችሁ» የሚለውን ቃል ስትሰሙ ወይም ሌሎች ሲባሉ ስታዩ ምን ይሰማችኋል?
2. ሰዎች ጥፋታቸውን ማመን የማይፈልጉት ለምንድን ነው?
3. «የሰውን ሕይወት ማሽቆልቆል» በተመለከተ የተገለጹት አራቱ ደረጃዎች ምን ምን ናቸው? ምክንያቱስ ምን ነበረ?
4. ሰዎች ስለ እግዚአብሔር የተገለጠውን እውነት በዐመጽ የሚከለክሉት ለምንድን ነው? እንደዚህ ባለ ትግል ውስጥ የገባችሁት መቼ ነበር?
5. ከጣዖት አምልኮ ወደ ምግባረ ብልሹነት ለማምራት አንድ እርምጃ ብቻ የሚቀረው ለምንድን ነው?
6. ከኃጢአታቸው የተነሣ «እግዚአብሔር አሳልፎ ሰጣቸው» ሲል ምን ማለቱ ነው»? (1:24፣28)
7. የአይሁድን ሕዝብ በደል የሚያረጋግጡት ምስክሮች ማን ወይም ምን ናቸው?
8. የሮሜ መልእክት በተጻፈበት ወቅት፣ ስለ አይሁዳውያን እግዚአብሔር ያልተደሰተበት ነገር ምን ነበር?
9. በልዩ ሁኔታ ከመንከባከብ ይልቅ የእግዚአብሔር በረከት ለአይሁድ ምንን ሰጣቸው? እግዚአብሔር ለእናንተ ከሰጠው በረከት አንጻር እውነት የሚሆነው እንዴት ነው?
10. በሮሜ 3:10-18 («ቸርነት የሚያደርግ የለም») የሚለውን ሐረግ በሕይወት ልምድ ከምናውቃቸው መልካም ሥራ ከሚሠሩ ደግ ሰዎች አብረን የምናስኬደው እንዴት ነው?

# ተስማማ

## ምዕራፍ ሦስት

## አባታችን አብርሃም

(ሮሜ 3:21-4:25)

1. የ«መጽደቅ» እና የ«መቀደስ» ግልጽ ትርጉሞች ምን ምን ናቸው? ሁለቱን የምንለያያቸው እንዴት ነው?
2. ሰባቱ የጽድቅ ባሕርያት ምን ምን ናቸው? እያንዳንዱን በራስህ ቃል አብራራ።
3. የአብርሃም እምነት ጽድቅን የሚገልጸው እንዴት ነው?
4. የብሉይ ኪዳን አማኞች የጸደቁት እንዴት ነበር? ዛሬስ አማኞች የሚጸድቁት እንዴት ነው?
5. የእንስሳት መሥዋዕት በብሉይ ኪዳን የሚቀርብበት ዓላማ ምን ነበር?
6. ጽድቅ በእምነት መሆኑን የሚያስተምሩ ቁልፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የትኞቹ ናቸው?
7. በበጎ ምግባርና በማመን መካከል ያለው ትስስር ምንድን ነው?
8. «ደኅንነት ነፃ ስጦታ ነው እንጂ ርካሽ አይደለም» ማለት ምን ማለት ነው?
9. እግዚአብሔር ለራሱ ቅዱስ ባሕርይና ሕግ በእውነት እየቆመ ኃጢአተኞችን እንዴት ሊያድናቸው ይችላል?
10. ቁጣን ማብረድ፣ መዋጀትና ደም የሚሉትን ቃላት የመገንዘቡ አስፈላጊነት ምንድን ነው?

# የጥናት ጥያቄዎች

## ምዕራፍ አራት

## እንደ ንጉሥ መኖር

(ሮሜ 5:1-21)

1. በሮሜ 3:20፤ 5:1፤ 8:1 እና 12:1 ላይ «እንግዲህ (ይህም)» የሚለው ጠቀሜታው ምንድን ነው?
2. ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞተ የሚለው፣ ስለ እግዚአብሔር ምንን ይገልጻል?
3. «በአንድ ሰው (በአዳም) ያለመታዘዝ በዓለም ሁሉ ላይ መፍረዱ ተገቢ ነውን?» የሚለውን ጥያቄ የምትመለከተው እንዴት ነው?
4. የመጽደቃችን መንፈሳዊ በረከቶች ምንድን ናቸው?
5. የምንጸድቀው እንዴት ነው? በሮሜ 5:1-21 የተገለጸው ምንድን ነው? ጽድቅ ለአንተ ምን ማለት ነው?
6. መከራ ክርስቲያናዊ ባሕርይን የሚቀርጸው እንዴት ነው?
7. ለአንተ ወደ እግዚአብሔር ፊት መቅረብ መቻል ማለት ምን ማለት ነው? ወደ እግዚአብሔር ፊት ለመቅረብ የማይችሉ ካሉ እነማን ናቸው?
8. አማኝ በዚህ ሕይወት ሊነግሥ የሚችለው በምን መንገድ ነው?
9. በሕግ፣ ኃጢአትና በጸጋ መካከል ያለው ዝምድና ምንድን ነው?

# ምዕራፍ አምስት

## ለመኖር መሞት

(ሮሜ 6:1-23)

1. ጽድቅ በእምነት እንደሆነ በሚያስተምረው አስተምህሮ ላይ የሚነሡት ሦስት ተቃውሞዎች ምን ምን ናቸው? ለእያንዳንዱ መልስ የምትሰጠው እንዴት ነው?
2. መጽደቅ እንደ ሕያው ግንኙነት የሚቆጠረው ለምንድን ነው?
3. ጳሐፊው አንዳንድ ክርስቲያኖች «መሃል ሰፋሪ» ናቸው ሲል ምን ማለቱ ነው?
4. የጥምቀት ትርጉሙ ምንድን ነው?
5. አንድ አማኝ ከኃጢአት ጋር ያለው ግንኙነት ምንድን ነው?
6. ዕወቁ፣ ቁጠሩና አቅርቡ በሚሉት በእያንዳንዱ ቃል ዙሪያ በኃጢአት ላይ ድልን የምናገኝባቸው መንገዶች ምን ምን ናቸው?
7. ራሳችንን ለእግዚአብሔር የምናቀርበው እንዴት ነው?
8. እግዚአብሔር ብልቶቻችንን ለምን ይፈልጋል?
9. ብልቶቻችንን ለጌታ አሳልፈን ባንሰጥ ምን ይመጣብናል?
10. መውደድ (ቁ. 14-15)፣ ነጻነት (ቁ. 16-20) እና ፍሬ (ቁ. 21-23) ራስን ከመስጠት (ከማቅረብ) ጋር የሚያያዙት እንዴት ነው?

# የጥናት ጥያቄዎች

## ምዕራፍ ስድስት

## ክርስቲያኖች እና ሕግ

(ሮሜ 7:1-25)

1. የሕግ ሥልጣን ምንድን ነው? (7:1-6)
2. ጳውሎስ የጋብቻን ምሳሌ በመጥቀስ እኛ ከሕግ ጋር ያለንን ግንኙነት ለማብራራት የሞከረው እንዴት ነው?
3. በማመናችን ምክንያት ያገኘነው ከሕግ በታች ሳለን ያልነበረን ነገር ምን ነበር? ታዲያ ይሄ ምን ለውጥ ያመጣል?
4. ሕግ እኛን የሚያገለግልበት አራት መንገዶች ምን ምን ናቸው? (7:7-13)
5. ጳውሎስ «አትመኝ» የሚለውን ቃል ሕግን ለመተላለፍ ምሳሌ አድርጎ ያቀረበው ለምን ይመስላችኋል?
6. ሕግ ሊረዳን የማይችለው ለምንድን ነው? (7:14-25)
7. ወግ አጥባቂነት ምን ማለት ነው?
8. በክርስቲያን ሕይወት ወግ አጥባቂነት ምን ተጽዕኖ አለው? እንዴትስ ከዚህ ከወግ አጥባቂነት እስራት ነፃ እንወጣለን?
9. ሕግን አለመታዘዝና መልካም ኑሮ መኖር የማይቻለው ለምንድን ነው? ጥሩ የመሥራት ምሥጢሩ ምንድን ነው? ለምን?
10. በዘመናችን የመንፈስ ቅዱስ ሚና ምንድን ነው?

## ተስማማ

## ምዕራፍ ሰባት

# ነጻነትና ፍጻሜው

(ሮሜ 8:1-39)

1. በሮሜ 8:1-39 ጳውሎስ ለአማኞቹ የጻፈው መልእክት ምንድን ነበር? ይህ ከሮሜ 7 ጋር በምን ይዛመዳል?
2. አማኝ ከሕግ ጋር ያለው አዲስ ግንኙነት ምንድን ነው?
3. በዊርዝቢ ተጠቃለው የቀረቡት አራቱ መንፈሳዊ ነጻነቶች ምን ምን ናቸው? እነዚህ ነጻነቶች ሕይወትህን የሚዳስሱት እንዴት ነው?
4. ጳውሎስ «ኩነኔ የለባቸውም» ከሚለው በተጨማሪ ያሰፈራቸው ሦስት አሳቦች ምን ምን ናቸው? ይህን እውነት በሕይወትህ በመግለጥ ትኖራለህን?
5. ከሽንፈት ነፃ ስለ መውጣት የተገለጹት አራት ንጽጽሮች ምን ምን ናቸው?
6. የኃጢአት ሥር ምንድን ነው? ይህን የምታየው በየትኛው የሕይወትህ ክፍል ነው?
7. በሮሜ 8:18-30 መሠረት፣ «የሚቃትተው» ማን ነው? «መቃተቱስ» መቼ ይቆማል?
8. አማኞችን ከተስፋ መቁረጥ በእውነት ነፃ የሚያወጣው ማን ነው?
9. በጌታና በአማኝ መካከል መለያየት እንደሌለ ማረጋገጥ የምትችለው እንዴት ነው?
10. ከእግዚአብሔር ጋር ያለህን ሕይወት ስትቃኝ፣ ከነጻነቶቹ አንዱን ወይም ሁለቱን በግልህ በሕይወትህ እንዴት መግለጥ ትችላለህ?

## የጥናት ጥያቄዎች

## ምዕራፍ ስምንት

# እግዚአብሔር ተሳሳተን?

(ሮሜ 9:1-33)

1. ጳውሎስ ስለ እስራኤል የሚናገሩትን እነዚህን ምዕራፎች ለምን በመልእክቱ ውስጥ አካተተ?
2. በእምነት ስለ መጽደቅ ከሚያወሱት ከመጀመሪያዎቹ ስምንት ምዕራፎች ሮሜ 9-11 የሚገናኘው እንዴት ነው?
3. «ተስማማ» የሚለው ጭብጥ ከእስራኤል ሕዝብ ጋር የሚያያዘው እንዴት ነው?
4. የእስራኤል ያለፈው ታሪኳ የእግዚአብሔርን ባሕርይ የሚያጎላው እንዴት ነው?
5. እስራኤል ያላት ተስፋ ምንድን ነው?
6. ለደኅንነት መሠረት የሆኑትና ያልሆኑት ነገሮች ምን ምን ናቸው?
7. እግዚአብሔር አንዳንዶቹን መርጦ፣ ሌሎቹን ስለ መተዉ ለሚነሡት ተቃውሞዎች የምንሰጣቸው ሦስት መልሶች ምን ምን ናቸው?
8. ደኅንነትን በተመለከተ የእግዚአብሔር ሉዓላዊነትና የሰውን ድርሻ የምታስታርቃቸው እንዴት ነው?
9. አብዛኞዎቹ አይሁድ ያላገኙትን ጽድቅ አሕዛብ ያገኙት እንዴት ነው?
10. የራሱ ወገኖች ወደ ትክክለኛው ጽድቅ ባለመድረሳቸው ጳውሎስ ምን ተሰማው? አንተስ የጠፉትን ስታስብ ምን ይሰማሃል?

# ተስማማ

## ምዕራፍ ዘጠኝ

## የተዛባ ጽድቅ

(ሮሜ 10፡1-21)

1. በሮሜ 10፡1-13 የተጠቀሱትና እስራኤል መሢሑን ያልተቀበለችባቸው ምክንያቶች ምን ምን ናቸው?
2. ጳውሎስ በሮሜ 10፡14-17 ላይ አይሁድ መሢሑን ላለመቀበላቸው መፍትሔ አድርጎ የጠየቀው ምንድን ነው?
3. ያለመቀበላቸው ውጤቶች በሮሜ 10፡18-21 እንደተመለከተው ምን ምን ናቸው?
4. እስራኤላውያን የእግዚአብሔርን ጽድቅ ያልተረዱት ለምንድን ነበር?
5. በሕግ የሚገኝ ጽድቅ በእምነት ከሚገኝ ጽድቅ የሚለየው በምንድን ነው?
6. ዛሬ እውቀት ዐልባ ቅናት የምታየው የት ነው?
7. በሮሜ 10፡14-17 ላይ ተመሥርተን የወንጌል መልእክተኛነትን ሥራ በተግባር ለማዋል የምንችለው እንዴት ነው?
8. ቤተ ክርስቲያን መልእክተኞችን እንድትልክ ዶክተር ሃሪሰን በቅዱሳት መጻሕፍት ያገኟቸው አራት ምክንያቶች ምን ምን ናቸው?
9. የወንጌል ወደ አሕዛብ መላክ ለአይሁድም ሆነ ለአሕዛብ የምሕረት እርምጃ የሆነው እንዴት ነው?
10. በክርስቶስ ማመን ማለት ምን ማለት ነው?

# የጥናት ጥያቄዎች

## ምዕራፍ አሥር

## እግዚአብሔርና ያልተቋጫው የእስራኤል ነገር

(ሮሜ 11:1-36)

1. እስራኤል የወደፊት ተስፋ እንዳላት ለማመልከት ጳውሎስ የጠራቸው አምስት ምስክሮች እነማን ናቸው?
2. እያንዳንዱ ምስክር ለእስራኤል የወደፊት ዕጣ ፈንታ ምን አስተዋጽኦ አለው?
3. ሮሜ 11 በዘመናችን ላለነው ቤተ ክርስቲያን ሊውል የማይችለው ለምንድን ነው?
4. የጳውሎስ መለወጥ «ምሳሌ» የሚሆነው በምን መልኩ ነው?
5. የዳኑት ቅሬታዎች ያመኑት አይሁድ ከሆኑ የቀሩት እስራኤላውያን ምን ይሆናሉ?
6. እግዚአብሔር ከአይሁድ ጋር ያለውን ነገር እንዳልቋጨ ለማሳየት ጳውሎስ ምን ምሳሌ ተጠቀመ?
7. «እስራኤል ሁሉ ይድናል» በሚለው ጥቅስ የተጠቃለሉት እነማን ናቸው?
8. አሕዛብ በእስራኤል ላይ እብሪተኛ ለመሆን የተፈተኑት ለምንድን ነው?
9. «ሥነ መለኮት ቡራኬ ይሆናል»፣ የሚለው ሐረግ ብዙ ጊዜ እውነት የሚሆነው ለምንድን ነው?
10. ሮሜ 10 ከሮሜ መልእክት ጭብጥ «ተስማማ» ከሚለው ጋር የሚያያዘው እንዴት ነው?

## ተስማማ

## ምዕራፍ አሥራ አንድ

# እውነተኛ ግንኙነት እውነተኛ አኗኗር ነው

(ሮሜ 12:1-13:14)

1. አስተምህሮና ተግባር፣ እምነትና ባሕርይ፣ ትምህርትና ባሕርይ፣ ትምህርትና ኑሮ በሚሉት ጥንዶች መካከል ያለው ግንኙነት ምንድን ነው? እነዚህ ከኅብረት ጋር የሚዛመዱት እንዴት ነው?

2. ጳውሎስ በሮሜ 12:1-2 የጠቀሳቸው የክርስቲያናዊ መሰጠት እርከኖች ምን ምን ናቸው?

3. እግዚአብሔር ልቦናችንን የሚያድሰው እንዴት ነው? በዚህ ውስጥ የእኛ ድርሻ ምንድን ነው?

3. ፈቃዳችንን ለጌታ መስጠት የምንችለው እንዴት ነው?

4. በክርስቶስ አካል ለመንፈሳዊ አገልግሎትና ዕድገት ያስፈልጋሉ ብለው ዌርዝቢ የሚያምኑባቸው ነገሮች ምንድን ናቸው?

5. አማኞች መንፈሳዊ ስጦታዎቻቸውን በተመለከተ ስሕተት ሊፈጽሙ የሚችሉባቸው ሁለት ጽንፎች ምንና ምን ናቸው?

6. በአካል ውስጥ ፍሬያማ የሆነ አገልግሎት የሚሰጥ ክርስቲያን ሁለት ምልክቶች ምን ምንድን ናቸው?

7. ሰዎች ስሕተት በእኛ ላይ ሲሠሩ ምላሻችን ምን መሆን አለበት? ይህ አስቸጋሪ የሚሆንብን ለምንድን ነው? ጠላቶችህን ለመውደድ የተቸገርከው መቼ ነበር?

8. ክርስቲያን ለመንግሥት መገዛት ያለበት ለምንድን ነው? ሌላ አማራጭ የለምን?

9. ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን «መልበስ» ማለት ምን ማለት ነው?

# የጥናት ጥያቄዎች

## ምዕራፍ አሥራ ሁለት

## ክርስቲያኖች ሳይስማሙ ሲቀሩ

(ሮሜ 14:1-15:7)

1. «ግልጽ ባልሆኑ» ጉዳዮች ላይ ጳውሎስ የሰጠን የምሪት መርሆች ምን ምን ናቸው? የእነዚህ ጉዳዮች ምሳሌዎች ምን ምን ናቸው?
2. «ግልጽ ባልሆነ» ጉዳይ ክርስቲያኖች አንዳንድ ጊዜ የማይስማሙት ለምንድን ነው?
3. ደካማ ክርስቲያን ተብለው የተፈረጁት እነማን ናቸው? ጠንካራ ክርስቲያን የተባሉትስ?
4. ሮሜ 14:1-12 እርስ በርስ ስለመቀባበል የሚናገረው ምንድን ነው?
5. እንደ ሮሜ 14:13-23 እርስ በርሳችን የምንተናነጸው እንዴት ነው?
6. በሮሜ 15:1-7 በተገለጸው መሠረት አንዳችን ሌላችንን ለማስደሰት ምን ማድረግ እንችላለን?
7. ኢየሱስን እንደ ጌታ ማግኘት ምን ማለት ነው? በሌሎች አማኞች ላይ እንዳንፈርድ ሕይወታችንን የሚቀይረው እንዴት ነው?
8. ራስ ወዳድነትን አስወግደን ሌሎችን ለማስደሰት ልንቀርባቸው የሚገቡን ሁለት የመንፈሳዊ ኃይል ምንጮች እነማን ናቸው? የትኛው ሊቀድም ይገባል ትላለህ?
9. አማኞች «በአንድ ልብ ሆናችሁ» (15:5) ሲል ምን ማለቱ ነው?
10. እነዚህ አሳቦች በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናችን የሚተገበሩት እንዴት ነው?

## ምዕራፍ አሥራ ሦስት

# ሰው በእንቅስቃሴ ላይ

(ሮሜ 15:8-16:27)

1. ሮሜ 14-16ን ስታነብ፣ ተለይተው የተጠቀሱት አገልግሎቶች ምን ምን ናቸው?

2. ኢየሱስ ክርስቶስ የአገልግሎታችን ታላቅ ምሳሌ እንደ መሆኑ፣ ከእርሱ የአገልግሎት ባሕርያት ልንወስዳቸው የሚገቡን ነገሮች ምን ምን ናቸው?

3. የጳውሎስ አምስት የአገልግሎት ባሕርያት ምን ምን ናቸው?

4. ይሄን ያህል ብዛት ያላቸው ግላዊ ሰላምታዎች ጥቅም ምንድን ነው?

5. ጳውሎስ ረዥም የሆነ ቡራኬ የሰጠው ለምንድን ነው? (16:17-27)

6. በዘመናችን ባለችው ቤተ ክርስቲያን አማኞችን የበለጠ ለማገልገል ተሳትፎ የምናደርገው እንዴት ነው?

7. በጳውሎስ አገልግሎት የድንቅና ተአምራት ዓላማ ምን ነበር?

8. ከከተማ ወጣ ብለህ ቆይተህ ለቤተ ክርስቲያንህ ደብዳቤ የምትጽፍ ቢሆን፣ ሰላምታህን የምታቀርበው ለማን ይሆን ነበር? ስለ እነርሱስ ምን ትል ነበር?

9. ይሄንን መጽሐፍ አንብበህ ስትጨርስ ለግሌ በተለየ መንገድ አግዞኛል የምትለው ያገኘኸው ትምህርት አለ?

10. እነዚህን እውነታዎች በሕይወትህ የምትጀምረው፣ ወይም የምትቀጥለውና ወይም ተግባራዊ የምታደርገው እንዴት ነው?

# «... ሁን» በሚል ርእስ ታትመው
# በስርጭት ላይ የሚገኙ መጻሕፍት

1. ለጌታ የተገዛህ ሁን (የማቴዎስ ወንጌል)
2. ተግተህ አገልግል (የማርቆስ ወንጌል)
3. ርኅሩኅ ሁን (የሉቃስ ወንጌል 1-13)
4. የበረታህ ሁን (የሉቃስ ወንጌል 14-24)
5. ሕያው ሁን (የዮሐንስ ወንጌል ም. 1-12)
6. የተለወጣችሁ ሁኑ (የዮሐንስ ወንጌል 13-28)
7. በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተመላለስ (የሐዋ. ሥራ 1-12)
8. ደፍረህ መስክር (የሐዋርያት ሥራ 13-28)
9. *ተስማማ (ሮሜ)*
10. ጠቢብ ሁን (1ኛ ቆሮንቶስ)
11. ተጽናና (2ኛ ቆሮንቶስ)
12. አርነት መውጣት (ገላትያ)
13. ፍለጋ የሌለውን ባለጸግነት ውረስ (ኤፌሶን)
14. ደስተኛ ሁን (ፊልጵስዩስ)
15. ፍጹም ሁን (ቆላስይስ)
16. ለምጽአቱ ተዘጋጅ (1ኛና 2ኛ ተሰሎንቄ)
17. ታማኝ ሁን (1ኛና 2ኛ ጢሞቴዎስ፥ ቲቶና ፊልሞና)
18. በማየት ሳይሆን በእምነት ተመላለስ (ዕብራውያን)
19. ተስፋ አድርግ (1ኛ ጴጥሮስ)
20. ንቃ (2ኛ ጴጥሮስ፥ 2ኛና 3ኛ ዮሐንስ፥ ይሁዳ)
21. እውነተኛ ሁን (1ኛ ዮሐንስ)
22. በብስለት ማደግ (የያዕቆብ መልእክት)
23. ድል አድራጊ ሁን (የዮሐንስ ራእይ)

BIBLE BASED BOOKS
SIM PUBLISHING

መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ያደረጉ መጻሕፍት